17ልወድቅ ተቃርቤአለሁ፤
ከሥቃዬም ከቶ አልተላቀቅሁም።
18በደሌን እናዘዛለሁ፤
ኀጢአቴም አውካኛለች።
19ብርቱዎች ጠላቶቼ ብዙ ናቸው፤
ያለ ምክንያት የሚጠሉኝም ስፍር
ቍጥር የላቸውም።
20መልካሙን ስለ ተከተልሁ፣
በበጎ ፈንታ ክፉ የሚመልሱልኝ ጠሉኝ።
21እግዚአብሔር ሆይ፤ አትተወኝ፤
አምላኬ ሆይ፤ ከእኔ አትራቅ።
22ጌታዬ መድኅኔ ሆይ፤
እኔን ለመርዳት ፍጠን።

## መዝሙር 39

### ታላቅ እግዚአብሔር - ታናሽ ሰው

*ለመዘምራን አለቃ፣ ለኤዶታም፤ የዳዊት መዝሙር*

1እኔ፣ "በአንደበቴ እንዳልበድል፣
መንገዴን እጠብቃለሁ፤
ክፉዎችም በእኔ ዘንድ እስካሉ ድረስ፣
ልጓም በአፌ አስገባለሁ" አልሁ።
2እንደ ዲዳ ዝም አልሁ፤
ለበጎ ነገር እንኳ አፌን ዘጋሁ፤
ሆኖም ጭንቀቴ ባሰ።
3ልቤ በውስጤ ጋለ፤
በማሰላሰልበትም ጊዜ እሳቱ ነደደ፤
ከዚያም በአንደበቴ እንዲህ ተናገርሁ፤
4"እግዚአብሔር ሆይ፤ የሕይወቴን ፍጻሜ፣
የዘመኔንም ቍጥር አስታውቀኝ፤
አላፊ ጠፊ መሆኑንም ልረዳ።
5እነሆ፤ ዘመኔን በስንዝር ለክተህ
አስቀመጥህ፤
ዕድሜዬም በፊትህ እንደ ኢምንት ነው፤
በእርግጥ የሰው ሁሉ ሕይወት ተን ነው።
ሴላ
6ሰው የጥላ ውልብታ ነው፤
በከንቱም ይታወካል፤
ለማን እንደሚሆን ሳያውቅ ሀብት
ንብረት ያከማቻል።
7"ጌታ ሆይ፤ አሁንስ ወደ ማን ልመልከት?
ተስፋዬ በአንተ ላይ ነው።
8ከኀጢአቴ ሁሉ አድነኝ፤
የሰነፎች መሣለቂያ አታድርገኝ።
9ይህን ያደረግህ አንተ ነህና፣
ዝም እላለሁ፤ አፌንም አልከፍትም።
10ከንድህን አንሣልኝ፤
ከእጅህ ምት የተነሣ ደክሜአለሁና።
11ሰዎችን ስለ ኀጢአታቸው ለመቅጣት
ትገሥጻቸዋለህ፤
ሀብታቸውንም ብል እንደ በላው
ታደርጋለህ፤
በእርግጥ ሰው ሁሉ ተን ብቻ ነው።
ሴላ

38፥17 ቍ7፤ኢዮ 6፥10፤መዝ37፥24
38፥18 ዘሌ26፥40
38፥19 መዝ18፥17፤25፥19፤35፥19
38፥20 ዘፍ44፥4፤ መዝ54፥5፤59፥10፤119፥23፤1ዮሐ3፥12
38፥21 መዝ10፥1፤22፥11፤27፥9፤35፥22፤71፥12፡18፤119፥8
38፥22 1ዜና16፥35፤መዝ22፥19፤40፥13
39፥1 1ነገ2፥4፤ኢዮ 1፥22፤6፥24፤መዝ34፥13፤119፥9፡59፤ምሳ20፥11፤ያዕ1፥26፤3፥2
39፥2 ቍ9፤ኢዮ 31፥34፤መዝ6፥3፤25፥17፤31፥10፤77፥4
39፥3 መዝ1፥2፤48፥9፤77፥12፤119፥15፤ኤር5፥14፤20፥9፤23፥29፤ሉቃ24፥32
39፥4 ዘፍ47፥9፤ ኢዮ7፥7፤14፥2፡5
39፥5 ኢዮ7፥7፤10፥20፤መዝ62፥9፤89፥45፤102፥23
39፥6 ኢዮ8፥9፤27፥17፤መዝ102፥11፤127፥2፤መክ6፥12፤ሉቃ12፥20፤ያዕ1፥11፤4፥14
39፥7 መዝ9፥18፤25፥5
39፥8 ዘዳ28፥37፤ መዝ6፥4፤32፥1፤51፥1፡14፤69፥7፤79፥4፤ኢሳ 43፥28፤53፥5፡8፡10፤ ዳን 9፥16 39፥9 ቍ2፤መዝ 38፥13፤ኢሳ38፥15 39፥10 ዘፀ9፥3፤2ዜና 21፥14፤ሕዝ 7፥9፤24፥16 39፥11 ዘዳ28፥20፤ኢዮ7፥7፤13፥28፤መዝ 90፥7፤94፥10፤ኢሳ26፥16፤51፥8፤66፥15፤ሕዝ5፥15፤ሉቃ12፥33፤ያዕ5፥2፤ 2ጴጥ2፥16

94፥18፤ 121፥13 ይመ)፤ ይህንንም የተናገረው የግል ሕይወቱ በተናጋበት ወይም አስቸጋሪ ሁኔታ በደረሰበት ጊዜ ነው።

*38፥17-20፤* ጤናውን እያጣ በሄደ ቍጥር፣ የጠላቶቹ ጕልበት እያየለ መጣ።

38፥17 *ልወድቅ፤* ሞት የከበበው መሰለው (የ13፥4 ማብ ይመ)።

*38፥18፤* ቍ3-4፤ መዝ32 ይመ።

*38፥19-20፤* ኀጢአት በመሥራቱ ጌታን በድሎአል፤ ነገር ግን አሁን በሚያጠቁት ጠላቶቹ ላይ አንዳች በደል አላደረሰም (የ35፥19 ማብ ይመ)።

38፥20 *መልካሙን፤* በሥነ-ምግባር ረገድ ነቀፋ የሌለበት ማለት ነው (34፥14 ይመ)።

*38፥21-22፤* በመደምደሚያ ላይ በድጋሚ የቀረበ አቤቱታ ነው።

38፥21 *ከእኔ አትራቅ፤* ሆን ተብሎ የሚሠራ ኀጢአት ከሚያስከትለው አስከፊ ነገር ውስጥ አንዱ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትን ማጣት ነው (ከ22፥19፤ 35፥22፤ 71፥12 ጋር ያነጻጽሩ)፤ የእግዚአብሔርን ምሕረት ከተረዱና የመንፈስ ቅዱስም ማደሪያ ከሆኑ በኋላ ሆን ብሎ ኀጢአት መሥራት እጅግ አሳዛኝና መራራም ተሞክሮ ነው።

*መዝሙር 39፤* መዝሙረኛው የሰው ሕይወት እጅግ ከንቱና ምናምንቴ በመሆኑ የተሰማውን ጥልቅ ሐዘን የሚገልጥበት ጸሎት ነው። ይህንንም የተረዳው በፈጸመው ኀጢአት ምክንያት (ቍ8) እግዚአብሔር በሕመም ስለገሠጸው ነው (ቍ10-11)። መዝሙር 38 የሚናገረው መዝሙረኛው በጠላቶቹ ፊት ዝም ስለማለቱ ሲሆን መዝሙር 39 ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት ዝም ስለ ማለቱ ነው። ሁለቱም መዝሙሮች በሕመም ጊዜ (እግዚአብሔር "በገሠጸው" ጊዜ ቍ11፤ 38፥1) የቀረቡ ጸሎቶች ናቸው፤ ሁለቱም መዝሙሮች በደለኛነትን ይቀበላሉ፤ በእግዚአብሔር መታመን ተገቢ መሆኑንም ያስገነዝባሉ። የመዝ40 መግቢያን ይመ። ከዚህም በተጨማሪ ይህ መዝሙር ከመዝ90 ጋር በብዙ ረገድ ተወራራሽነት አለው፤ እንዲሁም መዝሙር 49 ይመ።

39ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ4 የርእስ ማብ ይመ። *ኤዶታም፤* ዳዊት ከነበሩት ሦስት የመዘምራን አለቃ ውስጥ አንዱ ነው (1ዜና16፥41-42፤ 25፥1፡6፤ 2ዜና5፥12፤ በ2ዜና35፥15 ላይ "ባለ ራእዩ" ተብሎአል)። ኤዶታም ምናልባት በ1ዜና6፥44 እና በ15፥19 ላይ "ኤታን" የተባለው ሊሆን ይችላል፤ ይህ ከሆነ ደግሞ አሳፍ የጌድሶን ቤተ ሰብ ተጠሪ ኤማን ደግሞ የቀዓት ቤተ ሰብ ተጠሪ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ኤዶታምም የሜራሪ ቤተ ሰብ ተጠሪ ሊሆን ይችላል፤ እነዚህ ሁሉ የሌዊ ወንዶች ልጆች ናቸው (1ዜና 6፥16፡33፡39፡43-44 ይመ)። የመዝ62፤ 77፤ 89 ርእስን ይመ።

*39፥1-3፤* የመዝሙሩ መግቢያ ነው፤ ምንም ነገር ላለመናገር ቢወስንም፣ ሥቃዩን እስከ መጨረሻው አፍኖ መቀመጥ አልቻለም።

*39፥1፤* የክፉዎች ንግግር አስቈጥቶት መጥፎ ነገር እንዳይናገር ለአንደበቱ ልጓም አደረገለት (መዝ 73 ይመ)።

*39፥2-3፤* ታምቆ የተቀመጠ ሥቃይ ሕመምን ያባብሳል እንጂ ምንም መፍትሔ አያመጣም (ኤር20፥9)።

*39፥4-6፤* የሰው የሕይወት ዘመን አጭር መሆኑን እንዲያስተውልና ይህንንም በጸጋ እንዲቀበል የቀረበ ጸሎት ነው።

39፥4 *የዘመኔንም ቍጥር፤* 78፥39 እና የ37፥20 ማብ ይመ።

39፥5 *በፊትህ እንደ ኢምንት፤* 90፥4 ይመ። *ተን፤* ቍ11፤ 144፥4፤ ኢዮ14፥2፤ መክ6፥12 ይመ።

*39፥6፤* የመጽሐፈ መክብብ ማጠቃለያ በመሆን ሊያገለግል ይችላል።

*39፥7-11፤* በተሰበረ ልብ የቀረበ ጸሎት ነው፤ መዝሙረኛው የሚለምነው እግዚአብሔር አለንጋውን እንዲያነሳለት ብቻ ነው።

39፥8 *አድነኝ፤* ከጠላቶቼ ታደገኝ ማለቱ ነው። *የሰነፎች መሣለቂያ፤* እግዚአብሔር ካልታደገው በቀር በዐመፀኞችና በሰነፎች እጅ (14፥1 ይመ) መሣለቂያ መሆኑ አይቀርም (22፥7-8፤ 69፥6-12 ይመ)።

39፥10 *ከእጅህ ምት፤* 32፥4፤ 38፥2 ይመ።

39፥11 *ለመቅጣት ትገሥጻቸዋለህ፤* 6፥1፤ 38፥1 ይመ። *በእርግጥ ተን፤* ኢሳ2፥22 እና ማብ ይመ፤ ቍ1፤ 144፥4፤ ኢዮ 14፥2፤ መክ6፥12 ይመ።

*39፥12-13፤* በተሰበረ ልብ የቀረበው ጸሎት ከቀድሞው

12"እግዚአብሔር ሆይ፤ ጸሎቴን ስማ፤
ጩኸቴን አድምጥ፤
ልቅሶዬንም ቸል አትበል፤
በአንተ ፊት እኔ መጻተኛ ነኝና፤
እንደ አባቶቼም እንግዳ ነኝ::
13ላለመመለስ ከመሰናበቴ በፊት፣
ዳግመኛ ደስ ይለኝ ዘንድ ዐይንህን
ከላዬ አንሣ::

## መዝሙር 40

### የምስጋናና የርዳታ ልመና ጸሎት

40፥13-17 ተጓ ምብ-መዝ70፥1-5

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር*

1እግዚአብሔርን ደጅ ጠናሁት፤
እርሱም ዘንበል አለልኝ፤ ጩኸቴንም
ሰማ::
2ከሚውጥ ጕድጓድ፣
ከሚያዘቅጥ ማጥ አወጣኝ፤
እግሮቼን በዐለት ላይ አቆመ፤
አካሄዴንም አጸና::
3ለአምላካችን የሚሆን ውዳሴ፣
አዲስ ዝማሬን በአፌ ላይ አኖረ፤
ብዙዎች ያያሉ፤ ይፈራሉም፤
በእግዚአብሔር ይታመናሉ::
4እግዚአብሔርን መታመኛው ያደረገ፣
ወደ ትዕቢተኞች የማይመለከት፣
የሐሰት አማልክትን[ጠ] ወደሚከተሉት
የማያይ፣
ሰው ብፁዕ ነው::
5እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤
አንተ ያደረግኸው ድንቅ ነገር ብዙ
ነው፤
ለእኛ ያቀድኸውን፣
ሊዘረዝርልህ የሚችል ማንም የለም፤
ላውራው ልናገረው ብል፣
ስፍር ቍጥር አይኖረውም::
6መሥዋዕትንና ቍርባንን አልፈለግህም፤
ጆሮቼን ግን ከፈትህ፤[ጨ]
የሚቃጠል መሥዋዕትን፣
የኀጢአትንም መሥዋዕት አልሻህም::
7እኔም እንዲህ አልሁ፤ "እነሆ፤ መጥቻለሁ፤
ስለ እኔ በመጽሐፍ ተጽፎአል፤
8አምላኬ ሆይ፤ ፈቃድህን ላደርግ እሻለሁ፤
ሕግህም በልቤ ውስጥ አለ::"
9በታላቅ ጉባኤ ውስጥ ጽድቅን አበሠርሁ፤

39፥12 ዘፍ23፥4፤ 47፥9፤ዘሌ25፥23፤ዘዳ 1፥45፤2ነገ20፥5፤1ዜና 29፥15፤መዝ17፥1፤ ዕብ 11፥13
39፥13 ኢዮ10፥21
40፥1 መዝ6፥9፤ 31፥22፤34፥15፤37፥7፤116፥1፤145፥19
40፥2 ኢዮ9፥31፤ 30፥19፤መዝ7፥15፤27፥5፤31፥8፤69፥14
40፥3 ዘፀ14፥31፤መዝ 28፥7፤52፥6፤64፥9፤9 6፥1፤ራእ5፥9
40፥4 ዘዳ31፥20፤ መዝ4፥2፤26፥1፤34፥8፤84፥12፤101፥5፤138፥6፤ምሳ3፥34፤16፥5፤ ኢሳ65፥5፤1ጴጥ5፥5
40፥5 ዘዳ4፥34፤ መዝ 71፥15፤75፥1፤ 105፥5፤136፥4፤ 139፥17:18
40፥6 ዘፀ21፥6፤1ሳሙ 15፥22፤መዝ50፥8፤ 51፥16፤ኢሳ1፥11፤ ኤር 6፥20፤ሆሴ6፥6፤ አሞ5፥22
40፥7 ኢዮ19፥23፤ ኤር36፥2፤45፥1፤ሕዝ 2፥9፤ዘካ5፥1
40፥8 ዘዳ6፥6፤ ኢዮ 22፥22፤ማቴ26፥39፤ ሮሜ7፥22፤ዕብ10፥5-7
40፥9 ኢሱ22፥22፤ መዝ22፥25:31

[ጠ]4 ወይም *ሐሰትን ወደሚከተሉት* ተብሎ መተርጐም ይችላል::
[ጨ]6 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ግን፣ *አካልን ግን አዘጋጀህልኝ* ይላል::

ይልቅ አጅግ በተሰበረ ልብ በድጋሜ ቀርቦአል::

39፥12 ***መጻተኛ እንግዳ፤*** በዚህ ዓለም በእግዚአብሔር ፊት ሲመላለስ ኑሮውን ሁሉ የሚያየው እንደ ስደተኛ ወይም እንደ መጻተኛ ነው::

39፥13 ***ዐይንህን ከላዬ አንሣ፤*** ኢዮ7፥17-19፤ 10፤20-21፤ 14፥6 ይመ:: ***ዳግመኛ ደስ ይለኝ ዘንድ፤*** ኢዮ9፥27፤ 10፥20 ይመ:: ***ከመሪሳቴ በፊት፤*** ከሞት ባሻገር ስላለው ዓለም::

***መዝሙር 40፤*** አስጨናቂ መከራ በከበበው ጊዜ ያቀረበው ጸሎት ነው:: የሐዘኑ መንሥኤ ምን እንደ ሆነ በውል አልተጠቀሰም፤ ዳዊት ግን በመዝ38-39 እና 41 ላይ እንዳስታወቀው፣ ይህ ሁሉ መከራ የደረሰበት በፈጸመው ኀጢአት ምክንያት መሆኑን (ቍ 12 ይመ) ተገንዝቦአል፤ (የመዝ39 እና 41 መግቢያን ይመ):: ሥቃዩ የተባባሰበት ጠላቶቹ በእርሱ ሥቃይ በመደሰታቸውና በመጓደዳቸው ምክንያት ነው፤ ይህ ርእስ ጕዳይ በዚህ መዝሙርና በመዝሙር 38-39 ላይ በዐቢይ ርእስ ጕዳይነት ተንጸባርቆአል (የመዝ6ን መግቢያ ይመ):: ጸሎቱ የሚጀምረው እግዚአብሔር ከዚህ ቀደም ስላደረገለት ምሕረት ምስጋና በማቅረብና (ቍ 1-5) ለእግዚአብሔርም ያሳየውን ታማኝነት በመግለጽ ነው (ቍ 6-10):: መዝሙረኛው እግዚአብሔር ረዳቱ እንዲሆን ልመናውን የሚያቀርበው እነዚህን ሁለት ጕዳዮች መሠረት በማድረግ ነው (ቍ 11-17):: በመዝ44 እና 89 ላይ የተመለከተውን ረዘም ያለ የጸሎት መግቢያ ይመ:: መዝ70 በዚህ ምዕራፍ በቍ13-17 ላይ ከሚገኘው ሐሳብ ጋር ተመሳሳይነት አለው::

40ርእስ፤ ***ለመዘምራን አለቃ፤*** የመዝ 4 የርእስ ማብ ይመ::

***40፥1-5፤*** እግዚአብሔር ከዚህ ቀደም ስላደረገው ምሕረት የቀረበ ምስጋና ነው (የመዝ9ን መግቢያ ይመ)::

***40፥1-3፤*** ዳዊት በገጠመው ታላቅ መከራ ጊዜ እግዚአብሔር ያሳየው ቸርነት ለእግዚአብሔር ምስጋና እንዲያቀርብና ሌሎችንም ወደ እምነት እንዲመራ አነቃቅቶታል (የ7፥17 እና 9፥1 ማብ ይመ)::

***40፥2፤*** መዝ 30፥1 እና ማብ ይመ::

40፥3 ***አዲስ ዝማሬን፤*** የ33፥3 ማብ ይመ:: ***ብዙዎች ያያሉ፤*** ዳዊት ካቀረበው ምስጋና የተነሣ ነው (18፥49፤ 22፥22-31 ይመ፤ እንዲሁም የ9፥1 ማብ ይመ):: ***ይፈራሉም፤*** የ34፥8-14 ማብ ይመ::

***40፥4-5፤*** እግዚአብሔርን በእርሱ ለሚታመኑ ሁሉና (ቍ 4) ለሕዝቡም ለእስራኤል (ቍ 5) ያለውን ቸርነት ያሳያል::

***40፥4፤*** ኤር17፥7 ይመ:: በእርሱ የሚታመኑ ሁሉ የተባረኩ በመሆናቸው፣ ለጌታ የቀረበ ምስጋና ነው (32፥1-2፤ 146፥5 ይመ):: ***ትዕቢተኞች፤*** የ31፥23 ማብ ይመ:: ***ብፁዕ፤*** የ1፥1 ማብ ይመ::

40፥5 ***ድንቅ ነገር፤*** የ9፥1 ማብ ይመ:: ***ያቀድኸውን፤*** እግዚአብሔር ለእስራኤል ያሰበውንና ያቀደውን ነገር ሁሉ የሚያደርገው አስቀድሞ በወሰነው መሠረት ነው (ኢሳ 25፥1፤ 46፥10-11 ይመ)::

***40፥6-8፤*** ዳዊት ለእግዚአብሔር ፈቃድ ምን ያህል ተገዥ እንደ ሆነ ያሳያል፤ የዕብ10፥5-10 ጸሓፊ በዚህ ቦታ የተጠቀሱትን ነገሮች ለክርስቶስ ተጠቅሞባቸዋል (ማብ በዚያው ቦታ ይመ)::

40፥6 ***መሥዋዕትንና ቍርባንን ... አልሻህም፤*** መዝሙረኛው እግዚአብሔር በሕጉ ላይ ያስታወቃቸው የመሥዋዕትና የመንጻት ሥርዐቶች በራሳቸው ብቁ እንዳልሆኑና ራስን ከልብ ለእግዚአብሔር መስጠትንና ለእርሱም ብቻ ታማኝ መሆንን ሊተኩ እንደማይችሉ ተረድቶአል (1ሳሙ15፥22፤ ኢሳ1፥11-17፤ ኤር7፥22-23፤ ሚክ6፥6-8):: ልክ እንዲሁ የአዲስ ኪዳን አማኝ ራሱን ከልብ ለእግዚአብሔር ሳይሰጥ የውሃ ጥምቀትን ሊወስድ፣ የጌታ እራትን ሊካፈልና በመዝሙርና በአምልኮም ሥርዐቶች ላይ ንቁ ተሳታፊ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን የትኛውም ሃይማኖታዊ ሥርዐት ለእግዚአብሔር ያለንን ታማኝነትና ታዛዥነት ሊተካ አይችልም፤ ከእምነት የሆነ መታዘዝ ከሌለ ሁሉም ሥርዐት ብቻ ሆኖ ይቀራል (ከሮሜ1፥5 ጋር ያነጻጽሩ)::

40፥7 ***እነሆ መጥቻለሁ፤*** ምናልባት ዳዊት በንግሥናው ወቅት ራሱን ለጌታ አሳልፎ የሰጠበትን ሁኔታ ሊያመለክት ይችላል:: ***ስለ እኔ በመጽሐፍ ተጽፎአል፤*** አንዳንዶች በዘዳ 17፥14-15 ላይ ያለውን ትንቢት ሳያመለክት አይቀርም ይላሉ፤ ይሁን እንጂ የዚህ መዝሙር ዐውደ ንባብ በእጅጉ የሚያመለክተው "መጽሐፍ" የሚለው ቃል አንድ ንጉሥ በሚነግሥበት ወቅት የግዛቱ መተዳደሪያና ቃል ኪዳንም አድርጎ የሚይዘውን የሕጉን ቅጅ ነው (ዘዳ17፥18-20፤ 2ነገ11፥12 ይመ፤ ከ1ነገ2፥3 ጋር ያነጻጽሩ)::

40፥8 ***ሕግህም በልቤ ውስጥ አለ፤*** እግዚአብሔር ሊያየው የሚመኘው "ከእምነት የሆነ መታዘዝ" ፈቃዱን ለማድረግ ደስ የሚለውን እምነትና ሕጉንም በልቡ ውስጥ ለመስወር ደስ የሚለውን እምነት ነው (ከ119፥11፤ ከዮሐ15፥17 ጋር ያነጻጽሩ)::

***40፥9-10፤*** የዳዊት ሕይወት በምስጋና መሞላቱንና የእግዚአብሔርንም ታማኝነትና ምሕረት ዘወትር ለማወጅ መነሣቱን ያሳያል:: እግዚአብሔር ከእንስሳት መስዋዕት አብልጦ የሚወደው እንዲህ ያለውን መሥዋዕት ነው (50፥7-15:23 ይመ)::

40፥9 ***በታላቅ ጉባኤ፤*** የ1፥5 እና የ9፥1 ማብ ይመ:: ***ጽድቅን፤*** የ4፥1 ማብ ይመ:: ***አበሠርሁ፤*** 68፥11፤ 96፥2 ይመ፤ የምሥራች ቃል አድርጌ እናገረዋለሁ ማለቱ ነው (1ነገ1፥42፤ ኢሳ40፥9፤

እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ
እንደምታውቀው፣
ከንፈሮቼን አልገጠምሁም::
10ጽድቅህን በልቤ አልሸሸግሁም፤
ታማኝነትህንና ማዳንህን እናገራለሁ፤
ምሕረትህንና እውነትህን፣
ከታላቅ ጉባኤ አልደበቅሁም::
11እግዚአብሔር ሆይ፤ ምሕረትህን
አትንፈገኝ፤
ቸርነትህና እውነትህ ዘወትር ይጠብቁኝ፤
12ስፍር ቍጥር የሌለው ክፋት ከቦኛልና፤
የኀጢአቴ ብዛት ስለ ያዘኝ ማየት
ተስኖኛል፤
ከራሴ ጠጕር ይልቅ በዝቶአል፤
ልቤም ከድቶኛል::
13እግዚአብሔር ሆይ፤ ታድነኝ ዘንድ
ፈቃድህ ይሁን፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ እኔን ለመርዳት
ፍጠን::
14ነፍሴን ለመንጠቅ የሚፈልጉ፣
ይፈሩ፤ ይዋረዱም፤
ጕዳቴንም የሚሹ፣
ተዋርደው በመጡበት ይመለሱ::
15በእኔ ላይ፣ "እሰይ! እሰይ!" የሚሉ፣
በራሳቸው እፍረት ይደንግጡ::
16አንተን የሚፈልጉ ሁሉ ግን፣
ሐሤት ያድርጉ፤ በአንተም ደስ
ይበላቸው፤
ዘወትር የአንተን ማዳን የሚወዱ፣
"እግዚአብሔር ከፍ ከፍ ይበል" ይበሉ::

40፥10 መዝ22፥22 ፤89፥1
40፥11 መዝ26፥3፤ 61፥7፤ምሳ20፥28፤ዘካ 1፥12
40፥12 መዝ25፥17 ፤38፥4፤65፥3፤69፥4፤7 3፥26
40፥13 መዝ22፥19 ፤38፥22
40፥14 1ሳሙ20፥1 ፤አስ9፥2፤መዝ35፥4: 26
40፥15 መዝ35፥21
40፥16 ዘዳ4፥29፤ 1ዜና28፥9፤መዝ9፥2: 10፤35፥27፤119፥2
40፥17 መዝ18፥2፤ 20፥2፤86፥1፤109፥22 ፤119፥60፤144፥3
41፥1 ዘዳ14፥29፤ ኢዮ24፥4፤25፥17
41፥2 ዘዳ6፥24፤ዕዝ 9፥9፤መዝ12፥5፤32፥7 ፤37፥22፤71፥20፤119 ፥88፤159፤138፥7፤14 3፥11
41፥3 2ሳሙ13፥5 ፤2ነገ1፥4፤መዝ6፥6
41፥4 ዘዳ32፥39 ፤6፥2፤9፥13፤51፥4
41፥5 መዝ38፥12
41፥6 ዘሌ19፥16፤ መዝ12፥2፤101፥7፤ ምሳ26፥24፤ማቴ5፥11

17እኔ ድኻና ችግረኛ ነኝ፤
ጌታ ግን ያስብልኛል::
አንተ ረዳቴና አዳኜ ነህ፤
ስምላኬ ሆይ፤ አትዘግይ::

## መዝሙር 41

### የሕመምተኛና የብቸኛ ሰው ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር*

1ለድኾች የሚያስብ ሰው ምስጉን ነው፤
እርሱንም እግዚአብሔር በክፉ ቀን
ይታደገዋል::
2እግዚአብሔር ይጠብቀዋል፤ በሕይወትም
ያኖረዋል፤
በምድርም ላይ ይባርከዋል፤
ለጠላቶቹም ምኞትም አሳልፎ
አይሰጠውም::
3ታሞ ባለበት ዐልጋ ላይ እግዚአብሔር
ይንከባከበዋል፤
በበሽታውም ጊዜ መኝታውን
ያነጥፍለታል::
4እኔም፣ "እግዚአብሔር ሆይ፤ ምሕረት
አድርግልኝ፤
አንተን በድያለሁና ነፍሴን ፈውሳት"
አልሁ::
5ጠላቶቼ በክፋት በመናገር፣
"የሚሞተው መቼ ነው? ስሙስ
የሚደመሰሰው ምን ቀን ነው?"
ይላሉ::
6ሊጠይቀኝ የሚመጣ ቢኖር፣
በልቡ ስድብ እያጠራቀመ፣ ከዐንገት
በላይ ይናገራል፤

41፥27፤ 52፥7፤ 61፥1 ይመ):: *ከንፈሮቼንም አልገጠምሁም፤* እግዚአብሔርን ከማመስገን አይቈጠብም (38፥13-16፤ 39፥1 እና ማብ ይመ)::

40፥10 *በልቤ፤* የ4፥7 ማብ ይመ:: *ምሕረትህንና እውነትህን፤* የ26፥3 ማብ ይመ::

*40፥11-17፤* ርዳታን ለማግኘት የቀረበ ጸሎት ነው::

40፥11 *ቸርነትህና እውነትህ፤* በቤተ መቅደስ ውስጥ ለሁሉም ያውጅ የነበረውን ማለት ነው (ቍ10እና ማብ ይመ)::

40፥12 *የኀጢአቴ ብዛት ስለያዘኝ፤* "ስፍር ቍጥር የሌለው ችግር እንደ ከበበው" ሁሉ የኀጢአትም ብዛት አስጨንቆታል (መዝ38-39 እና መግቢያቸውን ይመ):: *ማየት ተስኖኛል፤* የ13፥3 ማብ ይመ:: *ከራሴ ጠጕር ይልቅ፤* ማቴ10፥30፤ ሉቃ 12፥7 ይመ:: *ልቤም፤* የ4፥7 ማብ ይመ::

*40፥14-15፤* በመዝ38፥12፤ 39፥8፤ 41፥5:7 ላይ እንደ ተገለጸው በሚያስጨንቅ ችግር ውስጥ እያለ እንኳን ጠላቶቹ አያርፉለትም (የ5፥9 ማብ ይመ):: በዳዊት መዝሙር ውስጥ ይህ ሁኔታ በተደጋጋሚ ተወስቶአል:: እርሱን ለማዋረድ ደፋ ቀና የሚሉ ሁሉ እነርሱም ይዋረዱ (የ5፥10 ማብ ይመ)::

40፥15 *እሰይ! እሰይ!* የ3፥2 ማብ ይመ::

40፥17 *ድኻና ችግረኛ፤* የእግዚአብሔርን ርዳታ በብርቱ ይሻል (የ34፥6 ማብ ይመ)::

*መዝሙር 41፤* ዳዊት በጠና በታመመ ጊዜ ምሕረትን ያገኝ ዘንድ ያቀረበው ጸሎት ነው፤ ሕመሙ ከፈጸመው ኀጢአት ጋር ዝምድና እንዳለው ተገንዝቦአል (ቍ4)፤ የመዝሙር 38-40 መግቢያን ይመ:: ጠላቶቹ ብቻ ሳይሆኑ "ወዳጆቼ" (ቍ9) የሚላቸውም እንኳ ሞቱን ይመኙለት ነበር (የ5፥9 ማብ ይመ)፤ ከሁሉ ግን የልብ ወዳጁ ያላቸው ሳይቀሩ በእርሱ ላይ በባላጋራነት መነሣታቸው እጅጉን አሳዝኖታል (የ31፥11-12 ማብ ይመ):: ይህ መዝሙር ተመሳሳይ ፍሬ ሐሳብ ላላቸው አራት መዝሙሮች መደምደሚያ ከመሆኑም በላይ "የአንደኛ መጽሐፍ" መዝጊያ በመሆንም ያገለግላል (ይህ አንደኛ መጽሐፍ "ምስጉን ነው" በሚለው ሐረግ ጀምሮ በዚሁ ይደመድማል):: ባወቃቀር ረገድ ሲታይ ይህ መዝሙር እኩሌል ሲሆን፣ እያንዳንዳቸው ሦስት ሦስት ስንኞች ባሏቸው በአራት አንጓዎች የተከፈለ ነው:: አንደኛውና አራተኛው አንጓ የመዝሙረኛው ጸሎት ከልብ የቀረበ መሆኑን ያሳያሉ፤ ሁለተኛውና ሦስተኛው አንጓ የጸሎቱን ፍሬ ሐሳብ የበለጠ ያብራራሉ:: ቍ13 የዚህ መዝሙር አካል ባይሆንም "አንደኛ መጽሐፍን" በምስጋና ይደመድማል (የቍ13 ማብ ይመ)::

41ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* በመዝሙር 4 ርእስ ላይ የተሰጠውን ማብ ይመ::

*41፥1-3፤* እግዚአብሔር ጤናውን እንደሚመልስለት በእርግጠኝነት የተናገረበት ቦታ ነው::

41፥1 *ለድኾች የሚያስብ ምስጉን ነው፤* በተለይ ንጉሥ ከሆነ ለደካሞች ቋሚ ጠበቃ መሆን አለበት (72፥2:4:12-14፤ 82፥3-4፤ ምሳ29፥14፤ 31፥8-9፤ ኢሳ11፥4፤ ኤር22፥16 ይመ):: *ምስጉን፤* የ1፥1 ማብ ይመ:: እግዚአብሔር "ለደካሞችና ለረዳት የለሾች ልዩ ጥንቃቄ ያደርግላቸዋል፤ ለእንዲህ ላሉ ወገኖች የሚራሩትንም ይባርካቸዋል፤ የቍ1-3 ሐሳብን ስናብራራው እንዲህ ማለት ይሆናል "ምሕረት የሚያደርጉ ምስጉኖች ናቸው ይማራሉና" (ማቴ5፥7)፤ ከእግዚአብሔር ርኅራኄ ጋር በመተባበር ሌሎችን በችግራቸው የምንረዳ ከሆነ እኛም መከራ በገጠመን ጊዜ እግዚአብሔር ይረዳናል (ቍ1)፣ ከጕዳት ይጠብቀናል (ቍ2)፣ ይባርከናል (ቍ2)፣ የሰይጣንን ኀይልና የጠላቶቻችንን ዛቻ ይደመስስልናል (ቍ2)፣ በታመምንም ጊዜ ከአጠገባችን ሆኖ ፈውስን ይሰጠናል (ቍ3 ይመ፤ ከ72፥2:4:12፤ ከዘዳ15፥7-11፤ ከምሳ 29፥14፤ ከኢሳ11፥4፤ ከኤር22፥16 ጋር ያነጻጽሩ)::

*41፥4-6፤* እግዚአብሔር ምሕረት እንዲያደርግና ፈውስም እንዲሰጥ የሚያሳስብ ጸሎት ነው::

41፥4 *በድያለሁና፤* የ32፥3-5 ማብ ይመ::

41፥5 *የሚሞተው መቼ ነው?* የ3፥2 ማብ ይመ:: *ስሙስ የሚደመሰሰው፤* የ9፥5 ማብ ይመ::

41፥6 *ሊጠይቀኝ፤* ታሞ በተኛ ጊዜ ሊጐበኘው የመጣውን ማለት ነው:: *ወሬም ይነዛል፤* የልብ ወዳጁ እንደ ሆነ ሰው ይናገ

ወጥቶም ወሬ ይነዛል።

[7]ጠላቶቼ ሁሉ ግንባር ፈጥረው
ይንሾካሾኩብኛል፤
እንዲህ እያሉም፣
የከፋ ነገር በላዬ ያውጠነጥናሉ፤
[8]“ክፉ ደዌ ይዞታል፤
ከእንግዲህም ከተኛበት አይነሣም።”
[9]እንጀራዬን ተካፍሎኝ የበላ፣
የምተማመንበትም የቅርብ ወዳጄ፣
በእኔ ላይ ተረከዙን አነሣ።

[10]*እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ግን ምሕረት
አድርግልኝ፤*
የእጃቸውን እንድከፍላቸው አስነሣኝ።
[11]ጠላቴ በላዬ ድል አላገኘምና፣
እንደ ወደድኸኝ በዚህ አወቅሁ።
[12]ስለ ጭንቀቴ ደግፈህ ይዘኸኛል፤
በፊትህም ለዘላለም ታኖረኛለህ።

[13]የእስራኤል ስምላክ *እግዚአብሔር*፣
ከዘላለም እስከ ዘላለም የተባረከ ይሁን፤
አሜን፤ አሜን።

## ሁለተኛ መጽሐፍ
## ከመዝሙር 42-72

## መዝሙር 42[a]

### በስደት ላይ ያለ ሌዋዊ ልቅሶ

*ለመዘምራን አለቃ፤ የቆሬ ልጆች ትምህርት።*

[1]ዋላ የምንጭ ውሃ እንደምትናፍቅ፣
ስምላክ ሆይ፤ ነፍሴም እንዲሁ አንተን
ትናፍቃለች።
[2]ነፍሴ ስምላክን፣ ሕያው ስምላክን ተጠማች፤
መቼ ነው ደርሼ፣ የስምላክን ፊት
የማየው?
[3]ሰዎች ቀኑን ሙሉ፣
“ስምላክህ የት አለ?” ባሉኝ ቍጥር፣
እንባዬ ቀንና ሌሊት፣
ምግብ ሆነኝ።
[4]ነፍሴ በውስጤ እየፈሰሰች፣
እነዚህን ነገሮች አስታወስሁኝ፤
ታላቅ ሕዝብ ወደ ስግዚስብሔር ቤት እየመራሁ፣
በእልልታና በምስጋና መዝሙር፣
በአእላፍ ሕዝብ መካከል፣
እንዴት ከሕዝቡ ጋር እሄድ እንደ
ነበር ትዝ አለኝ።
[5]ነፍሴ ሆይ፤ ለምን ትተክዢያለሽ?
ለምንስ በውስጤ ትታወኪያለሽ?

41፥7 መዝ71፥10
41፥8 2ነገ1፥4
41፥9 ዘኍ30፥2፤ 2ሳሙ15፥12፤ኢዮ 19፥14፡19፤መዝ55፥ 20፤89፥34፤ማቴ26፥ 23፤ሉቃ22፥21፤ዮሐ 13፥18
41፥10 ቍ4፤2ሳሙ 3፥39፤መዝ3፥3፤9፥13
41፥11 ዘኍ14፥8፤ መዝ25፥2
41፥12 ኢዮ4፥7፤ መዝ18፥35፤21፥6፤25 ፥21፤37፥17፤61፥7፤6 3፥8
41፥13 ዘፍ24፥27፤ መዝ72፥18፡19፤89፥5 2፤106፥48
42፥1 ዘዳ10፥7ኢዮ 19፥27፤መዝ18፥33፤ 119፥131፤ኢል1፥20
42፥2 ኢሱ3፥10፤ 1ሳሙ14፥39፤መዝ43 ፥4፤63፥1፤84፥7፤143፥ 6፤ማቴ16፥16፤ሮሜ 9፥26
42፥3 ቍ10፤ኢዮ 3፥24፤መዝ79፥10፤11 5፥2፤ኢል2፥17፤ሚክ 7፥10
42፥4 ኢሱ6፥5፤ 1ሳሙ1፥15፤ዕዝ3፥13 ፤መዝ35፥18፤ 55፥14
፤95፥2፤100፥4፤109፥30፤122፥1፤147፥7፤ኢሳ2፥2፤30፥29፤ዮና2፥9
42፥5 ኢዮ20፥2፤መዝ9፥1፤18፥46፤25፥5፤38፥6፤71፥14፤77፥3፤ ሰቆ3፥20፤ማቴ 26፥38

[a]ም42 በብዙ የዕብራይስጥ ቅጆች መዝሙር42 እና 43 አንድ መዝሙር ነው።

ራል። *በልቡ፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

*41፥7-9፤* ጠላቶቹና ወዳጁ ነን የሚሉ ሁሉ በአንድነት እንደተነሱበት የሚናገርበት ክፍል ነው።

41፥9 *እንጀራዬን ተካፍሎኝ፤ ... የምተማመንበት ወዳጄ፤* ከንጉሥ ጋር በአንድ ማዕድ የሚሳተፍ ሰው የተከበረና የታመነ ወዳጅ ነው (የ31፥11-12 ማብ ይመ)። መዝሙረኛው በዚህ ቦታ የሚናገረው ወዳጅነቱን በቃል ኪዳን ያተመውን ሰው ሳይሆን አይቀርም (የ23፥5 ማብ ይመ)። ኢየሱስ በዚህ ቍጥር ላይ የተመለከተውን ከራሱ ሕይወት ጋር እንዴት እንዳገናኘው ዮሐ13፥18 ይመ። እንደ ንጉሥ ዳዊት ሁሉ ከዳዊት ወገን የሆነው ይህ ታላቅ ልጅ ከሰዎች ጥላቻ ደርሶበታል፤ ታማኝ ወዳጆቼ የሚላቸውም ከድተውታል፤ በዚህም የአባቱን የዳዊት መከራ ተካፋይ ሆኖአል።

*41፥10-12፤* በልበ ሙሉነት የቀረበ ጸሎት ነው።

41፥10 *የእጃቸውን እንድከፍላቸው፤* ንጉሥ እንደ መሆኑ መጠን ላደረሱበት በደል ብድራቸውን እንድከፍል ማለቱ ነው።

41፥12 *ይዘኸኛል ... ታኖረኛለህ፤ ታጽናኛለህ።* *በፊትህም፤* የእስራኤል ሰማያዊ ንጉሥ አገልጋይ በመሆን ማለት ነው (አባባሉ ፈሊጣዊ አነጋገር መሆኑን ለመመልከት 101፥7፤ 1ሳሙ16፥22፤ 1ነገ10፥8፤ 17፥11 ይመ)። *ለዘላለም፤* በእግዚአብሔር ፊት እንዳይኖር የሚያደርገው አንዳች ኀይል የለም (2ሳሙ7፥15-16 ይመ)።

*41፥13፤* ለአምልኮ የተሰበሰበው ሕዝብ ‘በአንደኛ መጽሐፍ’ ላይ ለተባሉት ነገሮች ምላሻቸውን እንዲሰጡ የሚጋብዝ ቃለ-ውዳሴ ነው (72፥18-19፤ 89፥52፤ 106፥48፤ 150 ይመ)።

*መዝሙር 42-43፤* ከአስጨናቂ ጠላቶች እጅ ለመዳንና (42፥9፤ 43፥2) በእግዚአብሔርም ቤተ መቅደስ ውስጥ ተመልሶ ለመኖር የቀረበ ጸሎት ነው፤ እነዚህ ሁለት መዝሙሮች (ምንም እንኳ በሰብዐ ሊቃናት ትርጕም እንደ ሁለት መዝሙር ሆነው ቢቀርቡም) በአንድ ትንፋሽ የተነገሩ መሆናቸውን ልዩ ከሆነው አወቃቀራቸውና ከሚያስተሳልፉትም ተመሳሳይ ፍሬ ሐሳብ መረዳት ይቻላል። መዝ 43 ከመዝ 42 እንዲለይ የተደረገው ለተለየ የቅዳሴ ሥርዐት ሲባል ሊሆን ይችላል (የመዝ9ን መግቢያ ይመ)። የዚህ መዝሙር ተናጋሪ ከቆሬ ወገን የሆነና በቤተ መቅደሱም ውስጥ የቅዳሴ አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ሳይሆን አይቀርም (42፥4 እና የ42 ርእስ ማብ ይመ)። “እግዚአብሔርን የማይፈራ ሕዝብ” (43፥1) የተባሉት የመዝሙሩ ደራሲ ተማርኮ የሄደባቸው ሕዝቦች ሊሆኑ ይችላሉ (2ነገ12፥17-18 ይመ)። ይህ መዝሙር የመዝሙረኛው “ሁለተኛ መጽሐፍ” መጀመሪያ ሲሆን ይህ ሁለተኛ መጽሐፍ ከአንደኛው መጽሐፍ የሚለየው “ኤሎሂም” የሚለው የዕብራይስጥ ቃል በሁለተኛው መጽሐፍ ውስጥ በተደጋጋሚ መጠቀሱ ነው፤ በአንደኛው መጽሐፍ ውስጥ በተደጋጋሚ የተጠቀሰው ቃል “ያህዌ” የሚለው ነው። በአወቃቀር ረገድ ሲታይ የዚህ መዝሙር ሦስት አንጓዎች እኩኩል ሲሆኑ (እያንዳንዱ አንጓ አራት አራት ስንኞች አሉት) እያንዳንዱም አንጓ በተመሳሳይ አዝማቾች ተቀንብቦአል (42፥5፡11፤ 43፥5)። በመካከል ላይ ያለው አንጓ ግን እያደገ የመጣውን ሐሳብ በማቋረጥ እግዚአብሔርን ስለመታመን ያወሳል። ከአዝማቾቹ በስተቀር ጸሎቱ የተቀነበበው የእግዚአብሔርን መገኘት በመናፈቅና (42፥1) በመሠዊያው ፊት እግዚአብሔርን ለማመስገን ቃል በመግባት ነው (43፥4)። የዚህ ዐይነት አዝማች አወቃቀር ያላቸውን መዝሙሮች ለማየት 46፤49፤59፤80፤107 ይመ።

42ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ 4 የርእስ ማብ ይመ። *የቆሬ ልጆች፤* ወይም “ለቆሬ ልጆች” ለኤዶታም የመዝ39 ርእስን ይመ። “የቆሬ ልጆች” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ከቆሬ ወገን የሆኑትን ሌዋዊ መዘምራን ሲሆን በቅዳሴ ሥርዐት ላይ እንዲያገለግሉ የተሾሙት በዳዊት ነው። የቆሬ ወገኖች የሚወክሉት የሌዊን ልጅ የቀሐትን ቤተ ሰብ ነው። አሳፍ የጌርሶናውያን፣ ኤዶታም ደግሞ የመራሬ መዘምራን አለቃ እንደ ነበሩ ሁሉ፣ ኤማንም በዳዊት ዘመነ መንግሥት የቆሬ መዘምራን አለቃ ነበር (1ዜና6፥31-47 እንዲሁም የመዝ39 እና 88 ርእስን ይመ)። “በቆሬ ልጆች” ስም ከሚጠሩት ሰባት መዝሙሮች ውስጥ ይህ መዝሙር የመጀመሪያው ነው (42፥49)፤ ሌሎች አራት መዝሙሮች ደግሞ በሦስተኛው መጽሐፍ ውስጥ ይገኛሉ (መዝ 84-85፤ 87-88)።

*42፥1-4፤* በቤተ መቅደስ ውስጥ በእግዚአብሔር ፊት ለመሆን ያለውን ጉጉት ያመለክታል።

42፥1 *ዋላ የምንጭ ውሃ ለማግኘት እንደሚናፍቅ፤* ዋላ በተለይ አዳኞች በከበቡት ጊዜ ከምንጭ ውሃ ለመጠጣት እንደሚጓጓ ሁሉ መዝሙረኛውም አሳዳጆቹ ባየሉበት ጊዜ እግዚአብሔርን ለማየት ተጠምቶአል።

42፥2 *ሕያው አምላክን፤* ዘዳ5፥26 ይመ። *መቼ?* አሁን በቤተ መቅደስ ለመገኘት ሁኔታዎች አልፈቀዱለትም (ቍ9፤ 43፥1-2 ይመ)። *የማየው፤* ከእርሱ ጋር ኅብረት አደርጋለሁ ማለቱ ነው (ዘፀ19፥17፤ 29፥42-43፤ 30፥6፡36 ይመ)።

42፥3 *አምላክህ የት አለ?* የ10፥11 ማብ ይመ። *ቀንና ሌሊት፤* ቍ8፡10 ይመ።

42፥4 *ነፍሴ፤* የ6፥3 ማብ ይመ። *እየመራሁ፤* መዝሙረኛው በቤተ መቅደስ ውስጥ የመሪነት ሚና እንደ ነበረው ያመለክታል።

*42፥5፤* በእምነት ጸንቶ ስለመኖር የሚያሳስብ ነው

ተስፋሽን በእግዚአብሔር ላይ አድርጊ፤
አዳኜና [6]አምላኬን፣
ገና አመሰግነዋለሁና።

ነፍሴ በውስጤ ተክዛለች፤
ስለዚህ በዮርዳኖስ ምድር፣
በአርሞንኤም ከፍታ፣
በሚዛር ተራራ አስብሃለሁ።
[7]በፏፏቴህ ማስገምገም፣
አንዱ ጥልቅ ሌላውን ጥልቅ ይጣራል፤
ማዕበልህና ሞገድህ ሁሉ፣
ሙሉ በሙሉ አጥለቀለቀኝ።

[8]እግዚአብሔር ምሕረቱን በቀን ያዝዛል፤
ዝማሬውም በሌሊት በእኔ ዘንድ አለ፤
ይህም ለሕይወቴ አምላክ የማቀርበው
ጸሎት ነው።

[9]እግዚአብሔር ዐለቴን፣
"ለምን ረሳኸኝ?
ጠላትስ እያስጨነቀኝ፣
ለምን በሐዘን እመላለሳለሁ?" እለዋለሁ።
[10]ጠላቶቼ ቀኑን ሙሉ፣
"አምላክህ የት አለ?" እያሉ፣
በነገር ጠዘጠዙኝ፣
ዐጥንቴም ደቀቀ።

[11]ነፍሴ ሆይ፤ ለምን ትተክዢያለሽ?
ለምንስ በውስጤ ትታወኪያለሽ?
ተስፋሽን በእግዚአብሔር ላይ አድርጊ፣
አዳኜና አምላኬን፣
ገና አመሰግነዋለሁ።

42፥6 ቍ11፤ዘፍ 13፥10፤ዘኍ13፥29፤ ዘዳ3፥8፤4፥48፤መዝ43፥5፤63፥6፤77፥11
42፥7 ዘፍ1፥2፤7፥11፤መዝ69፥2፤ዮና2፥3
42፥8 መዝ16፥7፤ 57፥3፤77፥6፤133፥3፤ መክ5፥18፤8፥15
42፥9 ኢዮ20፥19፤ መዝ9፥13፤10፥11፤18፥31፤35፥14፤43፥2፤ 106፥42
42፥10 ቍ3፤ዘዳ 32፥27፤መዝ6፥2፤44፥16፤89፥51፤102፥8፤ 119፥42
42፥11 ቍ5፤መዝ 43፥5
43፥1 መሳ6፥31፤ መዝ25፥20፤36፥3፤10 9፥2
43፥2 መዝ35፥14፤ 42፥9፤44፥9፤74፥1፤8 8፥14፤89፥38
43፥3 2ሳሙ15፥25፤መዝ2፥6፤25፥5፤26፥3፤27፥1
43፥4 ዘፍ4፥21፤ መዝ16፥3፤21፥6፤26፥6፤42፥2፤84፥3
43፥5 መዝ42፥6
44፥1 ዘዳ32፥7፤ መሳ6፥13፤2ሳሙ7፥22፤1ዜና17፥20፤ኢዮ 37፥23፤ኤር26፥11

## መዝሙር 43[a]

### በስደት ላይ ያለ ሌዋዊ ልቅሶ

[1]አምላክ ሆይ፤ ፍረድልኝ፤
ከጽድቅ ከራቀ ሕዝብ ጋር ተሟገትልኝ፤
ከአታላዮችና ከክፉዎች ሰዎችም አድነኝ።
[2]አምላክ ሆይ፤ አንተ ብርታቴ ነህና፣
ለምን ተውኸኝ?
ጠላትስ እያስጨነቀኝ፣
ለምን በሐዘን እመላለሳለሁ?
[3]ብርሃንህንና እውነትህን ላክ፤
እነርሱ ይምሩኝ፤
ወደ ተቀደሰው ተራራህ፣
ወደ ማደሪያህ ያድርሱኝ።

[4]እኔም ወደ እግዚአብሔር መሠዊያ እቀርባለሁ፤
ፍጹም ደስታዬ ወደ ሆነው አምላክ
እሄዳለሁ፤
እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፣
በበገና አመሰግንሃለሁ።

[5]ነፍሴ ሆይ፤ ለምን ትተክዢያለሽ?
ለምንስ በውስጤ ትታወኪያለሽ?
ተስፋሽን በእግዚአብሔር ላይ አድርጊ፤
አዳኜና አምላኬን፣
ገና አመሰግነዋለሁና።

## መዝሙር 44

### ብሔራዊ ሰቆቃ

*ለመዘምራን አለቃ፤ የቆሬ ልጆች ትምህርት።[b]*

[1]አምላክ ሆይ፤ በጆሮአችን ሰምተናል፤

[a]43 በብዙ የዕብራይስጥ ቅጆች መዝሙር42 እና 43 አንድ መዝሙር ነው።
[b]44ርእስ የሥነ ጽሑፉን ትርጉ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።

(27፥13-14 እና የመዝ27 መግቢያን ይመ)።

*42፥6-10፤* ነፍሱ በእጅጉ የተጨነቀችበትን መንሥኤ ያመለክታል።

42፥6 *አመሰግነዋለሁና፤* መድኅን ስለ ሆነኝ አመሰግነዋለሁ ማለቱ ነው (የ7፥17፤ 9፥1 ማብ 43፥4 ይመ)። *ነፍሴ ትተክዛለች፤* ቍ5፡11፤ 43፥5 ይመ። *አስብሃለሁ፤* በስደት ላይ ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር ሐሤት የሚያደርግበት ኅብረት እንደ ነበረው እንደሚያስታውስ ሁሉ (ቍ4) አሁንም በስደት ላይ እያለ እግዚአብሔርንና የደረሰበትንም ሥቃይ ያስታውሳል (ቍ7፡9-10) ያም ሆኖ ግን ተስፋ ቢስ አይደለም (ቍ8)። *ምድር ... በሚዛር ተራራ፤* ምናልባት የመዝሙሩ ደራሲ ከእስራኤልና ከይሁዳ ውጪ በስደት ላይ እንዳለ ሊያመለክት ይችላል። በእግዚአብሔር ፊት ለመሆን የሚናፍቁና ልዩ መገለጡን የሚሹ ሁሉ የኀዘኑን ወዲያውኑ ላያገኙ ይችላሉ፤ ጠንካራ እምነት ያላቸው ግን አሁንም ከፊቱ አይርቁም፤ ልዩ መገለጡንም ተግተው ይፈልጋሉ። ጌታ ኢየሱስ ሙሉ በረከቱን የሚሰጠው እንዲሁ ተደላድለው ለተቀመጡት ክርስቲያኖች ሳይሆን ጽድቅን ለሚራቡና ለሚጠሙ መሆኑን እርሱ ራሱ ተናግሮአል (ማቴ5፥6)።

42፥7 *በፏፏቴ ... አንዱ ጥልቅ፤* መዝሙረኛው የደረሰበትን ጽኑ መከራ ምስል ከሣች በሆነ መንገድ አንድ በአንድ ይገልጣል፤ በተከታዮቹም ጥቅሶች ላይ የመዝሙረኛው ጭንቀት ሥዕላዊ በሆነ መልክ ቀርቦአል (69፥1-2፤ 88፥7፤ ዮና 2፥3፡5 እንዲሁም የ32፥6 ማብ ይመ)። በመዝሙረኛው ላይ እንዲህ ያሉ መዓቶች እንዲደርስ በማድረግ እግዚአብሔር በሥቃዩ ውስጥ ተሳትፎአል ማለት ይቻላል። ለመዝሙረኛው እግዚአብሔር "የረሳው" (ቍ9) ወይም "የተወው" (43፥2) ሊመስለው ይችላል። መዝሙረኛው ግን በዚህና በሕይወቱ ውስጥ ባለ ኀጢአት መካከል ምንም ዐይነት ተዛምዶ አላደረገም (መዝ44፡77 ይመ)።

*42፥8፤* መከራ እንደ፣ ጐርፍ ቢያጥለቀልቀውም አሁንም በአምላኩ እንደሚታመን ያረጋግጣል። እንዲህም ሲል "እግዚአብሔር ፍቅሩን በቀን ይልካል፣ ዝማሬውም በሌሊት አይለየኝም" ማለቱ ነው (ቍ3 እና የ3፥7 ማብ ይመ)። *እግዚአብሔር፤* በዚህ መዝሙር ውስጥ በዚህ ቦታ ብቻ ማለትም በመዝሙሩ እምብርት ላይ የሚገኝ ቃል ነው (መግቢያውን ይመ)። *ምሕረቱን ያዛል፤* አንድ መልእክተኛ ፈቃዱን ለማድረግ እንደሚሄድ ሁሉ እንዲሁ ምሕረቱን ይሰዳል (43፥3 ይመ)። *ምሕረቱን፤* የ6፥4 ማብ ይመ። *ዝማሬውም፤* ስለ ጌታ የሚያወሳ መዝሙር ነው። *ጸሎት፤* ምስጋናና ጸሎት በመዝሙረኛው ዘንድ አይነጣጠሉም።

*42፥9፤* በመዝ43፥2 ላይ ይኸው ሐሳብ በድጋሚ ተንጸባርቆአል። *ዐለቴን፤* የ18፥2 ማብ ይመ። *ለምን ረሳኸኝ? ... ለምን?* የ6፥3 ማብ ይመ። (እንዲሁም ከመጽሐፉ መግቢያ "ትምህርተ-መለኮት" የሚለውን ይመ)።

*42፥10፤* ቍ3 ይመ። *ዐጥንቴም፤* የ6፥2 ማብ ይመ።

*43፥1-4፤* ከጠላት እጅ ለመዳንና በእግዚአብሔርም ፊት እንደ ገና ተመልሶ ለመቅረብ የቀረበ ልመና ነው።

*43፥1፤* በፍርድ ቤት ቋንቋ የቀረበ ልመና ነው (የመዝ17 መግቢያን ይመ)።

*43፥2፤* በ42፥9 ላይ የተጠቀሰውን ሐሳብ እንደ ገና መልሶ ያስተጋባል።

43፥3 *ብርሃንህንና እውነትህን፤* የእግዚአብሔር መልእክተኛ በመሆን በሰውኛ አገላለጽ ቀርበዋል፤ እነርሱም የእግዚአብሔርን ማዳን እውን የሚያደርጉና (ብርሃን፤ የ27፥1 ማብ ይመ)፤ በእርሱም ስም ሆነው እንክብካቤውን እውን የሚያደርጉ ናቸው (እውነት፤ 26፥3፤ 30፥9፤ 40፥10 ይመ)፤ እነዚህ ወደ መቅደስህ ይምሩኝ ይላል መዝሙረኛው። *ወደ ተቀደሰውም ተራራህ፤* የ2፥6 ማብ ይመ።

*43፥4፤* የ7፥17 ማብ ይመ። *መሠዊያ፤* 26፥6 እና ማብ ይመ።

*መዝሙር 44፤* እስራኤላውያን ጠላት ከፍተኛ ሽንፈት ካደረሰባቸው በኋላ በሥቃይ ውስጥ ሆነው ያቀረቡት ልመና ነው። ከቍ17-22 ያለውን ሐሳብ መሠረት በማድረግ ብቻ ይህንን መዝሙር እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ለገባችው ቃል ኪዳን ታማኝ ካልሆነች በጠላት እጅ ከፍተኛ ሽንፈት ካደረሰባቸው ከሚለው ከነቢያት ትንቢት ጋር ማዛመድ አስቸጋሪ ነው። መዝሙሩ

አባቶቻችን በቀድሞ ዘመን፣
እነርሱ በነበሩበት ዘመን፣
ያደረግኸውን ነግረውናል።
[2]ሕዝቦችን በእጅህ አሳደህ አወጣሃቸው፤
አባቶቻችንን ግን ተከልሃቸው፤
ሕዝቦችን አደቀቅህ፤
አባቶቻችንን ግን ነጻ አወጣሃቸው።
[3]ምድሪቱን የወረሱት በሰይፋቸው
አልነበረም፤
ድልንም የተጐናጸፉት በክንዳቸው
አይደለም፤
አንተ ወደሃቸዋልና ቀኝ እጅህ፣
ክንድህና የፊትህ ብርሃን ይህን አደረገ።
[4]እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ንጉሤ ነህ፤[ሖ]
ያዕቆብም ድል እንዲያደርግ የወሰንህ
አንተ ነህ።
[5]በአንተ ጠላቶቻችን በመጡበት እንዲ
መለሱ እናደርጋለን፤
በስምህም ባላጋራዎቻችንን ከእግራችን
በታች እንረግጣለን።
[6]በቀስቴ አልተማመንም፤
ሰይፌም አያስጥለኝም።
[7]አንተ ግን በጠላቶቻችን ላይ ድልን
ትሰጠናለህ፤
ባላንጣዎቻችንንም ታሳፍራለህ።
[8]ዘወትር በእግዚአብሔር እንመካለን፤
ስምህንም ለዘላለም እንወድሳለን። ሴላ
[9]አሁን ግን እነሆ ትተኸናል፤
አሳፍረኸናልም፤
ከሰራዊታችንም ጋር አትወጣም።

44፥2 ዘፀ15፥17፤ ኢሱ3፥10፤መሳ4፥23፤ 2ዜና14፥13፤መዝ80፥9፤ኢሳ60፥21፤ኤር32፥23፤ሐሥ7፥45
44፥3 ዘፀ15፥16፤ዘዳ4፥37፤ኢሱ24፥12፤ መዝ77፥15፤78፥54፤ 79፥11፤89፥10፡15፤ 98፥1፤ኢሳ40፥10፤ 52፥10፤63፥5
44፥4 መዝ5፥2፤21፥5፤24፥7
44፥5 ኢሱ23፥5፤ መዝ60፥12፤108፥13
44፥6 ዘፍ48፥22፤ ሆሴ1፥7
44፥7 ዘዳ20፥4፤ኢዮ8፥22
44፥8 መዝ30፥12፤ 34፥2፤52፥1፤1ቆሮ1፥31፤2ቆሮ10፥17
44፥9 ዘዳ8፥3፤ 31፥17፤ኢሱ7፥12፤ መዝ43፥2፤107፥39፤ 108፥11፤ኢሳ5፥15
44፥10 ዘሌ26፥17፤መሳ2፥14
44፥11 ቍ22፤ዘሌ26፥33፤መዝ9፥11፤ ኤር12፥3፤ሕዝ6፥8፤ ዘካ2፥6
44፥12 ዘዳ32፥30፤ ኢሳ50፥1፤52፥3፤ኤር15፥13
44፥13 ዘዳ28፥37፤ 2ዜና29፥8፤መዝ79፥4፤80፥6፤89፥41፤ኢሳ30፥3፤ኤር25፥9፤42፥18፤44፥8፤ሕዝ23፥32፤ሚክ2፥6
44፥14 1ነገ9፥7፤

[10]ከጠላት ፊት እንድናፈገፍግ አደረግኸን፤
ባላንጣዎቻችንም ዘረፉን።
[11]እንደሚታረዱ በጎች አደረግኸን፤
በሕዝቦችም መካከል በተንኸን።
[12]ሕዝብህን በርካሽ ዋጋ ሸጥኸው፤
ከሽያጩም ያገኘኸው ትርፍ የለም።
[13]ለጎረቤቶቻችን ስድብ፣
በዙሪያችን ላሉትም መሣቂያና መዘበቻ
አደረግኸን።
[14]በሕዝቦች ዘንድ መተረቻ፣
በሰዎች መካከል በንቀት ራስ መነቅነቂያ
አደረግኸን።
[15]ውርደቴ ቀኑን ሙሉ በፊቴ ነው፤
ፊቴም ዕፍረትን ተከናንቦአል።
[16]ይህም ከሚዘልፍና ከሚያላግጥ ሰው
ድምፅ የተነሣ፣
ከጠላትና ከተበቃይ ሁኔታ የተነሣ ነው።
[17]አንተን ሳንረሳ፣
ለኪዳንህም ታማኝነታችንን ሳናጓድል፣
ይህ ሁሉ ደረሰብን።
[18]ልባችን ወደ ኋላ አላለም፤
እግራችንም ከመንገድህ አልወጣም።
[19]አንተ ግን ተኰላዎች በሚውሉበት ቦታ
ሰባብረህ ጣልኸን፤

2ነገ19፥21 44፥15 ዘፍ30፥23፤ 2ዜና32፥21፤መዝ34፥5፤35፥26
44፥16 ሳሙ-18፥25፤መዝ10፥13፤42፥10፤55፥3፤74፥10፤ኤር11፥19፤ሮሜ12፥19 44፥17 ዘዳ6፥12፤32፥18፤መዝ119፥16፡61፡153፡176፤ምሳ3፥1 44፥18 መዝ119፥ 51፡157
44፥19 2ዜና14፥13 ፤ኢዮ3፥5፤30፥29፤ መዝ51፥8፤ኢሳ34፥13

[ሖ]4 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም የሱርስቱ ቅጅ *ንጉሤ ነህ፤ አምላኬም ነህ* ይላሉ፤ ዕብራይስጡ ደግሞ፣ *ንጉሤ እግዚአብሔር ሆይ፤* ይላል።

ምናልባት የይሁዳን መንግሥት ተመክሮ ሳያጣቅስ (ሳያመለክት) አይቀርም (ይሁዳ እስከ 586 ዓ.ቅ.ክ ድረስ በመንግሥትነት ቈይታለች)፤ ይህም ምናልባት በኢዮሣፍጥ ወይም በሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት ሊሆን ይችላል። ባወቃቀር ረገድ ሲታይ የመዝሙሩ ዐቢይ ሐሳብ አንዱ በሌላው ላይ እየተነባበረ እስከ መጨረሻው ቍጥር ድረስ ይዘልቃል። የመዝሙሩ አወቃቀር የጥንት አሶራውያንና በባቢሎናውያን ለቤተ መቅደሶቻቸው የሚሰሩትን ጉልላት ይመስላል። አሶራውያንና ባቢሎናዉያን ለቤተ መቅደሶቻቸው የሚሰሩት ጕልላት እንደ ፒራሚድ ያለ ወይም እንደ ተራራ ያለ ቅርጽ ነው ያለው (ዘፍ11፥4 እና ማብ ይመ)። በመዝሙሩ ውስጥ በመጀመሪያ የምናገኘው እግዚአብሔር ከዚህ ቀደም ስለሰጣቸው ድል የቀረበ ምስጋና (ቍ1-8) ሲሆን በሁለተኛው ደረጃ የምናገኘው ደግሞ ከዚህ በፊት ስለደረሰባቸው ሽንፈትና ስላስከተለውም ጣስ ነው (ቍ9-16)፤ በሦስተኛ ደረጃ ንጹሕ መሆናቸውን የሚገልጽ አቤቱታ የቀረበ ሲሆን (ቍ17-22) በመጨረሻም ጸሎት (ምልጃ) ቀርቦአል (ቍ23-24)። አንዱ ባንዱ ላይ እየተነባበረ የቀረበው ዐቢይ ሐሳብ (ቀድሞ የተደረገላቸውን ምሕረት የሚያስታውስ፣ አሁን ያሉበትን መከራ የሚያወሳውና ለገቡት ቃል ኪዳን ታማኝ መሆናቸውን የሚገልጸው) ሁሉም በየራሱ የሚያቀርበው የርዳታ ጥሪ አለ (መዝ40 እና መግቢያውን እንዲሁም በመዝ40፤ 89 ላይ የቀረበውን መቅድም ይመ)።

*44ርእስ፤* የመዝ 42 የርእስ ማብ ይመ።

*44፥1-8፤* እግዚአብሔር ከዚህ ቀደም ስለ ሰጣቸው ድል የቀረበ ምስጋና ነው፤ ድሎችም (1) እስራኤል በተስፋዪቱ ምድር ላይ መተከሏንና (ቍ1-3)፤ (2) በተስፋዪቱም ምድር ያለሥጋት ተደላድላ መቀመጧን የሚያወሱ ናቸው (ቍ4-8)።

*44፥1፤* 78፥3 ይመ።

44፥3 *የፊትህ ብርሃን፤* የ4፥6 እና የ13፥1 ማብ ይመ።

44፥4 *ንጉሤ (የእኔ)፤* በዚህ ቦታና በዚህ መዝሙር ውስጥ በአንደኛ መደብ ነጠላ ቍጥር የተነገረው ተውላጠ ስም የሚወክለው መላውን ሕዝብ ነው፤ የመዝ 30 የርእስ ማብ ይመ። *ያዕቆብ፤* የ14፥7 ማብ ይመ።

44፥5፡8 *በስምህም፤* ቍ20፤ እንዲሁም የ5፥11 ማብ ይመ።

*44፥9-16፤* አሁን ግን ትተኸናል፤ (1) ሽንፈትን እንድንቀምስ አድርገኸናል (ቍ9-12)፤ (2) በጠላቶቻችንም ፊት እንድናፍር አድርገኸናል (ቍ13-16 ይመ) ማለት ነው።

44፥9 *ትተኸናል፤* እንደ መዝሙረኛው አስተያየት የእግዚአብሔር ሕዝብ ሥቃይና ሽንፈት የደረሰባቸው እግዚአብሔር ስለ ተዋቸው ነው (ቍ9-16)፤ መዝሙረኛው ግን በሁኔታው ግራ የተጋባ ይመስላል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር የተዋቸው የገቡትን ቃል ኪዳን ሳያፈርሱ ነው (ቍ17-19)። ከዚህ ላይ መዝሙረኛው የሚያንጸባርቀው የእግዚአብሔርን ልጆች ተመክሮ ነው፤ እንደ ኢዮብ ምንም ነቀፋ የሌለባቸው ሰዎች፣ የእግዚአብሔር ጥበቃ ሊለያቸው፣ በመከራ፣ በጨለማና በፈተና ሕይወት ውስጥ ሊያልፉ ይችላሉ፣ ይህ ዐይነቱ ገጠመኝ ምን እንደ ሚመስልም በቍ22 ላይ ተመልክቶአል።

44፥11 *እንደሚታረዱ በጎች አደረግኸን፤* እረኛና ንጉሣችን የሆንኸውን ያህል ከጠላት እጅ አላዳንከንም ማለቱ ነው (ቍ4 እና፤ የ23፥1 ማብ ይመ)።

44፥12 *ሕዝብህን … ሸጥኸው፤* ዋጋ እንደሌለው ንብረት ቈጠርከን ማለቱ ነው (ዘፀ32፥30፤ መሳ2፥14 ይመ)፤ *በርካሽ ዋጋ፤* ፋይዳ ቢስ አደረግኸን ማለቱ ነው (ኢሳ52፥3፤ ኤር15፥13 ይመ፤ ከኢሳ43፥3-4 ጋር ያነጻጽሩ)።

44፥14 *ራሳቸውን ይነቀንቁብናል፤* ያላግጡብናል ማለቱ ነው (64፥8 ይመ)።

44፥16 *ሊበቀለኝ በሚሻ ጠላት፤* 8፥2 እና ማብ ይመ።

*44፥17-22፤* ለአንተ ያለንን ታማኝነት አላጓደልንም፤ (1) ለቃል ኪዳንህ ያለን አክብሮትም ከቶ አልተለወጠም (ቍ17-19)፤ (2) ወደ ባእዳን አማልክትም እንዳልሄድን አንተ ራስህ ታውቃለህ (ቍ20-22)።

44፥17 *ለኪዳንህም፤* ዘፀ19-24 ይመ።

44፥18 *ልባችን፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *ከመንገድህ፤* በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ላይ ቍልጭ ብሎ ከተመለከተው መንገድ ማለት ነው (የ5፥8 ማብ ይመ)።

44፥19 *ተኰላዎች በሚውሉበት፤* ሰው የማይኖርበት ጠፍ ቦታ ማለት ነው። *አንተ ግን ሰባብረህ ጣልኸን፤* ይህ ግን ለቃል

በሞት ጥላም ሸፈንኸን።

20የአምላካችንን ስም ረስተን፣
እጃችንንም ወደ ባዕድ አምላክ ዘርግተን
ቢሆን ኖሮ፣
21እግዚአብሔር ይህን ማወቅ ይሳነዋልን?
እርሱ ልብ የሰወረውን የሚረዳ ነውና።
22ይሁን እንጂ ቀኑን ሙሉ ስለ አንተ
ሞትን እንጋፈጣለን፤
እንደሚታረዱ በጎችም ተቈጥረናል።

23ጌታ ሆይ፤ ንቃ! ለምንስ ትተኛለህ?
ተነሥ፤ ለዘላለምም አትጣለን።
24ፊትህን ለምን ትሰውራለህ?
መከራችንንና መጠቃታችንን ለምን
ትረሳለህ?

25ነፍሳችን ዐፈር ውስጥ ሰጥማለች፤
ሆዳችንም ከምድር ጋር ተጣብቆአል።
26ተነሥና እርዳን!
ስለ ምሕረትህ ስትል ተቤዠን።

## መዝሙር 45

### የንጉሣዊ ሰርግ መዝሙር

ለመዘምራን አለቃ፤ "በጽጌረዳ" ዜማ፤ የቆሬ ልጆች ትምህርት፤ የፍቅር መዝሙር[T]

1ልቤ መልካም ሐሳብ አፈለቀ፤
የተቀኘሁትን ቅኔ ለንጉሥ አሰማለሁ፤
አንደበቴም እንደ ባለ ሙያ ጸሓፊ ብርዕ
ነው።

2አንተ ከሰዎች ሁሉ ይልቅ ውብ ነህ፤
ከንፈሮችህም የጸጋ ቃል ያፈልቃሉ፤
ስለዚህ እግዚአብሔር ለዘላለም ባርኮሃል።
3ኀያል ሆይ፤ ሰይፍህን በወገብህ ታጠቅ፤
ግርማ ሞገስንም ተላበስ።
4ስለ እውነት፣ ስለ ትሕትና ስለ ጽድቅ፣
ሞገስን ተጐናጽፈህ በድል አድራጊነት
ገሥግሥ፤
ቀኝ እጅህም ድንቅ ተግባር ታሳይ።
5የሾሉ ፍላጻዎችህ በንጉሥ ጠላቶች ልብ
ይሰካሉ፤
ሕዝቦችም ከእግርህ በታች ይወድቃሉ።

44፥20 ዘፀ20፥3፤ዘዳ32፥18፤መሳ3፥7፤ኢሳ43፥12፤ኤር5፥19
44፥21 1ሳሙ16፥7፤1ነገ8፥39፤ምሳ15፥11፤ኤር12፥3፤17፥10
44፥22 ቍ11፤ኢሳ53፥7፤ኤር11፥19፤12፥3፤ሮሜ8፥36
44፥23 መዝ7፥6፤59፥5፤74፥1፤77፥7፤78፥65
44፥24 ዘዳ26፥7፤32፥20፤መዝ13፥1፤ሰቆ5፥20
44፥25 መዝ119፥25
44፥26 ዘኍ10፥35፤መዝ6፥4፤12፥5፤26፥11፤102፥13
45 ርዕስ መሓ1፥1
45፥2 መዝ21፥6፤ሉቃ4፥22
45፥3 ዘዳ32፥41፤2ሳሙ1፥19፤ኢዮ40፥10፤መዝ21፥5፤149፥6፤ራእ1፥16
45፥4 ዘዳ4፥34፤መዝ21፥8፤65፥5፤66፥3፤ሶፎ2፥3፤ራእ6፥2
45፥5 ዘኍ24፥8፤ ዘዳ32፥23፤መዝ9፥13፤92፥9

[T]45ርእስ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።

ኪዳንህ ታማኞች አለመሆናችንን የሚያሳይ ማረጋገጫ አይደለም። *በሞት ጥላም፤* "ብርሃን" በሚለው ዘይቤ አማካይነት የሚታሰበው በጎ ነገር ሁሉ ታጥቶአል ማለት ነው (የ30፥1፤ የ36፥9 ማብ ይመ)።

44፥20 *እጆቻችንንም ...ዘርግተን ቢሆን ኖሮ፤* ጸሎት ብና ቀርብ ኖሮ ማለት ነው።

44፥22 *ይሁን እንጂ፤* ወይም "እንደ እውነቱ ከሆነ" አልያም፣ "አምላክ ሆይ፤ አንተ ታውቃለህ" ማለት ነው። እስራኤል ከግብፅ ቈይታዋ ጀምሮ (ዘፀ1 ይመ) ከእግዚአብሔር ጋር ያላት ወዳጅነት የአሕዛብን ጠላትነት አትርፎላታል (ማቴ 10፥34 ይመ)። ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ መሠረት በማድረግ ይህንን ንባብ ከክርስቲያናዊ ማኅበረ ሰብነት ጋር እንዴት እንዳገናዘበው ለማየት ሮሜ8፥36 ይመ።

*44፥23-26፤* ርዳታን ለማግኘት የቀረበ ምልጃ ነው፤ (1) ብሶታችንን ተመልከት (ቍ 23-24)፤ (2) እኛን ለመርዳት ተነሥ (ቍ 25-26 ይመ፤ የመዝ16ን መግቢያ ይመ)።

44፥23 *ንቃ፤* የ7፥6 ማብ ይመ። *ለምንስ ...?* የ6፥3 ማብ ይመ (እንዲሁም በመግቢያው ላይ "ትምህርተ መለኮት" የሚለውን ይመ)።

44፥24 *ፊትህን ... ትሰውራለህ፤* የ13፥1 ማብ ይመ።

44፥25 *ዐፈር ውስጥ ሰጥማለች፤* ከሞት አፋፍ ላይ ደርሰናል (22፥29 እና ማብ፤ እንዲሁም የ30፥1 ማብ ይመ)።

44፥26 *ተነሥና፤* የ3፥7 ማብ ይመ። *ተቤዠን፤* የ25፥22 ማብ ይመ። *ስለ ምሕረትህ፤* የ6፥4 ማብ ይመ።

*መዝሙር 45፤* ንጉሡ በሚያገባበት ዕለት ለንጉሡ ክብር የቀረበ መዝሙር ነው (የመዝሙሩን ርእስ ይመ)። ይህ ንጉሥ ከዳዊት ሥርወ መንግሥት የወጣ ሳይሆን እንደማይቀር ምንም ጥርጥር የለውም፤ መዝሙሩ በተለያዩ ንጉሣውያን ሰርግ ላይ ሳይዘመር አይቀርም። ሙሽራዋ የውጭ አገር ልዕልት በመሆ (ቍ 10፥12) ሰርጉ የንጉሡ ዝና በዓለም ሁሉ የናኘ መሆኑን ያሳያል (የቍ 9 ማብ ይመ)። ከዚህ በተጨማሪ ንጉሡ ዓለምን ያንቀጠቀጠ ታላቅ ሰው ስለመሆኑ በመዝሙሩ ውስጥ በግልጽ ተመልክቶአል (ቍ 3-5 ይመ፤ ከመዝ2፤110 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ ንጉሥ የዳዊት ልጅ እንደ መሆኑ መጠን ወደ ፊት የሚመጣውን ክርስቶስን ይወክላል። እስራኤላውያን ወደ ምርኮ ከሄዱ በኋላ ይህ መዝሙር በዳዊት ዙፋን ላይ ለሚቀመጠውና በተስፋም ለሚጠበቀው መሲሕ እንዲውል ተደርጎአል (ቍ 6-7 ከክርስቶስ ሕይወት ጋር እንዴት እንደ ተገናዘበ ዕብ1፥8-9 ይመ)። ይህ መዝሙር በዘሌዋውያን መዘምራን መዘመሩ በንዑስ ርእሱ ላይ ተመልክቶአል። መዝሙሩ ከቤተ መቅደሱና (የእስራኤል ሰማያዊ ንጉሥ በምድር የሚያድርበት) ከዳዊት ሥርወ መንግሥት (በመጽሐፈ ሳሙኤል፣ በመጽሐፈ ነገሥትና በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ላይ እንደ ተገለጸው በእግዚአብሔር የተሾሙ እንደራሴዎች ናቸው) ጋር ካለው ጥብቅ ትስስር ጋር ካገናዘብነው በሌዋውያን መዘመሩ ብዙም የሚያስደንቅ አይደለም። ይህ መዝሙር በቤተ መቅደሱ ውስጥ ከሚያገለግሉ ሰዎች መካከል የወጣ ቃል በመሆኑ መዝሙሩ ከቤተ መቅደሱ ውስጥ የወጣ ማለትም በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠው የሠረፀ ስለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። ባወቃቀር ረገድ ሲታይ መዝሙሩ በቍጥር 1 እና 17 የተቀነበበ ሲሆን ቍጥር 2 እና 16 ደግሞ በመጀመሪያው ቅንብብ ውስጥ ሁለተኛ ቅንብብ በመሆን ያገለግላሉ፤ የሁሉም አትኩሮት ግን በንጉሡ ላይ ነው። መዝሙሩ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት፤ አንደኛው ክፍል ለንጉሡ የተነገረውን ቃል የያዘ ሲሆን (ቍ 3-9) ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ለሙሽራዪቱ የተነገረውን ቃል ይዞአል (ቍ 10-15)። እነዚህ ሁለት ክፍሎች እያንዳንዳቸው ሌሎች ሁለት ክፍሎችን ይዘዋል፤ ክፍሎቹም ተመሳሳይ የሆኑ ሞዴሎችን ያንጸባርቃሉ፤ (1) (ሀ) ለንጉሡ የቀረበ ምክር (ቍ 3-5)፤ (ለ) የንጉሡ ክብር (ቍ 6-9)፤ (2) (ሀ) ለሙሽራዋ የቀረበ ምክር (ቍ 10-11)፤ (ለ) የሙሽራዋ ክብር (ቍ 12-15)፤

45ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ4 የርእስ ማብ ይመ። *ቅኝት፤* የመዝ 9 የርእስ ማብ ይመ። *በጽጌረዳ፤* የመዝ 69 የርእስ ማብ ይመ። "አበባዬ" የሚለው ቃል በመዝ 60 እና 80 ርእሶች ላይ "የቃል ኪዳን አበባ" የሚለውን ሐረግ ባጭሩ የሚገልጽ ቃል ሳይሆን አይቀርም። *የቆሬ ልጆች፤* የመዝ 42 የርእስ ማብ ይመ። *ትምህርት፤* የመዝ32 የርእስ ማብ ይመ።

*45፥1፤* ቍ 17ን ይመ፤ በዚህ ቍጥር ላይ እንደሚታየው የንጉሡ መታሰቢያ ሕያው ሆኖ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ እንደሚያደርግ ተናጋሪው ቃል ይገባል። *ልቤ፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

45፥2 *ከሰዎች ሁሉ ይልቅ ውብ፤* አንድ ንጉሥ ከሁሉ ይልቅ አምሮና ደምቆ እንደሚገኝ፣ አንተም እንዲሁ ሆነሀል ማለቱ ነው (1ሳሙ9፥2፤ 16፥18 ይመ)፤ ከተራ ሰው ግን በብዙ ይለያል፤ እንዲያውን የአምላክ አምሳል አለው (የቍ 6 ማብ ይመ)። *ከንፈሮችህም የጸጋ ቃል ያፈልቃሉ፤* ምሳ22፥11፤ መክ 10፥12 ይመ፤ ከኢሳ50፥4፤ ከሉቃ4፥22 ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም በቍ 16 ላይ እንዲህ ያለው መልካም ንጉሥ በልጆቹ አማካይነት ሕያው ሆኖ እንደሚኖር የተገለጸበትን ክፍል ይመ። *ለዘላለም፤* የቍ 6 ማብ ይመ።

*45፥3-5፤* ሰይፍን ይዘህ ድል እየመታህ ሂድ፤ በግርማ የተንቆጠቆጠ ልብስም ልበስ፤ ዙፋንህንም ቀድሞ ከምታለብሰው የክብር ልብስ በበለጠ አሸብርቀው የሚል ሐሳብ የያዘ ነው (ቍ 8)።

45፥3 *ግርማ ሞገስንም፤* 21፥5 ማብ ይመ።

45፥4 *ጽድቅ፤* የ1፥5 ማብ ይመ። *ድንቅ ተግባር፤* 66፥5፤ 106፥22፤ 145፥6 ይመ።

45፥5 *ሕዝቦችም ከእግርህ በታች ይወድቃሉ፤* 2፥8-9፤ 110፥1-2፡5-6 ይመ።

*45፥6-9፤* ፍትሕና ጽድቅ የንጉሡ አክሊሎች ናቸው (መዝ 72 ይመ)።

6አምላክ ሆይ፤ ዙፋንህ ከዘላለም እስከ
ዘላለም ይኖራል፤
የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር
ናት።
7ጽድቅን ወደድህ፤ ዐመፃን ጠላህ፤
ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ፣
ከጓደኞችህ ይልቅ አንተን የደስታ ዘይት
ቀባህ።
8ልብስህ ሁሉ በከርቤ፣ በአደስና በጥንጁት
መዐዛ ያውዳል፤
በዝኆን ጥርስ ከተዋቡ ቤተ
መንግሥቶችም፣
የበገናና የመሰንቆ ድምፅ ደስ ያሰኙሃል።
9ከተከበሩት ሴቶችህ መካከል የነገሥታት
ሴቶች ልጆች ይገኛሉ፤
ንግሥቲቱም በኦፊር ወርቅ አጊጣ
በቀኝህ ቆማለች።
10ልጄ ሆይ፤ አድምጪ፤ አስተዉይ፤
ጆሮሽንም አዘንብይ፤
ሕዝብሽንና የአባትሽን ቤት እርሺ።
11ንጉሥ በውበትሽ ተማርኮአል፤
ጌታሽ ነውና አክብሪው።
12የጢሮስ ሴት ልጅ እጅ መንሻ ይዛ
ትመጣለች፤[ሀ]
ሀብታሞችም ደጅ ይጠኑሻል።
13የንጉሥ ልጅ ከላይ እስከ ታች ተሸልማ
እልፍኝ ውስጥ አለች፤
ልብሷም ወርቀ ዘቦ ነው።
14በጥልፍ ሥራ ባጌጠ ልብስ ወደ ንጉሥ
ትወሰዳለች፤
ደናግል ጓደኞቿም ተከትለዋት፣
ወደ አንተ ይመጣሉ።
15በደስታና በሐሤት ወደ ውስጥ
ይመሯቸዋል፤
ወደ ንጉሡም ቤተ መንግሥት ይገባሉ።
16ወንዶች ልጆችህ በአባቶችህ እግር
ይተካሉ፤
ገዦችም አድርገሽ በምድር ሁሉ
ትሾሚያቸዋለሽ።
17ስምሽን በትውልድ ሁሉ ዘንድ መታሰቢያ
አደርጋለሁ፤
ስለዚህ ሕዝቦች ከዘላለም እስከ ዘላለም
ያወድሱሃል።

45፥6 ዘፍ21፥33፤
ሰቆ5፥19
45፥7 መዝ2፥2፤
11፥5፤23፥5፤33፥5፤
ኢሳ45፥1፤61፥1፤ዘካ
4፥14፤ዕብ1፥8-9
45፥8 ዘፍ37፥25፤ዘፀ
30፥24፤ዘኍ24፥6፤
1ነገ22፥39፤መዝ144፥
9፤150፥4፤ምሳ27፥9፤
መሓ1፥3፤4፥10፤ኢሳ
38፥20፤ዮሐ 19፥39
45፥9 ዘፍ10፥29፤
1ነገ2፥19፤መሓ6፥8፤
ኢሳ62፥5
45፥10ሩት1፥11፡
16፤ኤር5፥1
45፥11 አስ1፥11፤
ሰቆ2፥15፤ኤፌ5፥33፤
1ጴጥ3፥6
45፥12 ኢሱ19፥29፤
1ነገ9፥16፤2ዜና9፥24
45፥13 ዘፀ39፥3፤
ኢሳ61፥10
45፥14 መሳ5፥30፤
አስ2፥15፤መሓ1፥3
45፥15 አስ8፥17
45፥16 1ሳሙ2፥8፤
መዝ68፥27፤113፥8
45፥17 ዘፀ3፥15፤
መዝ21፥4፤33፥11፤11
9፥90፤135፥13፤
138፥4፤ራእ22፥5
46፥1 ዘዳ4፥30፤
መዝ9፥9፤18፥1፡6፤25
፥17፤34፥18፤37፥39፤
61፥3፤73፥26፤91፥2፡9

## መዝሙር 46[ለ]

### እግዚአብሔር ከእኛ ጋር

*ለመዘምራን አለቃ፤ የቆሬ ልጆች መዝሙር፤ በደናግል የዜማ ስልት የሚዘመር፣ መዝሙር።*

1አምላካችን መጠጊያችንና ኀይላችን፣
በሚደርስብን መከራ ሁሉ የቅርብ
ረዳታችን ነው።

[ሀ]12 ወይም፣ *የጢሮሳውያን ልብስ ተከህና ከሰጦታዎቹ መካከል አለ ተብሎ መተርጐም ይቻላል።*
[ለ]ም46 ርእስ ምናልባት የሙዚቃውን ሁኔታ ሊያሳይ ይችላል።

45፥6 *አምላክ ሆይ፤* ንጉሡ በእግዚአብሔር የተሾመ እንደ ራሴ በመሆኑ የንጉሡ ዙፋን የእግዚአብሔር ዙፋን ተደርጐ ሳይቈጠር አልቀረም። ምናልባትም ንጉሡ እንደ "አምላክ" ታይቶም ሊሆን ይችላል። ከዳዊት ሥርወ መንግሥት የወጣው ንጉሥ ("እግዚአብሔር የቀባው" 2ሳሙ19፥21)፣ ከእግዚአብሔር ጋር ልዩ ግንኙነት ስለ ነበረው በንግሥናው ወቅት የክብር ማዕረግ ተሰጥቶት "የእግዚአብሔር ልጅ" ተብሎአል (2፥7፤ 2ሳሙ7፥14፤ 1ዜና28፥6 ይመ፤ ከ89፥27 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይህ መዝሙር ንጉሡን የሚያወድስ በተለይም ክብሩንና ሞገሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ በመሆኑ (ቍ3) ከፍ ባለ የማዕረግ ስም "አምላክ" ተብሎ መጠራቱ ከቶ አይበዛበትም (ከኢሳ9፥6 ጋር ያነጻጽሩ)። ከዳዊት ሥርወ መንግሥት ለሚወጣው ንጉሥ እንዲህ ባለ ሁኔታ መነገሩ በደንብ የሚገባን የዕብራውያን መልእክት ጸሓፊ እንዳደረገው ነገሩ ከክርስቶስ ጋር ተያይዞ ሲቀርብ ነው (ዕብ1፥8-9)። (በአማርና ደብዳቤዎች ላይ እንደሚታየው በፓለስቲና ይኖሩ የነበሩ ነገሥታቶች አስገባሪዎቻቸው የሆኑትን የግብፅ ፈርዖኖች 'አምላኬ' እያሉ ይጠራቸው ነበር፤ በመግቢያው ላይ "ከብሉይ ኪዳን ጋር የሚዛመዱ ጥንታዊ ጽሑፎች" የሚለውን ይመ)። *ከዘላለም እስከ ዘላለም፤* ቍ2፥17 ይመ፤ እንዲህ ያሉ አባባሎች የሚነገሩት የአንድን ንጉሥ ታላቅነት ለማሳየት ነው (የ21፥4 ማብ ይመ)። እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ከገባው ቃል ኪዳን አኳያ ሲታይ ደግሞ፣ አባባሉ የላቀ ክብር ተሰጥቶት ይገኛል (89፥4፡29፡36፤ 132፥12፤ 2ሳሙ7፥16 ይመ)። በዳዊት ልጅ በክርስቶስ በኩልም ይኸው አባባል ሙሉ በሙሉ ተፈጽሞአል።

45፥7 *ከጓደኞችህ፤* ከሌላ አገር የመጡ የንጉሡ እንግዶች ሳይሆኑ አይቀርም። *የደስታ ዘይት፤* በሠርጉ ዕለት ራሱንና ሰውነቱን ሁሉ ከተቀባው ዘይት ይልቅ እግዚአብሔር ልዩ መዐዛ ባለው በሐሤት ዘይት ቀባው (23፥5፤ ኢሳ61፥3 ይመ)።

*45፥8-9፤* የንጉሡ ሰርግ ምን ያህል ሞገስ እንዳለው ያመለክታል።

45፥8 *በከርቤ፤* የዘፍ37፥25፤ የመሓ1፥13 ማብ ይመ። *የጠበድ፤* የዘፀ25፥6 ማብ ይመ። *በዝሆን ጥርስ ከተዋቡ ቤተ መንግሥቶችም፤* 1ነገ22፥39፤ አሞ3፥15፤ 6፥4 ይመ።

45፥9 *የነገሥታት ሴቶች ልጆች፤* በቤተ መንግሥቱ ውስጥ የሚቀመጡ እመቤቶች (1ነገ11፥1-3 ይመ) ወይም በሰርጉ ላይ እንዲገኙ የተጋበዙ እንግዶች ሲሆኑ ንጉሡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን እውቅናና ታላቅነት ይወክላሉ። *በኦፊር ወርቅ አጊጣ፤* አለ በተባለ አልማዝና (የዘፍ10፥29፤ የ1ነገ9፥28 ማብ ይመ) ክቡር በሆነ ወርቅ አጊጣ ማለት ነው።

*45፥10-15፤* ከቤተ መንግሥት ወገን ለሆነችው ንግሥቲት የተነገረ ቃል ነው።

*45፥10-11፤* ሞገስ ላለው ንጉሥህ ፍጹም ታማኝ ሁን።

*45፥12-15፤* የንግሥቲቱን ያመለክታል።

45፥12 *የጢሮስ ሴት ልጅ፤* የጢሮስ ከተማና ነዋሪዎቿ ሰውኛ በሆነ ዘይቤ ተገልጸዋል (የ2ነገ19፥21 ማብ ይመ)። ለዳዊት ሥርወ መንግሥት ዕውቅና ከሰጡት መካከል የጢሮስ ንጉሥ የመጀመሪያው የውጭ አገር መሪ ሲሆን (2ሳሙ5፥11 ይመ)፣ ሰሎሞንም ከዚህ መንግሥት ጋር የጠበቀ ግንኙነት ነበረው (1ነገ5፤ 9፥10-14፡26-28 ይመ)። ጢሮስ በሜድትራኒያን ባሕር ዳርቻ አካባቢ የምትገኝ የንግድ ማእከል ስትሆን በብልጽግናዋም በዓለም ዙሪያ የታወቀች ናት (ኢሳ23፤ሕዝ26፥1-28፡19 ይመ)። *ሀብታሞችም፤* በአገርሽ እንደሚገኙት ባለሀብቶች ማለት ነው። *ደጅ ይጠኑሻል፤* የዚህ ንጉሥ ሚስት እንደ መሆንሽ መጠን ባንቺ ዘንድ ከበሬታን ማግኘት ይፈልጋሉ።

45፥14 *ደናግል ጓደኞቿም፤* እርሷም "ጓደኞች" አሏት (ቍ7 ይመ) እነርሱም የሚንከባከቧትን ሴቶች ሳይሆኑ አይቀሩም። ወደ አንተም፤ ወደ ንጉሡ ማለት ነው።

45፥16 *ልጆችህ፤* የንጉሡ ልጆች ማለት ነው። *በአባቶችህ እግር ይተካሉ፤* የዘር ሐረጉ እስከ ቀጠለ ድረስ ማለት ነው፤ ምናልባትም በክብር ከአባቶቻቸው የላቁ ሊሆኑ ይችላሉ ማለት ሊሆን ይችላል (የቍ2 ማብ ይመ)።

*45፥17፤* የቍ1 ማብ ይመ። *ከዘላለም እስከ ዘላለም፤* የቍ6 ማብ ይመ።

*መዝሙር 46፤* ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ከተማ በመሆኗ የቀረበ ምስጋና ነው (ማርቲን ሉተር "አምላካችን ኀያል ምሽግ ነው" የሚለውን መዝሙር የደረሰው ከዚህ መዝሙር በመነሣት ነው)። በዐቢይ ሐሳብ ረገድ ይህ መዝሙር ከመዝ48 ጋር (እንዲሁም መዝ76፤ 87 ይመ) ጥብቅ ትስስር አለው፤ መዝ47 ግን እግዚአብሔር የምድር ገዥ መሆኑን በአጽንኦት ያሳያል። ይህ መዝሙር ምናልባት ከስደት በፊት የተደረሰ ሳይሆን አይቀርም። ሆኖም "የእግዚአብሔርን ከተማ" (ቍ4) እና በዚህም ምድር የጌታ መንበር የሆነችውን ከተማ አስመልክቶ የተደረሰ መዝሙር (መዝ48 ይመ) በመሆኑ ለእስራኤል የተስፋ መዝሙር ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር የመላው ዓለም ንጉሥ ነው። መዝ

2 ስለዚህ ምድር ብትነዋወጥ እንኳ፣
ተራሮችም ወደ ባሕር ጥልቅ ቢሰምጡ
አንፈራም::
3 ውሆች ቢያስገመግሙ፣ ዐረፋ ቢደፍቁም፣
ተራሮችም ከውሆቹ ሙላት የተነሣ
ቢንቀጠቀጡም አንደናገጥም::
ሴላ
4 የእግዚአብሔርን ከተማ፣
የልዑልን የተቀደሰ ማደሪያ ደስ
የሚያሰኝ የወንዝ ፈሳሾች አሉ::
5 እግዚአብሔር በመካከሏ ነው፤ አትናወጥም፤
አምላክ በማለዳ ይረዳታል::
6 ሕዝቦች በዐመፅ ተነሡ፤ መንግሥታትም
ወደቁ፤
ድምፁን ከፍ አድርጎ አሰማ፤ ምድርም
ቀለጠች::
7 የሰራዊት አምላክ ከእኛ ጋር ነው፤
የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው::
ሴላ

8 ኑና የእግዚአብሔርን ሥራ፣
ምድርንም እንዴት ባድማ እንዳደረጋት
እዩ::
9 ከዳር እስከ ዳር ጦርነትን ከምድር
ያስወግዳል፤
ቀስትን ይሰብራል፤ ጦርን ያነክታል፤
ጋሻንም[ሐ] በእሳት ያቃጥላል::
10 "ዕረፉ፤ እኔም አምላክ እንደ ሆንሁ
ዕወቁ፤
በሕዝቦች ዘንድ ከፍ ከፍ እላለሁ፤
በምድርም ላይ ከፍ ከፍ እላለሁ::"

፤142፥5፤ኢሳ33፥16፤ ኤር16፥19፤17፥17፤ ሰቆ 3፥57፤ኢል3፥16 ፤ናሆ1፥7፤ሉቃ1፥54 **46፥2** ቍ6፤ዘፍ4፥7 ፤ዘፀ15፥8፤መዝ3፥6፤ 18፥7፤82፥5፤97፥5፤ ኢሳ13፥13፤24፥1:19 :20፤54፥10፤ኤር4፥23 ፤ዳን11፥19፤አሞ8፥14 ፤9፥5፤ሚክ1፥4፤ናሆ1፥ 5፤ዕን3፥6፤ራእ6፥14 **46፥3** መሳ5፥5፤ኢዮ 9፥26፤መዝ93፥3፤ኢሳ 17፥13፤ኤር5፥22፤ ሕዝ1፥24፤ራእ19፥6 **46፥4** ዘፍ2፥10፤ 14፥18፤2ሳሙ15፥25፤ መዝ1፥3፤48፥1:8፤87 ፥3፤101፥8፤ራእ3፥12፤ 22፥1 **46፥5** ዘዳ23፥14፤ 1ዜና5፥20፤መዝ26፥8 ፤125፥1፤ኢሳ12፥6፤ ዘካ2፥5 **46፥6** ቍ2፤ኢዮ 12፥23፤መዝ29፥3፤68፥32፤74፥23፤102፥22፤ኢሳ 5፥30፤13፥4:13፤ 17፥12፤23፥11፤33፥3፤ሕዝ26፥18፤ማቴ 4፥8 **46፥7** ቍ11፤ዘፍ 21፥22፤1ሳሙ1፥11፤መዝ18፥2፤20፥1 **46፥8** መዝ 66፥5፤ኢሳ17፥9፤ 64፥10፤ዳን 9፥26፤ሉቃ21፥20 **46፥9** መዝ37፥15፤ኢሳ2፥4፤9፥5፤ 22፥6፤ሕዝ39፥9፤ሆሴ2፥18 **46፥10** ዘዳ4፥35፤1ነገ18፥36:39፤መዝ 18፥46፤100፥3፤ኢሳ2፥11፤37፥16:20፤43፥11፤ 45፥21 ፤ሕዝ36፥23

[ሐ]9 ወይም ሠረገላንም ተብሎ መተርጐም ይችላል::

ሙሩ በመጀመሪያ የተደረሰው በቤተ መቅደስ ውስጥ የቅዳሴ መዝሙር እንዲሆን ታስቦ ነው:: የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች (ወይም የሌዋውያን መዘምራን) የመዝሙሩን የመግቢያ አንጓና (ቍ1-3) ምላሹን (ቍ7፥11) ሲዘምሩ የሌዋውያን መሪዎች ደግሞ ሁለተኛውንና ሦስተኛውን አንጓ ዘምረው ሊሆን ይችላል (ቍ4-6:8-10):: ባወቃቀር ረገድ ሲታይ ከተደጋጋሚ አዝማቾች በስተቀር (ቍ7:11) መዝሙሩ ሦስት እኩኩል አንጓዎች ያሉት ሲሆን እያንዳንዱም አንጓ ሦስት ቍጥሮች አሉት:: ተደጋጋሚ አዝማች ያላቸውን መዝሙሮች ለመመልከት የመዝ42-43ን መግቢያ ይመ::

46ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ4 የርእስ ማብ ይመ:: *የቆሬ ልጆች፤* የመዝ42 የርእስ ማብ ይመ:: *አላሞት፤* (አግራጌ ትርጕሙን ይመ) የዕብራይስጡ ቃል ትርጕም "ደናግል" ይላል በዚህ ትርጕም መሠረት መዘምራኑ በሰልፍ ወደ ቤተ መቅደሱ ሲጓዙ ደናግሉ ከበሮ እየመቱ ያጅቧቸው እንደ ነበር ሊያሳይ ይችላል (68፥25):: *ዝማሬ፤* የመዝ30 የርእስ ማብ ይመ::

*46፥1-3፤* ዓለማት ቢንኰታኰቱና በጥልቅ ውሃም ውስጥ ቢሰጥሙም ወይም ፍጥረታትም ከዚህ በፊት እንዳልተፈጠሩ ቢሆኑም (104፥6-9፤ ዘፍ1፥9-10) ወይም ደግሞ ከጥንት ጀምሮ የነበረው ጥልቁ ሁሉንም የሚውጥ ቢመስልም እግዚአብሔር መታመኛቸው በመሆኑ ከቶ አይፈሩም:: በዚህ ቦታ በታወከ ባሕር የተመሰለው ነውጥ የሚያመለክተው የእስራኤልን ህልውና የሚፈታተኑ ጠላቶችን ነው (ቍ6:8-10፤ 65፥5-8 ይመ)::

*46፥4-6፤* የእግዚአብሔር ጥበቃና ጸጋ ያልተለያትን ጽዮንን ይገልጻል፤ ብርቱና ኀያል የሆነው አምላክ ከተማዋን ያጸናል፤ በውስጧም ይኖራል፤ ይህ ደግሞ ለከተማዋ ትልቅ ማጽናኛ ነው::

46፥4 *የወንዝ፤* እንደ ቴብስ (ናሆ3፥8)፣ እንደ ደማስቆ (2ነገ5፥12)፣ እንደ ነነዌ (ናሆ2፥6:8)፣ ወይም እንደ ባቢሎን ሁሉ (137፥1)፣ ኢየሩሳሌምም ወንዝ የላትም፤ ይሁን እንጂ የተለየ "ወንዝ" አላት:: በዚህ ቦታ የ36፥8 "ወንዝ" (የዚህኑ ማብ ይመ) ተለዋጭ ዘይቤ የማያቋርጠውንና የመንፈስ ተሐድሶም የሚሰጠውን የእግዚአብሔርን በረከት ያመለክታል፤ ይህም የእግዚአብሔርን ከተማ የዔደን ገነት ያደርጋታል (ዘፍ 2፥10፤ ኢሳ 33፥21፤ 51፥3 ይመ፤ እንዲሁም ከሕዝ31፥4-9 ጋር ያነጻጽሩ):: *የእግዚአብሔርን ከተማ፤* ቍ5 ይመ፤ በተለይም መዝ48 ይመ:: *የልዑሉን፤* ኀያሉ እግዚአብሔር ማለት ነው (57፥2፤ ዘፍ14፥9 እንዲሁም የ3፥7 ማብ ይመ:: *ማደሪያ፤* የ9፥11 ማብ ይመ:: *የወንዝ ፈሳሾች፤* የእግዚአብሔር "ወንዝ" የተባለው ሳያቋርጥ በሕዝቡ መካከል የሚፈሰውን ጸጋውን፣ ክብሩንና ኀይሉን ነው (ከቍ11፤ ከኢሳ 8፥6፤ ከሕዝ47፥1፤ ከራእ3፥12፤ 22፥1 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይህ ሕይወትን የሚሰጥ ንጹሕ ውሃ ከእግዚአብሔር አብ (ኤር2፥13)፣ ከእግዚአብሔር ወልድና (ዘካ13፥1፤ ዮሐ4፥14) ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ (7፥38-39) ዘንድ ይፈልቃል፤ የሚፈልቀውም ከእግዚአብሔር ዙፋን ወይም መንበር ሲሆን በምድር ያሉ ቅዱሳንንና (ዮሐ4፥13-14፤ 7፥38) በሰማይ ያሉ ቅዱሳንን (ራእ 22፥1)ዘወትር ያድሳል:: የዚህ ወንዝ ትልቁ በረከት የእግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል መገኘት ነው (ቍ5)፤ ይህም "የሰራዊት ጌታ ከእኛ ጋር ነው" እንደሚለው ነው (ቍ7:11)::

46፥5 *በማለዳ፤* ጎሕ ሲቀድ ማለትም ከተሞች የሚወረሩበት ሰዓት ሲቃረብ ማለት ነው፤ የጌታ ርዳታ የጨለማን ፍርሀት አስወግዶ የትድግናውን ወጋገን ያመጣል (44፥19 እና ማብ ይመ፤ ለምሳሌ ያህልም ከኢሳ 37፥36 ጋር ያነጻጽሩ)::

46፥6 *መንግሥታትም ወደቁ፤* ከእግዚአብሔር አሸናፊነት የተነሣ ነው የሚወድቁት (ቍ8-9፤ 48፥4-7 ይመ):: *ይናወጣሉ፤* ቍ3እና የቍ1-3 ማብ፤ እንዲሁም 2፥1-3፤ ራእ11፥18 ይመ:: *ድምፁን ከፍ አድርጎ፤* 2፥5፤ 9፥5፤ ኤር25፥30፤ አሞ1፥2 እንዲሁም 104፥7 ይመ:: የእግዚአብሔርን አስፈሪነትና (የመዝ29ን መግቢያ ይመ) የቍጣውንም አሸባሪነት የሚያሳይ ነው (18፥13፤ ኢሳ2፥10 ይመ):: *ምድርም ቀለጠች፤* በመብረቅ እንደ ተመታች ዐይነት ማለት ነው (97፥4-5 ይመ)::

*46፥7፤* የሕዝቡ የሐሤት ምላሽ ነው (በቍ11 ላይም ተመሳሳይ ሁኔታ ይታያል):: *የሰራዊት አምላክ፤* የ1ሳሙ1፥3 ማብ ይመ:: *የያዕቆብ፤* የ14፥7 ማብ ይመ::

*46፥8-10፤* እግዚአብሔር አሕዛብን ድል በመንሣቱ የተገኘውን ይገልጻል፤ ይፋ ያደርጋል::

46፥8 *ኑና እዩ፤* እግዚአብሔር በዓለም ላይ ያደረገውን ድል ያስተውሉ ዘንድ የቀረበ ጥሪ ነው (48፥8 እና ማብ ይመ):: *የእግዚአብሔርን፤* በመዝሙረ ዳዊት "ሁለተኛ መጽሐፍ" ውስጥ ተዘውትሮ ያልተጠቀሰ ቃል በመሆኑ በዚህ ቦታ ይህ ቃል የተጠቀሰው ለአጽንዖት ነው:: *ምድርንም፤* በዐመፀኛ ሕዝቦች መካከል ማለት ነው::

*46፥9፤* ከእንግዲህ በእርሱ ከተማ ላይ ጥቃት አይሰነዘርም፤ ጥቅሱ ምናልባት በመላው ዓለም ላይ ስለሚሰፍነው ሰላም ሳያመለክት አይቀርም (የ65፥6-7 ማብ ይመ):: *ይሰብራል ... ያነክታል፤ ያቃጥላል፤* 76፥3፤ እንዲሁም 1ሳሙ2፥4 ይመ:: መሲሕ በእስራኤል ጠላቶች ላይ ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ ድልን እንደሚቀዳጅ ለማየት ኢሳ9፥2-7 ይመ::

*46፥10፤* እግዚአብሔር ለመንግሥታት ሲናገር ድምፁ ከዳር እስከ ዳር ያስተጋባል (ቍ6 ይመ)፤ ይህም የመዝሙሩ የመጨረሻው ከፍተኛ ሐሳብ ነው:: *ዕረፉ፤* በ1ሳሙ15፥16 ("ተወው በቃ") ላይ እንደ ተመለከተው ሁሉ በዚህም ቦታ የዚህ ሐረግ የዕብራይስጡ ፍች "ይበቃል" የሚል ሳይሆን አይቀርም:: *ዕወቁ፤* አስተውሉ፤ ልብ አድርጉ ማለት ነው:: *በሕዝቦች ዘንድ ከፍ ከፍ እላለሁ፤* እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል የፈጸማቸው ታላላቅ ተግባራት በመላው ዓለም በሚገኙ ሕዝቦች ዘንድ ዓለም አቀፍ ዕውቅናን ያመጣለታል፤ ይህ ሐሳብ በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ዐቢይ ሐሳብ ነው (22፥27፤ 47፥9፤ 57፥5:11፤ 64፥9፤ 65፥8፤ 66፥1-7፤ 67፥2-5፤ 86፥9፤ 98፥2-3፤ 99፥2-3፤ 102፥15)፤ ይህ ዐቢይ ሐሳብ በሌሎችም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ይገኛል (ዘፀ7፥5፤ 14፥4:18፤ ዘሌ26፥45፤ ዘኍ14፥15፤ 1ሳሙ 17፥46፤ 1ነገ 8፥41-43፤ 2ነገ 19፥19፤ ሕዝ 20፥41፤ 28፥25፤ 36፥23፤ ዕን2፥14 ይመ):: ይህ እውነታ ማለትም ይህ ድንቅ የማዳን ሥራ በጌታችን መወለድ፣ ሕይወት፣ ሞት፣ ትንሣኤና ክብር እውን ሆኖ የታየ ሲሆን፣ ይኸው እውነታም በእርሱ ዳግም ምጽአት የመጨረሻውን ፍጽምና ያገኛል::

11የሰራዊት አምላክ ከእኛ ጋር ነው፤
የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው።
ሴላ

## መዝሙር 47

### እግዚአብሔር፣ የእስራኤል ንጉሥ የዓለም ጌታ

*ለመዘምራን አለቃ፤ የቆሬ ልጆች መዝሙር።*

1ሕዝቦች ሁላችሁ እጆቻችሁን አጨብጭቡ፤
ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ ለእግዚ
አብሔር እልል በሉ።
2በምድር ሁሉ ላይ ታላቅ የሆነው ንጉሥ፣
ልዑል *እግዚአብሔር* የሚያስፈራ ነውና።
3ሕዝቦችን ከእኛ በታች አደረገ፤
*መንግሥታትንም* ከእግራችን *ሥር*
አስገዛልን።
4ለሚወደው ለያዕቆብ ክብር የሆነችውን፣
ርስታችንን እርሱ መረጠልን።
5አምላክ በእልልታ፣
*እግዚአብሔር* በመለከት ድምፅ ዐረገ።
6አምላካችንን አወድሱት፤ አወድሱት፤
ንጉሣችንን አወድሱት፤ አወድሱት፤
7*እግዚአብሔር* የምድር ሁሉ ንጉሥ ነውና፤
ምርጥ ዝማሬ[ጣ] አቅርቡለት።
8እግዚአብሔር በሕዝቦች ላይ ነግሦአል፤
እግዚአብሔር በተቀደሰ ዙፋኑ ላይ
ተቀምጦአል።
9ከአብርሃም አምላክ ሕዝብ ጋር፣
የሕዝቦች መኳንንት ተሰበሰቡ፤
የምድር ነገሥታት[ጣ] የእግዚአብሔር ናቸውና፤
እርሱም እጅግ ከፍ ከፍ ያለ ነው።

46፥11. ቍ7፤መዝ 20፥1
47፥1 2ነገ11፥12 ፤መዝ33፥3
47፥2 ዘፍ14፥18፤ ዘዳ7፥21፤መዝ2፥6፤48፥2፤95፥3፤ማቴ5፥35
47፥3 መዝ18፥39፡47፤ኢሳ14፥6
47፥4 መዝ2፥8፤16፥6፤78፥55፤አሞ 6፥8፤8፥7፤1ጴጥ1፥4
47፥5 ዘኍ10፥2፤ 2ሳሙ6፥15፤ኢዮ 8፥21፤መዝ68፥18፤ 106፥5፤ኤፌ4፥8
47፥6 2ሳሙ22፥50
47፥7 1ዜና16፥7፤ ዘካ14፥9፤ቈላ3፥16
47፥8 1ነገ22፥19፤ 1ዜና16፥31፤መዝ9፥4 ፤ራእ4፥9
47፥9 ኢዮ25፥2፤ መዝ46፥10፤97፥9
48፥1 ዘዳ33፥19፤ 2ሳሙ22፥4፤1ዜና16፥25፤መዝ2፥6፤18፥3፤

## መዝሙር 48

### የእግዚአብሔር ተራራ ጽዮን

*ዝማሬ፤ የቆሬ ልጆች መዝሙር*

1*እግዚአብሔር* ታላቅ ነው፤
በአምላካችን ከተማ በተቀደሰው ተራራ
ከፍ ያለ ምስጋና ይገባዋል።

46፥4፤86፥10፤87፥1፤96፥4፤99፥2፤135፥5፤147፥7፤ኢሳ11፥9፤32፥16፤ኤር10፥6፤31፥23፤ዳን9፥16፤ሚክ4፥1፤ዘካ8፥3

ጣ7 ዕብራይስጡ ማሽኪል ይላል፤ ይኸውም የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የሙዚቃውን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።
ጣ9 ወይም ጋሻዎች

*46፥11፤* የቍ7 ማብ ይመ።

*መዝሙር 47፤* የአጥናፈ ዓለም ገዥ ለሆነው ለእስራኤል አምላክ የቀረበ ምስጋና ነው፤ ምስጋናው የቀረበው ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ ምስክር እንዲሆን ነው።ይህ መዝሙር ታላቁን ንጉሥ ለማመስገን ከተደረሱትና ከመዝ92-100 መካከል ካሉት መዝሙሮች ተርታ የሚመደብ ነው፤ በዚህ ቦታ ግን መዝ46 እና 48 የሚያያዝ ሲሆን በጽዮን ላይ የነገሠው አምላክ "በምድር ሁሉ ላይ ታላቅ ንጉሥ" (ቍ2:7፤ 48፥2 ይመ) መሆኑን ያመለክታል። መዝሙሩ የተደረሰው ንጉሣዊ አገዛዝ በተጀመረበት ወቅት ሲሆን ዐበይት በሆኑ በዓላት ላይ በቤተ መቅደስ ውስጥ በቅዳሴ መልክ የሚዘመር ነው። የዚህ መዝሙር ልዩ ድባቡ፣ መቼቱ ወይም (ዐውዱ) የዳስ በዓል ነው (ዘሌ23፥34 ይመ)፤ ይህ በዓል ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ለማስመረቅ ቀን-ቀጠሮ የያዘበት በዓል ነው (1ነገ8፥2 ይመ)። በመዝ24 እና 68 ላይ እንደ ተመለከተው ሁሉ ይህ መዝሙር የቅዳሴ ጉዞ (ቍ5) መዝሙር ሳይሆን አይቀርም። ከጊዜ በኋላ ይህ መዝሙር በአይሁዶች የዘመን መለወጫ በዓል ላይ በቤተ መቅደስ ውስጥ እንዲዘመር ተደርጎአል። ቤተ ክርስቲያንም የጌታን ዕርገት ለማክበር ይህንን መዝሙር ትጠቀምበታለች (ቍ5 ይመ)። ባወቃቀር ረገድ ሲታይ ቍ5 እና 6 በሁለት በሁለት ቤት በመቀናጀት የመዝሙሩ እምብርት በመሆን ያገለግላሉ (የ6፥6 ማብ ይመ)። የመዝሙሩ እምብርት በቅዳሴ ሥርዐት ሂደት የተለየ ዜማን ወክሎ ሊገኝ ይችላል።

*47ርእስ፤* የመዝ42 የርእስ ማብ ይመ።

*47፥1-4፤* ሕዝቦች ሁሉ በመላው ምድር ላይ ጌታ በሆነው አምላክ ሐሤት እንዲያደርጉ ተጠርተዋል፤ የምድር ሕዝቦች ሁሉ የወንጌል መልእክት እንደሚደርሳቸው በብሉይ ኪዳንም አስቀድሞ የተነገረ መሆኑን ያሳያል (የ9፥1 ማብ ይመ)።

47፥1 *ሕዝቦች ሁላችሁ ... አጨብጭቡ፤* ንጉሥ በሚነግሥበት ጊዜ (2ነገ11፥12፤ እንዲሁም 98፥8 ይመ)፣ ወይም በሌላ የደስታ ዕለት ማለት ነው (ኢሳ55፥12 ይመ)። *እልል በሉ፤* 1ነገ1፥40፤ 2ነገ 11፥14 ይመ።

*47፥2-3፤* የምድር ሁሉ ጌታ የሕዝቡን የእስራኤልን የወደፊት ዕድል አስተካክሎአል (105፥6፤ 135፥4፤ዘፀ9፥29፤ 15፥1-18፤ 19፥5-6፤ ዘዳ7፥6፤ 14፥2፤ ኢሳ41፥8 ይመ)።

47፥2 *የሚያስፈራ ነውና፤* 68፥35፤ 89፥7፤ 99፥3፤ 111፥9 ይመ፤ እንዲሁም የ45፥4 ማብ ይመ። *ልዑል እግዚአብሔር፤* የዘፍ 14፥19 ማብ ይመ። *ታላቅ የሆነው ንጉሥ፤* የአሦር ንጉሥ ነገሥታት ዘወትር የሚጠቀሙበት ማዕርግ ነው (የ2ነገ 18፥19 ማብ ይመ)።

*47፥3፤* 2ሳሙ5፥17-25፤ 8፥1-14፤ 10 ይመ።

47፥4 *ርስታችንን፤* የተስፋዪቱን ምድር ነው (ዘፍ12፥7፤ 17፥8፤ ዘፀ 3፥8፤ ዘዳ 1፥8፤ ኤር3፥18 ይመ)። *ክብር የሆነችውን፤* በእጆቱ ሐሤት ሚያደርግበትን ነው። *ያዕቆብ፤* የ14፥7 ማብ ይመ።

*47፥5-6፤* የግጥሙ ዕንብርት ነው (የ6፥6 ማብ ይመ)። እነዚህ ቍጥሮች እግዚአብሔር በቅዳሴ ሥርዐት ታጅቦ ወደ ቤተ መቅደሱ ውስጥ ሲገባ ያመለክታሉ፤ ይህም የቃል ኪዳኑ ታቦት በሰዎች ታጅቦ ወደ ቤተ መቅደሱ ውስጥ የገባበትን ሁኔታ የሚወክል ሳይሆን አይቀርም። ታቦቱ የእግዚአብሔር ዙፋን ተምሳሌት ነው፤ ቤተ መቅደሱ ደግሞ የሰማይ ዙፋኑ ትእምርት ነው (መዝ24፥68 ይመ)።

47፥5 *በእልልታ ... በመለከት ድምፅ፤* የቍ1 ማብ ይመ። በዚህ ቦታ ቀንደ መለከቱ እግዚአብሔር ኀያል ንጉሥ መሆኑን ያውጃል (98፥6፤ ዘፀ19፥16:19፤ ኢሱ6፥4 ይመ)።

*47፥7-9፤* እግዚአብሔር የመላው ዓለም ንጉሥ መሆኑን የሚያውጅ ክፍል ነው።

47፥7 *እግዚአብሔር የምድር ሁሉ ንጉሥ ነውና፤* 2ሳሙ 15፥10፤ 2ነገ9፥13፤ ኢሳ52፥7 ይመ። *ዝማሬ፤* ቅኔ ነው፤ የመዝ 32 የርእስ ማብ ይመ።

47፥8 *በቅዱስ ዙፋኑ ላይ ተቀምጦአል፤* መላውን ዓለም በመዳፉና በአገዛዙ ሥር አድርጐ በሚገዛበት በቅድስተ ቅዱሳን ዙፋኑ ላይ አለ ማለት ነው (ኤር17፥12 ይመ)። ይህ ቍጥር በዮሐንስ ራዕይ ላይ በተደጋጋሚ ተጠቅሶአል (ራእ4፥9:10፤ 5፥1፡7:13፤ 6፥16፤ 7፥10:15፤ 19፥4 ይመ)።

*47፥9፤* ሕዝቦች ሁሉ የእስራኤል አምላክ ታላቅና ወደር የማይገኝለት ንጉሥ መሆኑን ያስተውላሉ፤ ይህም እግዚአብሔር በመጨረሻ ሁሉንም እንደሚገዛ አስቀድሞ ያመለክታል (የ46፥10 ማብ ይመ)። *እንደ አብርሃም አምላክ ሕዝብ ሁሉ፤* ስለዚህ ለአብርሃም የተሰጠው ተስፋ ይፈጸማል (ዘፍ12፥2-3፤ 17፥4-6፤ 22፥17-18 ይመ)። *ነገሥታት፤* የ3፥3 አግራጭ ትርጉም ይመ፤ ከኢሳ 2፥2፤ 56፥7 ጋር ያነጻጽሩ።

*መዝሙር 48፤* ጽዮን የታላቁ ንጉሥ ከተማና የሕዝቡም መሸሸጊያ በመሆኗ የቀረበ ምስጋና ነው (የመዝ46-47ን መግቢያ ይመ)። ይህ መዝሙር ወደ ቤተ መቅደስ ለአምልኮ በመጡ ምእመናን ፊት በሌዋውያን መዘምራን የተዘመረ ሊሆን ይችላል። የዚህ መዝሙር አወቃቀርና ዐቢይ ሐሳብ ማራኪ በሆነ መንገድ ተዛምደዋል። የመጀመሪያውና የመጨረሻው ቍጥሮች በአንድ ላይ በመሆን የጽዮን አምላክ መጽናኛ መሆኑን ያበስራሉ። የመዝሙሩ እምብርት ማለትም ቍ8 (የ6፥6 ማብ ይመ) የመዝሙሩን ዐቢይ ሐሳብ በአጭሩ ያቀርባል። የመዝሙሩን ዐቢይ ሐሳብ አራት አንጓዎች (በዕብራይስጡ እኩኩል የሆነ ቅርጽ አላቸው፤ ሦስት ስንኞች፣ አራት ስንኞች፣ አራት ስንኞች፣ ሦስት ስንኞች)፣ አሳድገውታል፤ (1) የጽዮን ውበቷ የማትደፈር የእግዚአብሔር ምሽግ መሆኗ ነው (ቍ2-3)፤ (2) ጠላት ጽዮንን ለማጥፋት የሚያደርገው ሙከራ ሁሉ መና ይሆናል (ቍ 4-7) (3) በእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ጽዮን ሐሤት ታደርጋላችሁ (ቍ9-11)፤ ይህም ከሁለተኛው አንጓ ጋር የተሳሰረ ነው (4) ጽዮን የማትደፈር ምሽግ ናት (ቍ12-13)፤ ይህ ደግሞ ከመጀመሪያው አንጓ ጋር የተያያዘ ነው (የቍ2:7:10:13 ማብ ይመ)።

48ርእስ፤ *መዝሙር፤* የመዝ 30 የርእስ ማብ ይመ። *የቆሬ ልጆች፤* የመዝ 42 የርእስ ማብ ይመ።

48፥1 *በአምላካችን ከተማ በተቀደሰው ተራራው፤* መዝ 46፥4 ይመ። *በአምላካችን፤* በዚህ መዝሙር ላይ በዚህ ቦታ ብቻ እና

2የምድር ሁሉ ደስታ የሆነው፣
በሰሜን በኩልʻ በርቀት የሚታየው፣
በከፍታ ላይ አምሮ የደመቀው የጽዮን
ተራራ፣
የታላቁ ንጉሥ ከተማ ነው::
3እግዚአብሔር በአዳራሾቿ ውስጥ ሆኖ፤
ብርቱ ምሽግ እንደ ሆናት
አስመስክሮአል::

4እነሆ፤ ነገሥታት ተባብረው መጡ፤
አንድ ላይ ሆነውም ገሠገሡ::
5አይተውም ተደነቁ፤
ደንግጠውም ፈረጠጡ::
6ምጥ እንደ ያዛት ሴት፣
በዚያ ብርክ ያዛቸው::
7የምሥራቅ ነፋስ የተርሴስን መርከብ
እንደሚሰባብር፣
አንተ አብረከረከሃቸው::

8እንደ ሰማን፣
በሰራዊት አምላክ ከተማ፣
በአምላካችን ከተማ፣
እንዲሁ አየን፤
እግዚአብሔር ለዘላለም ያጸናታል:: ሴላ

9አምላክ ሆይ፤ በቤተ መቅደስህ ውስጥ
ሆነን፣
ምሕረትህን እናስባለን::
10አምላክ ሆይ፤ ምስጋናህ እንደ ስምህ፣
እስከ ምድር ዳርቻ ይዘልቃል፤
ቀኝ እጅህም ጽድቅን የተሞላች ናት::
11ስለ ፍርድህ፣
የጽዮን ተራራ ሐሤት ታድርግ፤
የይሁዳ መንደሮችም ደስ ይበላቸው::

12በጽዮን አካባቢ ተመላለሱ፤ ዙሪያዋንም
ሂዱ፤
የጥበቃ ግንቦቿንም ቍጠሩ፤
13ለሚቀጥለው ትውልድ ትናገሩ ዘንድ፣
መከላከያ ዕርዶቿን ልብ ብላችሁ
ተመልከቱ፤
መጠበቂያ ማማዎቿን እዩ::
14ይህ አምላክ ከዘላለም እስከ ዘላለም
አምላካችን ነውና፤
እስከ መጨረሻው የሚመራንም እርሱ
ነው::

## መዝሙር 49

### የሀብት ከንቱነት

ለመዘምራን አለቃ፤ የቆሬ ልጆች መዝሙር::

1እናንተ ሕዝቦች ሁላችሁ፤ ይህን ስሙ፤

ʻ2 *ዛፎን የሚለው የዕብራይስጡ ቃል የተቀደሰ ተራራን ወይም የሰሜንን አቅጣጫ ሊያመለክት ይችላል::*

48፥2 ኢሱ13፥27፤ መዝ2፥6፤50፥2፤ሰቆ 2፥15፤ሕዝ16፥14፤ ማቴ5፥35
48፥3 ቍ13፤መዝ 18፥2፤122፥7
48፥4 2ሳሙ10፥1-19
48፥5 ዘፀ15፥16፤ ኢሳ13፥8፤ኤር46፥5፤ ዳን5፥9
48፥6 ዘፍ3፥16፤ ኢዮ4፥14
48፥7 ዘፍ10፥4፤41፥6፤1ነገ10፥22፤22፥48
48፥8 ኤር23፥6፤ ዘካ8፥13፤14፥11
48፥9 መዝ6፥4፤ 39፥3
48፥10 ዘዐ6፥3፤ኢሱ 7፥9፤1ሳሙ2፥10፤ መዝ22፥27፤65፥5፤98፥3፤100፥1፤ኢሳ 11፥12፤24፥16፤ 42፥10፤49፥6
48፥11 መዝ97፥8
48፥12 ነህ3፥1
48፥13 ቍ3፤2ሳሙ 20፥15፤መዝ71፥18፤ 78፥6፤109፥13፤ኢሳ 26፥1፤ሰቆ2፥8፤ዕን2፥1
48፥14 መዝ25፥5፤ 73፥24፤ምሳ6፥22፤

በመዝሙሩ ዕንብርት (ቍ8) እንዲሁም መዝጊያ (ቍ 14) ላይ ብቻ ይገኛል:: *በተቀደሰው ተራራ፤* 43፥3፤ እንዲሁም የ2፥6 ማብ ይመ::

*48፥2-3፤* የጽዮን ተራራ ከፍ ያለችና ማንም የማይደርስ ባት መሆኑን ይገልጻል::

48፥2 *አምሮ፤* ውበቱ የተመሠረተው በመጠጊያነቷ ላይ ነው (የ27፥4 ማብ ይመ):: *በከፍታ፤* በአካባቢዋ ከሚገኙት ተራሮች ሁሉ የላቀች ባትሆንም የእግዚአብሔር ተራራ በመሆኗ፣ በዓለም ዙሪያ ካሉ "ተራራዎች" ሁሉ እርሷ "የላቀች ከፍተኛ" ተራራ ናት (68፥15-16 እና ማብ፤ ኢሳ2፥2 ይመ):: *የምድር ሁሉ ደስታ፤* ንግሥተ ሳባ አድናቆቷን እንደ ገለጸች (1ነገ 10፥1-3 ይመ)፣ ሌሎች ሕዝቦችም እንዲሁ አድናቆታቸውን ይገልጻሉ:: *በሰሜን በኩል፤* የኦሎምፒያ ተራራ ለግሪካውያን፣ "የአማልክት አምላክ" ለሚሉት ለዚዎስ ምሽግ እንደ ሆነ ሁሉ፣ የዛፎን ተራራም ፊን ቂያውያን "የአማልክት አምላክ" ለሚሉት ለኤል የተቀደሰ ማደ ሪያ ነው:: *የታላቁ ንጉሥ፤* የ47፥2 ማብ ይመ::

*48፥3፤* የጽዮን ጥላ ከለላ ቅጽሮቿ ሳይሆኑ ራሱ እግዚአ ብሔር አምላክ ነው:: ቀጣዩም አንጓ የሚያብራራው ይህንን እውነታ ነው (የቍ12-13 ማብ ይመ):: *ምሽግ፤* ቍ13 ይመ::

*48፥4-7፤* የሞገደኛ ሕዝቦች ጥቃት ሁሉ ከንቱ ሆኖ ይቀ ራል፤ ታላቁም ንጉሥ በጽዮን እንዳለ ባወቁ ጊዜ በድንጋጤ ይሸሻሉ:: ይህ መዝሙር የተደረሰው በኢዮሣፍጥ ዘመን በኅብረት ሊያጠቁ የመጡ አገሮች እንዳልነበሩ መቅረታቸውን (2ዜና 20 ይመ) ወይም በሕዝቅያስ ዘመን አሦራውያን በሰይፍ መመታታ ቸውን (2ነገ19፥35-36 ይመ) በማስታወስ ሳይሆን አይቀርም::

48፥7 *የተርሴስን መርከቦች፤* በሜድትራኒያን ባሕር ላይ የማ ይታጡ የሀብታም ነጋዴዎች ታላላቅ መርከቦች ናቸው (1ነገ 10፥22 ይመ):: *የምሥራቅ ነፋስ፤* ሐሥ27፥14፤ እንዲሁም 1ነገ 22፥48 ይመ:: *የምሥራቅ፤* ከፍ ሲል የቀረበውን የዚህን መዝሙር መግቢያ ይመ::

*48፥8፤* የመዝሙሩ እምብርትና ዐቢይ ሐሳብ ነው (የ6፥6 ማብ ይመ):: *እንደ ሰማን ... አየን፤* እንደ ኢዮ42፥5 ሁሉ "አየን" የሚለው ቃል የነገሩን ጣሪያ ያሳያል:: ሊሰሙ የቻሉትም "እነርሱ በነበሩት ያደረግኸውን አባቶቻቸው ስለነገሯቸው" ነው (44፥1፤ 78፥3 ይመ) አሁን ግን በመቅደሱ ውስጥ በሚካሄደው የቅዳሴ ሥርዐት አማካይነት፣ የእግዚአብሔር ከተማ ምን ያህል የታፈረች መሆኗን አይተዋል:: *በሰራዊት አምላክ፤* የ1ሳሙ1፥3 ማብ ይመ:: *በአምላካችን፤* የቍ1 ማብ ይመ::

*48፥9-11፤* እግዚአብሔር በጽዮን ፊት ያደረገውን ድንቅ ሥራ በመመልከት ለአምልኮ ወደ ቤተ መቅደስ የመጡ ምዕ መናን ሁኔታውን በሐሤት ያሰላስላሉ::

48፥9 *በቤተ መቅደስህ፤* በቤተ መቅደሱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ማለት ነው:: *ምሕረትህ፤* የ6፥4 ማብ ይመ:: በቍ10-11 ላይ በግልጽ እንደሚታየው የመዝሙሩ ደራሲ ሊያሳየን የሚፈ ልገው እግዚአብሔር ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ ለሕዝቡ የገለጸውን የኪዳኑን ፍቅር ነው (31፥21፤ 40፥9-10 ይመ)::

48፥10 *ስምህ፤* የ5፥11 ማብ ይመ:: *ይዘልቃል፤* ከቤተ መቅደስ ተነሥቶ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ይሰፍናል ማለት ነው (9፥11፤ 22፥27 ይመ):: *ቀኝ እጅህም፤* በዕብራይስጥ ፈሊጣዊ አነጋገር ውስጥ ስውር በሆነ አገላለጽ ደቡባዊ አቅጣጫን ያመለ ክታል:: *ጽድቅን፤* የጽድቅ ሥራ ማለት ነው (40፥9-10 እና ማብ፤ እንዲሁም የ4፥1 ማብ ይመ)::

48፥11 *ስለ ፍርድህ፤* እግዚአብሔር ጽዮንን ሲታደግ የሚ ሰጠውን ትክክለኛ ፍርድ ማለት ነው::

*48፥12-13፤* ሕዝቡ በቤተ መቅደሱ ውስጥ "በዐይናቸው ካዩት" (ቍ8) እውነታ የተነሣ በጽዮን ዙሪያ ያለውን መከላከያ አስተዋሉ:: የጽዮን ግንብ፣ ቅርጽና ምሽግ እግዚአብሔር ራሱ በሕዝቡ ዘንድ መገኘቱ ነው::

48፥13 *ለሚቀጥለው ትውልድ፤* በቀጥታ ሲተረጐም "የሚ መጣው ትውልድ" ማለት ነው፤ በዕብራይስጥ ፈሊጣዊ አገላለጽ፣ "የሚቀጥለው" የሚለው ቃል ምዕራባዊ አቅጣጫን ያመለክታል::

48፥14 *አምላካችን፤* የቍ1 ማብ ይመ:: *የሚመራንም፤* ታላቁ እረኛና ንጉሥ (የ23፥1 ማብ ይመ):: *መጨረሻው፤* በቀ ጥታ ሲተረጐም "ሞት" ማለት ነው::

*መዝ49* ይህ መዝሙር በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚነገር መዝሙር ሲሆን የተጻፈውም መዝ46-48ን ተከትሎ ነው (የመዝ ሙርን መጽሐፍን መግቢያ ይመ):: መዝሙሩ በዚህ ዓለም ሲኖሩ በሀብታቸውና በራሳቸው ተመክተው ተደላድለን እንቀመጣለን የሚሉ ሰዎች ሞኞች እንደ ሆኑ ያስተምራል (መዝ52 ይመ):: የመዝሙሩ ጸሐፊ ሌዋዊ ሲሆን ሀብት የለሽ ወይም ያጣ የነጣ ሰው መሆን ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ ያውቃል (ዘኍ18፥21-24፤ ዘዳ14፥27-29)፤ እንዲሁም የብዙ ሀብታሞችን አመለካከት መዝኖአል (ቍ5-6 ይመ):: ጸሐፊው ሰዎች ሁሉ ከንቱ አስተ ሳሰባቸውን ተገንዝበው ጥበቡን እንዲያስተውሉ ጥሪ ያቀርባል (ቍ1-2)፤ ይኸውም በባለጸጋዎች ሀብት የተማረኩ ሁሉ ዐይና ቸውን ከዚያ እንዲመልሱ ለማድረግ ነው:: አይቀሬው ሞት ከደጅ ይጠብቃቸዋል፤ ዕጣ ፈንታቸውም እርሱው ይሆናል፤ በመ ጨረሻም "ቅኖች ... ይገዟቸዋል" (ቍ14):: ይህ መዝሙር የተጻፈው ከድኅረ ምርኮ በኋላ ሳይሆን አይቀርም፤ የመዝ37 ማብ ይመ::

*49ርእስ፤* የመዝ 42 ርእስ ማብ ይመ::

በዓለም የምትኖሩ ሁሉ፤ ይህን
አድምጡ::
2 ዝቅተኞችና ከፍተኞች፤
ባለጠጎችና ድኾች ይህን በአንድነት
ስሙ::
3 አፌ የጥበብን ቃል ይናገራል፤
የልቤም ሐሳብ ማስተዋልን ይሰጣል::
4 ጆሮዬን ወደ ምሳሌ አዘነብላለሁ፤
እንቆቅልሼንም በበገና እፈታለሁ::
5 የአጭበርባሪዎች ክፋት በከበበኝ ጊዜ፣
በክፉ ቀን ለምን እፈራለሁ?
6 በሀብታቸው የሚመኩትን፣
በብልጽግናቸውም የሚታመኑትን ለምን
እፈራለሁ?
7 የሌላውን ሕይወት መቤዠት የሚችል
ሰው፣
ወይም ለእግዚአብሔር ወጆ የሚከፍልለት
ማንም የለም::
8 የነፍስ ቤዛ ውድ ነውና፤
በቂ ዋጋም ከቶ ሊገኝለት አይችልም፤
9 በዚህም ዘላለም ይኖራል፣
መበስበስንም አያይም::
10 ጠቢባን ሟች መሆናቸው የሚታይ ነው፤
ቂልና ሞኝም በአንድነት ይጠፋሉ፤
ጥሪታቸውንም ለሌላው ጥለው ይሄዳሉ::
11 መሬቶችን በስማቸው ቢሰይሙም፣
መቃብራቸው የዘላለም ቤታቸው፣
ከትውልድ እስከ ትውልድም

ኢሳ49፥10፤57፥18፤58፥11
49፥1 መዝ33፥8፤78፥1፤ኢሳ1፥2
49፥2 መዝ62፥9
49፥3 መዝ37፥30፤119፥130
49፥4 ዘኍ12፥8፤1ሳሙ16፥16፤መዝ33፥2፤78፥2፤ምሳ1፥6፤ሕዝ12፥22፤16፥44፤18፥2-3፤ሉቃ4፥23
49፥5 መዝ23፥4፤27፥1
49፥6 ኢዮ22፥25፤36፥19፤መዝ10፥3፤73፥12፤ኤር48፥7
49፥8 ዘኍ35፥31፤ማቴ16፥26
49፥9 መዝ16፥10፤22፥29፤89፥48
49፥10 ኢዮ27፥17፤መዝ92፥6፤94፥8፤መክ2፥16፡18፡21፤ሉቃ12፥20
49፥11 ዘዳ3፥14፤መዝ106፥31፤ማር5፥3፤ሉቃ8፥27
49፥12 ቍ20፤ኢዮ14፥2፤2ጴጥ2፥12
49፥13 ሉቃ12፥20
49፥14 ዘኍ16፥30፤ኢዮ21፥13፤መዝ9፥17፤55፥15፤ኢሳ14፥2፤ኤር43፥11፤ሕዝ31፥14፤ዳን7፥18፤1ቆሮ6፥2
49፥15 ዘፍ5፥24፤መዝ56፥13፤ሆሴ

መኖሪያቸው ይሆናል::
12 ሰው በሀብቱ እንደ ተከበረ አይዘልቅም፤
ታይተው የሚጠፉ እንስሳትን
ይመስላል::[ˆ]
13 ይህ የተላላዎች ዕድል ፈንታ፣
የእነርሱንም አባባል ተቀብለው
ለሚከተሏቸው፣
መጨረሻ ግብ ነው:: ሴላ
14 እንደ በጎች ለሲኦል[‡] የተዳረጉ ናቸው፤
ሞትም እረኛቸው ይሆናል፤
ቅኖች በማለዳ ይገዟቸዋል፤
አካላቸው ከክብር ቤታቸው ርቆ፣
በሲኦል ይፈራርሳል::
15 እግዚአብሔር ግን ነፍሴን[†] ከሲኦል እጅ
ይቤዠኛል፤
በእርግጥም በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት
አለኝ:: ሴላ
16 ሰው ባለጠጋ ሲሆን፣
የቤቱም ክብር ሲበዛለት አትፍራ፤
17 በሚሞትበትም ጊዜ ይዞት የሚሄደው
አንዳች የለምና፤
ክብሩም አብሮት አይወርድም::

13፥14 49፥17 መዝ17፥14 ፤1ጢሞ6፥7

[ˆ]12 በሰብዓ ሊቃናት ትርጕምና በሱርስቱ ቅጂ ቍ12 ከቍ20 ጋር አንድ ዐይነት ነው፤ ዕብራይስጡ ግን ከዚህ ይለያል::
[‡]14 በዚህ እና በቍ15 ላይ ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል አንዳንድ የእንግሊዝኛ ቅጆች ግን *መቃብር* ይላሉ::
[†]15 *ወይም ሕይወቴን*

*49፥1-4፤* የመዝሙሩ መግቢያ ነው::

*49፥1-2፤* የጥበብ መምህራን በሚናገሩት ዐይነት የተነገረ ሳይሆን (34፥11፤ ምሳ1፥10፡18፤ 2፥1) ነቢያት በሚናገሩት ዐይነት የተነገረ ነው (1ነገ22፥28፤ ኢሳ34፥1፤ ሚክ1፥2 ይመ)::

*49፥3፤* ማቴ 12፥34 ይመ:: ***የጥበብን፤*** በመጽሐፈ ምሳሌ መግቢያ ላይ "የጥበብ መጻሕፍት" የሚለውን ክፍል ይመ:: ***የልቤም፤*** የ4፥7 ማብ ይመ::

49፥4 ***ጆሮዬን ... አዘነብላለሁ፤*** ጥበብን ከመናገሩ በፊት እርሱ ራሱ ጥበብን "ማድመጥ" አለበት፤ እውነተኛ ጥበብ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው (ኢዮ28 ይመ):: ***በበገና፤*** ጸሓፊው በመንፈስ ምሪት ውስጥ ስለ መሆኑ ሌላው ማስረጃ ነው (1ሳሙ10፥5-6፤ 2ነገ3፥15 ይመ)::

*49፥5-11፤* ምስኪኖችና ኀይል የለሾች ሀብታሞች ከበው ሲያስፈራሯቸውና ሲያስጨንቋቸው መፍራት የለባቸውም፤ ዕጣ ፈንታቸው ሞት ነው::

*49፥7-9፤* ሀብት ከሞት ማምለጫ ሊሆን አይችልም፤ ሕይወትን "ለመቤዠት" የሚከፈለው ክፍያ እንኳ ከሞት ማዳን አይችልም (ከዘፀ21፥30፤ ከዘሌ25፥47-49 ጋር ያነጻጽሩ):: ሕይወትን ከሞት የሚቤዥ እግዚአብሔር ብቻ ነው (ቍ15 እና ማብ ይመ)::

*49፥10፤* ዐይኖቹን በራሱ ላይ ያደረገ ሰው (መክ2፥14) ጥበበኞች እንኳ ሀብታቸውን ለሌላ ሰው ትተው (መክ2፥18፡21) እንደሚሞቱ ይገነዘባል (መክ7፥2፤ 9፥5 ይመ):: ታዲያ ሞኞች ከሞት እንዴት ሊያመልጡ ይችላሉ (73፥18-20፤92፥6-7 ይመ):: እንዲሁም 89፥48፤ ኢዮ30፥23፤ መክ2፥14-16 ይመ:: ***ጠቢባን ... ቂሎች፤*** በመዝ37 ላይ "ጻድቃን" ... "ክፉዎች" የተባሉት ናቸው:: ***ጥሪታቸውን፤*** አብዛኛውን ጊዜ በክፉ መንገዳቸው የተከማቸ ሀብት ነው (ቍ5):: ***ለሌላው፤*** ለልጆቻቸው ግን አይደለም (የ37፥29፤ እንዲሁም 39፥6፤ ሉቃ12፥20-21 ይመ)::

*49፥11፤* ምንም እንኳ በመቃብራቸው ላይ ሐውልት ለማሠራትና በንብረቶቻቸው ላይ ስማቸውን ለማስጠራት (ዘኍ32፥41 ይመ) ሀብታቸውን ሁሉ ቢከሰክሱም መቃብር "የዘላለም ቤታቸው" (መክ12፥5) ይሆናል የሚለው አባባል ምፀት ሆኖ ይፈጸምባቸዋል::

*49፥12፤* ስምን ለማስታወስ በመቃብር ላይ የሚጻፍ ነው (የ10፥18 ማብ፤ እንዲሁም መክ3፥19፤ 7፥2 ይመ)፤ ከዚህም በላይ የመዝሙሩ አዝማች ስንኝ ነው (የመዝ42-43 መግቢያን ይመ)::

*49፥13-15፤* የእነርሱና የእኔ ዕጣ ፈንታ እንዲህ ከሆነ ታዲያ፣ "ለምን እፈራለሁ?" (ቍ5)::

49፥13 ***የእነርሱንም፤*** ኑሮ እንደ ተሳካለት ሰው ማለት ነው (ቍ6 ይመ)::

49፥14 ***እንደ በጎች፤*** ሞት እንደ እረኛ ሆኖ ወደ መቃብር ይመራቸዋል:: ***ሞትም ይበላቸዋል፤*** ሞት (ወይም መቃብር) በቃኝን የማያውቅ ጨካኝ አውሬ ሆኖ መመሰሉን በ69፥15፤ 141፥7፤ ምሳ1፥12፤ 27፥20፤ 30፥15-16፤ ኢሳ5፥14፤ ዮና2፥2 ላይ ይመ:: ይህ ምሳሌያዊ አገላለጽ የተወረሰው ከከናዓናውያን ሥነ-ተረት ሲሆን "ሞት" የተባለው አምላክ በሞት ተመስሎአል:: አንድ የከነዓናውያን ጽሑፍ "ሞትን አትቅረቡ፤ ያለበለዚያ እንደ በግ ይውጣችኋል" ይላል:: ***ይገዟቸዋል፤*** ዘሌ26፥17፤ ኢሳ14፥2 ይመ፤ በቍ5 ላይ ከተባለው ነገር ጋር ሲታይ ምናልባት "ድል ያደርጓቸዋል" የሚል ሐሳብ አለው:: ***በማለዳ፤*** ቍ15፡19 እና የ6፥5፤ 11፥7፤ 16፥9-11፤ 17፥15 ይመ:: ይሁን እንጂ የመዝ57 መግቢያን ይመ::

*49፥15፤* የቍ7-9 ማብ ይመ:: ***ከሲኦል እጅ ይቤዠኛል፤*** እነዚህ ቃሎች የሚያመለክቱት በሰዎች ሁሉ ላይ ከሚደርሰው ሞት ይታደገኛል (ለጊዜውም ቢሆን) የሚለውን ሐሳብ ቢሆንም (ይኸውም በኢዮ5፥20 ላይ እንደ ተመለከተው ነው፤ 116፥8 ይመ) ዐውደ ንባቡ እንደሚያሳየው ግን ጸሓፊው ጻድቅ ሰው በመሆኑ ስለ ወደ ፊት ዕጣ ፈንታው እየተናገረ ነው:: ምናልባት የጸሓፊው ሐሳብ በእግዚአብሔር ሰማያዊ ቤተ መቅደስ ውስጥ ከእርሱ ጋር እሆናለሁ የሚል ሳይሆን አይቀርም፤ ይህም በአይሁዳውያን ሥነ-መለኮት ውስጥ "በአብርሃም እቅፍ" ከሚለው ሐሳብ ጋር ተመሳሳይ ነው (ሉቃ16፥22፤ የ6፥5፤ የ11፥7፤ የ16፥9-1፤ የ17፥15 ማብ ይመ):: ***ነፍሴን፤*** ሕይወቴን ማለት ነው (የ6፥3 ማብ ይመ):: ***በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት አለኝ፤*** 73፥24፤ እንዲሁም ዘፍ 5፥24 እና ማብ ይመ::

*49፥16-19፤* የሀብታሞች ጊዜያዊ ሀብት ልባችሁን አይስረቀው ማለት ነው::

49፥16 ***የቤቱም፤*** ንብረቱ ሁሉ ማለት ነው (ዘፀ20፥17 ይመ)::

18በሕይወት ሳለ ራሱን እንደ ተባረከ
ቢቈጥርም፣
ሰዎች በበለጸግህ ጊዜ ቢያወድሱህም፣
19ብርሃን ከቶ ወደማያዩት፣
ወደ አባቶች ማኅበር ይቀላቀላል።
20ሰው በሀብቱ እንደ ተከበረ አይዘልቅም፤
ታይተው የሚጠፉ እንስሳትን
ይመስላል።

## መዝሙር 50
## በመንፈስና በእውነት ማምለክ

የአሳፍ መዝሙር

1ኀያሉ አምላክ፣ *እግዚአብሔር* ተናገረ፤
ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መግቢያ
ድረስ
ምድርን ጠራት።
2ፍጹም ውብ ከሆነችው ከጽዮን፣
እግዚአብሔር አበራ።
3አምላካችን ይመጣል፤ ዝምም አይልም፤
የሚባላ እሳት በፊቱ፣
የሚያስፈራ ዐውሎ ነፋስም በዙሪያው
አለ።
4በሕዝቡ ይፈርድ ዘንድ፣
በላይ ያለውን ሰማይንና ምድርን እንዲህ
ብሎ ይጠራል፤
5"በመሥዋዕት ከእኔ ጋር ኪዳን የገቡትን፣
ቅዱሳኔን ወደ እኔ ሰብስቧቸው።"
6ሰማያት ጽድቁን ያውጃሉ፤
እግዚአብሔር ራሱ ፈራጅ ነውና። ሴላ
7"ሕዝቤ ሆይ፤ ስማኝ፤ ልንገርህ፤
እስራኤል ሆይ፤ በአንተ ላይ ልመስክር፤
አምላክህ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።
8ስለ መሥዋዕትህ አልነቅፍሁህም፤
የሚቃጠል መሥዋዕትህማ ሁልጊዜ
በፊቴ ነው።
9እኔ ግን ኮርማህን ከበረት፣
ፍየሎችህንም ከጕረኖ የምፈልግ
አይደለሁም፤

49፥18 መዝ10፥6፤ ሉቃ12፥19
49፥19 ዘፍ15፥15፤ ኢዮ33፥30
49፥20 ቍ 12፤ምሳ 16፥16
50፥1 ኢሱ22፥22፤ መዝ113፥3
50፥2 ዘዳ33፥2፤ መዝ 2፥6፤48፥2፤ ሰቆ2፥15
50፥3 ቍ 21፤ዘሌ 10፥2፤ኢዮ37፥9፤መዝ 18፥8፤83፥15፤96፥13 ፤107፥25፤147፥18፤ ኢሳ29፥6፤30፥28፤ 42፥14፤64፥12፤65፥6 ፤ዮና1፥4፤ናሆ1፥3
50፥4 ዘዳ4፥26፤ 31፥28፤ኢሳ1፥2፤ዕብ 10፥30
50፥5 ዘፀ24፥7፤ዘዳ 7፥6፤2ዜና6፥11፤መዝ 18፥25
50፥6 ዘፍ16፥5፤ ኢዮ9፥15፤መዝ19፥1
50፥7 ዘፀ20፥2፤ መዝ48፥14፤ዕብ2፥4
50፥8 2ሳሙ22፥16 ፤መዝ40፥6
50፥9 ዘሌ1፥5፤16፥5 ፤ዘኍ32፥16

49፥19 *ብርሃን፤* የ27፥1፤ የኢሳ53፥11 ማብ ይመ።

*49፥20፤* የመጨረሻ ቃል ነው፤ የቍ12 ማብ ይመ።

*መዝሙር 50፤* ጌታ የኪዳኑ ሕዝብ እርሱን ለማምለክ በቤተ-መቅደስ ሲሰበሰብ በታሪካቸውና በሕይወታቸው ውስጥ ያከናወነውን ነገር ልብ እንዲሉ ጥሪ ያቀርባል (ይህ መዝሙር በመዝ46-49 ላይ ከሰፈረው ሐሳብ ጋር ትስስር አለው፤ የእነዚህን መዝሙሮች መግቢያ ይመ)። መዝሙሩ የተደረሰው በቤተ መቅደሱ ውስጥ ሥርዐተ ቅዳሴ በሚደረግበት ጊዜ እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር የገባችውን ኪዳን እንድታድስ ለማድረግ ነው። የሌዋውያኑ የመዘምራን ቡድን መሪ በጌታ ስም እስራ ኤልን ይናገራል (መዝ15፤ 24 ይመ፤ ሁለቱም ከዚህ ጋር ተመሳ ሳይ በሆነ የቅዳሴ ሥርዐት ላይ ሳያዳምጡ አይቀርም)። ይህ የቅዳሴ መዝሙር ከዳስ በዓል ጋር ዝምድና ሊኖረው ይችላል (ዘዳ31፥9-13፤ እንዲሁም የመዝ47ን መግቢያ ይመ)። ይህ መዝ ሙር ከንቱ መሥዋዕትን ወይም በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት የሌለውን መሥዋዕት የሚኰንን በመሆኑ ከአሞጽ፣ ከሚክያስና ከኢሳይያስ ትንቢቶች ጋር ተመሳሳይነት አለው፤ መዝሙሩ ከክርስቶስ ልደት በፊት በስምንተኛው ምእተ ዓመት መገባደጃ ወይም በሰባተኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ ላይ ሳይጻፍ አልቀረም። ሌሎች ሊቃውንት ግን ከኢዮስያስ የተሐድሶ እርም ጃና (2ነገ22፥1-23፡25) ከኤርምያስ የአገልግሎት ዘመን ጋር ያገናኙታል። በአወቃቀር ደረጃ ሲታይ መዝሙሩ ሦስት ክፍሎች አሉት፤ (1) የእስራኤል የኪዳን አምላክ "መጥቶ" ሕዝቡን የእርሱን ሥራ እንዲያስተውል ያውጃል (ቍ1-6)፤ (2) ቅን ልብ ላላቸው ጌታ የሰጠው ምክር (ቍ7-15)፤ (3) በመካከላቸው የሚገኙትን ክፉዎች በብርቱ መውቀሱ (ቍ16-23 ይመ)።

*50ርእስ፤* ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ልማድ መሠረት፣ "የአሳፍ መዝሙር" ይባላል፤ ወይም "ለአሳፍ" ማለት ሊሆን ይችላል (በመዝ39 ርእስ ላይ፣ "ለኤዶታም" የሚለውን ይመ)፤ ወይም በአሳፍ እግር ተተክተው ለሚያገለግሉ ለእርሱ ዝርያዎች ሊሆን ይችላል፤ ይህ መዝሙር ከሌሎች የአሳፍ መዝሙሮች (73-83) የሚለየው የመዝሙሩ ዐቢይ ሐሳብ ከመዝ46-49 ጋር ዝምድና ስላለው ነው። አሳፍ ከሦስቱ የዳዊት የመዘምራን ቡድን መሪዎች ውስጥ አንዱ ነበር (የመዝ39 የርእስ ማብ ይመ)።

*50፥1-6፤* በቤተ መቅደስ አምልኮ ሲደረግ ጌታ ወደ ሕዝቡ የሚመጣው ሕዝቡን ሊያስተካክልና ሊገሥጽ ነው (ቍ3)፤ የጽዮን አምላክ የሲና አምላክ መሆኑን እስራኤል ማወቅ አለባት (ዘፀ 19፥16-20 ይመ)።

50፥1 *ኀያሉ አምላክ እግዚአብሔር ፤* በዚህ ቅደም ተከ ተል መሠረት በሌላ ቦታ ተጽፎ የምናገኘው በኢሱ22፥22 ላይ ብቻ ነው (በዚያ ክፍል የተሰጠውን ማብ ይመ)። መዝ50 እግዚ አብሔር የሚጠራባቸውንና የሚታወቅባቸውን በርካታ ስሞችና ማዕረጎች የያዘ በመሆኑ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው መዝሙር ነው (በአጠቃላይ ሰባት ናቸው፤ በቍ1 ላይ ሦስቱ የተጠቀሱ ሲሆን የቀሩት አራቱ ደግሞ በቀሪው ቍጥሮች ላይ ተጠቅሰዋል፤ የቍ6፡14፡21-22 ማብ ይመ)። *ምድርን፤* "ሰማይና ምድርን" (ቍ4) እንዲሁም "ሰማያትም" (ቍ6) የሚለውን ይመ። ሙሴ በእግዚ አብሔርና በእስራኤል መካከል የተደረገውን ኪዳን በሞዓብ ምድር በሚያድስበት ጊዜ፣ ሰማይና ምድር ሦስተኛ ወገን ምስክር እንዲሆኑ እነርሱን ይጠራል (ዘዳ30፥9፤ 31፥28)። ጌታ እነዚህን ምስክሮች ጠርቶ አሁን ለሕዝቡ የሰጠው ቃል ከቀድ ሞው ኪዳን ጋር ፍጹም የተስማማ መሆኑን ያረጋግጣል (ኢሳ1፥2 ይመ)።

50፥2 *ፍጹም ውብ፤* ምክንያቱም እግዚአብሔር በመካከሏ ይኖራል (ከመዝ 27፥3-4፡11፤ 28፥12 ጋር ያነጻጽሩ)። *አበራ፤* ሥራውን ለመሥራት ሲመጣ ክብሩን ይገልጣል (80፥1፤ 94፥1፤ ዘዳ 32፥2 ይመ፤ ከሕዝ 28፥7፡17 ጋር ያነጻጽሩ)፤ የሚመጣ ውም ሕዝቡን ፊት ለፊት ሊጋፈጥ እንጂ በኢሳይያስ ም 1 ወይም በሚክያስ ም1 ላይ እንደ ተጠቀሰው ፍርድን ሊያመጣ አይ ደለም።

50፥3 *ይመጣል፤* በቤተ መቅደሱ ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ (የ28፥2 ማብ፤ እንዲሁም ኢሳ26፥21፤ ሚክ1፥3 ይመ) በኪሩቤል መካከል በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠበት ስፍራ ማለት ነው (80፥1፤ 99፥1፤ 1ሳሙ4፥4፤ 2ሳሙ6፥2፤ 2ነገ19፥15 ይመ)። *ዝምም አይልም፤* ከእንግዲህ ኀጢአታቸውን ዝም ብሎ አያልፍም (ቍ21 ይመ)። *እሳት... ዐውሎ ነፋስም፤* ዘፀ19፥16፡18 ይመ።

50፥4 *ይፈርድ ዘንድ፤* ሕዝቡ በኪዳኑ መሠረት መኖር ያለመኖራቸውን እንዲመሰክሩ ሰማይና ምድርን ይጠራል።

50፥5 *ኪዳን ያገቡትን፤* የ4፥3 ማብ ይመ። *በመሥዋዕት፤* ኪዳኑ ከሚጸናባቸው ነገሮች መካከል አንዱ መሥዋዕት ነው (ዘፀ24፥4-8 ይመ)፤ እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር የገባችውን ቃል ኪዳን እንደምትጠብቅ የምትገልጸውም መሥዋዕት በማቅረብ ነው።

50፥6 *ያውጃሉ፤* የቍ1 ማብ ይመ። *ጽድቁን፤* የ4፥1 ማብ ይመ። *ፈራጅ፤* በሕዝቡ ላይ ጌታ ነው (በዕብራይስጡ "ፈራጅ" የሚለውንና "ንጉሥ" የሚለውን ቃል ለመግለጽ የገቡት አንዳንድ ጊዜ ተመሳሳይ ትርጕም ይዘው ይገኛሉ፤ ለምሳሌ ኢሳ33፥22 ይመ)፤ "ፈራጅ" የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ማዕረግ የሚገ ልጽ ቃል ነው (የቍ1 ማብ ይመ)፤ ይህም በ94፥2፤ በዘፍ18፥25፤ በመሳ11፥27 ላይ እንደ ተመለከተው ነው።

*50፥7-15፤* እግዚአብሔር ሕዝቡን ያርማል፤ ያስተካክላል።

50፥7 *ሕዝቤ፤* "አምላካችን" (ቍ3) እንዲሁም "አም ላክህ" (እዚህ ላይ) የሚሉት ቃላት በቃል ኪዳን መተሳሰርን ያመለክታሉ። *አምላክህ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤* ዘፀ19፥3-6፤ ዘሌ 19፥2-4፡10፡25፡ 31፡34፡36፤ 20፥7፡24፤ 22፥33፤ 23፥22 ይመ።

*50፥8-13፤* እስራኤል በቂ መሥዋዕት ከማቅረብ ወደ ኋላ አላለችም (ቍ8)፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ያለእነርሱ መሥ ዋዕት የማይሆንለት ይመስል እርሱ ከእኛ የሚፈልገው ያዘዘ ንን መሥዋዕት እንድናቀርብለት ብቻ ነው ወደሚል ድም ዳሜ ደርሰው ነበር። ይህ አመለካከት በእስራኤል ተጎራባች ሕዝ ቦች መካከል እጅግ የተስፋፋ አመለካከት ነው፤ የ40፥6 ማብ ይመ።

[10]የዱር አራዊት ሁሉ፣
በሺ ተራራዎች ላይ ያለውም እንስሳ
የእኔ ነውና::
[11]በየተራራው ያለውን ወፍ ሁሉ
ዐውቃለሁ፤
በሜዳ የሚገኘው ተንቀሳቃሽ ፍጡር
ሁሉ የእኔ ነው::
[12]ብራብ ለአንተ አልነግርህም፤
ዓለምና በውስጧ ያለውም ሁሉ የእኔ
ነውና::
[13]ለመሆኑ፣ እኔ የኰርማ ሥጋ እበላለሁን?
የፍየልንስ ደም እጠጣለሁን?
[14]ለእግዚአብሔር የምስጋና መሥዋዕት
አቅርብ፤
ለልዑልም ስእለትህን ስጥ::
[15]በመከራ ቀን ጥራኝ፤
አድንሃለሁ፤ አንተም ታከብረኛለህ::"
[16]ክፉውን ግን እግዚአብሔር እንዲህ ይለዋል፤
"ሕጌን ለማነብነብ፣
ኪዳኔንም በአፍህ ለመናገር ምን መብት
አለህ?
[17]ተግሣጼን ትጠላለህና፤
ቃሌንም ወደ ኋላህ ትጥላለህ::
[18]ሌባውን ስታይ አብረኸው ነጐድህ፤
ዕድል ፈንታህንም ከአመንዝሮች ጋር
አደረግህ::
[19]አፍህን ለክፋት አዋልህ፤
እንደበትህም ሽንገላን ጐነጐነ::
[20]ተቀምጠህ ወንድምህን ትማሽው፤
የእናትህንም ልጅ ስም አጐደፍህ::
[21]ይህን አድርገህ ዝም አልሁ፤
እንዳንተም የሆንሁ መሰለህ::
አሁን ግን እገሥጽሃለሁ፣
ፊት ለፊትም እወቅስሃለሁ::
[22]"እናንተ እግዚአብሔርን የምትረሱ፤ ይህን
ልብ በሉ፤
አለበለዚያ ብትንትናችሁን አወጣለሁ፤
የሚያድናችሁም የለም::
[23]የምስጋናን መሥዋዕት የሚሠዋ
ያከብረኛል፤
መንገዱንም ቀና ለሚያደርግ፣
የእግዚአብሔርን ማዳን አሳየዋለሁ::"[ሀ]

50፥10 መዝ104፥20:24፤ኢሳ56፥9፤ሚክ5፥8
50፥11 መዝ8፥7፤80፥13፤ማቴ6፥26
50፥12 ዘፀ19፥5፤ዘዳ10፥14፤ኢዮ3፥11፤መዝ24፥1፤1ቆሮ10፥26
50፥14 ዘኍ30፥2፤ዕዝ1፥4፤መዝ7፥8፤27፥6፤66፥13፤76፥11
50፥15 መዝ3፥7፤4፥1፤22፥23፤69፥17፤81፥7፤86፥7፤107፥6፤142፥2፤ኢሳ55፥6፤58፥9፤ዘካ13፥9፤ያዕ5፥13
50፥16 መዝ25፥10፤ኢሳ29፥13
50፥17 1ነገ14፥9፤ምሳ1፥22
50፥18 ኢዮ22፥15፤ሮሜ1፥32፤1ጢሞ5፥22
50፥19 መዝ10፥7፤36፥3፤52፥2፤101፥7
50፥20 ማቴ10፥21
50፥21 መዝ6፥1፤18፥15፤76፥6፤85፥5፤104፥7፤ኢሳ42፥14፤50፥2፤57፥11፡16፤62፥1፤64፥12፤
50፥22 ዘዳ32፥39፤ኢዮ8፥13፤ኢሳ17፥10፤ሚክ5፥8
50፥23 መዝ9፥14፤85፥13፤91፥16፤98፥3

## መዝሙር 51

### የኀጢአት ኑዛዜ

ለመዘምራን አለቃ፤ ዳዊት ወደ ቤርሳቤህ ከገባ በኋላ፣ ነቢዩ ናታን ወደ እርሱ በመጣ ጊዜ፤ የዳዊት መዝሙር::

[1]እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደ ቸርነትህ መጠን፣
ምሕረት አድርግልኝ፤
እንደ ርኅራኄህም ብዛት፣
መተላለፌን ደምስስ::

፤ኢሳ52፥10 51 ርዕስ2ሳሙ 11፥4፤12፥1 51፥1 2ሳሙ12፥13፤24፥14፤2ዜና6፥21፤ነህ4፥5፤9፥27፤መዝ9፥13፤25፥7፡39፥8፤86፥15፤119፥88፤ኢሳ63፥7 ፤ሐሥ3፥19

[ሀ]23 ወይም *መንገዱን ለሚገዘብ*

50፥10 *በሺህ፤* እዚህ ላይ ቃሉ የገባው ብዙ ቍጥርን ለማመልከት ዘይቤአዊ በሆነ አገባብ ነው::

50፥12 *ዓለምና በውስጧ ያለውም፤* 24፥1 እና ማብ ይመ::

*50፥14-15፤* እስራኤል እግዚአብሔር ላሳያት ምሕረት የምስጋና መሥዋዕት በማቅረብና (ቍ14) መከራ በደረሰባት ጊዜ ወደ እርሱ በመጸለይ (ቍ15፤ 116፥17-19 ይመ) በእርሱ ላይ ብቻ የምትደገፍ መሆኗን እንድታሳይ ይፈልጋል:: እንዲህ የሚያደርጉ ሰዎች እግዚአብሔር ለጸሎታቸው መልስ እንደሚሰጥ በተስፋ መጠባበቅ ይችላሉ (ይህም በቍ23 ላይ በግልጽ ተመልክቶአል):: እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጠውን የምግባር ሕግ እንዲታዘዙ ይፈልጋል (ቍ16-21 እና የ40፥6 ማብ ይመ)::

50፥14 *የምስጋና መሥዋዕት፤* ዘሌ17፥12-13 ይመ:: *ለእግዚአብሔር ... ለልዑልም፤* ልዑል እግዚአብሔር ማለት ነው (57፥2 እና የ3፥7 ማብ ይመ):: *ስእለትህን፤* በመከራ ጊዜ ከጸሎት ጋር የሚቀርቡ ስእለቶች አብዛኛውን ጊዜ ከምስጋና መሥዋዕት ጋር የሚቀርቡ (66፥13-15 ይመ) ሲሆን እግዚአብሔር ለሕዝቡ ጸሎት መልስ ሲሰጥ ስእለት ከምስጋና ጋር ያቀርባል (የ7፥17 ማብ ይመ):: እንዲሁም ዕብ13፥15 ይመ:: *ለልዑልም፤* የቍ1 ማብ ይመ:: የዘፍ14፥19 ማብ ይመ::

50፥15 *በመከራ ጊዜ ወደ እኔ ጩኸ፤* በችግርና በመከራ ጊዜ እውነተኛ አማኞች ሁሉ ሳያቋርጡ እንዲጸልዩ ጌታ ጥሪ ያቀርባል:: እግዚአብሔር ጸሎታችንን መስማት ይፈልጋል፤ *ሊረዳንም ይሻል፤* እርሱ ሕዝቡን የሚታደግ አምላክ በመሆኑ ለእርሱ ምስጋና ማቅረብ ተገቢ ነው:: *ታከብረኛለህ፤* ስእለታቸው የደረሰ ሁሉ ለቃል ኪዳኑ መታዘዝና ጌታን ስለውለታው ማመስገን አለባቸው (ቍ23 ይመ)::

*50፥16-23፤* ጌታ ክፉዎችን ይገሥጻል::

50፥16 *ሕጌን ለማነብነብ፤* በኪዳኑ የቅዳሴ ሥርዐት ውስጥ ሕጉን መላልሶ መናገር አንዱ ክፍል ነው::

50፥17 *ተግሣጼን ትጠላለህ፤* ሥርዐቱን ይጠብቃሉ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ሕግ የሕይወታቸው መመሪያ አላደረጉም::

50፥19 *አፍህን ለክፋት አዋልህ፤* የ5፥9 ማብ ይመ::

*50፥21፤* ክፉዎች የእግዚአብሔርን ምሕረትና "ዝምታ" ወስደው የራሳቸውን ጠማማ ትምህርት እንዲያንጸባርቅ ያደርጋሉ (መክ8፥11፤ ኢሳ42፥14፤ 57፥11 ይመ):: *እንዳንተም ... የሆንሁ መሰለህ፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ፤ ዘፀ3፥14 እና ማብ ይመ (የቍ1 ማብ ይመ):: *ፊት ለፊትም፤* በአንተ ላይ ያለኝን ክስ ዐይንህ እያየ አቀርባለሁ ማለት ነው::

50፥22 *እግዚአብሔርን፤* ምንም እንኳ በመጽሐፈ ኢዮብ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጠቅሶ የሚገኝ ቃል ቢሆንም ይህ ቃል (ስም) ለእግዚአብሔር ተሰጥቶ የሚገኘው በጣም ጥቂት ጊዜ ነው (በዕብራይስጥ "ኤሎሃ" ነው):: የቍ1 ማብ ይመ::

*50፥23፤* የቍ14-15 ማብ ይመ::

*መዝሙር 51፤* ዳዊት ይቅርታንና መታደስን እንዲያገኝ ያቀረበው የልብ ጸሎት ነው:: የተሰበረ ልብ ያለው በደለኛ ያቀረበው ጸሎት እንደ መሆኑ መጠን ጌታ በም.50 በሕዝቡ ላይ ላቀረበው ወቀሳ ተገቢ ምላሽ ነው (ቍ16ን ከም 50፥8-15 ጋር ያነጻጽሩ):: ይህ መዝሙር ከመዝ25 ጋር በብዙ ረገድ ይገናኛል:: በክርስቲያኑ ኅብረተ ሰብ ዘንድ ይህ መዝሙር ከሰባቱ የንስሓ መዝሙሮች መካከል አንዱ ነው (የመዝ6 መግቢያን ይመ):: መዝሙሩ እኩል በሆኑ ሐሳቦች የተዋቀረ ነው:: የመዝሙሩ የመጀመሪያ ሁለት ቍጥሮች እንደ መግቢያ ሲያገለግሉ የመጨረሻ ሁለት ቍጥሮች ደግሞ እንደ መደምደሚያ ያገለግላሉ፤ በመግቢያውና በመደምደሚያው መካከል ላይ የሚገኙት አራት አንጓዎች በቅደም ተከተል አምስት ስንኝ፣ ሦስት ስንኝ፣ ሦስት ስንኝና አምስት ስንኝ ይዘዋል:: መዝሙሩ የተቀነበበው ዳዊት ለራሱ ባቀረበው ጸሎትና (ቍ1-2) ለጽዮን ባቀረበው ጸሎት ነው (ቍ18-19):: የንጉሡም ሆነ የከተማዋ ደኅንነትና ውድቀት እርስ በርሱ የተሳሰረ ነው (28፥8 እና የ3፥8 ማብ ይመ)::

51ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ4 ርእስ ማብ ይመ:: *በመጣ ጊዜ፤* በዳዊት ሕይወት የሆነውን ነገር በ2ሳሙ11፥1-12፥25 ላይ ይመ፤ የም3 ርእስ ማብ ይመ::

*51፥1-2፤* ምሕረት ይቅርታን ያስገኛል (ሉቃ18፥13 ይመ):: ተመሳሳይ ሐሳብ የወከሉ ቃላት እንዴት ተደራርበው እንደ ቀረቡ አስተውል፤ ምሕረት፣ የማይናወጥ ፍቅር፣ ታላቅ ርኅራኄ፣ ደምስስ፣ እጠብ፣ አንጻ፣ መተላለፍ፣ በደል፣ ኀጢአት (ስለ መጨረሻዎቹ ሦስት ተደራራቢ ሐሳቦች የ32፥5 ማብ ይመ)::

51፥1 *እንደ ቸርነትህ፤* የ6፥4 ማብ ይመ:: *ደምስስ፤* ቍ9 ይመ:: ይህ አባባል እግዚአብሔር የዳዊትን ኀጢአት የመዘገበበት ጥቅል መጽሐፍ እንዳለ ያሳያል (የ9፥5 ማብ ይመ):: "መተላለፌን ደምስስ" ሲል ይቅር በለኝ ማለት ነው (ኤር

2በደሌን ፈጽሞ እጠብልኝ፤
  ከኀጢአቴም አንጻኝ።

3እኔ መተላለፌን አውቃለሁና፤
  ኀጢአቴም ዘወትር በፊቴ ነው።
4በውሳኔህ ትክክል፣
  በምትሰጠው ፍርድም ንጹሕ ትሆን ዘንድ፣
አንተን፣ በእርግጥ አንተን ብቻ በደልሁ፤
  በፊትህም ክፉ ነገር አደረግሁ።
5ስወለድ ጀምሮ በደለኛ፣
  ገና እናቴም ስትፀንሰኝ ኀጢአተኛ ነኝ።
6እነሆ፤ እውነትን ከሰው ልብ ትሻለህ፤[+]
  ስለዚህ ጥልቅ ጥበብን በውስጤ
    አስተምረኝ።[‡]

7በሂሶጵ እርጬኝ፤ እኔም እነጻለሁ፤
  እጠበኝ፤ ከበረዶም ይልቅ ነጭ
    እሆናለሁ።
8ሐሤትንና ደስታን አሰማኝ፤
  ያደቀቅሃቸው ዐጥንቶቼም ደስ
    ይበላቸው።

51፥2 ሩት3፥3፤ ምሳ20፥30፤ኢሳ4፥4፤ ኤር2፥22፤13፥27፤ ሕዝ36፥25፤ዘካ13፥1፤ ማቴ23፥25-26፤ሐሥ 22፥16፤ዕብ9፥14፤ 1ዮሐ1፥9
51፥3 ኢሳ59፥12
51፥4 ዘፍ20፥6፤ 1ሳሙ15፥24፤ሉቃ15 ፥21፤ሮሜ3፥4
51፥5 ዘሌ5፥2፤ኢዮ 5፥7
51፥6 ኢዮ9፥4፤ 34፥32፤መዝ119፥66፤ 143፥10
51፥7 ዘፀ12፥22፤ ዘኍ19፥6፤ኢሳ1፥18፤ 4፥4፤43፥25፤44፥22፤ ሕዝ36፥25፤ዘካ13፥1 ፤ዕብ9፥19
51፥8 ዘፀ12፥46፤ ኢሳ35፥10፤ኤር33፥ 11፤ኢል1፥16
51፥9 2ሳሙ12፥13 ፤ኤር16፥17፤ዘካ4፥10

9ፊትህን ከኀጢአቴ መልስ፤
  በደሌንም ሁሉ ደምስስልኝ።

10ኣምላኬ ሆይ፤ ንጹሕ ልብ ፍጠርልኝ፤
  ቀና የሆነውንም መንፈስ በውስጤ
    አድስ።
11ከፊትህ አትጣለኝ፤
  ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ
    አትውሰድ።
12የማዳንህን ደስታ መልስልኝ፤
  በእሺታ መንፈስም ደግፈህ ያዘኝ።
13እኔም ለሕግ ተላላፊዎች መንገድህን
    አስተምራለሁ፤
  ኀጢአተኞችም ወደ አንተ ይመለሳሉ።

51፥10 መዝ24፥4፤ 78፥37፤ሕዝ18፥31፤ 36፥26፤ማቴ5፥8፤ሐሥ 15፥9 51፥11 ዘፍ4፥14፤ ዘፀ33፥15፤መዝ27፥9፤71፥9፤106፥33፤ 138፥8፤ኢሳ63፥10፤ኤፌ4፥30 51፥12 ኢዮ33፥26፤መዝ18፥35፤ 110፥3 51፥13 ዘፀ33፥13፤ኢዮ33፥27፤መዝ1፥1፤ሐሥ9፥21-22

+6 በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጒም በትክክል አይታወቅም።
‡6 *አስተምረህኛል ወይም ትፈልጋለህ*

18፥23፤ ኢሳ43፥25 *ይመ*)። የምድር ነገሥታት እነርሱ ባሉበት ዘመን የተፈጸመውን ነገር እንደሚመዘግቡ ሁሉ እግዚአብሔርም እርሱ በሚያስተዳድረው ዓለም ውስጥ የሚፈጸመውን ነገር እንደ ሚመዘግብ (56፥8፤ 87፥6፤ 130፥3፤ 139፥16፤ ነህ13፥14፤ ዳን 7፥10፤ እንዲሁም ዘፀ32፥32-33 *ይመ*።

*51፥2፤* ቊ7 *ይመ*። *እጠብ፤* የቈሸሸ ልብስ እንደሚ ታጠብ ዐይነት ማለት ነው። *አንጻኝ፤* በፊትህ ንጹሕ አድርገኝ ማለት ነው (ዘሌ11፥32 *ይመ*)።

*51፥3-6፤* የኀጢአት ኑዛዜ፤ ከምሳ28፥13፤ 1ዮሐ1፥9 *ጋር ያነጻ ጽሩ*።

51፥3 *ኀጢአቴም ዘወትር በፊቴ ነው፤* አንድ አማኝ በኀጢ አት ሲወድቅ፣ የኀጢአት ይቅርታ ቶሎ ላይሰማው ይችላል፤ እግ ዚአብሔር ይቅር ካለው በኋላ እንደ ገና ሊባርከው እንደሚችል የሚጠራጠርበት ጊዜ አለ። የድነትን በረከት በማግኘቱ ሲፍለቀ ለቅ የነበረው አማኝ በኀጢአት ማጥ ውስጥ ሲወድቅ፣ ይቅርታን እንዳገኘ ሳይሰማው ለብዙ ጊዜ በንስሐ ውስጥ ሊመላለስ ይችላል፤ ከዳዊት ሕይወት እንደምንማረው የእግዚአብሔርን በረከት ካገኙ በኋላ በኀጢአት ውስጥ መውደቅ እጅግ አስፈሪ ነው።

51፥4 *አንተን ብቻ፤* ዳዊት ከሁሉም በላይ የበደለው እግዚ አብሔርን እንደ ሆነ አመነ (2ሳሙ12፥13 *ይመ*፤ ከዘፍ20፥6፤ 39፥9፤ ሉቃ15፥18 *ጋር ያነጻጽሩ*)። ዳዊት በግልጽ የተጠቀሰውን የኪዳን ሕግ ተላልፎአል (ዘፀ20፥13-14፡17)። *በውሳኔህ ... በፍር ድም፤* ጌታ በነቢዩ በናታን አማካይነት እንዳደረገው ማለት ነው (2ሳሙ12፥7-12)። ይህ ሐሳብ በአዲስ ኪዳን ላይ እንዴት እንደ ተጠቀሰ ሮሜ3፥4 *ይመ*።

*51፥5፤* እንዲህ ያለ ባሕርይ በእርሱ ላይ ሊታይ የቻለው ከእርሱነቱ የተነሣና (ቊ6) ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ ነው (58፥3፤ ዘፍ8፥21፤ ከዮሐ9፥34፤ ከኤፌ2፥3 *ጋር ያነጻጽሩ*)። ከዚህ *ጋር* ተመሳሳይ የሆነ ሐሳብ በመጽሐፈ ኢዮብ ላይ የተገለጸ ሲሆን (14፥4፤ 15፥14፤ 25፥4-6) *መንሥኤው* ግን የተለየ ነው።

*51፥6፤* እዚህ ላይ ትልቅ ንጽጽር ይታያል፤ እግዚአብሔር ከሚፈልገውና ካስተማረው *ጋር* የሚቃረን ነገር አደረገ። ይሁን እንጂ በቊ7 እና 10 ላይ ካቀረበው ልመና እንደምንረዳው *መዝሙረኛው* ተስፋ የሚያደርገው በእነዚህ የእግዚአብሔር "*መው ደድና*" የእግዚአብሔር "*ትምህርት*" ላይ ነው። *እውነትን፤* በዚህ አገባቡ ቅን ማለት ነው። *ጥልቅ፤* 139፥13-16፤ ኢዮ 38፥36 *ይመ*። *ጥበብን፤* ራሱን ለኀጢአት አሳልፎ የሚሰጥ ሁሉ ሞኝ ነው፤ የእግዚአብሔርን ሕግ በልቡ የሚሰውር ግን ጥበበኛ ነው (37፥30-31 *ይመ*)። *በውስጤ፤* በውስጥ የሚገኝ እጅግ የምስጢ ራዊ ክፍል ነው።

*51፥7-9፤* ይቅርታን ለማግኘት እንደ ገና የቀረበ ጸሎት ነው።

51፥7 *እርጬኝ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም ከበደል አንጻኝ ማለት ነው። *በሂሶጵ፤* ሥነ*መንጻት ሥርዐት ያገለግላል፤ የዘፀ12፥22 ማብ *ይመ*። *እነጻለሁ፤* በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ሥርወ ቃል በቊ2 ከተመለከተው "አንጻኝ" ከሚለው *ጋር* አንድ ነው። *ከበረ ዶም ... ነጭ እሆናለሁ፤* የቈሸሸ ልብስ መታጠብ እንዳለበት ሁሉ እርሱም *መታጠብ ያስፈልገዋል* (የቊ2 ማብ *ይመ*)። እግዚ አብሔር ካነጻው ግን የሚነጻው የሰው ቋንቋ ሊገልጸው ከሚች ለው በላይ ነው (ኢሳ1፥18፤ ዳን7፥9፤ ራእ7፥14፤ 19፥14 *ይመ*)።

51፥8 *ሐሤትንና ... አሰማኝ፤* በደስታ ልከበብ ማለት ነው (32፥7 እና ማብ፤ እንዲሁም 35፥27 *ይመ*)፤ ወይም ደግሞ ኀጢ አቴ እንደ ተሰረየ የሚያስታውቀኝን ደስታ የሚሰጠኝን የትንቢት ቃል አሰማኝ ማለት ነው፤ ይህም ኀጢአቱ ይቅር ለመባሉ ዋስትና ነው (2ሳሙ12፥13 *ይመ*)። *ዐጥንቶቼም፤* የ6፥2 ማብ *ይመ*።

51፥9 *ፊትህን ... መልስ፤* "ዘወትር በፊቴ ከሆነው" ኀጢ አት ማለት ነው (ቊ3)። *ደምስስልኝ፤* የቊ1 ማብ *ይመ*።

*51፥10-12፤* ንጹሕ ሆኖ እንዲገኝ ያቀረበው ጸሎት ነው፤ ይኸውም ንጹሕ ልብ፣ ጽኑ የታማኝነት መንፈስና ቀና የሆነ የአገ ልጋይነት መንፈስ እንዲኖረው ማለት ነው። ይህ ሁሉ እውን ሊሆን የሚችለው ግን እግዚአብሔር ካልተወውና መንፈስ ቅዱ ስን ካልወሰደበት ነው። ልመናው እውን ከሆነለት የእግዚአብሔር የድነት ደስታ ግራ የተጋባችውን ነፍሱን ደስ ያሰኛታል።

51፥10 *ፍጠርልኝ፤* አዲስ ልብ ስጠኝ ማለት ነው፤ ይህን አዲስ ልብ አሁን ባለበት ሁኔታ ሊያገኝ አይችልም (ቊ5 *ይመ*)፤ ይህን ሊያደርግ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው (ዘፍ1፥1፤ ኢሳ 65፥17፤ ኤር31፥22 *ይመ*)። *ልብ፤* የ4፥7 ማብ *ይመ*።

*51፥11፤* ሁለቱ ጥያቄዎች በመሠረቱ አንድ ዐይነት ናቸው (139፥7፤ ሕዝ39፥29 *ይመ*)፤ ዳዊት ይህን ጸሎት ያቀረበው የሳኦልን ተተፍቶ መጣልን እያስታወሰ ነው (1ሳሙ16፥1፡14፤ 2ሳሙ7፥15 *ይመ*)። በዚህ ጸሎቱ እስራኤልን ለማስተዳደር ብቁ የሚያደርገውን መንፈስ እግዚአብሔር እንዳይወስድበት ልመና አቅርቦአል (1ሳሙ16፥13 *ይመ*፤ 2ሳሙ23፥1-2 *ጋር ያነጻጽሩ*)። *ቅዱስ መንፈስህንም፤* በብሉይ ኪዳን ይህ ሐረግ የሚገኘው 63፥10-11 ላይ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ዓለማትን የመፍጠር ሐሳቡን እውን ያደረገው (104፥30፤ ዘፍ1፥2፤ ኢዮ33፥4 *ይመ*)፣ የሰውን ዘር የመቤዠት ዓላማውን ያከናወነው (ኢሳ32፥15፤ 44፥3፤ 63፥11፡14፤ ሐጌ2፥5 *ይመ*)፣ ለመረጣቸው ተልእኮ አገልጋዮቹን ብቁ ያደረገው (ዘፀ31፥3፤ ዘኍ11፥29፤ መሳ3፥10፤ 1ሳሙ10፥6፤ 16፥13፤ ኢሳ 11፥2፤ 42፥1 *ይመ*)፣ ነቢያቱ ትንቢት እንዲናገሩ ያነቃቃውና (ዘኍ24፥2-3፤ 2ሳሙ23፥2፤ ነህ9፥30፤ ኢሳ59፥21፤ 61፥1፤ ሕዝ11፥5፤ ሚክ3፥8፤ ዘካ7፥12 *ይመ*) ለአገልግሎታቸው ምሪት የሰጠው በመንፈሱ ነው (1ነገ18፥12፤ 2ነገ2፥16፤ ኢሳ 48፥16፤ ሕዝ2፥2፤ 3፥14 *ይመ*)። በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር እንደ ፈቃዱ እንዲኖሩ፣ "አዲስ ልብና... አዲስ መንፈስ" ለሕ ዝቡ የሚሰጠው በመንፈሱ ነው (ሕዝ36፥26-27፤ እንዲሁም ኤር 24፥7፤ 32፥39፤ ሕዝ11፥19፤ 18፥31 *ይመ*)።

*51፥13-17፤* ውዳሴ ለማቅረብ የተገባ ስእለት ነው (የ7፥17 ማብ *ይመ*)።

*51፥13፤* እግዚአብሔር ኀጢአቱን ይቅር ስላለውና ከበደ ልም ስላነጻው እግዚአብሔርን *ያመሰግናል*፤ ለኀጢአተኞችም የእ ግዚአብሔርን ሕግ ያስተምራል (መዝ34 እና የ32፥8-10 ማብ

14የድነቴ አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤
ደም ከማፍሰስ አድነኝ፤
አንደበቴም ስለ ጽድቅህ በእልልታ
ይዘምራል።
15ጌታ ሆይ ከንፈሮቼን ክፈት፤
አፌም ምስጋናህን ያውጃል።
16መሥዋዕትን ብትወድ ኖሮ ባቀረብሁልህ
ነበር፤
የሚቃጠል መሥዋዕትም ደስ
አያሰኝህም።
17እግዚአብሔር የሚቀበለው መሥዋዕት
የተሰበረ መንፈስ ነው፤[ኀ]
እግዚአብሔር ሆይ፤
አንተ የተሰበረውንና የተዋረደውን
ልብ አትንቅም።

18በበጎ ፈቃድህ ጽዮንን አበልጽጋት፤
የኢየሩሳሌምንም ቅጥሮች ሥራ።
19የጽድቅ መሥዋዕት፣ የሚቃጠል
መሥዋዕትና፣
ሙሉ የሚቃጠል መሥዋዕት ያን
ጊዜ ደስ ያሰኝሃል፤
ኮርማዎች በመሠዊያህ ላይ
የሚሠዉትም ያን ጊዜ ነው።

## መዝሙር 52

### የክፉዎች ዕጣ ፈንታ

ለመዘምራን አለቃ፤ ኤዶማዊው ዶይቅ ወደ ሳኦል መጥቶ፣ "ዳዊት ወደ አቢሜሌክ ቤት መጥቶአል" ብሎ በነገረው ጊዜ፤ የዳዊት[ነ] ትምህርት

1ኀያል ሆይ፤ በክፋት ለምን ትኵራራለህ?
አንተ በእግዚአብሔር ዐይን የተናቅህ፣
እንዴትስ ዘወትር ትታበያለህ?
2አንተ ማታለልን ሥራዬ ብለህ የያዝህ፤
አንደበትህ እንደ ሰላ ምላጭ፣
ጥፋትን ያውጠነጥናል።
3ከበጎ ነገር ይልቅ ክፋትን፣
እውነትን ከመናገር ይልቅ ሐሰትን
ወደድህ። ሴላ
4አንተ አታላይ አንደበት ሆይ፤
ጐጂ ቃላትን ሁሉ ወደድህ!

5እግዚአብሔር ግን ለዘላለም ያንኰታኵትሃል፤
ይነጥቅሃል፤ ከድንኳንህም መንጥቆ
ያወጣሃል፤
ከሕያዋንም ምድር ይነቅልሃል። ሴላ
6ጻድቃን ይህን ዐይተው ይፈራሉ፤
እንዲህ እያሉም ይሥቁበታል፤
7"እግዚአብሔርን መጠጊያ ያላደረገ፣
ነገር ግን በሀብቱ ብዛት የተመካ፣
በክፋቱም የበረታ፣
ያ ሰው እነሆ!"

8እኔ ግን በእግዚአብሔር ቤት፣
እንደ ለመለመ የወይራ ዛፍ ነኝ፤
ከዘላለም እስከ ዘላለም፣
በእግዚአብሔር ምሕረት እታመናለሁ።
9ስላደረግኸው ነገር ለዘላለም
አመሰግንሃለሁ፤
ስምህ መልካም ነውና ስምህን ተስፋ
አደርጋለሁ፤
በቅዱሳንም መካከል አመሰግንሃለሁ።

[ኀ]17 ወይም አምላክ ሆይ፤ የእኔ መሥዋዕት የተሰበረ ተብሎ መተርጐም ይችላል።
[ነ]ርእሱ ምናልባት የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።

51፥14 2ሳሙ12፥9፤መዝ5፥8፤25፥5፤35፥28፤39፥8፤68፥20፤71፥15፤88፥1
51፥15 ዘፀ4፥15
51፥16 1ሳሙ15፥22
51፥17 ምሳ15፥8፤ሐጌ2፥14፤ማቴ11፥29
51፥18 መዝ69፥35፤102፥16፤147፥2፤ኢሳ14፥32፤44፥26፤51፥3፤ዘካ1፥16-17
51፥19 ዘዳ33፥19፤መዝ66፥13፤15፤96፥8፤ኤር17፥26
52 ርዕስ 1ሳሙ21፥7፤22፥9
52፥1 መዝ10፥3፤44፥8፤94፥4
52፥2 ዘኍ6፥5፤መዝ5፥9፤50፥19
52፥3 ዘፀ10፥10፤1ሳሙ12፥25፤መዝ58፥3፤ኤር9፥5፤አሞ5፥14-15፤ዮሐ3፥20፤ራእ21፥8
52፥4 መዝ5፥9፤10፥7፤109፥2፤120፥2፡3፤ምሳ10፥31፤12፥19
52፥5 ዘዳ28፥63፤29፥28፤ኢዮ28፥13፤40፥12፤ኢሳ22፥19፤ሕዝ17፥24
52፥6 ኢዮ22፥19
52፥7 2ሳሙ22፥3፤መዝ49፥6፤ምሳ11፥28፤ማር10፥23
52፥8 መዝ1፥3፤6፥4፤13፥5፤ራእ11፥4
52፥9 ዘዳ7፥6፤ኢዮ7፥6፤መዝ16፥3፤25፥3፤30፥12፤54፥6

ይመ)። መንገድህን፤ 25፥4 እና ማብ ይመ።

51፥14፤ እግዚአብሔር ይቅር ሲል ምስጋና መቅረቡ የማይቀር ነው። ጽድቅህን፤ የ4፥1 ማብ ይመ።

51፥15 ከንፈሮቼን ክፈት፤ የምሻውን ይቅርታና ቅድስናን በመስጠት ማለት ነው።

51፥16፤ የ40፥6 ማብ ይመ።

51፥17 የተሰበረ መንፈስ ... የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ፤ እግዚአብሔር ከመሥዋዕት ይልቅ እጅግ የሚያስደስተው ችግር በመጣ ጊዜ ወደ እርሱ የሚመለከተውንና ኀጢአት በሠራ ጊዜ በንስሐ መንፈስ የእርሱን ምሕረት የሚጠይቀውን ትሑት ልብ ነው (50፥7-15 እና ማብ፤ እንዲሁም 34፥17-18 ይመ)።

51፥18-19፤ ስለ ጽዮን የቀረበ ጸሎት ነው (የ3፥8 ማብ ይመ)

51፥19 የጽድቅ መሥዋዕት፤ እንደዚህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛል፤ እዚህ ላይ ለእግዚአብሔር የሚቀርቡ መሥዋዕቶች እግዚአብሔር ያደረገውን ምሕረት ከሚያወድሱ ምስጋናዎች ጋር ይቀርባሉ (50፥14-15 እና ማብ ይመ)።

መዝ52 እብሪተኛና ክፉ ጠላት ባስጨነቀው ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ያለ ፍርሀት በሙሉ ልብ ይታመናል። ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት ቆሞአል፤ ተመሽጎ ካለበት ከፍተኛ ስፍራ ላይ ሆኖ በሚያስጨንቁት ጠላቶቹ ላይ የውግዘት ቃሉን ያሰማል (ይህ የውግዘት ቃል በኢሳ22፥15-19 ላይ ከተመለከተው ከነቢዩ የውግዘት ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው)፤ ይህ መዝሙር ከጥቡብ መዝሙራት ጋር የማይቈጠር ቢሆንም ከመዝ49 ጋር በብዙ ረገድ ተመሳሳይ ነው። የዳዊትን ጠላቶች ማንነት በዝርዝር የሚያሳየው ይህ መዝሙር ከመዝ51 መንፈስ ጋር ተነጻጻሪ ነው። ዳዊት በጐልያድ ላይ ያሰማውን ዛቻ በ1ሳሙ17፥45-47 ይመ።

52ርእስ ለመዘምራን አለቃ፤ የመዝ 4 የርእስ ማብ ይመ። የዳዊት ትምህርት፤ የመዝ32 የርእስ ማብ ይመ። በ ... ጊዜ፤ የመዝ3 የርእስ ማብ ይመ። በዚህ ክፍል ስለ ተወሳው ታሪክ 1ሳሙ22፥9-10 ይመ።

52፥1-4፤ ከጠላቶቹ የደረሰበትን ክስ የሚገልጽ ክፍል ነው።

52፥1 ለምን? በምን መብት? ማለት ነው፤ 50፥16፤ ኢሳ3፥15 ይመ። ትኵራራለህ? በንግግርና በተግባር (75፥4-5 ይመ)። ኀያል ሆይ፤ በራሱ ግምት ማለት ነው (ኢሳ22፥17 ይመ)።

52፥2 አንደበትህ፤ ቍ4፤ እንዲሁም የ5፥9 ማብ ይመ።

52፥3፤ መላ አስተሳሰብህ ረክሶአል ማለት ነው። ወደድህ፤ መረጥህ ማለት ነው።

52፥4 አንደበት፤ የቍ2 ማብ ይመ።

52፥5-7፤ የጠላቶቹ ዕጣ ፈንታ ምን እንደ ሆነ ተገልጾአል (በቀጥታ ባይሆንም ጸሎት ነው)፤ እግዚአብሔር በሰይፍ ይመታሃል፤ ጻድቃንም ያላግጡብሃል።

52፥5፤ በሦስት የተገመደውን ምስል ከሳች አነጋገር ልብ በል፤ "ያንኰታኵትሃል"፣ "ያወጣሃል"፣ "ይነጥቅሃል"። እብሪተኞቹ ጠላቶች በመዝ49 ላይ እንደ ተመለከተው መጨረሻቸው እንደ ባለጠጋዎች ዐይነት ይሆናል። ከድንኳንህም፤ ኢዮ18፥14 ይመ። ይነቅልሃል፤ ከቍ8 ጋር ያነጻጽሩ።

52፥6 ጻድቃን፤ የ1፥5 ማብ ይመ። ይፈራሉ፤ ከውድቀት ይማራሉ (40፥3 እና የ34፥8-14 ማብ ይመ)።

52፥7፤ መዝ49 ይመ።

52፥8-9፤ የዳዊት ዋስትና ወይም አለኝታ እግዚአብሔር ነው።

52፥8 እንደ ... የወይራ ዛፍ፤ በመቶ ለሚቈጠሩ ዓመታት እንደሚኖረው ዐይነት ነው። እንደሚለመልም፤ 1፥3 ይመ፤ ከቶ አይነቀልም (ቍ5 ይመ)። በእግዚአብሔር ቤት፤ የወይራ ዛፍ በቤተ መቅደስ ቅጥር ግቢ ውስጥ አይተከልም፤ ዳዊት ግን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ መሸሸጊያው አደረገ (15፥1፤ 23፥6፤ 27፥4፤61፥4 እና ማብ ይመ)፤ ስለዚህ ከክፉ ተሰውሮአል (27፥5 እና ማብ ይመ)። ምሕረት፤ የ6፥4 ማብ ይመ።

52፥9፤ ውዳሴ ለማቅረብ ስእለት ይገባል (የ7፥17 ማብ ይመ)። ስምህ፤ የ5፥11 ማብ ይመ። በቅዱሳንም፤ የ4፥3 ማብ ይመ)።

## መዝሙር 53

### አምላክ የለሾች

53፥1-6 ተጓ ምብ-መዝ14፥1-7

ለመዘምራን አለቃ፤ በማኸላት፤ የዳዊት ትምህርት።[ᵞ]

[1]ቂል በልቡ፣
"እግዚአብሔር የለም" ይላል።
ብልሹዎች ናቸው፤ ተግባራቸውም ጸያፍ ነው፤
በጎ ነገርን የሚያደርግ አንድ እንኳ የለም።

[2]በማስተዋል የሚመላለስ፣
እግዚአብሔርን የሚፈልግ እንዳለ ለማየት፣
እግዚአብሔር ከሰማይ፣
ወደ ሰው ልጆች ተመለከተ።

[3]ሁሉም ወደ ሌላ ዘወር አሉ፤
በአንድነትም ተበላሹ፤
አንድ እንኳ፣
በጎ የሚያደርግ የለም።

[4]ሰው እንጀራ እንደሚበላ ሕዝቤን የሚበሉት፣
እግዚአብሔርንም ጠርተው የማያውቁት፣
እነዚያ ክፉ አድራጊዎች ከቶ አይማሩ ምን?

[5]የሚያስፈራ ነገር በሌለበት፣
በዚያ፣ በፍርሀት ተዋጡ፤
እግዚአብሔር የዘመቱብህን ሰዎች ዐጥንት በተነ፤
እርሱ እግዚአብሔር ስለ ናቃቸው፣ አንተ አሳፈርሃቸው።

[6]ምነው ለእስራኤል የሚሆን መዳን ከጽዮን በወጣ!
እግዚአብሔር የሕዝቡን ምርኮ በሚመልስበት ጊዜ፣
ያዕቆብ ሐሤት ያድርግ፤ እስራኤል ደስ ይበለው።

53፥1 መዝ10፥4፤ 74፥22፤107፥17፤ምሳ 10፥23
53፥2 2ዜና15፥2፤ መዝ33፥13፤82፥5፤ ኤር4፥22፤8፥8
53፥3 ሮሜ3፥10-12
53፥5 ዘሌ26፥17 ፤2ነገ7፥20፤23፥14፤ ኢዮ8፥22፤መዝ141፥7 ፤ኤር6፥30፤8፥1፤14፥ 19፤ሰቆ5፥22፤ሕዝ6፥5

## መዝሙር 54

### ለፍትሕ አምላክ የቀረበ አቤቱታ

ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች፤ ዚፋውያን ወደ ሳኦል መጥተው፣ "ዳዊት በእኛ ዘንድ ተደብቆአል" ባሉት ጊዜ፤ የዳዊት ትምህርት።[ᴬ]

[1]እግዚአብሔር ሆይ፤ በስምህ አድነኝ፤
በኀይልህም ፍረድልኝ።
[2]እግዚአብሔር ሆይ፤ ጸሎቴን ስማልኝ፤
የአፌንም ቃል አድምጥ።

[3]ባዕዳን ተነሥተውብኛልና፤
ግፈኞች ነፍሴን ሽተዋታል፤
እግዚአብሔርንም ከምንም አልቈጠሩም። ሴላ

[4]እነሆ፤ እግዚአብሔር ረዳቴ ነው፤
ጌታም ደግፎ ይይዘኛል።

[5]የገዛ ክፋታቸው በሚያደቡብኝ ላይ ይመለስባቸው፤
በቃልህ ታማኝ ነህና አጥፋቸው።

[6]በበጎ ፈቃድ መሥዋዕት እሠዋልሃለሁ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ መልካም ነውና፣
ለስምህ ምስጋና አቀርባለሁ፤
[7]ከመከራ ሁሉ ታድጎኛልና፤
ዐይኔም የጠላቶቼን ውድቀት ለማየት በቅቶአል።

54፥ ርዕስ1ሳሙ 23፥19፤26፥1
54፥1 1ሳሙ24፥15፤ 2ዜና20፥6፤መዝ20፥1
54፥2 መዝ4፥1፤5፥1 ፤55፥1
54፥3 1ሳሙ20፥1፤ መዝ18፥48፤36፥1፤86 ፥14፤140፥1፤4፥11
54፥4 1ዜና5፥20፤ መዝ18፥35፤20፥2
54፥5 ዘዳ32፥35፤ መዝ89፥49፤94፥23፤ ምሳ24፥12፤ኢሳ42፥3
54፥6 ዘሌ7፥12፡16፤ ዕዝ1፥4፤መዝ27፥6፤ 44፥8፤52፥9፤69፥30፤ 138፥2፤142፥7፤ 145፥1
54፥7 መዝ34፥6፤ 59፥10፤92፥11፤112፥ 8፤118፥7

[ᵞ]ርእሱ ምናልባት የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።
[ᴬ]ርእሱ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።

---

*መዝሙር53፤* የክፉ ሰዎችን ሞኝነት የሚገልጽ ሲሆን፣ የመዝ 14 ግልባጭ ነው ማለት ይቻላል፤ የዚህን መዝሙር መግቢያ ይመ (በሁለቱ መዝሙሮች መካከል ያለው ዐቢይ ልዩነት፣ እዚህ ላይ "ያህዌ" በሚለው ቃል ፈንታ "ኤሎሂም" የሚለው ቃል ገብቶአል፤ የቊ5 ማብ ይመ)። የመጀመሪያው መዝሙር (መዝ14) ምናልባት በ2ዜና20 ላይ የተጠቀሰውን ታሪክ መሠረት በማድረግ የተጻፈ ሊሆን ይችላል። መዝሙሩ እዚህ ላይ የሚያገለግለው በመዝ52 ላይ የተጠቀሱትን እብሪተኛ ሞኞች የሚያወግዝ ማብራሪያ ሆኖ ነው።

53ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ4 የርእስ ማብ ይመ። *ማኸላት፤* ምናልባት የቅኝት ስም ሊሆን ይችላል (የመዝ9ን የር እስ ማብ ይመ)። *ትምህርት፤* የመዝ32 የርእስ ማብ ይመ።

*53፥1-4፤* የ14፥1-4 ማብ ይመ።

*53፥5፤ ምንም* እንኳ ከ14፥5-6 ጋር በብዙ ረገድ ቢለያይም መሠረታዊ ሐሳቡ ግን አንድ ዐይነት ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚያስጨንቁትን አምላክ የለሾች ይበታትናቸዋል። *ምንም የሚያስፈራ ነገር በሌለበት፤* የሚያስፈራቸው ነገር ሳይኖር የፍርሃት ሰለባ ሆኑ። የእግዚአብሔር ርግማን የወረደው በእስራኤል ላይ ሳይሆን በእነርሱ ላይ ነው (ዘሌ26፥36-37፤ እንዲሁም መሳ7፥21፤ 2ነገ3፥22-23፤ 7፥6-7፤ ምሳ28፥1 ይመ)። *ዐጥንት በተነ፤* ድል በተደረገበት ሜዳ ላይ ሬሳቸው ሳይቀበር በየስፍራው እንደ ተበተነ ቀረ (ኢሳ14፥18-20፤ ኤር 8፥2 እና ማብ ይመ)። *እግዚአብሔር ስለ ናቃቸው፤* እርሱን እንደናቁት እር ሱም ናቃቸው።

*53፥6፤* የ14፥7 ማብ ይመ።

*መዝ54* ዳዊት እንዲሞት ከሚመኙ ጠላቶቹ እግዚአብሔር እንደ ታደገው ያቀረበው ጸሎት ነው። እንደ መዝ3፥4፤13 ሁሉ ይህም ጸሎት አጭር ነው፤ ይሁን እንጂ በይዘቱም ሆነ በዐይነቱ በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ከሚገኙት ጸሎቶች ጋር አንድ ዐይነት ነው። መዝሙሩ ሙሉ በሙሉ እኩቱል ነው፤ ጸሎቱ የተቀነበበው ዳዊት ነጻ እንዲወጣ ባቀረበው ጩኸትና (ቊ1) በጠላቶቹ ላይ ድል ሲያደርግ በዐይኑ እንደሚያይ በተነገረው ቃል ነው (ቊ7)። በጌታ እንደሚተማመን (ቊ4) የተነገረው ቃል የሚገኘው በጸሎቱ ማእከላዊ ክፍል ላይ ነው (42፥8 እና የ6፥6 ማብ ይመ)። የመግቢያው አንጓ እንደ መደምደሚያው ሁሉ ሁለት ስንኞች አሉት፤ ቊ3 እና 5 ግን ከተቀረው ጸሎት ለየት ያለ ሐሳብ ይዘዋል።

54ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ 4 የርእስ ማብ ይመ። *በበገናዎች፤* የመዝ4 የርእስ ማብ ይመ። *ትምህርት፤* የመዝ 32 የርእስ ማብ ይመ። *ጊዜ፤* ስለ የትኛው ጊዜ እንደ ሆነ በ1ሳሙ 23፥19 ላይ ይመ፤ እንዲሁም የመዝ3 የርእስ ማብ ይመ።

*54፥1-2፤* እግዚአብሔር ጕዳዩን እንዲያይለት ያቀረበው ጸሎት ነው (መዝ17 ይመ)።

54፥1 *በስምህ፤* ቊ6፤ እንዲሁም የ5፥11 ማብ ይመ።

*54፥3፤* በጠላቶቹ ላይ ያቀረበው ክስ ነው። *ስለ እግዚአብሔርንም ከምንም አልቈጠሩም፤* በመዝ 53 ላይ እንደ ተጠቀሱት ዐይነት ማለት ነው።

*54፥4፤ የሚታመንበት* እንዳለው የገለጸበት ክፍል ሲሆን፣ የመዝሙሩ ማእከላዊ ክፍል ነው (42፥8 እና ማብ ይመ)።

*54፥5፤* የእጃቸውን እንዲሰጣቸው ያቀረበው ልመና ነው።

*54፥6፤* ውዳሴ እንደሚያቀርብ የገባው ቃል ነው (የ7፥17 ማብ ይመ)። *ለስምህ፤* ቊ1 እንዲሁም የ5፥11 ማብ ይመ።

*54፥7፤* ጸሎት እንደሚሰማ እርግጠኛ መሆኑን የሚገልጽ ነው (የ3፥8 ማብ ይመ)።

*መዝ55፤* ቀድሞ ወዳጁ በነበረ ሰው የሚመራ ሤራ በኢየሩሳሌም ውስጥ በተቀሰቀሰ ጊዜ፣ ያቀረበው ጸሎት ነው። እዚህ ላይ የተገለጸው ታሪክ አቤሴሎም በንጉሡ ላይ ባመፀ ጊዜ ከነበረው ሤራ ጋር ተመሳሳይ ነው (2ሳሙ15-17 ይመ)። ከተማዋ በብጥብጥ ውስጥ ናት፤ አደጋ በየትኛውም ስፍራ አለ፤ ሙሉ እምነት የሚጣልበት ሰው ማግኘት አስቸጋሪ ነው፤ አሉባልታ፣ ሐሰተኛ ወሬና ስም ማጥፋት በየስፍራው ናኝቶአል።

## መዝሙር 55

### በስደት ጊዜ የቀረበ ጸሎት

ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች፤ የዳዊት ትምህርት[ሀ]

[1]እግዚአብሔር ሆይ፤ ጸሎቴን ስማ፤
ልመናዬን ቸል አትበል፤
[2]ወደ እኔ ተመልከት፤ መልስልኝም።
በውስጤ ታውኬአለሁ፤
ተናውጬአለሁም፤
[3]በጠላት ድምፅ ተሸበርሁ፤
በክፉዎች ድንፋታ ደነገጥሁ፤
መከራ አምጥተውብኛልና፤
በቍጣም ተነሣሥተው ጠላት
ሆነውብኛል።

[4]ልቤ በውስጤ ተጨነቀብኝ፤
የሞት ድንጋጤም በላዬ መጣ።
[5]ፍርሀትና እንቅጥቃጤ መጣብኝ፤
ሽብርም ዋጠኝ።
[6]እኔም እንዲህ አልሁ፤ “ምነው የርግብ
ክንፍ በኖረኝ!
በርሬ በሄድሁና ባረፍሁ ነበር፤
[7]እነሆ፤ኰብልዬ በራቅሁ፣
በምድረ በዳም በሰነበትሁ ነበር፤ ሴላ

[8]ከዐውሎ ነፋስና ከውሽንፍር ሸሽቼ፣
ወደ መጠለያዬ ፈጥኜ በደረስሁ
ነበር።”

[9]ጌታ ሆይ፤ ግፍንና ሁከትን በከተማዪቱ
ውስጥ አይቼአለሁና፣
ግራ አጋባቸው፤ ቋንቋቸውንም
ደበላልቅ።
[10]ቀንና ሌሊት ቅጥሯ ላይ ወጥተው
ይዞሯታል፤
ተንኰልና መከራ በውስጧ አለ።

[11]ጥፋት በመካከሏ ይገኛል፤
ግፍና አታላይነትም ከጎዳናዋ
አይጠፉም።

[12]የሚዘልፈኝ ጠላት አይደለምና፤
ቢሆንማ ኖሮ በታገሥሁት ነበር፤
የሚጠላኝ፣ ራሱንም ቀና ቀና ያደረገብኝ
ባላንጣ አይደለም፤
ቢሆንማ ከእርሱ በተሸሸግሁ ነበር።

[13]ነገር ግን አድራጊው አንተ ነህ፤
እኩያዬ፣ ባልንጀራዬና ወዳጄ፤
[14]በእግዚአብሔርም ቤት አብረን በሕዝብ
መካከል ተመላለስን፤
ደስ የሚል ፍቅር በአንድነት ነበረን።
[15]ሞት ሳይታሰብ ድንገት ይምጣባቸው፤
በሕይወት ሳሉ ወደ ሲኦል[ለ] ይውረዱ፤
ክፋት በመካከላቸው አድራለችና።

[16]እኔ ግን ወደ እግዚአብሔር እጣራለሁ፤
እግዚአብሔርም ያድነኛል።
[17]በማታ፣ በጥዋትና በቀትር፣
እጮኻለሁ፤ እቃትታለሁም፤
እርሱም ድምፄን ይሰማል።
[18]በተቃውሞ የተነሡብኝ ብዙዎች
ናቸውና፣
ከተቃጣብኝ ጦርነት፣
ነፍሴን በሰላም ይቤዣታል።
[19]አካሄዳቸውን አልቀየሩምና፣
እግዚአብሔርንም አልፈሩትምና፣
ከጥንት ጀምሮ በዙፋኑ ላይ ያለ
እግዚአብሔር፣ ሴላ
ሰምቶ ያዋርዳቸዋል።

[20]ባልንጀራዬ የምለው ሰው እጁን
በወዳጆቹ ላይ ሰነዘረ፤
ቃል ኪዳኑንም አፈረሰ።

55፥1 መዝ27፥9፤ ሰቆ3፥56
55፥2 1ሳሙ1፥15-16፤መዝ4፥1፤77፥3፤86፥6-7፤142፥2
55፥3 2ሳሙ16፥6-8፤መዝ17፥9፤44፥16፤71፥11፤143፥3
55፥4 ኢዮ18፥11፤ መዝ6፥3
55፥5 ዘዳ28፥67፤ ኢዮ4፥14፤ኢሳ21፥4፤ ኤር46፥5፤49፥5፤ሕዝ7፥18፤2ቆሮ7፥15
55፥7 1ሳሙ23፥14
55፥8 መዝ31፥20፤ 77፥18፤ኢሳ4፥6፤25፥4፤28፥2፤29፥6፤32፥2
55፥9 ዘፍ4፥17፤11፥9፤መዝ11፥5፤ኢሳ59፥6፤ኤር6፥7፤ሕዝ7፥11፤ዕን1፥3፤ሐሥ2፥4
55፥10 1ጴጥ5፥8
55፥11 መዝ5፥9፤ 10፥7
55፥13 2ሳሙ15፥12
55፥14 መዝ42፥4፤ ሐሥ1፥16-17
55፥15 መዝ49፥14፤ 64፥7፤ምሳ6፥15፤ኢሳ29፥5፤47፥9:11፤ 1ተሰ5፥3
55፥17 መዝ5፥3፤ 88፥13፤92፥2፤141፥2፤ሐሥ3፥1፤10፥3: 9:30
55፥19 ዘፀ15፥18፤ ዘዳ33፥27፤መዝ29፥10፤36፥1፤64፥4፤78፥59
55፥20 መዝ7፥4፤ 41፥9

[ሀ]ርእሱ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።
[ለ]15 ዕብራይስጡ ሲኦል ይላል፤ አንዳንድ የእንግሊዝኛ ትጆች ግን መቃብር ይላሉ።

እንዲህ ባለው ጊዜ ዳዊት ቀስ ብሎ ገሸሽ ለማለት ፈለገ (ቍ6-8)፤ ይህ የማይሆንለት መሆኑን ሲረዳ ግን ታማኝ መሆኑን ወደ ሚያውቀው ጌታ ጕዳዩን አቀረበ። ባወቃቀሩ ይህ መዝሙር ርዳታን ለማግኘት በቀረበ ልመናና (ቍ1) “እኔ ግን በአንተ እታመናለሁ” (ቍ23) በሚለው የእምነት ቃል የተቀነበበ ነው።

55ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ 4 የርእስ ማብ ይመ። *በበገና፤* የመዝ4 የርእስ ማብ ይመ። *ትምህርት፤* የመዝ32 የርእስ ማብ ይመ።

*55፥1-3፤* እግዚአብሔር ጸሎቱን እንደሚሰማ በመግቢያው ላይ ያቀረበው ምልጃ ነው።

*55፥4-8፤* የልቡ ጭንቀት ነው።

*55፥4-5፤* አደጋ በየትኛውም ስፍራ አለ (31፥13 ይመ)፤ አደጋው ታላቅ ከመሆኑ የተነሣ፣ ሞት ራሱ የሚያንዣብብ ይመስላል (18፥4-5፤ 116፥3 ይመ)።

55፥4 *ልቤ፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *የሞት ድንጋጤም፤* 1ሳሙ5፥11፤ 15፥32፤ 28፥5፤ ኢዮ18፥14 ይመ።

*55፥6-8፤* አደገኛና አጥፊ ከሆኑ ሰዎች ለመሸሽ ሲል ቀስ ብሎ ገሸሽ ለማለት ፈለገ (እንዲሁም ኤር9፥2-6 ይመ)።

*55፥9-11፤* እግዚአብሔር የጠላቶቹን ሤራ ከንቱ እንዲያደርግለት ያቀረበው ጸሎት ነው።

55፥9 *ቋንቋቸውንም ደበላልቅ፤* ንግግራቸውንም ዘበራርቀው፤ በባቢሎን እንደ ሆነው የሤረኞችን ሐሳብ ደበላልቀው ማለት ነው (ዘፍ11፥5-9፤ 2ሳሙ17፥1-14 ይመ)። *በከተማዪቱ፤* ቍ11 ይመ፤ “በከተማዪቱ” የተባለችው ኢየሩሳሌም ናት።

55፥10 *ተንኰልና መከራ፤* የከተማ ጠባቂዎች ከተማውን ከበው እንደሚውሉ ማለት ነው (127፥1፤ 130፥6፤ ማሕ5፥7 ይመ)።

55፥11 *ግፍና አታላይነትም፤* የከተማ ጠባቂዎች የከተማውን መንገድ እየተዘዋወሩ እንደሚጠብቁ የእነርሱም ግፍና ማጭበርበር ከመንገዱ አልለይ አለ ማለት ነው (ማሕ3፥3 ይመ)።

*55፥12-14፤* የጠላትን ስድብና ሤራ መቋቋም ይቻል ይሆናል፤ የልብ ወዳጅ ከሆነው ሰው እንዲህ ያለ ነገር ሲመጣ ግን እንዴት ይቻል ይሆን?

55፥14 *በእግዚአብሔር ቤት፤* ወዳጅነታቸው የተመሠረተውና የተቀደሰው ለጌታ ባላቸው ታማኝነት ላይ ሲሆን ይህም በጌታ ፊትና በቤተ መቅደሱ ውስጥ በሚያመልኩት ሰዎች ፊት የታተመ ነው።

*55፥15፤* ጠላቶቹ የእጃቸውን እንዲያገኙ ያቀረበው ጸሎት ነው (የ5፥10 ማብ ይመ)። *ሞት ድንገት ይምጣባቸው፤* ሤረኞች የእርሱን ሞት ይመኙ ነበር። *በሕይወት ሳሉ ወደ መቃብር፤* ያለ ዕድሜአቸው ወደ መቃብር ይውረዱ ማለት ነው (ቍ23፤ ዘኍ16፥29-33፤ምሳ1፥12፤ኢሳ5፥14 ይመ)።

*55፥16-19፤* ጸሎቱ እንደሚሰማ እርግጠኛ መሆኑን የገለጸበት ክፍል ነው (የ3፥8 ማብ ይመ)።

55፥17 *በማታ፣ በጥዋትና በቀትር በጭንቅ እጮኻለሁ፤* ከዳን6፥10 ጋር ያነጻጽሩ።

55፥18 *ይቤዣታል፤* “ይታደገኛል” ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው።

*55፥19፤* ከገዛ መንገዳቸው “የማይመለሱትንና” እግዚአብሔርን የማይፈሩትን ሰዎች ዘላለማዊ የሆነው ንጉሥ ይፈርድባቸዋል (36፥1 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም መዝ14፡53 ይመ)።

55፥20 *በወዳጆቹ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም “በሰላም አብረ

21 አፉ ከቅቤ ይልቅ የለዘበ ነው፤
በልቡ ግን ጦርነት አለ፤
ቃሉ ከዘይት ይልቅ የለሰለሰ ነው፤
ይሁን እንጂ የተመዘዘ ሰይፍ ነው።

22 የከበደህን ነገር በእግዚአብሔር ላይ ጣል፤
እርሱ ደግፎ ይይዝሃል፤
የጻድቁንም መናወጥ ከቶ አይፈቅድም።

23 አንተ ግን፣ እግዚአብሔር ሆይ፤
ክፉዎችን ወደ ጥፋት ጒድጓድ
ታወርዳቸዋለህ፤
ደም የተጠሙ ሰዎችና አታላዮች፣
የዘመናቸውን እኩሌታ አይኖሩም።

እኔ ግን በአንተ እታመናለሁ።

## መዝሙር 56

### በእግዚአብሔር መደገፍ

ለመዘምራን አለቃ፤ "ርግቢቱ ሩቅ ባለው ወርካ ላይ" በተባለው ቅኝት፤ ፍልስጤማውያን በጌት በያዙት ጊዜ፤ የዳዊት ቅኔ°

1 እግዚአብሔር ሆይ፤ የሰዎች መረገጫ
ሆኛለሁና ማረኝ፤
ቀኑንም ሙሉ በውጊያ
አስጨንቀውኛል።

2 ጠላቶቼ ቀኑን ሙሉ በላዬ ቆሙ፤
በትዕቢት የሚዋጉኝ ብዙዎች
ናቸውና።

3 ፍርሀት በሚይዘኝ ጊዜ፣
እምነቴን በአንተ ላይ አደርጋለሁ።

4 ቃሉን በማመሰግነው አምላክ፣
በእግዚአብሔር ታምኛለሁ፤ አልፈራም፤
ሥጋ ለባሽ ምን ሊያደርገኝ ይችላል?

5 ቀኑን ሙሉ ቃሌን ያጣምሙታል፤
ዘወትርም ሊጐዱኝ ያሤራሉ።

6 ይዶልታሉ፤ ያደባሉ፤
ርምጃዬን ይከታተላሉ፤
ነፍሴንም ለማጥፋት ይሻሉ።

7 እግዚአብሔር ሆይ፤ ከቶ እንዳያመልጡ፣
ሕዝቦቹን በቍጣህ ጣላቸው።

8 ሰቆቃዬን መዝግብ፤
እንባዬን በዕቃህ አጠራቅም፤°
ሁሉስ በመዝገብህ የተያዘ አይደለምን?

9 ወደ አንተ በተጣራሁ ቀን፣
ጠላቶቼ ወደ ኋላቸው ይመለሳሉ፤
በዚህም፣ አምላክ ከጐኔ መቆሙን
ዐውቃለሁ።

10 ቃሉን በማመሰግነው አምላክ፣
ቃሉን በማመሰግነው በእግዚአብሔር፣

°ርእሱ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያ ሳይ ሊሆን ይችላል።
°8 እንባዬን በወይን አቍማዳህ ውስጥ ጨምር ወይም እንባ ዬን በመጽሐፍህ መዝግብ

55፥21 መዝ12፥2፤ 57፥4፤59፥7፤64፥3፤ ምሳ5፥3፤6፥24፤12፥18፤ራእ1፥16
55፥22 መዝ15፥5፤ 18፥35፤21፥7፤37፥24 ፤112፥6፤ማቴ6፥25-34፤1ጴጥ5፥7
55፥23 ኢዮ15፥32 ፤መዝ5፥6፤9፥15፤11፥1፤25፥2፤30፥3፤56፥3፤73፥18፤94፥13፤ኢሳ 14፥15፤ሕዝ28፥8 ፤ሉቃ8፥31
56፥1 መዝ6፥2፤ 17፥9፤57፥1-3
56፥2 መዝ35፥1: 25፤124፥3
56፥3 መዝ55፥4-5: 23
56፥4 ቍ10፤መዝ 27፥1፤118፥6፤ማቴ 10፥28፤ዕብ13፥6
56፥5 መዝ41፥7፤ 2ጴጥ3፥16
56፥6 መዝ17፥11፤ 59፥3፤71፥10፤94፥21 ፤ማር3፥6
56፥7 መዝ36፥12፤ 55፥23፤ምሳ19፥5፤ ሕዝ17፥15፤ሮሜ 2፥3፤ዕብ12፥25
56፥8 2ነገ20፥5፤ ኢሳ4፥3፤ዳን7፥10፤ 12፥1፤ሚል3፥16
56፥9 ዘኍ14፥8፤ዘዳ

ውት የሚኖሩትን" ማለት ነው (7፥4 ይመ)።

*55፥21፤* 28፥3፤ ምሳ5፥3-4 ይመ፤ እንዲሁም የ5፥9 ማብ ይመ። *በልቡ፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

*55፥22-23፤* ጸሎቱ እንደሚሰማ እርግጠኛ መሆኑን እንደ ገና ገለጸ።

55፥22 *የከበደህን ነገር በእግዚአብሔር ላይ ጣል፤* የሚያ ሳስብና የሚያስጨንቅ ነገር በደረሰብን ጊዜ ሸክማችንንና ጭንቀታች ንን በእርሱ ላይ እንድንጥል እግዚአብሔር ደጋግሞ መክሮናል። እግዚአብሔር ከኛ ጋር ሆኖ ሸክማችንን ያግዘናል። እግዚአብሔር የሕዝቡን ሸክም ለማገዝ ሁልጊዜ ዝግጁ ነው። በማቴ11፥28-30 ላይ ጌታ ለሕዝቡ የሚጨነቅ መሆኑን ሲያሳይ "ሸክማችሁ የከበ ደባችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ" ብሎአል። ሐዋርያው ጴጥሮስ ደግሞ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጭንቀቱን ሁሉ በጌታ ላይ እንዲጥል ሲያ ሳስብ እንዲህ ይላል "እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨን ቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት" (1ጴጥ5፥7)። ጳውሎስም የእግ ዚአብሔር ሰላም ልባችንና ኅሊናችንን እንደሚጠብቅ ተስፋ በመ ስጠት (ፊል4፥7 እና ማብ ይመ) ጭንቀታችንን ሁሉ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር እንድናቀርብ ይመክረናል።

55፥23 *ወደ ጥፋት ጒድጓድ፤* ወደ መቃብር ማለት ነው (የ30፥1 ማብ ይመ)። *የዘመናቸውን እኩሌታ አይኖሩም፤* የቍ15 ማብ ይመ።

*መዝ56፤* መዝሙረኛው ጠላቶቹ ባጠቁትና ሕይወቱንም ለማ ጥፋት ባስፈራሩት ጊዜ ያቀረበው ጸሎት ነው። ዕረፍት በሚነሣ ፍርሀት ፊት የሚያጽናና እምነት ነበረው። ባወቃቀር ደረጃ ሲታይ መዝሙሩ እግዚአብሔር ፊቱን ወደ እርሱ እንዲመልስ በሚያሳ ስብ ልመናና (ቍ1-2) በእግዚአብሔር እንደሚተማመን በሚያረጋ ግጥ ቃል የተቀነበበ ነው (ቍ12-13)። በውስጣዊው ቅንብብ ማለትም በቍ3-4 እና በቍ10-11 ላይ እግዚአብሔር ጽኑ መታመኛው እንደ ሆነ በአዝማች መካከል ደጋግሞ ይናገራል። ጸሎቱ ራሱ እየዳበረ የሚሄደው በመካከል ላይ ባሉት ቍጥሮች (ቍ5-9) ነው።

56 ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ4 የርእስ ማብ ይመ። *ቅኝት፤* የመዝ9 የርእስ ማብ ይመ። ቅኔ፤ የመዝ16 የርእስ ማብ ይመ። *ጊዜ፤* የመዝ3 የርእስ ማብ ይመ። እዚህ ላይ የተጠ ቀሰውን ታሪክ በ1ሳሙ21፥10-15 ላይ ይመ። እንዲሁም የመዝ 34ን ርእስና ማብ ይም። *በያዙት ጊዜ፤* ወይም "ሊይዙት በተ ቃረቡ ጊዜ" ማለት ነው።

*56፥1-2፤* እግዚአብሔር እንዲረዳው በመግቢያው ላይ ያቀ ረበው ምልጃ ነው።

56፥2 *ጠላቶቼ፤* የጠላት ዋና መሣሪያ ተናጻፊ ምላስ ነው (የ5፥9 ማብ ይመ)። *በትዕቢት፤* በኀይላቸው ስለሚተማመኑ ለዳዊት አምላክ ደንታ አልነበራቸውም (የመዝ3፥2፤ 5፥9፤ 10፥11 ማብ ይመ)።

*56፥3-4፤* ቍ10-11 ይመ። የሚያስፈራ ሁኔታ ቢገጥመ ውም በእግዚአብሔር እንደሚታመን ይገልጻል።

56፥4 *ቃሉን፤* ልመናቸውን ወደ እርሱ ሲያቀርቡ እግዚ አብሔር የሕዝቡ አምላክ እንደሚሆንና ከገጠማቸውም ችግር ሁሉ እንደሚታደጋቸው የሚያረጋግጥ ቃል ነው (50፥15፤ 91፥15፤ እንዲሁም 119፥74:81፤ 130፥5 ይመ)። *ሥጋ ለባሽ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "ሥጋ" የለበሰ ሰው ማለት ነው፤ ይህም ሰው ከኀያሉ እግዚአብሔር ጋር ሲነጻጸር ዐቅመ-ቢስ ደካማ ነው (የ10፥18 ማብ ይመ)።

*56፥5-7፤* መዝሙረኛው በጠላቶቹ ላይ ያቀረበውን ክስና ጠላ ቶቹ የእጃቸውን እንዲያገኙ የጠየቀበት ክፍል ነው (የ5፥9-10 ማብ ይመ)።

56፥5 *ቃሌን ያጣምሙታል፤* ቍ2 ይመ።

*56፥7፤* የ5፥10 ማብ ይመ። *በቍጣህ፤* የ2፥5 ማብ ይመ።

*56፥8-9፤* የመዝሙረኛውን ችግር በተለየ ዐይን እግዚ አብሔር እንዲመለከት የቀረበ ልመና ነው።

56፥8 *ሰቆቃዬን መዝግብ፤* እግዚአብሔር ችግርን፣ መከራ ንና ሥቃይን ሁሉ መዝግቦ ይይዛል (ከ139፥16፤ ከማቴ6፥25-32 ጋር ያነጻጽሩ)። እያንዳንዱ ቅን የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚያ ፈሰው እንባ ሁሉ በፊቱ ዋጋ አለው፤ በክብርም ቦታ ተመዝግቦ ይገኛል። ለእርሱ ስንል በዚህ ዓለም በተቀበልነው መከራ ልክ ይከፍለን ዘንድ ያሳለፍነውን መከራ ሁሉ መዝግቦታል። በሚ ደርስብን ፈተና ሁሉ ምንጊዜም ለእርሱ ታማኞች ሆነን ከቆምን፣ በሰማይ ቤት ከእርሱ ጋር በምንሆንበት ጊዜ የሰው ሐሳብ የማ ይደርስበትን ደስታና ክብር እንጐናጸፋለን (ሮሜ8፥17 እና ማብ፣ 1ጴጥ4፥14 እና ማብ ይመ)። ስለዚህ ችግር፣ ጭንቀት ወይም አሳዛኝ ነገር ሲደርስብን እንዲሁም ተስፋ የሚያስቈርጥ ሁኔታ፣ ሕመም፣ እንቅልፍ ማጣት፣ የገንዘብ ችግርና የሥራ ጫና ሁሉ አፋጦ ሲይዘን እግዚአብሔር በፍቅር እንደሚያየን መዘን ጋት የለብንም።

*56፥9፤* እግዚአብሔር የዳዊትን እንባ ቈጥሮ በመጽሐፍ ከመ ዘገበ ዳዊት ርዳኝ በማለት ያቀረበውን ልመና በእርግጥ ይሰማል።

*56፥10-11፤* የሚያስፈራ ነገር በሚገጥመው ጊዜ በጌታ

11 በስምሳክ ታምኛለሁ፤ አልፈራም፤
ሥጋ ለባሽ ምን ሊያደርገኝ ይችላል?
12 እግዚአብሔር ሆይ፤ የአንተ ስእለት
አለብኝ፤
የማቀርብልህም የምስጋና መሥዋዕት
ነው፤
13 በሕያዋን ብርሃን፣[a]
በእግዚአብሔር ፊት እመላለስ ዘንድ፣
ነፍሴን ከሞት፣[b]
እግሬንም ከመሰናከል አድንሃልና።

## መዝሙር 57

### በጨካኝ ጠላቶች ዘንድ

57፥7-11 ተጓ ምብ-መዝ108፥1-5

ለመዘምራን አለቃ፤ "አታጥፋ" በሚለው ቅኝት የሚዘመር፤ ከሳኦል ፊት ሸሽቶ በዋሻ በነበረበት ጊዜ፤ የዳዊት ቅኔ።[c]

1 ማረኝ፤ እግዚአብሔር ሆይ፤ ማረኝ፤
ነፍሴ አንተን መጠጊያ አድርጋለችና፤
በክንፎችህ ሥር እጠለላለሁ።
2 ለእኔ ያሰበውን ወደሚፈጽምልኝ ስምሳክ፣
ወደ ልዑል እግዚአብሔር እጮኻለሁ።
3 ከሰማይ ልኮ ያድነኛል፤
የረገጡኝን ያዋርዳቸዋል፤ ሴላ
እግዚአብሔር ምሕረቱንና ታማኝነቱን
ይልካል።
4 ነፍሴ በአንበሶች ተከብባለች፤
በሚዘነጣጥሉ አራዊት መካከል
ወድቄአለሁ፤
እነዚህም፣ ጥርሳቸው ጦርና ፍላጻ፣
ምላሳቸውም የተሳለ ሰይፍ የሆኑ
ሰዎች ናቸው።
5 እግዚአብሔር ሆይ፤ ከሰማያት በላይ
ከፍ ከፍ በል፤
ክብርህም በምድር ሁሉ ላይ ትስፋን።
6 ለእግሬ ወጥመድን ዘረጉ፤
ነፍሴንም አጐበጧት፤
በመተላለፊያዬ ላይ ጕድጓድ ቈፈሩ፤
ነገር ግን ራሳቸው ገቡበት። ሴላ
7 እግዚአብሔር ሆይ፤ ልቤ ጽኑ ነው፤
ልቤ ጽኑ ነው፤
እቀኛለሁ፤ አዜማለሁ።
8 ነፍሴ ሆይ፤ ንቂ!
በገናና መሰንቆም ተነሡ!
እኔም በማለዳ እነሣለሁ።
9 ጌታ ሆይ፤ በሕዝቦች መካከል አመሰግንሃለሁ፤
በሰዎችም መካከል እዘምርልሃለሁ፤
10 ምሕረትህ እስከ ሰማይ ከፍ ብላለችና፤

31፥6፤መዝ9፥3፤102፥2፤ሮሜ8፥31
56፥12 መዝ50፥14
56፥13 ኢዮ33፥30፤ መዝ30፥3፤33፥19፤49፥15፤86፥13፤107፥20፤116፥8
57 ርዕስ1ሳሙ22፥1፤24፥3፤መዝ142ርዕስ
57፥1 ሩት2፥12፤ መዝ2፥12፤9፥9፤34፥22፤ኢሳ26፥20፤ማቴ23፥37
57፥2 መዝ138፥8
57፥3 መዝ18፥9:16፤25፥10፤40፥11፤56፥1፤69፥14፤115፥1፤142፥6፤144፥5:7
57፥4 መዝ35፥17፤ 55፥21፤ምሳ30፥14
57፥5 ቊ11፤መዝ108፥5
57፥6 አስ6፥13፤ መዝ7፥15፤9፥15፤10፥9፤31፥4፤38፥6፤140፥5፤145፥14፤ምሳ28፥10፤መክ10፥8
57፥7 መዝ112፥7
57፥8 መዝ33፥2፤ 149፥3፤150፥3
57፥10 መዝ36፥5

[a] 13 ወይም እኔን ከሞት
[b] 13 ወይም በሕያዋን ምድር
[c] ርእሱ የሥነ ጽሑፉን ትርጉም ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።

የሚታመን መሆኑን እንደ ገና አረጋገጠ (ቊ3-4 ይመ)።

56፥12-13፤ ጸሎቱ እንደሚሰማ እርግጠኛ ነው (የ3፥8 ማብ ይመ)።

56፥12 ስእለት አለብኝ፤ ጸሎቱ እንደተሰማለት በመቍጠር ዳዊት ችግር በደረሰበት ጊዜ ለእግዚአብሔር የተሳለውን ስእለት መጠበቅ እንዳለበት ተገነዘበ (66፥14 እና የ7፥17 ማብ ይመ)።

56፥13 በሕያዋን ብርሃን፤ የተሟላ የሕይወት በረከት፤ የመዝ36፥9 ይመ። በእግዚአብሔር ፊት፤ የ11፥7 ማብ ይመ። ከመሰናከል፤ አማራጭ ትርጕሙን፤ የ35፥15 ማብ ይመ።

መዝ57፤ ጨካኝ ጠላቶች ባስጨነቁት ጊዜ እግዚአብሔር እንዲታደገው ያቀረበው ጸሎት ነው (ከመዝ56 ጋር በብዙ ረገድ የተሳሰረ ነው)። ይህ መዝሙር የአደጋን ጨለማ (ቊ4 "ተኛሁ") የደኅንነትን ንጋት (ቊ8 "በማለዳ እነሣለሁ") በዘይቤያዊ አባባል ያቀርባል። ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ምሳሌዎች በ30፥5፤ 46፥5፤ 59፥6:14:16፤ 63፥1:6፤ 90፥14 ይመ። ከቊ 7-11 ያለው ሐሳብ በ108፥1-5 ላይ እንደ ገና ተጠቅሶአል። መዝሙሩ እኩል ርዝመትና (ቊ1-5 እና ቊ6-11) ተመሳሳይ አወቃቀር ባላቸው ሁለት ክፍሎች የተደረሰ ነው። ሁለቱም ክፍሎች ባለ ሦስት ቤት ስንኞች የያዙ ሲሆን የሚጨርሱትም ተመሳሳይ በሆኑ አዝማቾች ነው (በሌላ ቦታ አዝማቾች እንዴት እንደገቡ ለማየት የመዝ42-43 መግቢያን ይመ)።

57 ርእስ፤ የመዝ56 የርእስ ማብ ይመ። አታጥፋ፤ የመዝ58፤ 59፤ 75 ርእሶችን ይመ። በነበረበት ጊዜ፤ እዚህ ላይ የተጠቀሰውን ታሪክ በ1ሳሙ24፥1-3ላይ ይመ፤ እንዲሁም የመዝ 142 ርእስ ይመ።

57፥1-5፤ ጸሎት ነው።

57፥1፤ እግዚአብሔር ከምሕረቱ የተነሣ እንዲረዳው በመጠጊያው ላይ ያቀረበው የልመና ጩኸት ነው። በክንፎችህ ጥላ ሥር፤ የ17፥8 ማብ ይመ።

57፥2-3፤ ጸሎቱ እንደሚሰማ እርግጠኛ ነው።

57፥2 ልዑል፤ የዘፍ14፥19 ማብ ይመ። ለእኔ ያሰበውን ወደ ሚፈጽምልኝ፤ 138፥8 ይመ። እግዚአብሔር ዳዊትን ንጉሥ አድርጐ ለመቀባት ያሰበውን ሐሳብ የዳዊት ጠላቶች መና እንዲያስቀሩት አይፈቅድላቸውም (1ሳሙ16፥1:12፤ 2ሳሙ7 ይመ)።

57፥3 ይልካል፤ እግዚአብሔር ባሪያውን እንዲታደጉ ከሰማይ (የ43፥3 ማብ ይመ) ፍቅርንና ታማኝነትን ይልካል (እዚህ ላይ ሁለቱም የተጠቀሱት በሰውኛ አነጋገር ነው፤ የ23፥6 ማብ ይመ)። ምሕረቱንና ታማኝነቱን፤ የ26፥3 ማብ ይመ። ፍቅሩ፤ የ6፥4 ማብ ይመ።

57፥4፤ መዝሙረኛው ያለበትን አስፈሪ ሁኔታ ይገልጻል። ወድቄአለሁ፤ በአንበሶች እንደ ተከበበ በግ ማለት ነው። በሚዘነጣጥሉ አራዊት፤ የመዝሙራት ጸሓፊዎች አብዛኛውን ጊዜ ጠላቶቻቸውን ከጨካኝ አውሬዎች ጋር ያነጻጽሯቸዋል (የ7፥2 ማብ ይመ)። (እዚህ ላይ የተጠቀሰው ተምሳሌታዊ አነጋገር በ2ሳሙ1፥23 ላይ ከገለጸው የሳኦልና የዮናታን ታሪክ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም)። ምላሳቸውም፤ የ5፥9 ማብ ይመ።

57፥5፤ እግዚአብሔር ባሪያዎቹን በመታደግ ታላቅ ኀይሉንና ክብሩን በፍጥረታት ሁሉ ላይ እንዲያሳይ የቀረበ ጸሎት ነው (7፥6-7፤ 21፥13፤ 46፥10፤ 59፥5:8፤ 113፥4-9 ይመ፤ ከዘፀ 14፥4፤ ከኢሳ26፥15፤ 44፥23፤ 59፥19 ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም የመዝ46፥10 ማብ ይመ)።

57፥6-11፤ እግዚአብሔር ስላደረገው ማዳን የቀረበ ውዳሴ ነው፤ መዝሙረኛው የእግዚአብሔርን ማዳን እንደሚያይ እርግጠኛ ነው። ከጸሎት ወደ እርግጠኛነት በድንገት ስለ ተደረገው እንዲህ ያለ ሽግግር የመዝ3፥8 ማብ ይመ።

57፥6፤ የመዝሙረኛው ጠላቶች ለእርሱ ባሰቡት መከራ እነርሱ ራሳቸው ተያዙ። ወጥመድን … ጕድጓድ፤ እንደ ዱር አውሬ አጠመዱት፤ ይሁን እንጂ የያዙት አንበሳ ነው።

57፥7፤ የፍርሀቱ መንሥኤ ሁሉ ተወገደ። ልቤ፤ የ4፥7 ማብ ይመ። ጽኑ ነው፤ ዋስትና አግኝቶአል (112፥7 ይመ)።

57፥8 ነፍሴ፤ ቃል በቃል ሲተረጐም "ክብሬ" ማለት ነው (የ7፥5 ማብ ይመ)። ንቂ … ተነሡ፤ የማዳኑን ማለዳ በደስታ ለመቀበል ነው (ኢሳ51፥9:17፤ 52፥1 ይመ)። በገናና መሰንቆ፤ የእግዚአብሔርን ማዳን በቤተ መቅደስ ሲያወድሱ እነዚህን በመሳሰሉ መሣሪያዎች (እዚህ ላይ በሰውኛ አነጋገር ገብተዋል) ይጠቀማሉ (71፥22፤81፥2 እንዲሁም የመዝ4 የርእስ ማብ ይመ)። በማለዳ እነሣለሁ፤ የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ በሐሤት እየጮኸ ያውጃል (እዚህም ላይ ማለዳ የሚለው ቃል በሰውኛ አነጋገር ገብቶአል፤ ከነዓናውያን ግን "ማለዳን" እንደ አምላክ እስከ ማየት ደርሰው ነበር)።

57፥9-10፤ ውዳሴ ለማቅረብ የገባው ስእለት ነው (የ7፥17፤ የ9፥1 ማብ ይመ)።

57፥10 ምሕረትህ፤ የ6፥4 ማብ ይመ። ምሕረትህ …

ታማኝነትህም እስከ ደመናት
ትደርሳለች።
[11]እግዚአብሔር ሆይ፤ ከሰማያት በላይ ከፍ
ከፍ በል፤
ክብርህም በምድር ሁሉ ላይ ትስፈን።

## መዝሙር 58

## የምድር ዳኞች ፈራጅ

*ለመዘምራን አለቃ፤ "አታጥፋ" በሚለው ቅኝት የሚዘመር፤ የዳዊት ቅኔ*[ሯ]

[1]ኀያላን ሆይ፤ በውኑ ጽድቅ ከአፋችሁ
ይወጣል?
የሰው ልጆች ሆይ፤ በቅን
ትፈርዳላችሁን?
[2]የለም፤ በልባችሁ ክፋትን ታውጠነጥናላችሁ፤
በእጃችሁም ዐመፅን በምድር ላይ
ትጐነጕናላችሁ።
[3]ክፉዎች በማሕፀን ሳሉ ከመንገድ የወጡ
ናቸው፤
ሲወለዱ ጀምሮ የተሳሳቱና ውሸታሞች
ናቸው።
[4]መርዛቸው እንደ እባብ መርዝ ነው፤
አልሰማ ብላ ጆሮዋን እንደ ደፈነች
እፉኝት ናቸው፤
[5]ጆሮዋንም የደፈነችው የመተተኛውን
ወይም የጠቢቡን ደጋሚ ቃል
ላለመስማት ነው።
[6]እግዚአብሔር ሆይ፤ ጥርሳቸውን በአፋቸው ውስጥ
ስበር፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ የአንበሶቹን መንጋጋ
አወላልቅ!
[7]ፈጥኖ እንደሚያልፍ ወራጅ ውሃ ይጥፉ፤
ቀስታቸውን ሲስቡ ፍላጻቸው ዱልዱም
ይሁን።
[8]ሲሄድ እንደሚቀልጥ ቀንድ አውጣ ይሁኑ፤
ፀሓይን እንደማያይ ጭንጋፍ ይሁኑ።
[9]የእሾኽ እሳት ገና ድስታችሁን ሳያሰማው፣
እርጥቡንም ደረቁንም እኩል በዐውሎ
ነፋስ ጠራርጎ ይወስዳቸዋል።[ፗ]
[10]ጻድቃን በቀልን ባዩ ጊዜ ደስ ይላቸዋል፤
እግራቸውንም በግፈኞች ደም
ይታጠባሉ።
[11]ሰዎችም፣ "በእርግጥ ለጻድቃን ብድራት

[ሯ] ርእሱ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።
[ፗ] 9 በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጉም በትክክል አይታወቅም።

57፥11 ቍ5፤መዝ 8፥1፤113፥4
58፥1 መዝ82፥2
58፥2 መዝ94፥20፤ ኢሳ10፥1፤ማቴ15፥19፤ሉቃ6፥38
58፥4 ዘኍ21፥6
58፥5 መዝ81፥11፤ መክ10፥11፤ኤር8፥17
58፥6 ኢዮ4፥10፤ መዝ3፥7
58፥7 ዘሌ26፥36፤ ኢዮ11፥16፤መዝ11፥2፤57፥4፤64፥3
58፥8 ኢዮ3፥16፤ ኢሳ13፥7
58፥9 ኢዮ7፥10፤ 21፥8፤መዝ118፥12፤ መክ7፥6
58፥10 ዘዳ32፥35፤ ኢዮ22፥19፤መዝ7፥9፤ 68፥23፤91፥8፤ኤር11፥20፤ሮሜ12፥17-21
58፥11 ዘፍ15፥1፤ 18፥25፤መዝ128፥2፤ ሉቃ6፥23

***ታማኝነትህም፤*** (ቍ3፤ የ36፥5 ማብ፤ እንዲሁም የ3፥7 ማብ ይመ)። ***እስከ ሰማያት ሰማያት፤*** የ36፥5 ማብ ይመ።

***57፥11፤*** የመዝሙሩ አዝማች ሲሆን (ቍ5 ይመ) እዚህ ላይ እግዚአብሔርን ለማወደስ ገብቶአል (18፥46፤ 30፥1፤ 34፥3፤ 35፥27፤ 40፥16፤ 70፥4፤ 92፥8፤ 97፥9፤ 99፥2፤ 113፥4፤ 148፥13 ይመ)።

***መዝ58፤*** የሰዎችን አካሄድ እንዲያቀና፣ ፍርድን የሚያጣምሙ ነገሮችን እንዲቀጣና የጻድቃንን ጕዳይ ተግቶ እንዲከታተል ልዑል ለሆነው እግዚአብሔር የቀረበ ጸሎት ነው (የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ይህን መዝሙር ኢየሱስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት ተከሶ በቀረበ ጊዜ ከሆነው ነገር ጋር አያይዛዋለች፤ ማቴ26፥57-68 እና ተጓ ምብ ይመ)። *ሥልጣን ፍትሕን ለማስፈን መሣሪያ እንጂ መጨቈኛ እንዳልሆነ* በብሉይ ኪዳን በሰፊው ተነግሮአል። በጥንት መካከለኛው ምሥራቅ የአስተዳደር ሥርዐት ውስጥ ንጹሓችን በተለይም ድኾችንና ደካሞችን ከጨቋኝ ሰዎች በተለይም ከሀብታሞች የጭካኔ አገዛዝ መጠበቅ ዐይነተኛ ቦታ ተሰጥቶታል። ከሳሙኤል ዘመን ጀምሮ ንጉሣዊ አገዛዝ እስካከተመበት ዘመን ድረስ የእስራኤል ኅብረተሰብ በፍትሕ መዛባት ተሠቃይቶአል (ለምሳሌም 1ሳሙ8፥3፤ ኢሳ1፥23፤ 5፥23፤ 10፥1-2፤ ሕዝ 22፥6፡12፤ አሞ5፥7፡10-13፤ ሚክ3፥1-3፡9-11፤ 7፥2 ይመ)። በዳዊት ዘመነ መንግሥት እንኳ ነገር ሁሉ ሥርዐትና መልክ አልነበረውም (2ሳሙ15፥1-4 ይመ)። የዚህ መዝሙር ዐቢይ ሐሳብ ምን እንደ ሆነ ለማወቅ መዝ82 ይመ። ባወቃቀር ደረጃ ሲታይ መዝሙሩ የተቀነበበው ክፉ ዳኞችን በመውቀስና (ቍ1-2) "ለጻድቃን" የሚያጽናና ቃል በመናገር ነው (ቍ9-11)። ከዚህ በተጨማሪ ቅንብቡ በትክክል የማይፈርዱ ሰዎች (ቍ1) በእግዚአብሔር እንደሚፈረድባቸው ይናገራል (ቍ11)።

58ርእስ ***ለመዘምራን አለቃ፤*** የመዝ4 የርእስ ማብ ይመ። ***በሚለው ቅኝት፤*** የመዝ9 የርእስ ማብ ይመ። ***አታጥፋ፤*** የመዝ 57፤ 59፤ 75 ርእሶችን ይመ። ***ቅኔ፤*** የመዝ16 የርእስ ማብ ይመ።

***58፥1-5፤*** ፍትሕን ለማዛባት እንደበታቸውን፣ ልባቸውንና እጃቸውን ባስተባበሩ (ቍ1-2) ዳኞች ላይ የቀረበ ክስ ነው።

58፥1 ***ገዦች፤*** ቃል በቃል ሲተረጐም፣ "አማልክት" ማለት ነው፤ በሰማይ የሚገኘውን የእግዚአብሔርን ፍርድ ቤት ወክለው በዚህ ምድር የእግዚአብሔርን ሐሳብ የሚያገለግሉ ናቸው (በዘፀ21፥6፤ 22፥8-9 የጽሑፉን ማብ፤ እንዲሁም ዘዳ1፥17፤ 2ዜና19፥6 ይመ)። ***በቅን ትፈርዳላችሁን?*** ፍትሕ ታብብ ትለምልም ማለት ነው።

58፥2 ***በልባችሁ፤*** ያ4፥7 ማብ ይመ። ***ዐመፅን ይሠራል፤*** ጭካኔ የተሞላበት ሥራ ለመሥራት ውሳኔ ያስተላልፉል ማለት ነው።

58፥3 ***በማሕፀን ሳሉ ... ሲወለዱ፤*** ጠማማ መንገዳቸው በድንገት የተከሠተ አይደለም፤ የሚያደርጉትን ነገር የሚያደርጉት እንደ ባሕርያቸው ነው (51፥5 ይመ)። እዚህ ላይ ይህ ቃል የሚናገረው ስለ ክፉዎች ነው፤ በዘፍ6፥5፤ 8፥21፤ በኢዮ14፥4፤ 15፥14-16፤ 25፥4-6 ላይ እንደ ተጠቀሰው የዚህ መዝሙር ጸሓፊ የሚናገረው ሰዎች ሁሉ እንዲህ ዐይነት ናቸው እያለ አይደለም። ***ክፉዎች፤*** ምን ዐይነት ባሕርይ እንዳላቸው በመዝ10 ላይ ይመ። ***ውሸታሞች፤*** ስለ እውነት አንድም ቀን ግድ ብሎአቸው አያውቅም (ዮሐ8፥44 ይመ)።

58፥4 ***መርዛቸው፤*** ከአፋቸው የሚወጣው ነገር እንደ እባብ መርዝ ገዳይና አጥፊ ነው (140፥3፤ ማቴ23፥33፤ ያዕ3፥8 ይመ)። ጆሮአቸውን አቀመዋል፤ የመታረምም ሆነ የመሻሻል ነገር ከቶ አይታይባቸውም፤ ልመናም ሆነ ዛቻ ከቶ አይመልሳቸውም።

***58፥6-8፤*** እግዚአብሔር ምድሪቱን እንዲህ ከመሰሉ ጠማማ ዳኞች እንዲያጸዳ የቀረበ ልመና ነው። ጸሓፊው በጥንት መካከለኛ ምሥራቅ በጣም የተለመደውን የርግማን ቃል እዚህ ላይ አውሎት ይገኛል (የ5፥10 ማብ ይመ)።

***58፥6፤*** የአፋቸው መሣሪያ (57፥4 ይመ) ይሰበር፤ ይድቀቅ። ***የአንበሶቹንም፤*** የ7፥2 ማብ ይመ።

58፥7 ***እንደሚያልፍ ውሃ፤*** መሬት ላይ ፈስሶ እንደሚሠርግ ውሃ ማለት ነው። ***ቀስታቸውን፤*** የእጃቸውን እንዲያገኙ የተናገረው ቃል ነው (57፥4 እና የ5፥9 ማብ ይመ)።

58፥8 ***ቀንድ አውጣ፤*** በጠራራ ፀሓይ በደንጊያ ላይ ሲሄድ እንደሚያር ቀንድ አውጣ ይሁኑ ማለት ነው።

***58፥9-11፤*** እግዚአብሔር በእርግጥ እንደሚፈርድባቸው እርግጠኛ ነው (የ3፥8 ማብ ይመ)።

***58፥9፤*** አማራጭ ትርጕሙን ይመ፤ ጥቅሱ ምናልባት የእግዚአብሔር ፍርድ ምን ያህል ፈጣን እንደሆነ ሳያመለክት አይቀርም፤ እዚህ ላይ ቃሉ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ፍርድ መምጣቱ የማይቀር መሆኑን ነው (የ37፥10 ማብ፤ እንዲሁም ሉቃ18፥7-8 ይመ)። ***እሾህ፤*** ከጫካ የሚለቀም እሾኻማ ቍጥቋጦ ለማገዶነት ያገለግል ነበር (118፥12፤ መክ7፥6 ይመ)። ***ጠራርጎ፤*** የሚጠፉት በዐውሎ ነፋስ ነው፤ ይህ ዐውሎ ነፋስ ከእግዚአብሔር የተላከ ዐውሎ ነፋስ ነው (ኢዮ27፥21 ይመ)።

58፥10 ***ጻድቃን፤*** እዚህ ላይ ቃሉ በአካሄዳቸው ጻድቅ የሆኑ ሰዎችን የሚያመለክት ሲሆን እነዚህ ሰዎች በደል የደረሰባቸው ሰዎች ናቸው (የ1፥5 ማብ ይመ)። ***በቀልን ባዩ ጊዜ፤*** በደል ያደረሱባቸው ሰዎች የእጃቸውን ሲያገኙ ማለት ነው። ***እግራቸውንም ... ደም ይታጠባሉ፤*** ምስል ከሳች አነጋገር ሲሆን የተወሰደውም ከጥንት መካከለኛው ምሥራቅ ነው (68፥23 ይመ)። ይህ አባባል የተወሰደው በጦር ሜዳ ድል የተቀዳጀ ሰራዊት ድሉን አጋኖ ለመናገር ከሚጠቀምባቸው ቃላቶች ላይ ነው።

***58፥11፤*** የመዝሙሩ ልዕለ ሐሳብ ነው፤ እግዚአብሔር

ተቀምጠላቸዋል፤
በእውነትም በምድር ላይ የሚፈርድ
ስምባክ አለ" ይላሉ።

## መዝሙር 59
## ከፉዎችን በመቃወም የቀረበ ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ "አታጥፋ" በሚለው ቅኝት የሚዜም፤ ዳዊትን ለመግደል ሰዎች ቤቱን ከብበው እንዲጠብቁት ሳኦል በላካቸው ጊዜ፤ የዳዊት ቅኔ[ኀ]*

1 ስምባክ ሆይ፤ ከጠላቶቼ እጅ አድነኝ፤
ሊያጠቁኝ ከሚነሡብኝም ጠብቀኝ።
2 ከክፉ አድራጊዎች ታደገኝ፤
ደም ከተጠሙ ሰዎችም አድነኝ።
3 እነሆ በነፍሴ ላይ አድብተዋልና፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ጨካኞች ያለ
በደሌ፣ ያለ ኀጢአቴ፤
በላዬ ተሰብስበው ዶለቱብኝ።
4 እነርሱ ያለ በደሌ ሊያጠቁኝ ተዘጋጅተው
መጡ፤
አንተ ግን ትረዳኝ ዘንድ ተነሥ፤
ሁኔታዬንም ተመልከት።
5 የሰራዊት ስምባክ፤ የሆንህ፣ አንተ የእስራኤል
ስምባክ፤ *እግዚአብሔር* ሆይ፤
ሕዝቦችን ሁሉ ለመቅጣት ተነሥ፤

59 ርዕስ1ሳሙ19፥11
59፥1 መዝ20፥1፤ 143፥9
59፥2 14፥4፤26፥9፤ 36፥12፤53፥4፤92፥7፤ 94፥16፤139፥19፤ምሳ 29፥10
59፥3 መዝ56፥6
59፥4 መዝ13፥3፤ 119፥3፤ማቴ5፥11
59፥5 9፥5፤44፥23 ፤69፥6፤80፥4፤84፥8፤ ኢሳ10፥3፤ኤር18፥23
59፥6 ቍ14፤መዝ 22፥16
59፥7 ኢዮ22፥13፤ መዝ55፥21፤94፥4፤ ምሳ10፥32፤12፥23፤ 15፥2:28
59፥8 መዝ2፥4፤ 37፥13፤ምሳ1፥26
59፥9 መዝ9፥9፤ 18፥1:2፤62፥2፤71፥3
59፥11 ዘዳ4፥9፤ 6፥12 ፤መዝ3፥3፤84፥ 9፤89፥10፤106፥27 ፤144፥6፤ኢሳ33፥3

በተንኰላቸው በደል የሚፈጽሙትንም
ሁሉ አትማራቸው። ሴላ
6 እንደ ውሻ እያላዘኑ፣
በምሽት ተመልሰው ይመጣሉ፤
በከተማዪቱም ዙሪያ ይራወጣሉ።
7 ከአፋቸው የሚወጣውን ተመልከት፤
ሰይፍ በከንፈራቸው ላይ አለ፤
"ማን ሊሰማን ይችላል?" ይላሉና።
8 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ ግን
ትሥቅባቸዋለህ፤
ሕዝቦችን ሁሉ በንቀት ታያቸዋለህ።
9 ብርታቴ ሆይ፤ አንተን እጠብቃለሁ፤
ስምባክ ሆይ፤ አንተ መጠጊያዬ ነህና።
10 እግዚአብሔር በምሕረቱ ይገናኘኛል፤
ስምባኬ የጠላቶቼን ውድቀት ያሳየኛል።
11 ጋሻችንም[ሐ] ጌታ ሆይ፤ አትግደላቸው፤
አለበለዚያ ሕዝቤ ይረሳል፤
በኀይልህ አንከራታቸው፤
ዝቅ ዝቅም አድርጋቸው።

[ኀ] ርእሱ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያ ሳይ ሊሆን ይችላል።
[ሐ] 11 ወይም ልዑል ተብሉ መተርጐም ይችላል።

በፍርደ-ገምድል "አማልክት" ላይ ፍርዱን ሲሰጥ (የቍ1 ማብ ይመ) በእግዚአብሔር ፍትሐዊ አገዛዝ ውስጥ ጽድቅ አሸናፊ መሆኑን ሰዎች ሁሉ ያስተውላሉ (የ46፥10 ማብ ይመ)። ከእን ግዲህ እነዚህ ወገኖች በሚል 3፥15 ላይ እንደ ተመለከቱት ሰዎች ተስፋ አይቈርጡም።

*መዝ59፤* ከጠላቶቹ እጅ እግዚአብሔር እንዲታደገው ያቀረበው ጸሎት ነው። በመዝሙሩ መቅድም ላይ እንደ ተመለከተው ይህ መዝሙር የተጻፈው በዳዊት ከሆነ ከበርካታ መንግሥታት ተውጣቶ የተደራጀ ሰራዊት ኢየሩሳሌምን በከበባት ጊዜ ከዳዊት ልጆች መካከል አንዱ እንደ ገና አስተካክሎ የጻፈው ሳይሆን አይቀርም፤ ይህም ሕዝቅያስ በአሦራውያን እንደተወረረው ዐይነት ነው (2ነገ18፥19 ይመ)። (አንዳንድ ሊቃውንት ይህ መዝሙር በዚህ መልክ የተጻፈው በነህምያ ነው ይላሉ፤ ነህ4 ይመ)። የመዝሙረኛው ጠላቶች የሚጠቀሙበት መሣሪያ አንደበት ነው፤ በምላሳቸው ይሰድቡታል፤ ይረግሙታል። በዚህ መዝሙር ውስጥ ጨለማና (ቍ6:14) ማለዳ (ቍ16) ምሳሌያዊ በሆነ አነጋገር ገብተዋል (የመዝ57 መግቢያን ይመ)። አወቃቀሩን በተመለከተ የመዝሙሩ ሁለት ክፍሎች (ቍ1-9:10-17) እያንዳንዳቸው ተመሳሳይ በሆኑ አዝማቾች የሚጨርሱ ሲሆን (ቍ9:17) እነዚህ ሁለት ክፍሎች ከማ ብቃታቸው በፊት የሚገኙት አንጓዎች የመዝሙረኛውን ጠላቶች ማንነት በግልጽ ይናገራሉ (ቍ6:14)። የመዝሙሩ የመጀመሪያ ክፍል በአብዛኛው ጸሎት ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ እግዚ አብሔር ከጠላቶቹ በእርግጥ እንደሚታደገው በእርግጠኛነት ይናገራል። በአጠቃላይ ሲታይ መዝሙሩ የተቀነበበው እግዚ አብሔር እንዲጠብቀው በሚያቀርበው ጩኸትና (ቍ1) እግዚ አብሔር የመዝሙረኛው "መጠጊያ" መሆኑን በሚገልጽ ቃል ነው (ቍ17)።

*59ርእስ፤* የመዝሙር 56 የርእስ ማብ ይመ። *አታጥፋ፤* የመዝ57፤58፤75 ርእሶችን ይመ። *ጊዜ፤* እዚህ ላይ የተጠቀሰውን ታሪክ በ1ሳሙ9፥11 ላይ ይመ።

*59፥1-2፤* እግዚአብሔር እንዲታደገው ያቀረበው ልመናና ጩኸት ነው።

59፥1 *አድነኝ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "ከፍ ወዳለና አስተ ማማኝ ወደ ሆነ ስፍራ አውጣኝ" ማለት ነው።

59፥2 *ከክፉ አድራጊዎች ... ደም ከተጠሙ ሰዎችም፤* ከጨካኝነታቸው የተነሣ መዝሙረኛውን ለማጥፋት የተነሡ ሰዎ ችን ማንነት ለመግለጽ የገባ ዘይቤ ነው።

*59፥3-5፤* ጠላቶቹ በስድባቸውና (ቍ10) በውሸታቸው (ቍ12) ተግባራቸው ትክክል መሆኑን ለማሳየት ይፍጨረጨራሉ፤ መዝሙረኛው ግን ንጹሕ ሰው መሆኑን በመግለጽ በደል ባደረ ሱበት ሰዎች ላይ እግዚአብሔር ፍርዱን እንዲሰጥ ይማጸናል (58፥11 ይመ)።

59፥3 *አድብተዋልና፤* 10፥8-9 እና የ7፥2 ማብ ይመ።

59፥4 *ተነሥ፤* የ3፥7 ማብ ይመ።

59፥5 *የሰራዊት አምላክ ... እግዚአብሔር፤* የ1ሳሙ1፥3 ማብ ይመ። *የእስራኤል አምላክ፤* ይህ መንግሥታትንና ሕዝቦ ችን እንዲቀጣ ወደ እስራኤል አምላክ ወደ እግዚአብሔር የቀ ረበው ልመና እንደሚያሳየው በመዝሙረኛው ላይ ጠላት መሆን ማለት በእስራኤል ላይ ጠላት መሆን ማለት ነው። *ተነሥ፤* የ7፥6 ማብ ይመ። *አትማራቸው፤* የ5፥10 ማብ ይመ። *በተንኰላቸው፤* አንዳንድ እስራኤላውያን ከጠላት ወገን በመሆን እነርሱም ጠላ ቶች ስለ መሆናቸው ግልጽ አይደለም፤ የዕብራይስጡ ቃል የሚያ ሳየው ግን "ተንኰለኞች" መሆናቸውን ብቻ ነው።

*59፥6-8፤* የሚታመነው በጌታ ብቻ ነው፤ እግዚአብሔር እንዲህ ያሉ የአራዊት መንጋዎችን በእርግጥ ያዋርዳቸዋል/ያላ ግጥባቸዋል (22፥16-17 ይመ)።

59፥6 *ከተማዪቱም ...፤* ምግብ ፍለጋ ሌሊት እንደሚዞሩ ውሾች ከተማዋን በዘበዙ (ቍ14-15 ይመ)።

59፥7 *ከከንፈራቸው ሰይፍ፤* የእነርሱ "መርገምና ውሸት" (ቍ 12) ነው። ይህ አባባል ምን ምስል ከሣች ትርጕም እንዳለው 57፥4 ይመ፤ እንዲሁም የ5፥9 ማብ ይመ። *ይላሉ፤* የ3፥2 ማብ ይመ።

59፥9 *እጠብቃለሁ፤* የቍ17 ማብ ይመ። ንጋትን (ደኅን ነትን) በናፍቆት እንደሚጠባበቅ ሰው መዝሙረኛውም በናፍቆት ይጠባበቃል፤ 130፥6 ይመ።

*59፥10-13፤* እንደ ገና በአዲስ መልክ የቀረበ ጸሎት ነው፤ መዝሙረኛው ጌታ ጸሎቱን እንደሚሰማና (ቍ10) መንግሥታ ትንም እንደሚቀጣ (ቍ5) እርግጠኛ ነው፤ እግዚአብሔር ድን ገት ጠራርጎ እንዲያጠፋቸው ሳይሆን፣ የሥቃይ ዘመናቸው አራ ዝሞ እንዲቀጣቸው መዝሙረኛው ይጸልያል፤ ይህንንም ያደረ ገው እስራኤል ("ሕዝቤ" ቍ11) ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ እንዳ ደረገችው (78፥11፤ 106፥13 ይመ) የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ እንዳትዘነጋ ነው። ሆኖም ጠላቶቹ በሐሰት ባደረሱበት በደል የእጃቸውን ሳያገኙ እንዳይቀሩ እግዚአብሔርን ይለምናል (ቍ12-13)።

59፥10 *በምሕረቱ፤* የ6፥4 ማብ ይመ።

*59፥11፤* የክፉዎች ቅጣት፣ ኀጢአት በእግዚአብሔር ፊት ምን ያህል አስጸያፊ እንደ ሆነ ያሳያል፤ በተለይም አንድ የማይ ረጋ ምላስ ጌታን ምን ያህል እንደሚያስቈጣ ትምህርት እንዲ ሆን ዳዊት ለመነ። *ጋሻችን፤* የ3፥3 ማብ ይመ። *አንከራታቸው፤* ማረፊያ እንደ ሌላቸው ወሮበሎችና (ዘፍ4፥12፤ 2ሳሙ15፥20፤ ሰቆ 4፥15) ምግባቸውን እንደሚያድኑ ውሾች ይሁኑ ማለት ነው (ቍ15፤ 109፥10፤ አሞ4፥8 ይመ)።

12ከአፋቸው ስለሚወጣው ኀጢአት፣
ከከንፈራቸውም ስለሚሰነዘረው ቃል፣
በትዕቢታቸው ይያዙ::
ስለ ተናገሩት መርገምና ውሸት፣
13በቍጣ አጥፋቸው፤
ፈጽመህም አስወግዳቸው፤
በዚህም እግዚአብሔር የያዕቆብ ገዥ መሆኑ፣
እስከ ምድር ዳርቻ ይታወቃል:: ሴላ
14እንደ ውሻ እያላዘኑ፣
በምሽት ተመልሰው ይመጣሉ፤
በከተማዪቱም ዙሪያ ይራወጣሉ::
15ምግብ ፍለጋ ይራወጣሉ::
ካልጠገቡም ያላዝናሉ::
16እኔ ግን ስለ ኀይልህ እዘምራለሁ፤
በማለዳም ስለ ምሕረትህ እዘምራለሁ፤
አንተ መጠጊያዬ፣
በመከራም ቀን ዐምባዬ ነህና::
17ብርታቴ ሆይ፤ ውዳሴ አቀርብልሃለሁ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ መጠጊያዬ፣
የምትወደኝም አምላኬ ነህና::

## መዝሙር 60
## ከሽንፈት በኋላ የቀረበ ብሔራዊ ጸሎት

60፥5-12 ተጓ ምብ-መዝ108፥6-13

59፥12 መዝ10፥7፤ 64፥8፤ምሳ10፥14፤12፥13፤ኢሳ2፥12፤5፥15፤ሶፎ3፥11
59፥13 መዝ83፥18፤104፥35
59፥15 ኢዮ15፥23
59፥16 ዘዳ4፥30፤ 1ሳሙ2፥10፤2ሳሙ22፥3፤መዝ5፥3፤88፥13፤ 101፥1፤108፥1
59፥17 ቍ10
60 ርዕስ2ሳሙ8፥13
60፥1 2ሳሙ5፥20፤መዝ44፥9፤79፥5፤ 80፥3
60፥2 2ዜና7፥14፤ መዝ18፥7
60፥3 መዝ71፥20፤ 75፥8፤ኢሳ29፥9፤51፥17፤63፥6፤ኤር25፥16፤ዘካ12፥2፤ራእ14፥10
60፥4 ኢሳ5፥26፤ 11፥10፡12፤18፥3
60፥5 ዘዳ33፥12፤ ኢዮ40፥14

ለመዘምራን አለቃ፤ "የኪዳን ጽጌረዳ":: በሚለው ቅኝት የሚዘመር፤[a] በሰሜናዊ ምዕራብ መስጴጦምያና[b] በማእከላዊ ሶርያ የሚኖሩትን አራማውያን[c] በወጋቸው ጊዜ፣ ኢዮአብም ተመልሶ በጨው ሸለቆ አሥራ ሁለት ሺህ ኤዶማውያንን በፈጀ ጊዜ፣ ለትምህርት፤ የዳዊት ቅኔ

1እግዚአብሔር ሆይ፤ ጣልኸን፤ አንኰታኰትኸን፤
ተቈጣኸንም፤ አሁን ግን መልሰህ
አብጀን::
2ምድሪቱን አናወጥሃት፤ ፍርክስክስ
አደረግሃት፤
ትንገዳገዳለችና ስብራቷን ጠግን::
3ለሕዝብህ አበሳውን አሳየኸው፤
ናላ የሚያዞር የወይን ጠጅ
እንድንጠጣም ሰጠኸን::
4ነገር ግን ከቀስት እንዲያመልጡ፣
ለሚፈሩህ ምልክት አቆምህላቸው:: ሴላ
5ወዳጆችህ ይድኑ ዘንድ፣
በቀኝ እጅህ ርዳን፤ መልስም ስጠን::

[a]ርእሱ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል::
[b]ርእሱ የአራማውያን ወይም የሰሜን ምዕራብ መስጴጦምያ ነው::
[c]ርእሱ በመካከለኛው ሶርያ የሚገኙት አራማውያንን የሚያመለክት ነው::

*59፥12፤* የቍ7 ማብ ይመ:: *በትዕቢታቸው፤* በጌታ ባሪያና በሕዝቡ ላይ ያሜሩት ሜራ ወጥመድ ሆኖ ይያዛቸው:: *መርገምና ውሸት፤* 10፥7 እና ማብ ይመ::

59፥13 *በዚህም ... ይታወቃል፤* እግዚአብሔር የእስራኤልን ጠላት ልክ ሲያስገባ የእስራኤል አምላክ የምድር ሁሉ ፈራጅ (58፥11ይመ) መሆኑን ዓለም ሁሉ ያውቃል:: *የያዕቆብ፤* የ14፥7 ማብ ይመ::

*59፥14-16፤* ጸሎቱ እንደሚሰማ እርግጠኛ ነው (የ3፥8 ማብ ይመ):: እግዚአብሔር በእምቢተኞች ውሾች ላይ እንደሚያፌዝ ሁሉ (ቍ6-8) መዝሙረኛውም እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ድል በማድረጉ በሐሤት ይዘምራል::

59፥16 *ኀይልህ ... ምሕረትህ ... መጠጊያዬ፤* አዝማቹን ይመ (ቍ9:17):: *በማለዳም፤* መግቢያውን ይመ::

*59፥17፤* መዝሙረኛው ውዳሴ ለማቅረብ ስእለት አቀረበ (የ7፥17 ማብ ይመ):: *እዘምራለሁ፤* በዕብራይስጥ "ዛማር"፤ የቍ9 ማብ ይመ:: በጨለማ በፍርሀት ውስጥ ሆኖ ይጠባበቅ ነበር፤ አሁን ግን በደኅንነት ንጋት ይዘምራል::

*መዝ60* ከውጭ ጠላት ምናልባትም ከኤዶምያስ (ቍ9 ይመ) ብርቱ መከራ ከደረሰባቸው በኋላ እግዚአብሔር እንዲታደጋቸው በሕዝቡ ሁሉ የቀረበ ጸሎት ነው:: በ2ዜና ም20 ላይ እንዳለው ሁሉ የዚህ ጸሎት መሪ ንጉሡ ራሱ (ቍ9) ሊሆን ይችላል:: ይህ መዝሙር እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደተወና (ቍ1) ከእንግዲህም በኋላ ከሰራዊታቸው ጋር አብሮ እንደማይወጣ ስለሚናገር ከመዝ44 ጋር ትስስር አለው:: ቍ5-12 እንደ ገና በ108፥6-13 ላይ ተጽፎ ይገኛል:: ባወቃቀር ደረጃ ይህ ጸሎት የተቀነበበው እግዚአብሔር ሕዝቡን በመተዉ ሕዝቡ በሚያሰማው ጩኸትና (ቍ1-3) እግዚአብሔር ሕዝቡን ቢተውም በጠላቶቻቸው ላይ ግን ድል እንደሚሰጣቸው በሚገልጸው የእምነት ቃል ነው (ቍ10-12):: ከጩኸትና ከልቅሶ ወደ ጽኑ መታመን የተደረገው ሽግግር የጸሎቱ ማእከላዊ ሐሳብ ነው:: ቍ4-8 እግዚአብሔር ፈጥኖ እንዲደርስለት ልመና ያቀረበበት ክፍል ሲሆን (ቍ5) ጽኑ መታመኛውም ይሄው ነው (ቍ4:6-8)::

*60ርእስ፤* የመዝ56 ርእስ ማብ ይመ:: *የቃል ኪዳን አበባ፤* የመዝ80 ርእስ እንዲሁም የመዝ45 ርእስ ማብ ይመ:: *ለትምህርት፤* ይህ ቃል በመዝሙረ ዳዊት ርእሶች ላይ ተጠቅሶ የሚገኘው እዚህ ላይ ብቻ ነው:: እስራኤል መማር ያለባትን ሌሎች መዝሙሮች በዘዳ31፥19:21፤ 2ሳሙ1፥18 ላይ ይመ:: መዝሙሩ ለተለያየ አገልግሎት በተለይም አገር አቀፍ ጥቃት በደረሰባቸው ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ እንደሚታመኑ ለመግለጽ የታሰበ ነው፤ አገልግሎቱም በመዝሙር 108 ላይ ተመልክቶአል:: *ጊዜ፤* እዚህ ላይ የተወሣው ታሪክ በ2ሳሙ8፤ 1ዜና18 (እንዲሁም ምናልባት በ2ሳሙ10) ላይ ተጠቅሶአል:: በሰሜን በኩል ከባድ ጦርነት ይካሄድ በነበረበት ሰዓት እስራኤላውያን ከኤዶምያስ ጋር ያደረጉት ጦርነት የኤዶምያስን ተንኰል የሚያሳይ ነው፤ ኤዶምያስ የእስራኤልን ግዛት ከፍሎ ለመውሰድ ያሰበ ይመስላል፤ ኤዶምያስ በከፈተው ጦርነት ስለቀናው የይሁዳን ደቡባዊ ድንበር ለመውሰድ ችሎአል::

*60፥1-3፤* እግዚአብሔር ሕዝቡን በመተዉ የቀረበ ልቅሶና (44፥9-16፤ 89፥38-45 ይመ) ሕዝቡን እንደ ገና እንዲጐበኝ የቀረበ ጸሎት ነው::

60፥1 *ተውኸን፤* ቢያንስ ለጊዜው ፊቱን ከሕዝቡ ሰውሮአል (30፥5 ይመ):: የሕዝቡ ድል መደረግ የተወሰደው እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደተቈጣ ተደርጎ ነው (ሆኖም እግዚአብሔር የተቈጣበት ምክንያት አልተጠቀሰም፤ ደግሞም በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል ያለው ግንኙነት አልተቋረጠም):: *አንኰታኰትኸን፤* ጐርፍ እንደሚያፈራርሰው አንተም እንዲሁ አፈራረስኸን ማለት ነው (2ሳሙ5፥20 ይመ)::

60፥2 *ምድሪቱን አንቀጠቀጥሃት፤* ምድርን እንደሚያናውጥ የመሬት መንቀጥቀጥ ማለት ነው፤ ምድርን የሚገለብጥ የመሬት መንቀጥቀጥ በጥንት ከነዓን ዐልፎ ዐልፎ ይከሠት ነበር::

60፥3 *ራስ የሚያዞር የወይን ጠጅ፤* እግዚአብሔር ከበረከትና ከደኅንነት ጽዋው ሳይሆን፣ ከቍጣው ጽዋ እንዲጠጡ አደረጋቸው (የ16፥5 ማብ ይመ)::

*60፥4-8፤* እግዚአብሔር ፈጥኖ እንዲደርስለት ያቀረበው ልመና ሲሆን ልመናውን እግዚአብሔር እንደሚሰማ እርግጠኛ ነው::

60፥4 *ለሚፈሩህ፤* የሚፈሩት አሕዛብ ሳይሆኑ የእርሱ ሕዝብ ናቸው (61፥5፤ እንዲሁም የዘፍ20፥11 ማብ ይመ):: *አቆምህላቸው፤* በቍ5 ላይ የተጠቀሰው ልመና በቍ4 ላይ ጀምሮአል:: *ምልክት፤* የጦር ሰራዊት ለጦርነት እንዲዘጋጅና ሰራዊቱን ለመምራት ያገለግላል:: ይህም በኢሳይያስና (5፥26፤ 11፥10:12፤ 13፥2፤ 18፥3፤ 30፥17፤ 49፥22፤ 62፥10) በኤርምያስ (4፥21፤ 50፥2፤ 51፥12:27) ላይ ተጠቅሶአል:: ቍ4ን እንደ ልመና ቃል መቍጠር ይቻላል፤ ልመናው እግዚአብሔር የእስራኤልን ሰራዊት እንዲመራና በጠላቶቻቸው ላይ ድል እንዲሰጣቸው የሚጠይቅ ነው:: *ቀስት፤* ጠላት የታጠቀው ቀስት ነው::

60፥5 *ወዳጆችህ፤* በ127፥2፤ በ2ሳሙ12፥25፤ በኤር 11፥15 ላይ እንደ ተጠቀሰው ሁሉ እዚህ ላይ የተጠቀሰው ቃል ልዩ መውደድን ያመለክታል::

*60፥6-8፤* ከጌታ ዘንድ የመጣ የሚያጽናና ቃል ነው፤ ምናልባት ከዚህ በፊት ከተገኘው ድል ላይ የተወሰደ ቃል ሳይሆን አይቀርም፤ እንዲህ ከሆነ ቃሉ/ታሪኩ "በእግዚአብሔር የጦርነት መጽሐፍ" (ዘኍ21፥14) ላይ ሳይጻፍ አይቀርም:: በእስራ

[6]እግዚአብሔር ከመቅደሱ እንዲህ ሲል
ተናገረ፤
"ደስ እያለኝ የሴኬምን ምድር
እሸነሽናለሁ፤
የሱኮትን ሸለቆ አከፋፍላለሁ።
[7]ገለዓድ የእኔ ነው፤ ምናሴም የእኔ ነው፤
ኤፍሬም የራስ ቍሬ ነው፤
ይሁዳም በትረ መንግሥቴ ነው።
[8]ሞዓብ የመታጠቢያ ገንዳዬ ነው፤
በኤዶምያስ ላይ ጫማዬን እወረውራለሁ፤
በፍልስጥኤም ላይ በድል እልል
እላለሁ።"
[9]ወደ ተመሸገው ከተማ ማን ያመጣኛል?
ማንስ ወደ ኤዶምያስ ይመራኛል?
[10]እግዚአብሔር ሆይ፤ የጣልኸን አንተ
አይደለህምን?
እግዚአብሔር ሆይ፤ ከሰራዊታችን ጋር
እኮ አልወጣ አልህ!
[11]በጠላት ላይ ድልን አቀዳጀን፤
የሰው ርዳታ ከንቱ ነውና።
[12]በእግዚአብሔር ክንደ ብርቱ እንሆናለን፤
ጠላቶቻችንን የሚረጋግጥልን እርሱ
ነውና።

60፥6 ዘፍ12፥6፤ 33፥17
60፥7 ዘፍ41፥52፤ 49፥10፤ዘኍ34፥19፤ ኢሱ13፥31
60፥8 2ሳሙ8፥1
60፥10 ኢሱ7፥12
60፥11 መዝ146፥3፤ምሳ3፥5
60፥12 ኢዮ40፥12፤ መዝ44፥5
61፥1 መዝ4፥1፤ 64፥1፤86፥6
61፥2 መዝ6፥2፤ 18፥2፤31፥2፤94፥22
61፥3 መዝ9፥9፤ 46፥1፤59፥9፤62፥7፤ ምሳ18፥10

## መዝሙር 61

### የግዞተኛ ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች የሚዘመር፤ የዳዊት መዝሙር*

[1]እግዚአብሔር ሆይ፤ ጩኸቴን ስማ፤
ጸሎቴንም አድምጥ።
[2]ልቤ በዛለ ጊዜ፣
ከምድር ዳርቻ ወደ አንተ እጣራለሁ፤
ከእኔ ይልቅ ከፍ ወዳለው ዐለት ምራኝ።
[3]አንተ መጠጊያዬ፣
ከጠላትም የምተገንብህ ጽኑ ግንብ

ኤል ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር የሚታየው የእስራኤል ድል ነሺ መለኮታዊ ተዋጊ ሆኖ ነው (ዘፀ15፥3፡13-18 ይመ)።

60፥6 *እሸነሽናለሁ ... አከፋፍላለሁ፤* በጦር ሜዳ ከእርሱ ጋር ከነበሩ አገልጋዮቹ ጋር ድል ያደረጋቸውን ግዛቶች ይከፋፍላል። *የሴኬምን ... የሱኮትን፤* ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብና በስተ ምሥራቅ የሚገኙ ግዛቶችን የሚወክሉ ሲሆን እነዚህን ግዛቶች እስራኤልና ጌታ የራሳቸው ገንዘብ አድርገው ወስደዋቸዋል (ዘፍ 33፥17-18፤ 1ነገ12፥25 ይመ)።

*60፥7፤* እስራኤል የጌታ ሕዝብ ናት፤ ድል አድርገው የያዙት ምድርና በዚያ ምድር እንዲሰፍር የተደረገው ሕዝብ ሁሉ የእርሱ ነው። *ገለዓድ ... ምናሴም፤* እኩሌታው የምናሴ ነገድ ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ በሚገኘው በገለዓድ ምድር እንዲኖር ሲደረግ ቀሪው እኩሌታ ነገድ ደግሞ ከኤፍሬም በስተ ሰሜን፣ ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ እንዲኖር ተደርጓአል (ኢሱ13፥29-31፤ 17፥5-11 ይመ)። *ኤፍሬም ... ይሁዳም፤* ሁለቱ የእስራኤል ታላላቅ ነገዶች ሲሆኑ አንደኛው በስተ ሰሜን በኩል የራሔል ነገዶች (የኤፍሬም) ወኪል ሲሆን ሌላው ደግሞ በስተ ደቡብ በኩል የልያ ነገዶች (የይሁዳ) ወኪል ነው። ዘፍ48፥13-20፤ 49፥8-12፤ ዘኍ 2፥3፡18፤ ኢሱ15-16 ይመ። ሁለቱ በአንድነት መላውን የእስራኤልን ነገድ ይወክላሉ (ኢሳ11፥13፤ ዘካ9፥13)። *የራስ ቍሬ፤* የኤፍሬም ነገድ ኀይለኛና ሞገደኛ ነገድ በመሆኑ (ዘዳ33፥17፤ መሳ7፥24-8፥3፤ 12፥1) እዚህ ላይ ዘይቤያዊ በሆነ መንገድ የእግዚአብሔርን የራስ ቍር ወክሎአል ገብቶአል። *በትረ፤* እንዲህ የተባለው ከይሁዳ ነገድ ስለሚመጣና (ዘፍ49፥10) አሁንም ስለመጣ (1ሳሙ16፥1-13) ነው፤ እርሱም የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚገዛ በእግዚአብሔር የተመረጠ ንጉሥ ነው (2ሳሙ7 ይመ)።

60፥8 *ሞዓብ ... በኤዶምያስ ... በፍልስጥኤም፤* ከእስራኤል ምሥራቃዊ፣ ደቡባዊና ምዕራባዊ ወሰን ዙሪያ የሚገኙ ሕዝቦች ሲሆኑ የእስራኤል ቋሚ ጠላቶች ናቸው (ዘፀ15፥14-15፤ እንዲሁም ዘፀ13፥17፤ ዘኍ20፥14-21 ይመ)። *የመታጠቢያ ገንዳዬ፤* በቤት ውስጥ የሚያገለግል እቃ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን ጌታ እግሩን ይታጠብበታል (ዘፍ18፥4)። ይህ ተለዋጭ ዘይቤ እዚህ ላይ ሊቀርብ የቻለው ሞዓብ ከሙት ባሕር በስተ ምሥራቅ በኩል በመገኘቱ ሳይሆን አይቀርም። *ጫማዬን እወረውራለሁ፤* ምናልባት አንድ ሰው የመሬት ባለቤትነቱን ለመግለጽ የሚጠቀምበት የተለምዶ ዘይቤ ሳይሆን አይቀርም (ከሩት4፥7 ጋር ያነጻጽሩ)።

*60፥9፤* መልስ አዘል ጥያቄ ሲሆን በቍ10-12 ላይ የተነገረውን የእምነት ቃል ያሳያል። *ያመጣኛል ... ይመራኛል፤* ምናልባት ራሱን ንጉሡን ሳይሆን አይቀርም (የመዝ60ን መግቢያ ይመ)፤ ሆኖም መላውን ሕዝብ ሊያመለክትም ይችላል (የመዝ30 ርእስ ማብ ይመ)። *ይመራኛል፤* እስራኤላውያን በምድረ በዳው ጕዞ ላይ ሳሉ እግዚአብሔር ከፊት ሆኖ ይመራቸውና (ዘፀ13፥21) የተስፋዪቱን ምድር ለመውረስ ሲገሠግሡ በገጠማቸው ፍልሚያ ሁሉ ውስጥ ጣልቃ እየገባ ይታደጋቸው እንደ ነበረ ማለት ነው (ዘፀ23፥27-28፤ 33፥2፤ ዘዳ9፥3፤ 31፥8)።

*60፥10-12፤* ድል እንደሚያገኝ እርግጠኛ ሆኖ የተናገረበት ክፍል ነው (የ3፥8 ማብ ይመ)።

60፥10 *የጣልኸን፤* ቍ1 ይመ።

60፥11 *ርዳታ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "አድነን" ማለት ነው (በቍ5 ላይ "ይድኑ ዘንድ" የሚለውን ይመ)። *የሰው፤* 33፥17 ይመ።

60፥12 *ድልን አቀዳጀን፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "ታላቅ ሥራ እናከናውናለን" ማለት ነው፤ በእግዚአብሔር ርዳታ እስራኤል እግዚአብሔር ያከናወነውን ዐይነት ታላቅ ሥራ ታከናውናለች (118፥15-16 ይመ)፤ በኤዶምያስም ላይ ድልን ትቀዳጃለች (በዘኍ24፥18 ላይ "በኀይል ያድጋል" የሚለውን ይመ)። *የሚረጋግጥልን፤* ድል እንደ ተቀዳጀ ሰራዊት ማለት ነው (ኢሳ 14፥19፡25፤ ኤር12፥10፤ ዘካ10፥5 ይመ)።

*መዝ61፤* እግዚአብሔር እርሱ ባለበት ስፍራ የእርሱ የሆነውን ሰው እንዲሰበስብ የቀረበ ጸሎት ነው። በመዝሙሩ ውስጥ የተወሣው ሁኔት በመዝ42-43 ላይ ከተወሣው ሁኔት ጋር ተመሳሳይ ነው። እዚህ ላይ ግን ስለ አንድ ንጉሥ ተጠቅሶአል (ቍ6)፤ የዚህ መዝሙር ጸሓፊ ዳዊት ከሆነ፣ ዳዊት ይህንን ጸሎት የጻፈው ከአቤሴሎም በሸሸ ጊዜ ሊሆን ይችላል (2ሳሙ 17፥21-29 ይመ)። ከዚህ የተለየ ሐሳብ ለማግኘት የቍ2 ማብ ይመ። መዝ61-64 በሚያስፈራ ሁኔታ ውስጥ በእግዚአብሔር መታመን ተገቢ ነው በሚለው አንድ የጋራ ዐቢይ ሐሳብ ተሳስረዋል። ባወቃቀር ደረጃ ሲታይ ጸሎቱ የተቀነበበው እግዚአብሔር ጩኸቱን እንዲያደምጥ በሚያሳስብ ቃልና (ቍ1) እግዚአብሔርን እንደ ሚያመሰግን ስእለት መሳሉን በሚያሳይ ቃል ነው (ቍ8)። የመዝሙሩ ዋና ክፍል በሦስት ጥንድ ጥንድ አንጓዎች የተዋቀረ ነው፤ ቍ2-3፡4-5፡6-7።

*61ርእስ፤* የመዝሙር 4 ርእስ ማብ ይመ።

*61፥1፤* እግዚአብሔር ጸሎቱን እንዲሰማ በመግቢያው ላይ ያቀረበው ልመና ነው።

*61፥2-3፤* ጸሎት ነው።

61፥2 *ከምድር ዳርቻ፤* በቍሙ ሲታይ የሚሰጠው ትርጕም ይህንን ይመስላል (42፥6 ይመ)፤ እዚህ ላይ ሐረጉ የሚያመለክተው ከሙታን ዓለም ማለትም ከመቃብር ጫፍ ላይ (63፥9 ይመ) የሚለውን ሊሆን ይችላል፤ መዝሙረኛው ሊሞት የተቃረበ መስሎታል። *ልቤ፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *ምራኝ፤* 23፥2 ይመ። *ዐለት፤* አስተማማኝ ስፍራ ማለት ነው (27፥5፤ 40፥2 ይመ)። *ከእኔ ይልቅ፤* ሊያገኘው የሚመኘውን አስተማማኝ ስፍራ ሊደርስበት አይችልም። ይህን ስፍራ ሊሰጠው የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፤ እግዚአብሔር "መጠጊያ ዐምባ" (31፥2፤ 71፥3፤ እንዲሁም18፥2፤ 62፥2፡6-7፤ 94፥22 ይመ) እንደ ሆነ በመዝሙረኞቹ አንደበት ብዙ ጊዜ ቢነገርም እዚህ ላይ ከፍ ያለው "ዐለት" ራሱ እግዚአብሔር ሳይሆን አይቀርም፤ መዝሙረኞቹም የሚጮኹት ወደዚህ ከፍ ወዳለው መጠጊያና ዐምባ ነው (ቍ3 ይመ)። ወይም ደግሞ ይህ ከፍ ያለው ዓለም የማይናወጠው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሊሆን ይችላል (ቍ4፤ እንዲሁም 27፥5 ይመ)።

*61፥3፤* ልመናውን ያቀረበበት ምክንያት በግልጽ ተጠቅሶአል፤ እግዚአብሔር አንድም ጊዜ ትቶት አያውቅም። *ከጠላትም፤* ይህን ጸሎት ያቀረበው በሞት ተከቦ ከሆነ፣ አሁን እያስጨነቀው ያለው ጠላት ሞት ነው (68፥20፤ 141፥8፤ ኢዮ33፥22፤ ኢሳ 25፥8፤ 28፥15፤ ኤር9፥21፤ ሆሴ13፥14፤ እንዲሁም 1ቆሮ15፥26 ይመ) የ49፥14 ማብ ይመ።

ሆነኸኛልና።

4በድንኳንህ ለዘላለም ልኑር፤
በክንፎችህም ጥላ ልከለል። ሴላ

5አምላክ ሆይ፤ ስእለቴን ሰምተሃልና፤
ስምህን የሚፈሩትንም ሰዎች ርስት
ለእኔ ሰጠህ።

6የንጉሡን ዕድሜ አርዝምለት፤
ዘመኑንም እስከ ብዙ ትውልድ
ጨምርለት፤

7በእግዚአብሔር ፊት ለዘላለም ይንገሥ፤
ይጠብቁት ዘንድ ምሕረትህንና
ታማኝነትህን አዘጋጅለት።

8ስለዚህ ለስምህ ዘወትር ውዳሴ አቀርባለሁ፤
ስእለቴንም በየጊዜው እፈጽማለሁ።

## መዝሙር 62

### ተስፋ በእግዚአብሔር ላይ ብቻ

*ለመዘምራን አለቃ፤ ለኤዶታም፤ የዳዊት መዝሙር*

1ነፍሴ ዕረፍት የምታገኘው በእግዚአብሔር
ብቻ ነው፤
ድነቴም የሚመጣልኝ ከእርሱ ዘንድ
ነው።

2ዐለቴና መድኀኒቴ እርሱ ብቻ ነው፤
መጠጊያዬም እርሱ ነው፤ ከቶም
አልናወጥም።

3ሰውን የምታጠቁት እስከ መቼ ነው?
ይህን የዘመመ ግድግዳ፣ የተንጋደደ
ዐጥር፣
ሁላችሁ ገፍታችሁ ልትጥሉት
ትሻላችሁ?

4ከታላቅ ክብሩ ሊያዋርዱት፣
ይህን አንድ ነገር ወጠኑ፤
ሐሰት ባለበት ነገር ደስ ይሰኛሉ፤
በአፋቸው ይመርቃሉ፤
በልባቸው ግን ይራገማሉ። ሴላ

5ነፍሴ ሆይ፤ ዐርፈሽ እግዚአብሔርን ብቻ
ጠብቂ፤
ተስፋዬ ከእርሱ ዘንድ ነውና።

6ዐለቴና መድኀኒቴ እርሱ ብቻ ነው፤
መጠጊያዬም እርሱ ነው፤ እኔም
አልናወጥም።*

7መዳኔና ክብሬ በእግዚአብሔር ነው፤
ብርቱ ዐለቴና መሸሸጊያዬ በእግዚአብሔር

61፥4 ዘዳ32፥11፤ መዝ15፥1፤ ማቴ 23፥37
61፥5 ዘፀ6፥3፤ ዘኍ 30፥2፤ ዘዳ33፥9፤ ነህ 1፥11፤ መዝ56፥12፤ 102፥15፤ ኢሳ59፥19፤ ማቴ6፥9
61፥6 1ነገ3፥14፤ መዝ21፥4
61፥7 መዝ40፥11፤ 41፥12፤ ሉቃ22፥69፤ ኤፌ1፥20፤ ቈላ3፥1
61፥8 ዘፀ15፥1፤ ዘኍ 30፥2፤ ዘዳ23፥21፤ መዝ 7፥17፤ 30፥4
62፥1 ቍ5፤ መዝ 5፥3
62፥2 ዘፀ15፥2፤ ኢዮ 29፥18፤ መዝ18፥31፤ 5 9፥9፤ 89፥26
62፥3 ኢሳ30፥13
62፥4 መዝ28፥3፤ 55፥21
62፥5 ቍ1
62፥7 መዝ61፥3

**6 ወይም *ልዑል እግዚአብሔር ድነቴና ክብሬ ነው*

*61፥4-5፤* ዐምባ ሊሆንለት በሚችለው በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ መኖር ይፈልጋል (27፥5 እና ማብ ይመ)።

61፥4 *በድንኳንህ፤* በመኖ ሪያህ ማለት ነው (2ሳሙ6፥17፤ 7፥2፤ 1ነገ1፥39፤ 2፥28-30 ይመ)። *ልኑር፤* የ15፥1 ማብ ይመ። *በክንፎችህም ጥላ፤* የ17፥8 ማብ ይመ።

*61፥5፤* ተስፋ የሚያደርግበት ምክንያት በግልጽ ተጠቅሶ አል፤ መዝሙረኛው (1) አንድም ከዚህ በፊት እግዚአብሔር ጸሎቱን መልሶለታል፤ ወይም (2) ምኞቱን እውን እንደሚያደ ርግለት እርግጠኛ ሆኖአል። *ስእለቴን፤* ጸሎቱን ያቀረበው ከስእለት ጋር ነው (50፥14፤ 66፥14፤ እንዲሁም የ7፥17 ማብ ይመ)። *ርስት፤* በተስፋዪቱ ምድር ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር የሚገኝ ስፍራ ሲሆን፣ ጌታ ተስፋ ከሰጣቸውና የእርሱ ከሆኑት ወገኖች ጋር የሚጋሩት መኖሪያ ነው (16፥6፤ 37፥18፤ 136፥21-22 ይመ)። *የሚፈሩትንም፤* 60፥4 እና ማብ ይመ። *ስምህን፤* የ5፥11 ማብ ይመ።

*61፥6-7፤* ንጉሡ ረጅም ዕድሜ እንዲኖር የቀረበ ጸሎት ነው፤ ይህን ጸሎት ያቀረበው ራሱ ንጉሡ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ደግሞ ሕዝቡ በካህናቱ ወይም በሌዋውያኑ በኩል ያቀረበው ጸሎት ሊሆን ይችላል፤ አንዳንድ የአይሁድ ሊቃውንት ይህ ክፍል የሚናገረው ስለ መሲሑ ነው የሚል አስተያየት አላቸው። በዚህ ክፍል የተነገረው ሐሳብ በታላቁ በዳዊት ልጅ በክርስቶስ ኢየሱስ አማካይነት ተፈጽሞአል።

*61፥6፤* ንጉሡ ለዘላለም ይኑር ማለት ነው (የ45፥6 ማብ ይመ)።

61፥7 *በእግዚአብሔር ፊት ... ይንገሥ፤* የ41፥12 ማብ ይመ። *ምሕረትህና ታማኝነትህ፤* የእግዚአብሔር መልክተኞች ሆነው በሰውኛ አገላለጽ ቀርበዋል (የ23፥6፤ የ43፥3 ማብ ይመ፤ እንዲሁም የ26፥3 ማብ ይመ)።

*61፥8፤* ውዳሴ ለማቅረብ ስእለት ተሳለ (የ7፥17 ማብ ይመ)።

*መዝ62፤* መዝሙረኛው ከዙፋኑ እንዲወርድ የሚመኙ ሤረኞች እጅግ ባስጨነቁት ጊዜ ራሱን ለእግዚአብሔር አሳልፎ ሰጠ። የዚህ መዝሙር ደራሲ ንጉሥ የነበረ ሰው ነው፤ ደራሲው ዳዊት ከሆነ ደግሞ ወቅቱ የሳኦል ቤተሰቦች እርሱን ከዙፋን ለማ ውረድ የተራወጡበት ጊዜ ሊሆን ይችላል። ቍ3 ዐቅም ያጣበት ጊዜ እንደነበር የሚናገር ሲሆን ይህም ዕርጅና እንደ ተጫጫነው ሊያመለክት ይችላል። መዝሙሩ በቀጥታ አይሁን እንጂ እግዚ አብሔር ብርታትን እንዲሰጥ የቀረበ ልመና ነው። በእግዚአብሔር ላይ መታመን ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ በማሳየት ረገድ ይህ መዝሙር አቻ የለውም (መዝ31 እና የመዝ61ን መግቢያ ይመ)። መዝሙሩ ሦስት ክፍሎች አሉት፤ ቍ1-4፣ 5-8፣ 9-12። በቍ1-2 ላይ የተጠቀሰውን ሐሳብ የሚያስተጋባው የመዝሙሩ መካከ ለኛ አንጓ (ቍ5-8) በእግዚአብሔር በመታመንና እርሱን ተስፋ በማድረግ ላይ ያተኩራል። መዝሙሩ የተቀነበበው በእግዚአብሔር መታመን የሚያስገኘውን ዕረፍት በሚገልጸው ሐረግና (ቍ1-2) በእርሱ መታመን የሚያስፈልግበትን ምክንያት በሚናገረው ሐረግ ነው (ቍ11-12)። የቀሩት ቍጥሮች የሚናገሩት (ቍ3-4፡9-10) ስለሚያስፈራሩት ሰዎች ነው።

*62ርእስ፤* የመዝ 39 ርእስ ማብ ይመ።

*62፥1-4፤* ሤራ ባሤሩበት ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ያሳየ ውን መታመን የሚገልጽ ክፍል ነው።

62፥1 *ድነቴም የሚመጣልኝ ከእርሱ ዘንድ ነው፤* ይህ መዝሙር የእግዚአብሔር ሕዝቦች ፈተና በበዛበት ሕይወት ውስጥ እንዴት መኖር እንዳለባቸው መልካም ምክር ይሰጣል። ችግር መከራና ተቃውሞ ከጠላቶቻችን በተሰነዘረብን ጊዜ አዳኛችንና የዘላለም መጠጊያችን ወደ ሆነው መመለስ አስፈላጊ ነው፤ እያን ዳንዱ አማኝ እንዲህ ለማለት መብቃት አለበት፤ (1) በእግዚ አብሔር ላይ ያለኝን መታመን መከራም ሆነ ሥቃይ ከቶ አያ ላላውም (ቍ2፡6)፤ ከእርሱ ዘንድ ያገኘሁት ደኅንነት ብቻ አይ ደለም፤ እርሱ ራሱ ዐለቴ፣ ድነቴና መጠጊያዬ ነው (ቍ6-7)። (2) ጭንቀትና ፍርሀት በገጠመኝ ጊዜ ሁሉ ራሴን ለእርሱ እሰጣለሁ፤ ምስጢሬን ሁሉ አዋየዋለሁ (ፊል4፥6 እና ማብ ይመ)። (3) በችግሬ ሁሉ እርሱ በርኅራኄና በፍቅር እንደሚደርስልኝ ስለ ማውቅ እርሱ ራሱ ስለ እኔ እንዲቆምልኝ በትዕግሥት እጠ ባበቃለሁ።

62፥1 *ነፍሴ፤* የ6፥3 ማብ ይመ። *ዕረፍት የምታገኘው፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "እፎይ ብላ የምታርፈው" ማለት ነው።

62፥2፡6 *አልናወጥም፤* የ10፥6 ማብ ይመ።

*62፥3፤* ሤራ ለሚዶልቱበት ሰዎች የቀረበ ጥያቄ ነው፤ ጥያቄውም ከቶ አይበቃችሁም? የሚል ነው። *የዘመመ ግድ ግዳ ... የተንገዳገደ ዐጥር፤* ዳዊት ያለበትን አሳሳቢ ሁኔታ ያሚ ያመለክት ዘይቤያዊ አነጋገር ነው፤ ምናልባት ዳዊት (1) ምንም ጕልበት እንደሌለው መግለጹ ነው፤ ወይም (2) እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደደረሰ መናገሩ ነው፤ ወይም (3) ጠላቶቹ እንደ "ምናምንቴና ርጋጭ" እንደሚቈጥሩት ማመልከቱ ነው።

62፥4 *ከታላቅ ክብሩ፤* ከዙፋኑ ማለት ነው። *ሐሰት ... ይራገማሉ፤* የ10፥7 ማብ ይመ። *ይመርቃሉ፤* ለምሳሌም "ንጉሡ ለዘላለም ይኑር" ይላሉ ማለት ነው (1ሳሙ10፥24፤ 2ሳሙ16፥16፤ እንዲሁም 1ነገ1፥25፡35፡39 ይመ)።

*62፥5-8፤* በእግዚአብሔር የሚታመን መሆኑን የገለጸበት ክፍል ነው፤ መዝሙረኛው እርሱ ራሱም ሆነ(ቍ5) ሕዝቡ (ቍ8) በእግዚአብሔር እንዲታመኑ ይመክራል።

62፥5 *ዐርፈሽ፤* የቍ1 ማብ ይመ፤ እምነት እምነትን ሲያ ጸና ይታያል (27፥13-14፤ 42፥5፡11፤ 43፥5 ይመ)።

ነው::
8ሰዎች ሆይ፤ ሁልጊዜ በእርሱ ታመኑ፤
ልባችሁን በፊቱ አፍስሱ፤
እግዚአብሔር መጠጊያችን ነውና:: ሴላ
9ከተናቀ ወገን መወለድ ከንቱ፣
ከከበረውም መወለዱ ሐሰት ነው::
በሚዛን ላይ ከፍ ብለው ቢታዩም፣
ሁሉም በአንድነት ከነፋስ የቀለሉ
ናቸው::
10በዝርፊያ አትታመኑ፤
በቅሚያም ተስፋ አታድርጉ፤
በዚህ ብትበለጽጉም፣
ልባችሁ ይህን አለኝታ አያድርግ::
11እግዚአብሔር አንድ ነገር ተናገረ፤
እኔም ይህን ሁለት ጊዜ ሰማሁ፤
ኀይል የእግዚአብሔር ነው::
12ጌታ ሆይ፤ ምሕረትም የአንተ ነው፤
አንተ ለእያንዳንዱ፣
እንደ ሥራው ትከፍለዋለህ::

## መዝሙር 63

### እግዚአብሔርን መፈለግ

በይሁዳ ምድር በዳ በነበረ ጊዜ፤ የዳዊት መዝሙር

1እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ አምላኬ ነህ፤
አንተን ከልብ እሻለሁ፤
ውሃ በሌለበት፣
በደረቅና በተራቈተ ምድር፣
ነፍሴ አንተን ተጠማች፤
ሥጋዬም አንተን ናፈቀች::
2ስለዚህ በመቅደስ ውስጥ አየሁህ፤
ኀይልህንና ክብርህንም ተመለከትሁ::
3ምሕረትህ ከሕይወት ይበልጣልና፤
ከንፈሮቼ ያመሰግኑሃል::
4እንግዲህ፣ በሕይወቴ ዘመን
አመሰግንሃለሁ፤
በአንተም ስም እጆቼን አነሣለሁ::
5ነፍሴ በቅቤና በስብ እንደሚረካ ሰው
ትረካለች፤
6በመኝታዬ አስብሃለሁ፤
ሌሊቱንም ሁሉ ስለ አንተ
አሰላስላለሁ::
7አንተ ረዳቴ ነህና፣
በክንፎችህ ሥር ተጠልዬ በደስታ
እዘምራለሁ::
8ነፍሴ አንተን የሙጥኝ ብላለች፤
ቀኝ እጅህም ደግፉ ይዞኛለች::
9ነፍሴን ለማጥፋት የሚሹ ግን፣

62፥8 1ሳሙ1፥15፤ መዝ37፥5፤42፥4፤ኢሳ 26፥4፤ማቴ26፥36-46
62፥9 ኢዮ7፥7፤መዝ 49፥2፤ኢሳ40፥15
62፥10 ኢዮ31፥25፤ መዝ12፥5፤ኢሳ61፥8 ፤ሕዝ22፥29፤ናሆ3፥1፤ ማቴ19፥23-24፤ 1ጢሞ6፥6-10:17
62፥11 1ዜና29፥11 ፤ራእ19፥1
62፥12 ኢዮ21፥31 ፤መዝ28፥4፤86፥5፤10 3፥8፤130፥7፤ማቴ16፥ 27፤ሮሜ2፥6፤1ቆሮ3፥ 8፤ቈላ3፥25
63፥1 መዝ42፥2፤84 ፥2፤143፥6
63፥2 ዘፀ16፥7፤መዝ 15፥1፤27፥4፤68፥24
63፥3 መዝ36፥7፤ 69፥16፤106፥45፤ 109፥21
63፥4 መዝ28፥2፤ 104፥33፤146፥2፤ኢሳ 38፥20፤1ጢሞ2፥8
63፥5 መዝ36፥8፤ ማቴ5፥6
63፥6 ዘዳ6፥4-9፤ መዝ16፥7፤119፥148፤ ማቴ14፥25
63፥7 ሩት2፥12፤

*62፥8፤* ለእግዚአብሔር ሕዝብ የተሰጠ ምክር ነው (31፥23-24 ይመ):: *ልባችሁን ... አፍስሱ፤* ከልብ በሆነ ጸሎት ቅረቡ ማለት ነው (ሰቆ2፥19 ይመ):: *ልባችሁን፤* የ4፥7 ማብ ይመ::

*62፥9-12፤* በዚህ ክፍል በአንድ በኩል ዐቅመ ቢስና ከንቱ ስለሆነው የሰው ልጅ ማንነት ሲገልጽ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኀያልና ታማኝ ስለሆነው ስለ እግዚአብሔር ማንነት ተገልጾአል::

*62፥9-10፤* ሰው የሚያስፈራ መስሎ ቢታይም ከቍጥር የሚገባ አይደለም (የ10፥8 ማብ ይመ)::

62፥9 *ከተናቀ ወገን መወለድ ... ከከበረውም መወለድ፤* በየትኛውም የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎች ማለት ነው፤ *ከን ቱ ... ከእስትንፋስ፤* ሰዎች በተለይም ሀብታሞችና ኀያላን ነፋስ ከሚበትነው ገለባ የተሻሉ መስለው ለመታየት ይፍጨረጨራሉ::

*62፥10፤* ሊያድናቸው በሚችለው በእግዚአብሔር በመ ታመን ሳይሆን የሚፈልጉትን ነገር በራሳቸው ዘዴና ብልሃት (በትክክለኛው መንገድ ወይም በማታለል) ለማግኘት ለሚፈልጉ ሰዎች (በመዝሙረኛው ላይ የሚያሤሩትን ጨምሮ) የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ነው፤ የመዝ 49 እጥርጥር ነው:: *ልባችሁ፤* የ4፥7 ማብ ይመ::

*62፥11-12፤* ደረጃ በደረጃ እየጐለበተ መጥቶ ከመጨረሻው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ ሐሳብ ነው፤ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ጽኑ መታመኛ እንደ ሆነ በድጋሚ ተገልጾአል:: *ኀይል ... ምሕረ ትም፤* ቃል የገባውን ነገር ሁሉ መፈጸም ይችላል፤ ሕዝቡን ለማ ዳንና ለመባረክ ዘወትር ዝግጁ ነው::

62፥11 *አንድ ነገር ... ሁለት ነገር፤* የአሞ 1፥3 ማብ ይመ::

62፥12 *ምሕረትም፤* የ6፥4 ማብ ይመ:: በመጨረሻ ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ያያሉ (የ4፥1 ማብ ይመ):: *እንደ ሥራው ... ትከፍለዋለህ፤* የኤር 17፥10፤ የ32፥19 ማብ ይመ::

*መዝ63፤* ጨካኝ ጠላቶች ባስጨነቁት ጊዜ እግዚአብሔርን ለማየትና የእርሱ መገኘት የሚሰጠውን ዋስትና ለማግኘት የቀረበ ጸሎት ነው:: መዝሙረኛው እግዚአብሔርን ለማየት ያለው ፍላጐት ምን ያህል ጽኑ እንደ ሆነ "ነፍሴ ...ተጠማች" (ቍ1) እንዲሁም "ነፍሴ ... ትረካለች" (ቍ5፤ 42፥1-2 ይመ) በሚሉት ተለዋጭ ዘይቤዎች በግልጽ ተጠቅሶአል:: እንደ መዝ62 ሁሉ ይሄም መዝሙር ጸሎት ነው:: ይህ መዝሙር ከዚያኛው መዝሙር ጋር የሚገናኘው "ሰማሁ" (62፥11) የሚለው "አየሁህ" (ቍ2፤ 48፥8 እና ማብ ይመ) ወደሚለው አድጎ በመገኘቱ ነው:: ጨለማ ከሞት (ቍ6) ንጋት ደግሞ ከደኅንነት (የቍ1 ማብ ይመ) ጋር እየተ ነጻጸሩ በድጋሚ ቀርበዋል (የመዝ57ን መግቢያ ይመ):: የጥንቷ ቤተክርስቲያን ይህን መዝሙር የኅብረት ጸሎት አድርጋ በየቀኑ ትጠቀምበት ነበር:: ባወቃቀር ደረጃ ሲታይ መዝሙሩ እግዚ አብሔርን የሚናፍቅና በእግዚአብሔር ደስ የሚሰኝ ሰው (ቍ11) በተናገረው ቃል ላይ የተመሠረተ ነው:: በቤተ መቅደሱ ውስጥ ያየውን ነገር (ቍ2) ሌሊት በዐልጋው ላይ የሰላስለዋል (ቍ6)፤ ይህም ጠላቶቹ እርሱን ጠልፎ ለመጣል ባጠመዱት ወጥመድ እነርሱ ራሳቸው እንደሚያዙ ያረጋግጥ ለታል (ቍ9-10)::

*63 ርእስ፤* የመዝ3 ርእስ ማብ ይመ:: *በነበረ ጊዜ፤* ሲወ ርድ ሲዋረድ በመጣው ወግ መሠረት ይህ አባባል ትክክል ከሆነ፣ እዚህ ላይ የተባለው ነገር የሚያመለክተው በ2ሳሙ15፥23-28፤ 16፥2:14፤ 17፥16:29 ላይ የተወሳውን *ታሪክ* ነው፤ ምክንያቱም መዝሙረኛው ንጉሥ እንደ ሆነ ተገልጾአል (ቍ11 ይመ)::

*63፥1፤* በፈተናው ጊዜ እግዚአብሔርን እጅግ እንደናፈቀ ያሳያል:: *ከልብ፤* በቀጥታ ሲተረጐም "ንጋት"፣ "ማለዳ" ለማለት ነው:: *ነፍሴ ... ሥጋዬም፤* ሁለንተናዬ ማለት ነው (የ6፥3 ማብ ይመ):: *በደረቅና በተራቈተ ምድር፤* "መልካም ምግብ" (ቍ5) ሊቀምስ አለመቻሉን የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው፤ ይህ ምግብ የሚገኘው "የእግዚአብሔርን ከተማ ደስ ከሚያሰኘው ወንዝ" ነው (46፥4 እና ማብ ይመ)::

*63፥2-5፤* በቤተ መቅደሱ ውስጥ ያየውን እያስተዋለ የተናገረው ቃል ነው፤ ይህም ተስፋውን አለምልሞለታል::

*63፥2፤* 27፥4፤ 48፥8 እና ማብ ይመ::

63፥3 *ምሕረትህ፤* የ6፥4 ማብ ይመ::

63፥4 *ስም፤* የ5፥11 ማብ ይመ:: *እጆቼን አነሣለሁ፤* እጆ ቼን የሚያነሣው ለምስጋና ነው::

63፥5 *ነፍሴ፤* የ6፥3 ማብ ይመ:: *በቅቤና በስብ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "መቅኔና ስብ" ማለት ነው::

*63፥6-8፤* "በቤተ መቅደሱ ውስጥ" ያየውን እያስታወሰ (ቍ2) ሌሊት ያሰላስላል::

63፥6 *በመኝታዬ፤* ሌሊት የንጋትን ማዳን ሲጠባበቅ ሳለ ማለት ነው:: *ሌሊቱንም ሁሉ፤* የመሳ7፥19 ማብ፤ እንዲሁም 119፥148፤ ሰቆ2፥19 ይመ::

63፥7 *በክንፎችህ ሥር፤* የ17፥8 ማብ ይመ::

*63፥9-10፤* ጠላቶቹ የእጃቸውን ያገኛሉ፤ የእርሱን ሕይወት ለማጥፋት ሲሯሯጡ መጥፊያቸውን አዘጋጁ (ዘፍ9፥5፤ ዘፀ21፥23፤ ዘዳ19፥21፤ እንዲሁም የመዝ5፥10 ማብ ይመ)::

63፥9 *ጥልቅ፤* የ30፥1 ማብ ይመ:: *ምድር፤* እዚህ ላይ መቃብር ወይም ሲኦል ማለት ነው (የ61፥2 ማብ ይመ)::

ወደ ምድር ጥልቅ ይወርዳሉ፤
10ለሰይፍ አልፈው ይሰጣሉ፤
የቀበሮዎችም ምግብ ይሆናሉ።

11ንጉሥ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለዋል፤
በእግዚአብሔርም ስም ቃል የሚገቡ ሁሉ
ይከብራሉ፤
የሐሰተኞች አንደበትም ትዘጋለች።

## መዝሙር 64

### የተሳዳቢዎች ቅጣት

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር*

1እግዚአብሔር ሆይ፤ የብሶት ቃሌን ስማ፤
ሕይወቴንም ከሚያስፈራ የጠላት ዛቻ
ከልላት።
2ከክፉዎች አድማ ሰውረኝ፤
ከዐመፀኞችም ሸንጎ ጋርደኝ።

3እነርሱ ምላሳቸውን እንደ ሰይፍ ይስላሉ፤
መርዘኛ ቃላቸውንም እንደ ፍላጻ
ያነጣጥራሉ።
4አሸምቀው ንጹሑን ሰው ይነድፉታል፤
ድንገት ይነድፉታል፤ አይፈሩምም።
5ክፉ ተግባር ለማከናወን እርስ በርስ
ይመካከራሉ፤
በሴር ወጥመድ ለመዘርጋት ይነጋገራሉ፤
“ማንስ ሊያየን ይችላል?”[ʻ] ይባባላሉ።
6ግፍን ያውጠነጥናሉ፤
ደግሞም፣ “የረቀቀች ሤራ
አዘጋጅተናል” ይላሉ፤
አቤት! ልቡ፣ አእምሮውም እንዴት
ጥልቅ ነው!

7እግዚአብሔር ግን በፍላጻው ይነድፋቸዋል፤
እነርሱም ድንገት ይቈስላሉ።
8በገዛ ምላሳቸው ያሰናክላቸዋል፤
ጥፋትንም ያመጣባቸዋል፤
የሚያዩአቸውም ሁሉ በትዝብት
ራሳቸውን ይነቀንቃሉ።

9የሰው ልጆች ሁሉ ይፈራሉ፤
የእግዚአብሔርን ሥራ በይፋ ያወራሉ፤
ያደረገውንም በጥሞና ያሰላስላሉ።
10ጻድቅ *በእግዚአብሔር* ደስ ይበለው፤
እርሱንም መጠጊያ ያድርገው፤
ልበ ቅኖችም ሁሉ ደስ ይበላቸው።

## መዝሙር 65

### የምስጋና መዝሙር

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት የምስጋና መዝሙር*

1እግዚአብሔር ሆይ፤ በጽዮን ለአንተ ውዳሴ
ይገባል፤[T]
ለአንተ የተሳልነውን እንፈጽማለን።
2ጸሎትን የምትሰማ ሆይ፤
የሰው ልጆች ሁሉ ወደ አንተ ይመጣሉ።

ʻ5 ወይም *ማንስ ሊያያቸው ይችላል* ተብሎ ሊተረጐም ይችላል።
T1 በዕብራይስጡ የዚህ ቃል ትርጉም በትክክል አይታወቅም።

መዝ27፥9፤118፥7
63፥8 ዘኍ32፥12፤ መዝ41፥12፤ሆሴ6፥3
63፥9 መዝ40፥14፤ 55፥15፤71፥20፤95፥4 ፤139፥15
63፥10 ኤር18፥21፤ ሰቆ5፥18፤ሕዝ35፥5፤ አሞ1፥11
63፥11 ኢዮ5፥16፤ ኢሳ19፥18፤45፥23፤ 65፥16፤ሮሜ3፥19
64፥1 መዝ140፥1፤ 142፥2
64፥2 ዘፀ1፥10፤መዝ 56፥6፤59፥2
64፥3 መዝ7፥13፤ 55፥21፤58፥7፤ኢሳ 49፥2
64፥4 ኢዮ9፥23፤ መዝ10፥8፤11፥2፤ 55፥19
64፥5 ኢዮ22፥13፤ መዝ91፥3፤119፥110፤ 140፥5፤141፥9
64፥8 ዘዳ28፥37፤ 2ነገ19፥21፤መዝ59፥ 12፤109፥25፤ምሳ 18፥7
64፥9 መዝ40፥3፤ ኤር51፥10
64፥10 ኢዮ22፥19፤ መዝ11፥1፤25፥20፤ 31፥2፤32፥11
65፥1 ዘዳ23፥21፤ መዝ2፥6፤116፥18
65፥2 መዝ86፥9፤

63፥10 *የቀበሮዎችም ምግብ፤* የጠላት ሬሳ ቀባሪ አጥቶ በጦር ሜዳ ወድቆ እንደሚቀር፣ ይህም የበለጠ ውርደትን እንደሚያስከትል ለማሳየት የገባ አባባል ነው (የ53፥5 ማብ ይመ)።

63፥11 *በእግዚአብሔርም ስም ቃል የሚገቡ ሁሉ፤* እግዚአብሔርን የሚፈሩ፣ በእርሱም የሚታመኑ ሁሉ ማለት ነው (ዘዳ6፥13 ይመ)። *የሐሰተኞች አንደበት፤* ውሸት እየተናገሩ ኑሮአቸውን የሚገፉ ማለት ነው።

*መዝ64፤* እግዚአብሔር ከክፉ ሤራ እንዲከልለው ያቀረበው ጸሎት ነው። መዝሙረኛው ያለበት ሁኔታ ከመዝ 62 ጋር ተመሳሳይ ሳይሆን አይቀርም (የመዝ62ን መግቢያ ይመ)፤ በዚህ ቦታ ግን ንጉሡ ያለበትን አጣብቂኝ የሚያመለክት ምንም ፍንጭ የለም፤ ክፉ ሤራ ያቀነባበሩበትም ሰዎች ከአገር ውስጥ ወይም ከውጭ ይምጡ ግልጽ አይደለም (የቍ2 ማብ ይመ)። በመዝሙረኛው ጸሎት ውስጥ ተዘውትሮ እንደሚታየው እርሱን ሁልጊዜ የሚያጠቃው የጠላት ምላስ ነው (የ5፥9 ማብ ይመ)። ጸሎቱ የተቀነበበው ልመና ጸሎትና (ቍ1-2) በእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ላይ ነው (ቍ9-10)። በመኻል ላይ (ቍ5-6) ክፉ ሤራ ያቀነባበሩበትን ሰዎች አጕል ድፍረት ይገልጻል። በቍ3-4 ላይ ጠላቶቹ በመርዛም ምላሳቸው እንዴት እንደሚነድፉት ሲናገር በቍ7-8 ላይ ደግሞ እግዚአብሔር በራሳቸው መርዛም ምላስ እንዴት መልሶ እንደሚያጠፋቸው ይገልጻል።

*64ርእስ፤* የመዝ4 ርእስ ማብ ይመ።

*64፥1-2፤* የእግዚአብሔርን ጥበቃ በጸሎት ይጠይቃል።

64፥1 *ስማ፤* በዕብራይስጥ “ደስ ይበላቸው” ከሚለው ሐረግ ጋር ተመሳሳይ ድምፀት አለው (ቍ10 እና ማብ ይመ)።

*64፥3-4፤* የጠላትን ጥቃት ያመለክታል።

64፥3 *ምላሳቸውን፤* የ5፥9 ማብ ይመ። *መርዘኛ ... ፍላጻ፤* 59፥7 ይመ።

64፥4 *አይፈሩምም፤* ማንም የማያያቸውና የማይበቀላቸው ይመስላቸዋል፤ ነገር ግን ቍ7-8 ይመ።

*64፥5-6፤* የጠላትን ንቀትና በራስ መተማመን ያሳያል።

64፥5 *ይላሉ፤* የ3፥2 እና 10፥11 ማብ ይመ።

64፥6 *ልቡ፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *ጥልቅ፤* ምሳ18፥4፤ 20፥5 ይመ።

*64፥7-8፤* እግዚአብሔር በሚሰጠው ትክክለኛ ፍርድ የሚታመን መሆኑን ይገልጻል፤ የዳዊት ጠላቶች በዳዊት ላይ ለመፈጸም ያሰቡትን እግዚአብሔር ይፈጽምባቸዋል (63፥9-10 እና ማብ ይመ)። *በፍላጻው ... ይነድፋቸዋል ... ምላሳቸው፤* ቍ3-4 ይመ።

64፥8 *ራሳቸውን ይነቀንቃሉ፤* 44፥14 ይመ።

*64፥9-10፤* ደስ የሚያሰኘውን የእግዚአብሔርን የፍርድ ውጤት ያሳያል፤ ሰዎች ሁሉ በፍርሀት ይዋጣሉ፤ ሲሆን ያዩትን ሁሉ ያወራሉ፤ ነገሩንም ያሰላስላሉ (የ46፥10 ማብ ይመ)። ጻድቅ ግን ደስ ይለዋል እግዚአብሔርንም መሸሸጊያው ያደርጋል፤ ስሙንም ይወድሳል።

*64፥9፤* 58፥11፤ እንዲሁም 40፥3፤ 52፥6፤ 65፥8 ይመ።

64፥10 *ጻድቅ፤* የ1፥5 ማብ ይመ። *ደስ ይበላቸው፤* በዕብራይስጥ ይህ ሐረግ የስንኙ (የመስመሩ) የመጀመሪያ ቃል ሲሆን “ስማ” ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ድምፀት አለው። ይህም ቃል የመዝሙሩ የመጀመሪያ ስንኝ (መስመር) የመጀመሪያ ቃል ነው፤ መዝሙረኛው ተመሳሳይ ድምፀት ባላቸው ቃላት የተጠቀመው ለአጽንኦት ነው።

*መዝ65፤* እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያደርገውን ታላቅ በጎነት የሚያወድስ መዝሙር ነው። ለጸሎታቸው መልስ በመስጠት፣ (1) ኀጢአታቸውን ይቅር ይላል፤ በቤተ መቅደስ ውስጥ ከሚገኘው “መልካም ነገሮች” እንዲረኩና ከእርሱም ጋር ያላቸውን ኅብረት እንዲቀጥሉ ያደርጋል (ቍ3-4)፤ (2) የዓለም ብጥብጥ አክትሞ እስራኤል በምድሯ በሰላም እንድትኖር ሁኔታዎችን ይቈጣጠራል (ቍ5-8)፤ (3) የተስፋዪቱን ምድር እውነተኛ ገነት ያደርጋታል (ቍ9-13)። ይህ መዝሙር አንድ ዐይነት ፍሬ ሐሳብ ያላቸው አራት ተከታታይ መዝሙሮች መጀመሪያ ነው።

*65ርእስ፤* የመዝ4 ማብ የመዝ30 ርእስን ይመ።

*65፥1-2፤* እግዚአብሔርን ለማመስገን ቃል ይገባል።

65፥1 *ይገባል፤* የ62፥1 አማራጭ ትርጕሙን ይመ። እዚህ ላይ ምስጋና በቤተ መቅደስ በሚኖር ሰው ተመስሎአል፤ በመሆኑም ሰዎች እግዚአብሔርን ለማመስገን የገቡትን ቃል ለመፈጸም (57፥8 ይመ) ሲመጡ ካልቀሰቀሱት በስተቀር በቤተ መቅደስ ይተኛል። *የተሳልነውን፤* በጸሎታቸው ጊዜ ቃል የገቡትን ነው (66፥14 እና የ7፥17 ማብ ይመ)።

65፥2 *የሰው ልጆች፤* ቃል በቃል ሲተረጐም “ሥጋ ለባሽ ሁሉ” ማለት ሲሆን በኢል2፥28 ላይ እንደ ተጠቀሰው ምናልባት የእግዚአብሔርን ሰዎች ሁሉ ሊያመለክት ይችላል። በ64፥9፤

[3]ኀጢአት ባጥለቀለቀን ጊዜ፣
አንተ መተላለፋችንን ይቅር አልህ::[ሀ]
[4]አንተ የመረጥኸው፣ ወደ ራስህ
ያቀረብኸው፣
በአደባባይህም ያኖርኸው ምስጉን ነው!
ከተቀደሰው መቅደስህ፣
ከቤትህም በረከት እንረካለን::
[5]እግዚአብሔር አዳኛችን ሆይ፤
በጽድቅ ድንቅ አሠራር መልስልን፤
አንተ ለምድር ዳርቻ ሁሉ፣
በርቀት ላለውም ባሕር ተስፋ ነህ::
[6]ተራሮችን በብርታትህ መሠረትህ፤
ኀይልንም ታጥቀሃል::
[7]አንተ የባሕሮችን ማስገምገም፣
የማዕበላቸውን ቍጨት፣
የሕዝቦችንም ሁከት ጸጥ ታደርጋለህ::
[8]ርቀው በምድር ዳርቻ ያሉት ከድንቅ
ሥራህ የተነሣ ይደነግጣሉ፤
የንጋትንና የምሽትን መምጫዎች፣
በደስታ እልል እንዲሉ ታደርጋቸዋለህ::
[9]ምድርን ትጐበኛለህ፤ ታጠጣለህም፤
እጅግ ታበለጽጋታለህም::
ለሰዎች እህልን ይለግሱ ዘንድ፣
የእግዚአብሔር ወንዞች ውሃን የተሞሉ
ናቸው፤
አንተ እንዲህ እንዲሆን ወስነሃልና::[ለ]
[10]ትልሚን በውሃ ታረሰርሳለህ፤
ቦይዋን ታስተካክላለህ፤
በካፊያ ታለሰልሳለህ፤
ቡቃያዋንም ትባርካለህ::
[11]ለዘመኑ በጎነትህን ታጐናጽፈዋለህ፤
ሠረገላህም በረከትን ተሞልቶ ይፈስሳል::
[12]የምድረ በዳው ሣር እጅግ ለመለመ፤
ኰረብቶችም ደስታን ተጐናጸፉ::
[13]ሜዳዎች መንጋ በመንጋ ሆኑ፤
ሸለቆችም በእህል ተሸፈኑ፤
እልል ይላሉ፤ ይዘምራሉም::

ኢሳ66፥23
65፥3 መዝ40፥12፤ 79፥9፤ሮሜ3፥25፤ዕብ 9፥14
65፥4 ዘኍ16፥5፤ መዝ33፥12፤36፥8
65፥5 ዘዳ4፥34፤መዝ 18፥46፤45፥4፤48፥10 ፤68፥19፤85፥4፤106፥ 22፤107፥23፤ኢሳ 64፥3
65፥6 መዝ18፥1፤ 93፥1፤ኢሳ51፥9፤አሞ 4፥13
65፥7 ዘዳ32፥41፤ መዝ2፥1፤74፥23፤89፥ 9፤93፥3-4፤107፥29፤ 139፥20፤ኢሳ17፥12-13፤ማቴ8፥26
65፥8 መዝ100፥2፤ 107፥22፤126፥2፤ኢሳ 24፥16፤52፥9
65፥9 ዘፍ27፥28፤ ዘሌ26፥4፤ዘዳ32፥14፤ መዝ68፥9-10፤ 104፥14፡24
65፥10 ዘዳ32፥2፤ 2ሳሙ1፥21፤ኢዮ 36፥28፤ሐሥ14፥17
65፥11 ዘዳ28፥12፤ ኢዮ36፥28፤መዝ 104፥28፤147፥14፤ ሉቃ6፥38፤ዮሐ10፥10
65፥12 ኢዮ28፥26፤ መዝ98፥8፤ኢል2፥22
65፥13 መዝ72፥16 ፤98፥8፤144፥13፤ኢሳ 14፥8፤30፥23፤44፥23፤ 49፥13፤55፥12፤ዘካ8፥12

ሀ3 *ወይም አንተ ተቤዠሀን*
ለ9 *ወይም አንተም ለዚህ ነው ምድርን ያዘጋጀሃት*

66፥1፡4፡8፤ 67፥3-5 እና በሌሎችም ክፍሎች ላይ እንደ ተጠቀሰው ሁሉ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ሐሳቡ ዓለም አቀፋዊ ባሕርይ እንዳለው ይናገራሉ:: *ይመጣሉ፤* እግዚአብሔር ብቸኛ አምላክ እንደ ሆነና የሕዝቡንም ጸሎት የሚሰማና እንደቸርነቱም መጠን የሚመልስ መሆኑን ለማመስገን ይሰበሰባሉ ማለት ነው::

*65፥3-4፤* የመጀመሪያውና ቀዳሚው በረከት ነው::

65፥3 *መተላለፋችንን ይቅር አልህ፤* ስለ በደላችን እንዲቀርብ ያዘዝከውን መሥዋዕት ተቀብለህ ኀጢአታችንን ይቅር አልህ (32፥1-2፤78፥38፤79፥9 እንዲሁም የዘሌ16፥20-22፤ 17፥11፤ የዕብ 2፥17፤ 9፥5፡7 ማብ ይመ)::

65፥4 *ምስጉን፤* የ1፥1 ማብ ይመ:: *አንተ የመረጥኸው ... ያቀረብኸው፤* ከእስራኤል ወገንና የእግዚአብሔርም ምርጥ ሕዝብ የሆነ ሰው (33፥12፤ ዘዳ 4፥37 ይመ) እግዚአብሔር በቤተ መቅደሱ እንዲኖር የተቀበለው ሰው ነው:: *በአደባባይህ እንዲኖሩ፤* የ15፥1 ማብ እና 23፥6 ይመ:: *ከቤትህም በረከት፤* ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚፈሱ በረከቶች ሁሉ ለማለት ነው (36፥8 እና ማብ ይመ)::

*65፥5-8፤* እግዚአብሔር መንግሥታትን ጸጥ ያደርጋል፤ ለእስራኤል ግን ሰላምን ይሰጣል፤ ጸሎቷንም ይመልስላታል::

65፥5 *ድንቅ ሥራዎች፤* እነዚህ ድንቅ ሥራዎች እግዚአብሔር፣ እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት ነጻ ያወጣውን፣ ከነዓናውያንን ድል እንዲመቱና ምድራቸውንም እንዲወርሱ ያስቻላቸውን፣ የእስራኤልንም ጠላቶች መድረሻ ያሳጣውን የሚያመለክቱ ናቸው (66፥3፤ 106፥22፤ 145፥6፤ ዘዳ10፥21፤ 2ሳሙ7፥23፤ኢሳ 64፥3 ይመ):: *በጽድቅ፤* እግዚአብሔር በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ያደረገውን የማዳን ሥራ የሚያወሳ ነው (የ4፥1 ማብ ይመ):: *ተስፋ፤* የዓለም ሕዝቦች እግዚአብሔርን ባያውቁም እንኳ እግዚአብሔር ግን ተስፋቸው ነው::

*65፥6-7፤* የፍጥረት አምላክ በታላቅ ኀይሉ አማካይነት ቅጥ ካጣውና ከተመሳሰቀለው ነገር ውስጥ ሥርዐት ያለውን ዓለም እንዳበጀ ሁሉ (ዘፍ1 ይመ)፣ እስራኤልም በተስፋዪቱ ምድር በጸጥታ መኖር እንድትችል (መዝ 33፡46 ይመ) ሕዝቡን በሚዋጅበት ጊዜ ለሕዝቡ ሰላምንና ሥርዐት ያለውን ሕይወት ይሰጣል (ኢሳ 2፥4፤ 11፥6-9፤ ሚክ 4፥3-4 ይመ)፤ የብሉይ ኪዳን ባለቅኔዎች አብዛኛውን ጊዜ እግዚአብሔር ሕዝቡን በሚዋጅበት ጊዜ ያደረጋቸውን ድንቅ ነገሮች በፍጥረት ጊዜ ካደረጋቸው ድንቅ ነገሮች ጋር ያነጻጽሩታል (74፥12-17፤ 89፥9-18፤ ኢሳ 27፥1፤ 40፥6-14፡21-31፤ 51፥9-11 ይመ)፤ ምክንያቱም ኀያል ፈጣሪነቱ ለኀያል ቤዛነቱ ዋስትና ነው:: *ተራሮችን ... መሠረትህ ... የባሕሮችን ... ጸጥ ታደርጋለህ፤* ፍጥረትን ሁሉ ያዛል (95፥4-5 ይመ)::

65፥7 *የሕዝቦችንም ሁከት፤* እግዚአብሔር፣ የእስራኤልን ሰላም ዘወትር የሚያደፈርሰውን የመንግሥታትን ሁከት ጸጥ ማድረጉ ቅጥ ያጣውንና የታወከውን የጥንት ውሃ ዝም ከማሰኘቱ ጋር ተነጻጽሮአል (የ32፥6፤ 33፥7 ማብ ይመ)::

*65፥8፤* እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ያደረጋቸውን ድንቅ ነገሮች ሕዝቦች ሁሉ (የማታ ማታ) ያስተውላሉ፤ እግዚአብሔርንም ይፈራሉ (የ46፥10 ማብ ይመ):: ፍጥረትም ሁሉ ሐሤት ያደርጋል (ቍ13 ይመ):: *ድንቅ ሥራዎች፤* "ምልክቶች" ለማለት ነው፤ እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ነጻ ባወጣ ጊዜ እንዳደረጋቸው ታላላቅ የማዳን ሥራዎች ያሉትን ያመለክታሉ (ዘዳ4፥34፤ መዝ78፥43፤ 105፥27፤ 135፥9 ይመ):: ምልክት እንደ መሆናቸውም መጠን እግዚአብሔር ሁልጊዜ በሥራ ላይ እንደ ሆነ የሚያስገነዝቡ ናቸው (ዮሐ2፥11 እና ማብ ይመ)::

*65፥9-13፤* እግዚአብሔር ለጸሎታቸው መልስ በመስጠት የተስፋዪቱን ምድር በመልካም ነገር ሁሉ ይባርካል::

65፥9 *የእግዚአብሔር ወንዞች፤* የ36፥8 ማብ ይመ::

65፥11 *በጎነትህን፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "መልካምነትህን" ማለት ነው (68፥10፤ 31፥19 እና ማብ ይመ)::

65፥13 *በደስታ እልል ይላሉ፤ ይዘምራሉ፤* መዝሙረኛው ሕይወት ባላቸው ቃላት ግዑዛን ፍጥረታት እንኳ ሳይቀሩ እግዚአብሔርን ስለ መልካምነቱ፣ ስለ በረከቱና ስለማዳኑ በዝማሬ ለመወደስ ከሰው ልጆች ጋር እንደሚሰለፉ ይገልጻል (89፥12፤ 96፥11-13፤ 98፥8-9፤ 103፥22፤ 145፥10፤ 148፥3-4፡7-10፤ ኢዮ38፥7፤ ኢሳ44፥23፤ 49፥13፤ 55፥12 ይመ)::

*መዝ66፤* እግዚአብሔር ጸሎትን ስለመለሰ የቀረበ ምስጋና ነው:: እግዚአብሔር የመዝሙሩን ደራሲ (ምናልባትም ንጉሡን) ከጠላት ዛቻ የታደገው ይመስላል፤ ይህ የማዳን ሥራ መላውን ሕዝብ የሚጨምር ነው:: ብዙዎች እንደ ሚናገሩት ከሆነ ይህ መዝሙር የሚያወሳው ይሁዳ በሚያስደንቅ ሁኔታ ከአሦራውያን እጅ ነጻ መውጣቷን ነው (2ነገ19 ይመ):: ውዳሴ የቀረበው የተሳለውን ስእለት ለመፈጸም ነው (ቍ13-14፤ የ7፥17 ማብ ይመ)፤ እንዲህ ያለው ምስጋናና ውዳሴ አብዛኛውን ጊዜ ከከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚደርሰው ሌሎችም በምስጋናውና በውዳሴው ውስጥ እንዲሳተፉ በማድረግ ነው (የ9፥1 ማብ ይመ):: በዚህ ቦታ የመዝሙረኛው ሕያው ቃላት የሚጀምሩም በሌሎችም ቦታዎች ላይ እንደሚታየው ጥሪ በማድረግ ነው (ለምሳሌ ያህል 67፥3-5፤ 68፥32፤ 98፥4፤ 99፥3፤ 100፥1፤ 117፥1 ይመ):: ይህ ጥሪ ከምድር ዳርቻ እስከ ምድር ዳርቻ ላሉትም ጭምር ቀርቦአል:: ይህ መዝሙር አራቱ ተከታታይ መዝሙሮች ከተባሉት ሁለተኛው ነው (የመዝ65ን መግቢያ ይመ):: መዝሙሩ በምስጋና ጥሪና (ቍ1-2) ምስጋናም ለማቅረብ ምክንያት በሆነው ነገር ተቀንብቦአል (19-20 ይመ በዕብራይስጥ ቋንቋ "ውዳሴ" እና "ጸሎት" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ድምፅት ያላቸው ቃላት ናቸው):: የመዝሙሩ የመጀመሪያ አንጓ አንድ ዐይነት አወቃቀር

## መዝሙር 66

### የኅብረት ምስጋና

ለመዘምራን አለቃ፤ ማኅሌት፤ መዝሙር

1 ምድር ሁሉ ለእግዚአብሔር እልል ይበል!
2 ለስሙ ክብር ዘምሩ፤
ውዳሴውንም አድምቁ!
3 እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት፤ “ሥራህ
እንዴት ግሩም ነው!
ጠላቶችህ ከኀይልህ ታላቅነት የተነሣ፣
በፊትህ ይርዳሉ።
4 ምድር ሁሉ ይሰግድልሃል፤
በዝማሬ ያመሰግኑሃል፤
ለስምህም ይዘምራሉ። ሴላ
5 ኑና፣ እግዚአብሔር ያደረገውን እዩ
በሰዎች መካከል ሥራው አስፈሪ ነው!
6 ባሕሩን የብስ አደረገው፤
ወንዙን በእግር ተሻገሩ፤
ኑ፣ በእርሱ ደስ ይበለን።
7 በኀይሉ ለዘላለም ይገዛል፤
ዐይኖቹ ሕዝቦችን ይመለከታሉ፤
እንግዲህ ዐመፀኞች ቀና ቀና አይበሉ። ሴላ
8 ሕዝቦች ሆይ፤ አምላካችንን ባርኩ፤
የምስጋናውንም ድምፅ አሰሙ።
9 እኛን በሕይወት የሚያኖረን፣
እግራችንንም ከመንሸራተት የሚጠብቅ
እርሱ ነው።
10 አምላክ ሆይ፤ አንተ ፈተንኸን፤
እንደ ብርም አነጠርኸን።
11 ወደ ወጥመድ አገባኸን፤
በጀርባችንም ሸክም ጫንህብን።
12 ሰዎች በራሳችን ላይ እንዲፈነጩ
አደረግህ፤
በእሳትና በውሃ መካከል አለፍን፤
የኋላ ኋላ ግን ወደ በረከት አመጣኸን።
13 የሚቃጠል መሥዋዕት ይዤ ወደ
መቅደስህ እገባለሁ፤
ስእለቴንም ለአንተ እፈጽማለሁ፤
14 በመከራ ጊዜ ከአፌ የወጣ፣
በከንፈሬም የተናገርሁት ስእለት ነው።
15 ፍሪዳዎችን የሚቃጠል መሥዋዕት
አድርጌ፣
አውራ በጎችንም የሚጤስ ቍርባን
አድርጌ አቀርብልሃለሁ፤
ኰርማዎችንና ፍየሎችንም እሠዋልሃለሁ። ሴላ
16 እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሁሉ፤ ኑና ስሙ፤
ለነፍሴ ያደረገላትን ልንገራችሁ።
17 በአፌ ወደ እርሱ ጮኽሁ፤
በአንደበቴም አመሰገንሁት።
18 ኀጢአትን በልቤ አስተናግጄ ቢሆን ኖሮ፣
ጌታ ባልሰማኝ ነበር።
19 አሁን ግን እግዚአብሔር በእርግጥ
ሰምቶኛል፤
ጸሎቴንም አድምጦአል።
20 ጸሎቴን ያልናቀ፣
ምሕረቱንም ከእኔ ያላራቀ፣
እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው።

66፥1 መዝ81፥1፤ 84፥8፤95፥1፤98፥4፤ 100፥1
66፥2 መዝ79፥9፤ 86፥9፤ኢሳ42፥8:12፤ 43፥21
66፥3 ዘጸ7፥21፤10፥21፤2ሳሙ22፥45፤ መዝ65፥5፤106፥22፤ 111፥6፤145፥6
66፥4 መዝ7፥17፤ 22፥27፤67፥3
66፥5 ቍ3፤መዝ 106፥22
66፥6 ዘፍ8፥1፤ዘፀ 14፥22፤ዘሌ23፥40፤ 1ቆሮ10፥1
66፥7 ዘፀ3፥16፤15፥18፤ዘኍ17፥10፤መዝ 11፥4፤112፥10፤140፥8፤145፥13
66፥8 መዝ22፥23
66፥9 ዘዳ32፥35፤ ኢዮ12፥5፤መዝ30፥3
66፥10 ዘፀ15፥25፤ ኢዮ6፥29፤28፥1፤ መዝ12፥6
66፥11 ዘፍ3፥17፤ ዘፀ1፥14፤መዝ38፥4፤ 142፥7፤146፥7፤ኢሳ 10፥27፤42፥7:22፤ 61፥1
66፥12 መዝ18፥19 ፤ኢሳ51፥23
66፥13 መዝ22፥25፤ 50፥14፤51፥19፤116፥14፤መክ5፥4፤ዮና2፥9
66፥15 ዘሌ16፥5፤ መዝ51፥19
66፥16 መዝ34፥11 ፤71፥15:24
66፥18 ዘዳ1፥45፤ 1ሳሙ8፥18፤ያዕ4፥3 66፥19 መዝ18፥6
66፥20 መዝ22፥24

ባላቸው ሁለት ዐበይት ሐሳቦች የሚከታተል ነው፤ ባለ ሦስት ቍጥር አንጓ በባለ አምስት ቍጥር አንጓ ተከትሎ ይገኛል። የመጀመሪያው ስንኝ (መስመር) የመጀመሪያው አንጓ (ቍ5) “ኑ ... እዩ” ብሎ ሲጀምር የመጀመሪያው ስንኝ (መስመር) ሁለተኛው አንጓ (ቍ16) “ኑ፤ አድምጡ” ማለት ይጀምራል።

*66ርእስ፤* የመዝ4 እና 30 ርእስ ማብ ይመ።

*66፥1-4፤* በምድር የሚኖሩ ሁሉ እግዚአብሔርን በደስታ እንዲያመሰግኑ ጥሪ ቀርቦላቸዋል።

66፥1 ***ምድር ሁሉ፤*** የ65፥2 ማብ ይመ።

66፥2 ***ለስሙ፤*** የ5፥11 ማብ ይመ።

66፥3 ***ግሩም፤*** ቍ5፤ እንዲሁም የ65፥5 ማብ ይመ። ***ይርዳሉ፤*** ኢሉ5፥11፤ 2ዜና20፥29 ይመ።

*66፥4፤* የ46፥10 ማብ ይመ።

*66፥5-7፤* እግዚአብሔር ቀይ ባሕርን ከፍሎ የእስራኤልን ሕዝብ እንዴት እንዳሻገረና መንግሥታትንም እንዴት እንደ ገዛ ያስታውሳል። መዝሙረኛው የእርሱን ነጻ መውጣት የሚያመሳስለው (ከፍ ሲል የተመለከተውን የዚህን መዝሙር መግቢያ ይመ) ቀይ ባሕርን በእግራቸው አቋርጠው ከተሻገሩት ሕዝቦች ጋር ነው፤ ይህም የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ ያሳያል (የእግዚአብሔርን ኀያል የማዳን ሥራ ከኀያል የፍጥረት ሥራው ጋር ለማነጻጸር፤ መዝ65፥5-7 ይመ)፤ የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ቀጣይነት እንዳለው መዝሙረኛው ይናገራል።

66፥5 ***ኑና... እዩ፤*** እግዚአብሔር በጥንት ዘመን የፈጸማቸው የማዳን ሥራዎች ዛሬም እርሱ በሚመለክበት በቤተ መቅደሱ ውስጥ “ይታያሉ” (46፥8፤ 48፥8-9 እና ማብ ይመ)። ***በሰዎች መካከል፤*** ለሕዝቡ ሲል ሊባል ይችላል።

66፥6 ***ውሆች፤*** ምናልባት የዮርዳኖስን ወንዝ ሊሆን ይችላል፤ ሆኖም ቃሉ በብዙ የሚያደላው ቀይ ባሕር ወደሚለው ነው።

66፥7 ***ዐመፀኞች፤*** በእግዚአብሔር ሕግና ሥርዐት ላይ የተነሡና ያመፁ ሕዝቦችን ነው (68፥6 ይመ)።

*66፥8-12፤* እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያደረገውን አዲስ የማዳን ሥራ በማወጅ ያመሰግናል።

66፥8 ***ሕዝቦች፤*** እግዚአብሔርን ለማመስገን የተሰበሰቡ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ (2ዜና20፥27-28 ይመ)።

66፥9 ***ከመንሸራተት፤*** የ38፥16 ማብ ይመ።

66፥10 ***ፈተንኸን ... አነጠርኸን፤*** ነገሩን ከአንድ አቅጣጫ ስንመለከተው የእግዚአብሔር ሕዝቦች በእምነታቸውና በታማኝነታቸው ምን ያህል ጽኑ እንደ ሆኑ የሚታወቀው በፈተና ውስጥ ሲያልፉ ነው። የተወሰደው የከበሩ ዕንቍዎችን ከሚያነጥሩ አንጥረኞች ነው፤ በከበሩ ዕንቍዎች ላይ ያሉ ማናቸውም ቈሻሻዎች እንዲጠሩ የሚደረገው በእሳት በማቅለጥ ነው (12፥6፤ 17፥3 ይመ)።

66፥11-12 ***አገባኸን ... አደረግህ፤*** የእግዚአብሔር አገዛዝ ሁሉን አቀፍ ነው፤ ጠላት ሕዝቡን በግፍ ሲያስጨንቅ እንደ ተመልካች ዝም የሚል አይደለም፤ ይልቁንም በዚህ ሁሉ ውስጥ የራሱን ቅዱስ ዐላማ ይፈጽማል (ኢሳ45፥7፤ አሞ3፥6 ይመ)። ***ወጥመድ ... ሸክም... እንዲፈነጩ፤*** ሦስቱ ተለዋጭ ዘይቤዎች የሚገልጹት የሕዝቡን መከራ ነው፤ ምርኮኞች ወህኒ ቤት ተጣሉ፤ የጦር ምርኮኞች ባሪያ ተደረጉ፤ ድል የተመቱ ሰራዊቶች በሠረገሎች ተዳጡ።

66፥12 ***በእሳትና በውሃ፤*** ጽኑ መከራን የሚያመለክቱ ተለዋጭ ዘይቤዎች ናቸው (ኢሳ43፥2 ይመ)። ***ወደ በረከት ስፍራ፤*** በጥሬ ትርጕሙ “በረከት ወደ ፈሰሰበት ስፍራ” ማለት ነው (23፥5 ይመ)። ከሚያስጨንቅ ሁኔታ ወጥተው በደስታ ወደ ተሞላ ሁኔታ ተሻገሩ።

*66፥13-15፤* ለእግዚአብሔር የተሳለውን ስእለት እንደሚፈጽም ይናገራል (የ7፥17 ማብ፤ እንዲሁም 50፥14፤116፥17-19 ይመ)።

66፥13 ***እገባለሁ፤*** ንጉሡ ነው።

*66፥16-20፤* ለእግዚአብሔር ምስጋናን በማቅረብ እግዚአብሔር ያደረገለትን ውለታ ለአምልኮ ለተሰበሰበው ማኅበረ ምዕመናን ይናገራል።

66፥16 ***እግዚአብሔርን የምትፈሩ፤*** የዘፍ20፥11 ማብ ይመ።

66፥17 ***አመሰገንሁት፤*** በብሉይ ኪዳን ውስጥ ውዳሴና ጸሎት አብረው የሚቀርቡ ነገሮች ናቸው (ፊል4፥6፤ 1ጢሞ2፥1 ይመ)።

66፥20 ***እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው፤*** ቍ8 ይመ። ***ምሕረቱንም፤*** የ6፥4 ማብ ይመ።

## መዝሙር 67

### የመከር ጊዜ መዝሙር

*ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች የሚዘመር፤ የዳዊት መዝሙር፤ ማኅሌት*

[1]እግዚአብሔር ይማረን፤ ይባርከን፤
ፊቱንም በላያችን ያብራ፤ ሴላ
[2]መንገድህ በምድር ላይ፣
ማዳንህም በሕዝቦች ሁሉ መካከል
ይታወቅ ዘንድ።
[3]እግዚአብሔር ሆይ፤ ሰዎች ያመስግኑህ፤
ሰዎች ሁሉ ምስጋና ያቅርቡልህ።
[4]ለሕዝቦች በቅን ስለምትፈርድላቸው፣
ሰዎችንም በምድር ላይ ስለምትመራ፣
ሕዝቦች ደስ ይበላቸው፤ በእልልታም
ይዘምሩ። ሴላ
[5]እግዚአብሔር ሆይ፤ ሰዎች ያመስግኑህ፤
ሰዎች ሁሉ ምስጋና ያቅርቡልህ።
[6]ምድር ፍሬዋን ሰጠች፤
እግዚአብሔር አምላካችንም ይባርከናል።
[7]እግዚአብሔር ይባርከናል፤
የምድርም ዳርቻዎች ሁሉ እርሱን
ይፈሩታል።

67፥1 ዘኍ6፥24-26
67፥2 መዝ98፥2፤ ኢሳ40፥5፤52፥10፤ 62፥1፡2፤ሐሥ10፥35፤ቲቶ2፥11
67፥3 ቍ5
67፥4 መዝ9፥4፤ 68፥32፤96፥10-13፤ 100፥1-2
67፥6 ዘፍ8፥22፤ 12፥2፤ዘሌ26፥4፤መዝ 85፥12፤ኢሳ55፥10፤ ሕዝ34፥27፤ዘካ8፥12
67፥7 መዝ2፥8፤ 33፥8
68፥1 ዘኍ10፥35፤ መዝ12፥5፤18፥14፤89፥10፤92፥9፤132፥8፤ 144፥6፤ኢሳ17፥13፤ 21፥15፤33፥3
68፥2 ዘኍ10፥35፤ መዝ9፥3፤22፥14፤37፥20፤80፥16
68፥3 መዝ64፥10፤ 97፥12
68፥4 ቍ33፤ዘዐ 6፥3፤20፥21፤ዘዳ33፥26፤2ሳሙ22፥50፤መዝ 7፥17፤30፥4፤66፥2፤8

## መዝሙር 68

### ብሔራዊ የድል መዝሙር

*ለመዘምራን አለቃ የዳዊት መዝሙር፤ ማኅሌት*

[1]እግዚአብሔር ይነሣ፤ ጠላቶቹ ይበተኑ፤
የሚጠሉትም ከፊቱ ይሽሹ።
[2]ጢስ እንደሚበንን፣
እንዲሁ አብንናቸው።
ሰም በእሳት ፊት እንደሚቀልጥ፣
ክፉዎችም እንዲሁ ከእግዚአብሔር ፊት
ይጥፉ።
[3]ጻድቃን ግን ደስ ይበላቸው፤
በእግዚአብሔር ፊት ሐሤት ያድርጉ፤
ደስታንና ፍስሓን የተሞሉ ይሁኑ።
[4]ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤ ለስሙም ተቀኙ፤
በደመናት ላይ የሚሄደውን ከፍ
አድርጉት፤[ሐ]
ስሙ *እግዚአብሔር* በተባለው ፊት፣

[ሐ]4 ወይም *በምድረ በዳ ለሚሄደው መንገድን አዘጋጁለት*

***መዝ67፤*** እግዚአብሔር በረከቱን እንዲሰጥ በኅብረት የቀረበ ጸሎት ነው። የመዝሙሩ ይዘት ቅርጽና ጥንካሬ እንደሚያመለክተው መዝሙሩ የአምልኮው ሥርዐት ከመጠቃለሉና ካህኑም የመጨረሻ ቡራኬውን ከመስጠቱ በፊት ሕዝቡ የሚያቀርበው የቅዳሴ ጸሎት ሳይሆን አይቀርም (የቍ1 ማብ ይመ)። እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚሰጠው በረከትና ስለ ሕዝቡም ሲል የሚያደርገው የማዳን ሥራ የሕዝቦችን ትኩረት ይስባል፤ እግዚአብሔርንም እንዲያመሰግኑ ያደርጋል (65፥2 ይመ)። ይህ መዝሙር ከአራቱ ተከታታይ መዝሙሮች ውስጥ ሦስተኛው ነው (የመዝ65ን መግቢያ ይመ)። መዝሙሩ ፍጹም እኩኩል የሆነ አወቃቀር አለው፤ በመዝሙሩ መግቢያ ላይ ያሉ ሁለት ቍጥሮች ስለ ጸሎት ሲያወሱ በመዝሙሩ መደምደሚያ ላይ ያሉት ሁለት ቍጥሮች ደግሞ እግዚአብሔር ለጸሎታቸው ስለሚሰጠው መልስ ያወሳሉ። የመዝሙሩ እምብርት (ቍ4) በሁለት አዝማቾች (ቍ3፡5) የተቀነበበ ሲሆን እግዚአብሔር ለሕዝቡ ካሳየው ምሕረት የተነሣ መላው ዓለም እንዳመሰገነው በመጥቀስ የጸሎት መልስ እንዲሰጣቸው ያሳስባል።

*67ርእስ፤* የመዝ4 እና 30ርእስ ማብ ይመ።

*67፥1-2፤* ጸሎት ነው።

*67፥1፤* የጸሎቱ ዕንብርት ሲሆን ካህናት ከሚሰጡት ቡራኬ ጋር የተዛመደ ነው (ዘኍ6፥24-26)። ***ፊቱንም ...ያብራ፤*** የ4፥6 እና 13፥1 ማብ ይመ።

*67፥2፤* እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠው ሞገስ በመላው ዓለም የታወቀ እስኪሆን ድረስ ተትረፍርፎ ይታይ (የ46፥10 ማብ ይመ)።

*67፥3-5፤* ማኅቃቂያ ነው። በቍ2 ላይ ያለውን ሐሳብ በማብራራት እግዚአብሔር ሕዝቡን በባረከ ጊዜ በመላው ዓለም የሚስተጋባውን ምስጋና ያመለክታል። የሕዝቡ ምኞት ሁለት ነው፤ (1) የእግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚሰጠውን የተትረፈረፈ በረከት በማየት ለእግዚአብሔር ምስጋና እንዲያቀርቡና (2) የዓለም ሕዝቦች በእስራኤል ምስጋና ላይ ምስጋናን እንዲጨምሩ ነው።

*67፥4፤* የእግዚአብሔር አገዛዝ ትክክለኛ መሆኑን በተረዱ ጊዜ የምድር ሕዝቦች በእግዚአብሔር ሐሤት ያድርጉ (98፥4-6፤ 100፥1 ይመ)።

*67፥6-7፤* እግዚአብሔር ሕዝቡን በባረከ ጊዜ የሚከሠተውን ነገር ያሳያል።

*67፥6፤* የተስፋዪቱ ምድር የተትረፈረፈ በረከቷን ትሰጣለች (65፥9-13 ይመ)።

***መዝ68፤*** የእስራኤልን አምላክ የእግዚአብሔርን አገዛዝ ታላቅነትና ኀያልነት የሚያወድስ ቅዳሴ ነው (የመዝ24፤47፤118፤132 መግቢያዎችን ይመ)። ከ1-18 ያሉት ቍጥሮች እግዚአብሔር ከሲና ተራራ (በሙሴ ዘመን) እስከ ጽዮን ተራራ ድረስ (በዳዊት ዘመን) ያደረገውን የድል ዘመቻ የሚያወሱ ሁነቶችን ይዘዋል። በሲና ተራራ ላይ የተፈጸመው ሁነት የእግዚአብሔር መንግሥት በሕዝቡ መካከል መመሥረቱን ያበስራል፤ የእግዚአብሔር ዙፋን ምልክት የሆነው የቃል ኪዳኑ ታቦት በኢየሩሳሌም መመሥረቱ የእግዚአብሔር የደኅንነት መንግሥት በምድር ላይ መመሥረቱን ያበስራል፤ ኢየሩሳሌምም የመንግሥቱ መናገሻ ከተማ ናት። የጥንት ቤተ ክርስቲያን በኤፌ4፥8-13 ላይ የተጠቀሰውን የዚህን መዝሙር ሐሳብ መሠረት በማድረግ መዝሙሩ ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ፣ እርገትና አገዛዝ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን በዚህ ክፉ ዓለም ላይ ስለሚኖራት ድል ትንቢታዊ ሐሳብ እንዳለው አድርጋ ታየዋለች። መዝ68 ከአራቱ ተከታታይ መዝሙሮች ውስጥ የመጨረሻው ነው (የመዝ65ን መግቢያ ይመ)። መዝሙሩ ከማጠቃለያው ቡራኬ ጋር ዘጠኝ አንጓዎች ይዞአል (ቍ19-20 ምናልባት ከቍ21-23 ጋር ሳይቀናጅ አይቀርም)። የመጀመሪያው አንጓ የቅዳሴውን አጀማመር ይጠቍማል፤ የመጨረሻው አንጓ ደግሞ የቅዳሴውን አጨራረስ ያሳያል፤ የመጨረሻው አንጓ እግዚአብሔር ገናና ግርማውን ለብሶ በመቅደሱ ውስጥ መሆኑን ያሳስባል። ሰባተኛው አንጓ (ቍ24-27) ወደ ቤተ መቅደስ የሚገባውን የቅዳሴ ሰልፍ ይገልጻል። በዚህ መሠረት ሦስተኛው አንጓ (ቍ7-10) ከሲና እስከ ተስፋዪቱ ምድር የተደረገውን የምድረ በዳ ጕዞ የሚያስታውስ ሲሆን አምስተኛው አንጓ ደግሞ (ቍ15-18) እግዚአብሔር ወደ መኖሪያው ወደ ጽዮን ተራራ መውጣቱን ያሳስባል። በሌላ በኩል ደግሞ ሁለተኛው አንጓ (ቍ4-6) የእግዚአብሔርን በጎነት የሚያንጸባርቅ ሲሆን አራተኛው ደግሞ (ቍ11-14) በከነዓን ነገሥታት ላይ ድል መቀዳጀቱን ያስታውሣል። ስድስተኛው አንጓ (ቍ19-23) እግዚአብሔር አንድ ቀን አሸናፊ እንደሚሆን በእርግጠኝነት የሚናገር ሲሆን፣ ስምንተኛው አንጓ ደግሞ (ቍ28-31) እግዚአብሔር በቀድሞ ዘመን እንዳደረገው ሁሉ ዛሬም ጠላትን ለማጥፋት ክንዱን እንዲያነሣ የሚጠይቅ ጸሎት ይዞአል።

*68ርእስ፤* የመዝ4፥30 ርእስ ማብ ይመ።

*68፥1-3፤* ጕዞው ገና ከመነሻው ላይ በቅዳሴ መልክ የሚያስታውሰው እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የሲናን ተራራ ትቶ ወደ ተስፋዪቱ ምድር ዘመቻውን መቀጠሉን ነው (ዘኍ10፥33-35 ይመ)

68፥1 ***ጠላቶቹ ይበተኑ፤*** የቍ30 ማብ ይመ።

68፥3 ***ጻድቃን፤*** እስራኤል የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደመሆኑ መጠን የእግዚአብሔርን መንግሥት መምጣት ከሚቃወሙት ("ከክፉዎች" ቍ2) ጋር በምንም አትመሳሰልም።

*68፥4-6፤* ቸር ስለ ሆነው የእግዚአብሔር አገዛዝ ውዳሴ ይቀርብ ዘንድ የቀረበ ጥሪ ነው።

68፥4 ***ለስሙም፤*** የ5፥11 ማብ ይመ። ***በደመና ላይ የሚሄደውን፤*** ለከነዓናውያን አምላክ የተሰጠ የማዕረግ ስም ስለ መሆኑ በከነዓናውያን ሥነ ጽሑፍ ላይ ተመልክቶአል፤ በዚህ ቦታ ግን ጌታ (በዓል ሳይሆን ያህዌ) ደመናትን ሠረገላው ማድረግ

እጅግ ደስ ይበላችሁ።
5እግዚአብሔር በተቀደሰ ማደሪያው፣
ለድኻ አደጉ አባት፣ ለባልቴቲቱም
ተሟጋች ነው።
6እግዚአብሔር ብቸኞችን በቤተ ሰብ መካከል
ያኖራል፤[ሙ]
እስረኞችን ነጻ አውጥቶ ያስፈነድቃል፤
ዐመፀኞች ግን ምድረ በዳ ይኖራሉ።
7እግዚአብሔር ሆይ፤ በሕዝብህ ፊት በወጣህ
ጊዜ፣
በምድረ በዳም በተጓዝህ ጊዜ፣ ሴላ
8በሲና ስምባክ፣ በእግዚአብሔር ፊት፣
በእስራኤል ስምባክ፣ በእግዚአብሔር ፊት፣
ምድር ተንቀጠቀጠች፤
ሰማያትም ዶፍ አወረዱ።
9እግዚአብሔር ሆይ፣ በቂ ዝናብ አዘነብህ፤
ክው ያለውን ርስትህን አረሰረስህ።
10መንጋህ መኖሪያው አደረጋት፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ ከበረከትህ ለድኾች
ሰጠህ።
11ጌታ እንዲህ ሲል ቃሉን አስተላለፈ፤
ትእዛዙን የሚያውጁትም ብዙ ሰራዊት
ናቸው፤
12"የሰራዊት ነገሥታት ፈጥነው ይሸሻሉ፤
በሰፈር የዋሉ ሴቶችም ምርኮን
ተካፈሉ።

3፥18፤96፥2፤100፥4፤
135፥3
68፥5 ዘፀ22፥22፤ዘዳ
10፥18፤26፥15፤መዝ1
0፥14፤ኤር25፥30
68፥6 መዝ25፥16፤
79፥11፤102፥20፤113
፥9፤146፥7፤ኢሳ35፥7
፤49፥10፤58፥11፤
61፥1፤ሉቃ4፥18
68፥7 ዘፀ13፥21፤
መዝ78፥40፤106፥14
68፥8 ዘዳ33፥2፤
2ሳሙ21፥10፤22፥8፤
መሳ5፥4:5፤መክ11፥3
68፥9 ዘዳ32፥2፤ኢዮ
36፥28፤ሕዝ34፥26
68፥10 ዘዳ28፥12፤
መዝ65፥9
68፥11 ሉቃ2፥13
68፥12 ኢሱ10፥16፤
መሳ5፥30
68፥13 ዘፍ49፥14
68፥14 መሳ9፥48፤
2ሳሙ22፥15
68፥15 ቍ22፤ዘኍ
21፥33፤መዝ36፥6፤
ኤር22፥20
68፥16 ዘዳ12፥5፤
መዝ2፥6፤132፥13:14
68፥17 2ነገ2፥11፤
ኢሳ66፥15፤ዳን7፥10፤
ዕን3፥8
68፥18 ዘኍ17፥10
መሳ5፥12፤መዝ7፥7፤4
7፥5፤ኤፌ4፥8

13በበጎች በረት መካከል[ሠ] ብትገኙ እንኳ፣
ክብር እንደ ተሠሩ የርግብ ክንፎች፣
በቅጠልያ ወርቅ እንደ ተለበጡ ላባዎች
ናችሁ።"
14ሁሉን ቻዩ[ሬ] በዚያ የነበሩትን ነገሥታት
በበተነ ጊዜ፣
በሰልሞን እንደሚወርድ በረዶ
አደረጋቸው።
15አንተ ብርቱ ተራራ፣ የባሳን ተራራ ሆይ፤
አንተ ባለ ብዙ ጫፍ ተራራ፣ የባሳን
ተራራ፤
16እናንተ ባለ ብዙ ጫፍ ተራሮች ሆይ፤
እግዚአብሔር ሊኖርበት የመረጠውን
ተራራ፣
በእርግጥ እግዚአብሔር ለዘላለም
የሚኖርበትን ተራራ ለምን በምቀኝነት
ዐይን ታያላችሁ?
17የእግዚአብሔር ሠረገላዎች እልፍ አእላፍ
ናቸው፤
ሺህ ጊዜም ሺህ ናቸው፤
ጌታ ከሲና ወደ መቅደሱ ገባ።
18ወደ ላይ ዓረግህ፤
ምርኮ አጋበስህ፤

[ሙ]6 *ወይም ብቸኞችን በገዛ ምድራቸው*
[ሠ]13 *ወይም በኮርቻ ማስቀመጫዎች*
[ሬ]14 ዕብራይስጡ *ሻዳይ* ይላል።

የሚችል እውነተኛ አምላክ መሆኑን ለማመልከት ገብቶአል (ቍ 33፤ 18፥9፤ 104፥3፤ ኢሳ19፥1፤ ማቴ26፥64 ይመ)።

*68፥5-6፤* እግዚአብሔር የደካሞች ጠባቃ ነው (10፥14፤ 146፥7-9፤ 147፥6፤ ዘዳ10፥18 ይመ)።

68፥6 *ብቸኞችን በቤተ ሰብ መካከል ያኖራል፤* ዘፀ1፥21፤ ሩት 4፥14-17፤ 1ሳሙ2፥5 ይመ። *እስረኞችን ነጻ አውጥቶ ያስፈነድቃል፤* እስራኤልን ከግብፅ መርቶ እንዳወጣ ሁሉ ችግረኞችንም እንዲሁ ነጻ ያወጣል (69፥33፤ 107፥10:14 ይመ)። *ዐመፀኞች፤* የቍ18 እና 66፥7 ማብ ይመ። *ምድረ በዳ፤* ለአትክልት ማብቀያ የሚሆን ዐፈር እንኳን የሌለው ባድማ ቦታ ማለት ነው (ሕዝ 26፥4:14 ይመ)።

*68፥7-10፤* እግዚአብሔር ከሲና ተራራ ተነሥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር ያደረገውን ዘመቻ ያስታውሳል (መሳ5፥4-5፤ ዕን3፥3-6 ይመ)።

68፥8 *ምድር ተንቀጠቀጠች፤* በሲና ተራራ ላይ ደርሶ የነበረውን መንቀጥቀጥ የሚያወሳ ነው (ዘፀ19፥18)። *ሰማያትም ዶፍ አወረዱ፤* እስራኤላውያን በምድረ በዳ በሚቅበዘበዙበት ወቅት ዝናብ መዝነቡን የሚጠቍም ፍንጭ በአምስቱ የሙሴ መጽሐፍ ላይ ምንም አልተጻፈም፤ በዚህ ቦታ ግን (እንዲሁም በመሳ5፥4) ዝናብ ከምድር መናወጥ ጋር በመሆን የእግዚአብሔር ገናና ክብር መግለጫ ሆኖአል። ምናልባት "ነጐድጓድና መብረቅ ከከባድ ደመና ጋር በሲና ተራራ ላይ በወረደ ጊዜ" ዝናብም ዘንቦ ሊሆን ይችላል (ዘፀ19፥16)። በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝቡ በጕዞ ላይ ሳለ የሚያረሰርስ ዝናብ ዘንቦ እንደ ነበር ቍ9 ይጠቍማል።

68፥9 *ክው ያለውን ርስትህን፤* የእስራኤልን ሕዝብ ለማለት ነው (ዘዳ9፥29 ይመ)።

68፥10 *አደረጋት፤* የተስፋይቱን ምድር ሳያመለክት አይቀርም። *ከበረከትህ፤* በቀጥታ ሲተረጐም "ከበጎነትህ" ማለት ነው (65፥11 እና ማብ ይመ)። *ሰጠህ፤* ከከነዓን ምርት (ኢሱ5፥11-12 ይመ)። *ለድኾች፤* እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርገውን የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል።

*68፥11-14፤* እግዚአብሔር በከነዓን ነገሥታት ላይ የተቀዳጃቸውን ድሎች ያስታውሳል።

68፥11 *ቃሉን አስተላለፈ፤* እግዚአብሔር የከነዓንን ነገሥታት እንደሚያሸንፍ አስቀድሞ በይፋ አስታውቆአል (ዘፀ23፥22-23:27-28:31፤ ዘዳ7፥10-24፤ 11፥23-25፤ ኢሱ1፥2-6 ይመ)። *አስተላለፈ፤* የእግዚአብሔርን የድል ዜና ያውጃሉ (ዘፀ15፥1-21፤ 1ሳሙ 18፥6-7፤ 2ዜና20፥26-28 ይመ)። *የሚያውጁትም፤* 40፥9 እና ማብ ይመ።

68፥13 *በበጎች በረት መካከል ብትገኙ እንኳ፤* በምሽግ ብታርፉም ለማለት ነው (መሳ5፥16 ይመ)። *የርግብ ክንፎች ... ተለበጡ ... ናችሁ፤* የእግዚአብሔር "ርግብ" የሆነችው እስራኤል (74፥19 እና ማብ ይመ፤ ከሆሴ7፥11 ጋር ያነጻጽሩ)፣ በምሽግ ውስጥ እንቅልፍ ቢወስዳትም እንኳ ከከነዓን ነገሥታት በተበዘበዘው ምርኮ በወርቅና በብር አጊጣለች። ይህ በቅኔ የጓን ፈሊጣዊ አነጋገር እስራኤል ለጦርነት ከመውጣቷ በፊት እግዚአብሔር ነገሥታትን ድል ማድረጉን በማስታወስ ያወድሳል (ኢሱ2፥8-11፤ 5፥1፤6፥16 እንዲሁም 2ሳሙ5፥24፤ 2ነገ7፥5-7፤ 19፥35፤ 2ዜና 20፥22-30 ይመ)።

68፥14 *ሁሉን ቻይ፤* የዘፍ17፥1 ማብ ይመ። *በሰልሞን እንደሚወርድ በረዶ፤* ሰልሞን በሴኬም አቅራቢያ ያለ ተራራ ነው (መሳ9፥46-48 ይመ)፤ አንዳንዶች ግን የቢል ድሩዝ ከሚባለውና ከባሳን በስተ ምሥራቅ ከሚገኘው ጥቍር የእሳተ-ገሞራ ተራራ ጋር ያመሳስሉታል፤ የስሙም ትርጕም "ጥቍር" ማለት ነው፤ ይህ ተራራ ከነጭ የብሓ ድንጋይ ከተሠራው የሊባኖስ (ነጭ) የተራራ ሰንሰለት በጣም የሚለይ ሲሆን፣ ንጽጽሩም በጥቍር ተራራ ላይ የተረጨ ነጭ በረዶ ይመስላል። ይህም ነገሥታት ጥለውት የሄዱትንና ሚዳውን ሁሉ የሸፈነውን የጦር መሣሪያ የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም (2ነገ7፥15 ይመ)።

*68፥15-18፤* የእግዚአብሔርን ወደ ጽዮን ተራራ መውጣት የሚያወድስ ነው።

*68፥15-16፤* በባሳን ተራራ ዙሪያ ያሉት ተራሮችና ረጅሙም የአርሞንኤም ተራራ እንኳ ሳይቀር እግዚአብሔር የጽዮንን ተራራ "ከፍ ያለች ተራራ" (የ48፥2 ማብ ይመ) እና የመንግሥቱም መንበር አድርጐ ስለ መረጣት፣ በዙሪያዋ ያሉ ተራሮች ሁሉ በቅናት ዐይን እንዲመለከቷት ተደርጐ ተገልጾአል።

68፥17 *የእግዚአብሔር ሠረገላዎች፤* በሰማይ ያለውን የእግዚአብሔርን ሰራዊት የሚገልጽ ሲሆን፣ በዚህ ቦታ ግን ከእልፍ አእላፋት ሰራዊቶች ኀይል ጋር ተያይዞአል (2ነገ6፥17፤ ዕብ 3፥8:15 ይመ)። ሮማውያን ዓለምን በሚገዙበት ሰዓት ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ሰራዊት የገለጸው "ሌጌዎን" (ማቴ26፥53) በሚለው ስያሜ ነው።

68፥18 *ወደ ላይ በወጣህ ጊዜ፤* ወደምትነግሥባት ወደ ጽዮን ተራራ ላይ ለማለት ነው (47፥5-6 እና ማብ፤ እንዲሁም 7፥7 ይመ)። *ምርኮ አጋበስህ ... ስጦታን ተቀብለህ፤* ብርቱ

እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፤ አንተ[ሀ] በዚያ
ትኖር ዘንድ፣
ከዐመፀኞችም ሳይቀር፣
ከሰዎች ስጦታን ተቀበልህ።
19ሸክማችንን በየዕለቱ የሚሸከምልን፣
አዳኝ አምላካችን፣ ጌታ ይባረክ። ሴላ
20አምላካችን የሚያድን አምላክ ነው፤
ከሞት ማምለጥ የሚቻለውም በጌታ
በእግዚአብሔር ነው።
21በእርግጥ እግዚአብሔር የጠላቶቹን ራስ፣
በኀጢአታቸውም የሚጸኑትን ሰዎች
ጠጕራም አናት ይፈነካክታል።
22ጌታ እንዲህ ይላል፤ "ከባሳን መልሼ
አመጣቸዋለሁ፤
ከባሕርም ጥልቀት አውጥቼ
አመጣቸዋለሁ፤
23እግርህ በጠላትህ ደም ውስጥ
እንዲጠልቅ፣
የውሻህም ምላስ ከጠላትህ ድርሻውን
እንዲያገኝ ነው።"
24አምላክ ሆይ፤ የክብር አካሄድህ ታየ፤
ይህም አምላኬና ንጉሤ ወደ ቤተ መቅደሱ
የሚያደርገው የክብር አካሄድ ነው።
25መዘምራን ከፊት፣ መሣሪያ የሚጫወቱ
ከኋላ ሆነው ሲሄዱ፣
ከበሮ የሚመቱ ቈነጃጅትም
በመካከላቸው ነበሩ።
26እግዚአብሔርን በጉባኤ አመስግኑት፤
ከእስራኤል ምንጭ የተገኛችሁ እግዚ
አብሔርን አመስግኑ።
27የሚመራቸው ትንሹ ብንያም ነው፤
በዚያ በብዙ የሚቈጠሩ የይሁዳ
መሳፍንት፣
እንዲሁም የዛብሎንና የንፍታሌም
መሳፍንት ይገኛሉ።
28እግዚአብሔር ሆይ፤ ኀይልህን እዘዝ፤[ለ]
አምላክ ሆይ ቀድሞ እንዳደረግህልን
አሁንም ብርታትህን አሳየን።
29በኢየሩሳሌም ስላለው ቤተ መቅደስህ፣
ነገሥታት እጅ መንሻ ያመጡልሃል።
30በሸምበቆ መካከል ያሉትን አራዊት፣
በሕዝቡ ጥጆች መካከል ያለውንም
የኮርማ መንጋ ገሥጽ፤
ብር ይገብር ዘንድም ይንበርከክ፤
ጦርነትን የሚወዱ ሕዝቦችንም
በትናቸው።
31መኳንንት ከግብፅ ይመጣሉ፤
ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር
ትዘረጋለች።
32የምድር መንግሥታት ሆይ፤
ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤
ለጌታ ተቀኙ። ሴላ
33ከጥንት ጀምሮ ከነበሩት ሰማያት በላይ
ለወጣው፣
በኀያል ድምፁ ለሚያስገመግመው ዘምሩ።

[ሀ]18 ወይም አናንተ
[ለ]28 ብዙ የዕብራይስጥ ቅጆች፣ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕምና የሱርስቱ ቅጅ እግዚአብሔር ሆይ፤ ኀይልህን ጥራ ይላሉ። አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን እግዚአብሔር ለአንተ ኀይል ይጠራልሃል ይላሉ።

68፥19 መዝ65፥5፤ 81፥6
68፥20 1ሳሙ10፥19፤ መዝ56፥13፤ ኤር45፥5፤ ሕዝ6፥8
68፥21 መዝ74፥14፤ 110፥5፤ ዕን3፥13
68፥22 ኢዮ36፥30፤ ማቴ18፥6
68፥23 1ነገ21፥19፤ 2ነገ9፥36፤ መዝ58፥10
68፥24 መዝ63፥2
68፥25 ዘፍ31፥27፤ 1ዜና6፥31፤15፥16፤2ዜና5፥12፤ ኢሳ5፥12፤ ራዕ18፥22
68፥26 ዘሌ19፥2፤ መዝ22፥22፤ ዕብ2፥12
68፥27 ዘኍ34፥21፤ መሳ5፥18፤ 1ሳሙ9፥21
68፥28 ዘፀ9፥16፤ መዝ29፥11፤ ኢሳ26፥12፤29፥23፤45፥11፤60፥21፤64፥8
68፥29 2ዜና9፥24፤ 32፥23
68፥30 ኢዮ40፥21፤ መዝ18፥14፤22፥12፤89፥10፤120፥7፤140፥2፤ ኢሳ27፥1፤34፥7፤51፥9፤ ኤር50፥27፤ ሕዝ29፥3
68፥31 ኢሳ11፥11፤ 18፥1፤19፥19፤43፥3፤ 45፥14፤ ሶፎ3፥10
68፥32 መዝ7፥17፤ 46፥6፤67፥4
68፥33 ዘፀ9፥23፤ ዘዳ33፥26፤ መዝ29፥3፡4፤ ኢሳ30፥30፤33፥3፤ 66፥6

ንጉሥ ጠላቶቹን ሁሉ ከሰባበረና ካንበረከከም በኋላ በጦር ሜዳ ላይ እንደሚያደርገው ዐይነት ማለት ነው። *ከዐመፀኞች፤* የእግዚአብሔርን መንግሥት ሲቃወሙ የነበሩት እንኳን (ቍ6 እና የ66፥7 ማብ ይመ) ለእግዚአብሔር ይገዛሉ፤ የእጅ መንሻም ይዘውለት ይመጣሉ። *አንተ በዚያ ትኖር ዘንድ፤* በሰዋስው ረገድ ከተመለከትነው "ወደ ላይ በወጣህ ጊዜ" ለሚለው ሐረግ እንደ ማሰሪያ በመሆን ያገለግላል። ጳውሎስ ይህንን ጥቅስ (በሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ላይ የተተረጐመውን) ወደ ሰማይ ላረገው ለክርስቶስ ተጠቅሞበታል (ኤፌ4፥8-13)፤ በዚህም መሠረት የክርስቶስ ዕርገት እግዚአብሔር በመናገሻ ከተማው በኢየሩሳሌም ለመሠረተው መንግሥት ቀጣይና ፍጻሜም እንደ ሆነ አመልክቶአል።

*68፥19-23፤* የእግዚአብሔር ብርቱ ክንድ የሕዝቡ መዳን እስኪፈጸም ድረስ የሚቀጥል መሆኑን በደስታ ይገልጻል።

68፥19 *ሸክማችንን ... ለሚሸከምልን፤* በጠላት እጅ በመውደቃችን ምክንያት ጠላቶቻችን ካሸከሙን ሸክም ይታደገናል (81፥6፤ ኢሳ9፥4፤ 10፥27 ይመ)። አንዳንድ ሰዎች ግን ይህንን ጥቅስ ከ55፥22 እና ከኢሳ46፥4 ጋር ያዛምዱታል።

68፥20 *ከሞት ማምለጥ፤* በጠላት አማካይነት ከሚደርስብን ሞት ወይም ከመጨረሻው ሞት እንደ ማለት ነው (የ6፥5፤ 11፥7፤ 16፥9-11፤ 17፥15፤ 49፥14-15 ማብ ይመ)።

*68፥21፤* እግዚአብሔር የሕዝቡን ሕይወት አስተማማኝ በሚያደርግበት ወቅት (ቍ20 ይመ) እርሱን የሚቃወሙትን ሁሉ ይፈረካክሳቸዋል። ... *አናት ይፈነካከታል፤* ዘኍ24፥17 ይመ።

68፥22 *አመጣቸዋለሁ፤* ከእግዚአብሔርና ከሰራዊቱም ፊት ሸሽተው የሄዱትን ጠላቶች ማለት ነው (ቍ12፡17 ይመ)። *ከባሳን ... ከባሕርም ጥልቀት፤* የመጀመሪያው (ቍ15 ይመ) ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ የሚገኝ ተራራማ ቦታ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሜድትራኒያን ባሕር ነው፤ በዚያም ሆነ በዚህ ጠላት ከቶ ሊያመልጥ አይችልም (አሞ9፥1-4 ይመ)።

*68፥23፤* የ58፥10 ማብ ይመ።

*68፥24-27፤* ሰልፉ ወደ ቤተ መቅደሱ በመቃረብ ላይ ነው (መዝ24፥47 ይመ)።

68፥25 *ከበሮ የሚመቱ ቈነጃጅትም፤* የኤር31፥4 ማብ ይመ።

*68፥27፤* ከትንሹ ከብንያም ጀምሮ እስከ ኀይለኛው እስከ ይሁዳ ድረስ፣ በሰሜንና በደቡብ የሚገኙ የእስራኤል ነገዶች ሁሉ ተወክለዋል። *የሚመራቸው ... ብንያም፤* የእስራኤልን ጠላቶች በመምታት ድልን መቀዳጀት የተጀመረው (1ሳሙ11፥11፤ 14፥20-23 ይመ)፣ የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ (ሳኦል) ከብንያም ወገን መሆኑን የሚያንጸባርቅ ሳይሆን አይቀርም።

*68፥28-31፤* እግዚአብሔር፣ ዘወትር የሚያስጨንቁ ጠላቶችን ድል ማድረጉን እንዲቀጥል የቀረበ ጸሎት ነው።

68፥28 *ኀይልህን እዘዝ፤* ወይም "ብርቱ ክንድህን አንሣ" ሊባል ይችላል።

68፥29 ... *ስላለው ቤተ መቅደስህ፤* ቤተ መንግሥትህ በኢየሩሳሌም ስለ ተመሠረተ ማለት ነው። *እጅ መንሻ ያመጡልሃል፤* ድል የተመቱ ነገሥታት ድል ለመታቸው ንጉሥ ስጦታን እንደሚያመጡ ሁሉ፣ ለአንተም ግብር በረከት በማምጣት ድል አድራጊነትህን ያጸናሉ (2ሳሙ8፥2፡6፡10፤ 2ነገ3፥4 ይመ)።

68፥30 *ገሥጽ፤* የ76፥6 ማብ ይመ። *በሸምበቆ መካከል ያሉትን አራዊት፤* ፈርዖንን ለማለት ነው (ሕዝ29፥3 ይመ)። *ጥጆች መካከል ያለውንም የኮርማ መንጋ፤* ፈርዖንን የሚያገለግሉ ኀያላን፣ ልዑላንና የሌሎች አገሮችን ደካማ ልዑላን ያመለክታል። በዚህ ቦታ ግብፅ ዐመፀኛ ነገሥታትን ወክላ ቆማለች፤ ይህም የሆነው እስራኤል በአንድ ወቅት በዓለም ላይ ኀያላን መንግሥት ከነበረችው ከግብፅ ጋር በነበራት ግጠሚኛና መዝሙሩም በተደረሰ ጊዜ ከእስራኤል አጎራባች አገሮች ውስጥ ግብፅ ታላቋ አገር በመሆኗ ነው። *ሕዝቦችንም በትናቸው፤* ቍ1 ይመ፤ እስራኤል በሰላም ትኖር ዘንድ (46፥9፤ 48፥4-7፤ 65፥7፤ 76፥3 ይመ) ነው።

*68፥32-35፤* የቅዳሴው ሰልፍ የመጨረሻው ደረጃ ላይ ደርሶአል፤ በዚህ ቦታ የዓለም መንግሥታት ሁሉ ወደ ሰማየ ሰማያት ለወጣውና በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ መኖሪያውን ላደረገው ለእስራኤል አምላክ ምስጋና እንዲያቀርቡ ጥሪ ተደርጎአል (መዝ47 ይመ)።

*68፥33፤* ቍ4 እና ማብ ይመ። *በኀያል የነጐድጓድ ድምፁ፤* የ29፥3-9 ማብ ይመ።

34ግርማው በእስራኤል ላይ፣
ኀይሉም ከደመናት በላይ ነው፣
ለእግዚአብሔርን ብርታት የአንተ ነው
በሉት::
35እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ በመቅደስህ ድንቅ
ነህ፤
የእስራኤል አምላክ ለሕዝቡ ኀይልና
ብርታትን ይሰጣል::

እግዚአብሔር ይባረክ!

## መዝሙር 69

### እንጕርጕሮ

*ለመዘምራን አለቃ፤ በ"ጽጌረዳ" ዜማ፤ የዳዊት መዝሙር*

1አምላክ ሆይ፤ አድነኝ፤
ውሃ እስከ ዐንገቴ ደርሶብኛልና::
2የእግር መቆሚያ በሌለው፣
በጥልቅ ረግረግ ውስጥ ሰጥሜአለሁ፤
ወደ ጥልቅ ውሃ ገባሁ፤
ሞገዱም አሰጠመኝ::
3በጩኸት ደከምሁ፤
ጕሮሮዬም ደረቀ፤
አምላኬን በመጠባበቅ፣
ዐይኖቼ ፈዘዙ::
4ያለ ምክንያት የሚጠሉኝ፣
ከራሴ ጠጕር በዙ፤
ሕይወቴን ለማጥፋት የሚፈልጉ፣
በከንቱም የሚጠሉኝ ብዙዎች ሆኑ፤
ያልሰረቅሁትን ነገር፣
መልሰህ አምጣ ተባልሁ::
5እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ሞኝነቴን
ታውቃለህ፤
በደሌም ከአንተ የተሰወረ አይደለም::
6ጌታ የሰራዊት አምላክ ሆይ፤
አንተን ተስፋ የሚያደርጉ፣
በእኔ ምክንያት አይፈሩ፤
የእስራኤል አምላክ ሆይ፤
አንተን አጥብቀው የሚሹ፣
ከእኔ የተነሣ አይዋረዱ::
7ስለ አንተ ስድብን ታግሻለሁና፤
እፍረትም ፊቴን ሸፍኖአልና::
8ለወንድሞቼ እንደ ባዕድ፣
ለእናቴም ልጆች እንደ እንግዳ
ሆንሁባቸው::
9የቤትህ ቅናት በላችኝ፤
የሚሰድቡህም ስድብ በላዬ ዐርፎአል::
10ነፍሴን በጾም ባስመረርሁ ጊዜ፣
እነርሱ ሰደቡኝ::
11ማቅ በለበስሁ ጊዜ፣
መተረቻ አደረጉኝ::
12በቅጥሩ ደጅ ለሚቀመጡት
የመነጋገሪያ ርእስ፣
ለሰካራሞችም መዝፈኛ ሆንሁ::
13እግዚአብሔር ሆይ፤ እኔ ግን
በወደድኸው ሰዓት፣
ወደ አንተ እጸልያለሁ፤

68፥34 ቍ28፤ መዝ45፥3
68፥35 ዘፍ28፥17፤ ዘዳ7፥21፤መዝ28፥6፤ 29፥11፤18፥1፤66፥20 ፤ኢሳ40፥29፤41፥10፤ 50፥2፤2ቆሮ1፥3
69፥1 መዝ32፥6፤ 42፥7፤ዮና2፥5
69፥2 ኢዮ30፥19
69፥3 መዝ6፥6፤ 119፥82
69፥4 መዝ25፥19፤ 35፥19፤38፥19፤40፥1 4፤119፥95፤ኢሳ 32፥7፤ዮሐ15፥25
69፥5 መዝ38፥5፤ 44፥21
69፥7 መዝ39፥8፤ 44፥15፤ኤር15፥15
69፥8 ኢዮ19፥13-15፤መዝ31፥11፤38፥ 11፤ኢሳ53፥3፤ዮሐ7፥5
69፥9 መዝ89፥50-51፤ዮሐ2፥17፤ሮሜ 15፥3
69፥10 መዝ35፥13
69፥11 2ሳሙ3፥31 ፤መዝ35፥13
69፥12 ዘፍ18፥1፤ 23፥10፤ኢዮ30፥9
69፥13 መዝ17፥7፤ 51፥1፤ኢሳ49፥8፤ 2ቆሮ6፥2

68፥35 *ድንቅ፤* 45፥4 እና ማብ ይመ:: *ለሕዝቡ ኀይልና ብርታትን ይሰጣል፤* የፍጥረት ሁሉ ጌታ እስራኤልን የራሱ ሕዝብ አድርጎአል (ዘፀ19፥5-6 ይመ)፤ በሕዝቡም መካከል አገዛዙን በማ ድረጉ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን የድል አድራጊነት ኀይል እንዲለ ማመድ አድርጕታል (29፥10-11 ይመ)::

*መዝ69፤* እግዚአብሔር ምሕረቱን እንዲያሳየውና የብዙ ጠላ ቶችም መዘባበቻ እንዳይሆን ቤዛ ሆኖ እንዲያድነው ያቀረበው ልመና ነው፤ ይህን ልመና ያቀረበው፣ በሠራው በደል ምክንያት (ቍ5 ይመ) እግዚአብሔር፣ "ያቈሰለው"(ቍ26 ይመ) እና ጠላቶ ቹም ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ኀይላቸውን አሰባስበው የሚያፌ ዙበትና የሚያሜኑበት አንድ እግዚአብሔርን የሚፈራ ንጉሥ ነው:: በጥንት ታሪክ እንደሚታወቀው ከሆነ የዚህ መዝሙር ደራሲ ዳዊት ሲሆን፣ መዝሙሩ መቼ እንደ ተደረሰ ግን አይታወቅም:: በመዝሙሩ ውስጥ የቀረበው ጸሎት አሁን ባለው ቅርጽ እን ደሚያመለክተው ይሁዳን ይገዛ የነበረው የዳዊት ልጅ በነበረበት ወቅት የተጻፈ ነው (ቍ35 ይመ):: ያም ንጉሥ ሕዝቅያስ ሳይሆን አይቀርም (2ነገ18-20፤ 2ዜና29-32 ይመ):: በዐቢይ ሐሳ ብና በቋንቋ ረገድ ይህ መዝሙር ከመዝሙር 32፤35፤38፤40 እና 109 ጋር በብዙ መልኩ ይዛመዳል (መዝ18 ይመ):: ከአስጨ ናቂ ጠላቶች እጅ ለመዳን ከቀረቡት ሦስት ተከታታይ መዝሙ ሮች ውስጥ ይህ መዝሙር የመጀመሪያው ነው:: የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች እንዲህ ያለው የጻድቃን ጩኸት የክርስቶስን ሥቃይ እንደሚያሳይ አስታውቀዋል፤ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከመዝ 22 በስተ ቀር ብዙ ጊዜ የተጠቀሰ አንድም መዝሙር የለም::

69ርእስ፤ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ4 ርእስ ማብ ይመ:: *በ ... ዜማ፤* የመዝ9 ርእስ ማብ ይመ:: *ጽጌረዳ፤* የመዝ45 ርእስ ይመ::

*69፥1-4፤* እግዚአብሔር እንዲያድነው በመግቢያው ላይ ያቀረበው ልመና ነው::

69፥1-2 *ውሃ ... በጥልቅ ረግረግ ... ጥልቅ ውሃ ... ሞገዱም፤* ብርቱ ጭንቀትን ለመግለጽ የሚውሉ የተለመዱ አባባሎች ናቸው (የ30፥1 እና 32፥6 ማብ ይመ):: በዚህ ቦታ ጭንቀቱ የደረሰበት እግዚአብሔር "ያቈሰለው" (ቍ26) ሲሆን በጠላቶቹ በኩል የደረሰበት ጥቃት ግን ከሁሉ የበለጠ ነው (ቍ14-15፡29 ይመ)::

69፥3 *ጕሮሮዬም ደረቀ፤* 22፥15 ይመ:: *ዐይኖቼ ፈዘዙ፤* 6፥7 እና ማብ ይመ::

69፥4 *ያለ ምክንያት ... በከንቱም፤* ምንም ያልበደላቸው ሰዎች አሳሩን አበዙበት (35፥19 እና ማብ ይመ):: *ከራሴ ጠጕር ብዙ፤* የ40፥12 ማብ ይመ:: *ተገደድሁ፤* ጠላቶቹ በሐሰት ስሙን እያጠፉት እንደ ሆነ የሚናገር ሥዕላዊ አገላለጽ ነው (5፥9 እና ማብ ይመ)::

*69፥5-12፤* እግዚአብሔር አገልጋዩን በሚቀጣበት ጊዜ ሌሎች እግዚአብሔርን በመተማመን የሚኖሩ በሁኔታው እንዳ ይሰናከሉ ይጸልያል:: ጸሐፊው እግዚአብሔር፣ "በቍስል" የመታው (ቍ26) በሠራው በደል ምክንያት መሆኑን አምኖአል (ቍ5)፤ ይሁን እንጂ ጠላቶቹን አንድም ጊዜ አልበደለም:: ከደረሰበት መከራ ጠላቶቹ የተነሣ "አንተን ብሎ የእግዚአብሔር ሰው" እያሉ አላገጡበት (22፥6-8፤ 42፥3፤ 79፥10፤ 115፥2፤ ኢዮ2፥9 ይመ):: በግልጽ ባይሆንም እግዚአብሔር መልሶ እንዲያቆመውና ንጹሕ መሆኑንም በጠላቶቹ ፊት እንዲመሰክርለት ይጸልያል::

69፥5 *ሞኝነቴን፤* በዚህ ቦታ ሞኝነት የሥነ-ምግባር ጕድለትን ያመለክታል::

*69፥8፤* የቅርብ ወዳጆቹ እንኳ ሸሹት (31፥11-12 እና ማብ ይመ)::

69፥9 *የቤትህ ቅናት በላችኝ፤* በደራሲው ላይ ያደረበት ቅንዓት በኢየሱስም ላይ በበለጠ አድሮአል (ዮሐ2፥17 ይመ):: *የሚሰድቡህም ስድብ፤* እግዚአብሔርን የሚሰድቡ በእግዚአብሔር ላይ የሚታመነውን አገልጋይም ይሰድባሉ (74፥18፡22-23፤ 2ነገ 18፥31-35 ይመ)፤ ይህም በኢየሱስ ላይ ደርሶአል (ሮሜ15፥3 ይመ)::

69፥10-11 *በጾም ባስመረርሁ ጊዜ ... ማቅ በለበስሁ ጊዜ፤* እግዚአብሔር እንዲምረውና እንዲታደገው በሚጸልይበት ጊዜ ራሱን በእግዚአብሔር ፊት በንስሓ ዝቅ አድርጎ መቅረቡን የሚገልጹ ምልክቶች ናቸው (35፥13 እና ማብ፤ እንዲሁም ዘፍ 37፥34፤ 2ሳሙ12፥16-17፤ኢዮ1፥13-14፤2፥15-17፤ዮና3፥5 ይመ)::

69፥12 *በቅጥሩ ደጅ ለሚቀመጡት ... ለሰካራሞችም፤* ከከተማ ሹሞች ጀምሮ እስከ ሰካራሞች ድረስ ሁሉም መሣቂያ መሣለቂያ አድርገውታል::

*69፥13-18፤* ቢያፌዙብኝም እንኳ ወደ አንተ እጸልያለሁ::

69፥13 *በወደድኸው ሰዓት፤* እግዚአብሔር ሊያድነው ቀርቦ

ስምዓከ ሆይ፤ በታላቅ ምሕረትህ፣
በማዳንህም እርግጠኝነት መልስልኝ::
[14]ከረግረግ አውጣኝ፤
እስጥም ዘንድ አትተወኝ፤
ከጥልቅ ውሃ፣
ከእነዚያ ከሚጠሉኝ ታደገኝ::
[15]ጐርፍ አያጥለቅልቀኝ፤
ጥልቅ ውሃም አይዋጠኝ፤
ጕድጓዱም ተደርምሶ አይዘጋብኝ::
[16]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ምሕረትህ በጎ ናትና
ስማኝ፤
እንደ ርኅራኄም ብዛት መለስ በልልኝ::
[17]ፊትህን ከባሪያህ አትሰውር፤
ጭንቅ ውስጥ ነኝና ፈጥነህ መልስልኝ::
[18]ወደ እኔ ቀርበህ ታደገኝ፤
ስለ ጠላቶቼም ተቤዠኝ::
[19]የደረሰብኝን ስድብ፣ ዕፍረትና ውርደት
ታውቃለህ፤
ጠላቶቼንም አንድ በአንድ
ታውቃቸዋለህ::
[20]ስድብ ልቤን ጕድቶታል፤
ተስፋዬም ተሟጦአል፤
አስተዛዛኝ ፈለግሁ፤ አላገኘሁምም፤
አጽናኝም ፈለግሁ፤ አንድም አልነበረም::
[21]ምግቤን ከሐሞት ቀላቀሉ፤
ለጥማቴም ሆምጣጤ ሰጡኝ::
[22]የቀረበላቸው ማዕድ ወጥመድ
ይሁንባቸው፤

69፥14 ቍ21፤መዝ 144፥7
69፥15 ዘኍ16፥33፤ መዝ28፥1፤124፥4-5
69፥16 መዝ63፥3
69፥17 መዝ22፥24፤ 50፥15፤66፥14፤ 143፥7
69፥18 መዝ49፥15
69፥19 መዝ22፥6
69፥20 ኢዮ16፥2፤ መዝ142፥4፤ኢሳ63፥5
69፥21 ዘኍ6፥3፤ ማቴ27፥34:48፤ማር 15፥23:36፤ሉቃ23፥ 36፤ዮሐ19፥28-30
69፥22 1ሳሙ28፥9 ፤ኢዮ18፥10
69፥23 ሮሜ11፥9-10
69፥24 መዝ79፥6፤ ኤር10፥25
69፥25 ዘሌ26፥43፤ ማቴ23፥38፤ሐሥ 1፥20
69፥26 ኢዮ19፥22፤ ዘካ1፥15
69፥27 ነህ4፥5፤መዝ 109፥14
69፥28 ዘፀ32፥32-33፤ሕዝ13፥9፤ሉቃ 10፥20
69፥29 መዝ20፥1
69፥30 መዝ28፥7፤ 34፥3
69፥31 መዝ50፥9-13፤51፥16
69፥32 መዝ22፥26

ለማኅበራቸውም አሽክላ ይሁን::
[23]ዐይኖቻቸው እንዳያዩ ይጨልሙ፤
ጀርባቸውም ዘወትር ይጕበጥ::
[24]መዓትህን በላያቸው አፍስስ፤
የቍጣህም መቅሠፍት ድንገት
ይድረስባቸው::
[25]ስፈራቸው ባድማ ይሁን፤
በድንኳኖቻቸው የሚኖር አይገኝ፤
[26]አንተ የመታኻቸውን አሳደዋልና፤
ያቈሰልኻቸውንም ሥቃያቸውን
አባብሰዋል::
[27]በበደላቸው በደል ጨምርባቸው፤
ወደ ጽድቅህም አይግቡ::
[28]ከሕይወት መጽሐፍ ይደምሰሱ፤
ከጻድቃንም ጋር አይጻፉ::
[29]ነገር ግን እኔ በሥቃይና በጭንቅ ላይ
እገኛለሁ፤
ስምዓከ ሆይ፤ ማዳንህ ደግፎ ይያዘኝ::
[30]የእግዚአብሔርን ስም በዝማሬ አወድሳለሁ፤
በምስጋናም ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ::
[31]ከበሬ ይልቅ፣
ቀንድና ጥፍር ካበቀለ እምቦሳም ይልቅ
ይህ *እግዚአብሔርን* ደስ ያሰኘዋል::
[32]ድኾች ይህን ያያሉ፤ ደስም ይላቸዋል፤
እናንተ እግዚአብሔርን የምትሹ ልባችሁ
ይለምልም!
[33]*እግዚአብሔር* ችግረኞችን ይሰማልና፤
በእስራት ያለውንም ሕዝቡን አይንቅም::

ሳለ ለማለት ነው (32፥6 እና ማብ እንዲሁም ኢሳ49፥8፤ 61፥2፤ 2ቆሮ6፥2 ይመ):: *በታላቅ ፍቅርህ፤* የ6፥4 ማብ ይመ::

69፥14-15 *ከረግረግ ... ከጥልቅ ውሃ ...ጐርፍ ... ጥልቀቱ፤* የቍ1-2 ማብ ይመ::

69፥15 *አይዋጠኝ፤* የ49፥14 ማብ ይመ:: *ጕድጓዱ፤* የ30፥1 ማብ ይመ::

69፥16 *ምሕረትህ፤* የ6፥4 ማብ ይመ::

69፥17 *ፊትህን ... አትሰውር፤* የ13፥1 ማብ ይመ::

69፥18 *ተቤዠኝ፤* የ25፥22 ማብ ይመ::

*69፥19-21፤* በመከራዬ ጊዜ እኔን በማጽናናት ፈንታ ሊሳለቁብኝና ሊያፌዙብኝ ከያሉበት ተሰበሰቡ (35፥11-16፤ 142፥4፤ ኢዮ 13፥4፤ 16፥2፤ 21፥34 ይመ)::

69፥20 *ልቤን፤* የ4፥7 ማብ ይመ::

69፥21 *ምግቤን ከሐሞት ... ለጥማቴም ሆምጣጤ፤* የሚያጽናናና እርሱን የሚያበረታታ ተስፋ በሚጠባበቅበት ሰዓት፣ ጠላቶቹ በሚበላውና በሚጠጣው ምግብ ውስጥ መራራ ነገር ቀላቅለው እንዲበላ እንዳደረጉት የሚያሳይ ምስል ከሣች ተምሳሌት ነው:: የወንጌል ጸሐፊዎች በተለይም ማቴዎስ በዚህ ቍጥር ላይ የጠቀሰው መከራ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ያሳለፈውን መከራ እንደሚያመለክት ገልጸአል (ማቴ27፥34:48፤ ማር15፥23:36፤ ሉቃ23፥36፤ ዮሐ19፥29 ይመ)::

*69፥22-28፤* እግዚአብሔር ጠላቶቹን እንዲበቀልለት ያቀረበው ነው (የ5፥10 ማብ ይመ)::

*69፥22-23፤* ጳውሎስ ይህንን ክፍል ክርስቶስን ከተቃወሙ አይሁዶች ጋር እንዴት እንዳዛመደው ለማየት ሮሜ11፥9-10 ይመ::

*69፥22፤* በምግቡ ላይ፣ "ሐሞት" በመጠጡም ላይ፣ "ሆምጣጤ" ጨምረው አቀረቡለት (ቍ21):: *የቀረበላቸው ማዕድ፤* የቃል ኪዳኑ ማኅተም የታተመበትን ገበታ (የ23፥5 ማብ ይመ) የሚያመለክት ሊሆን ይችላል:: ነገሩ እንዲህ ከሆነ ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር ማዕዳቸው ፍዳቸውን የሚቀበሉበት እንዲያደርገው የሚናገር ሳይሆን አይቀርም::

*69፥23፤* በመቍሰሉ አላግጠውበት ነበር (ቍ26)፤ አሁን ግን የእነርሱም ጀርባ እንዲጕብጥና (መዝ38፥5-8) ዐይናቸውም እንዲፈዝ (ቍ3 እና የ6፥7 ማብ ይመ) ይመኛል:: *ጀርባቸውም ... ይጕብጥ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "ሽንጦቻቸው ስፍራ ይልቀቁ" እንደ ማለት ነው፤ "ሽንጥ" ሆድን ወይም የታችኛውን የጀርባ ክፍል ያመለክታል፤ ሽንጥ ለጀርባ የጥንካሬ ምንጭ ነው (66፥11፤ ኢዮ40፥16 ይመ)::

69፥24 *መዓት ... ቍጣ፤* የ2፥5 ማብ ይመ:: *አፍስስ፤* እንደ ድንገተኛ ጐርፍ ማለት ነው::

*69፥25፤* ከስፍራው ለማስለቀቅ አሢረው ነበር፤ አሁን ግን እነርሱ ራሳቸው ከስፍራቸው እንዲለቁ ይጸልያል፤ ይህንኑ የፍርድ ቃል ጴጥሮስ ለይሁዳ ተጠቅሞበታል (ሐሥ1፥20)::

*69፥26፤* ጠላቶቹ ካደረሱበት ጥቃት ሁሉ ከፍተኛ በመሆኑ በተደጋጋሚ ጠቅሶታል::

*69፥27፤* በሐሰት ወንጅለውታል (ቍ4)፤ እነርሱም በሠሩት በደል ይወንጀሉ::

*69፥28፤* እንዲሞት አሢረውበታል፤ የእነርሱም ዕጣ ፈንታ ሞት ይሁን፤ *ከሕይወት መጽሐፍ፤* እግዚአብሔር በሕይወት እንዲኖሩ የባረካቸው ሰዎች ስማቸው የሚጻፍበት የእግዚአብሔር መዝገብ ነው (1፥3፤ 7፥9፤ 11፥7፤ 34፥12፤ 37፥17:29፤ 55፥22፤ 75፥10፤ 92፥12-14፤ 140፥13 ይመ):: የእግዚአብሔርን መዝገብ በተመለከተ ሌሎች ጥቅሶችን ለማየት የ9፥5 እና 51፥1 ማብ ይመ:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ "የሕይወት መጽሐፍ" የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ለዘላለም ሕይወት የተመደቡ ቅዱሳን ስማቸው የተጻፈበትን መዝገብ ነው (ፊል4፥3፤ ራእ3፥5፤ 13፥8፤ 17፥8፤ 20፥12:15፤ 21፥27 ይመ)::

*69፥29፤* እግዚአብሔርን ለማመስገን ቃል ከመግባቱ በፊት ልመናውን በአዲስ መልክ ያቀርባል:: *ደግፎ ይያዘኝ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም፣ "ዋስትና ወዳለው ከፍተኛ ስፍራ ይውሰደኝ" ማለት ነው::

*69፥30-33፤* ጸሎቱ ተሰሚነት እንዳገኘ በመተማመን (የ3፥8 ማብ ይመ) እግዚአብሔርን ለማመስገን ቃል ይገባል (የ7፥17 ማብ ይመ)::

69፥30 *የእግዚአብሔርን ስም፤* ቍ36 እና የ5፥11 ማብ ይመ::

69፥32 *ድኾች፤* የ34፥6 ማብ ይመ:: *ያያሉ ደስም ይላቸዋል፤* 22፥26 እና ማብ ይመ:: *ልባችሁ፤* የ4፥7 ማብ ይመ:: *ይለምልም፤* እግዚአብሔር የችግረኞችን ጸሎት የሚሰማ በመሆኑ ነፍሳቸው በደስታ ፈነጠዘ፤ ሲያፌዙበት በነበሩት ላይ ግን ቍጣ ዘነበባቸው::

[34]ሰማይና ምድር፣ ባሕርም፣
በውስጣቸውም የሚንቀሳቀስ ሁሉ
ያመስግኑት።
[35]እግዚአብሔር ጽዮንን ያድናታልና፤
የይሁዳንም ከተሞች መልሶ
ይሠራቸዋልና፤
ሕዝቡም በዚያ ይሰፍራል፤
ይወርሳታልም።
[36]የባሪያዎቹም ዘሮች ይወርሷታል፤
ስሙንም የሚወዱ በዚያ ይኖራሉ።

## መዝሙር 70

### የጭንቀት ጩኸት

70፥1-5 ተጓ ምብ-መዝ40፥13-17

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር፤ ለመታሰቢያ*

[1]አምላክ ሆይ፤ ታድነኝ ዘንድ ዘንበል በል፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ እኔን ለመርዳት
ፍጠን።
[2]ሕይወቴን ለማጥፋት የሚሹ፣
ይፈሩ፤ ሁከትም ይምጣባቸው፤
የእኔን መጐዳት የሚመኙ፣
በውርደት ወደ ኋላቸው ይመለሱ።
[3]በእኔ ላይ፣ "እሰይ! እሰይ!" የሚሉ፣
ተሸማቀው ወደ ኋላ ይመለሱ።
[4]ነገር ግን የሚሹህ ሁሉ፣
በአንተ ሐሤት ያድርጉ፤ ደስም
ይበላቸው፤
"ማዳንህን የሚወዱ ሁሉ ሁልጊዜ፣
እግዚአብሔር ከፍ ይበል!" ይበሉ።
[5]እኔ ግን ምስኪንና ችግረኛ ነኝ፤
አምላክ ሆይ፤ ፈጥነህ ድረስልኝ፤
ረዳቴም፣ ታዳጊዬም አንተ ነህና፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አትዘግይ።

## መዝሙር 71

### የሽማግሌ ጸሎት

71፥1-3 ተጓ ምብ-መዝ31፥1-4

[1]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተን መጠጊያ
አደረግሁ፤
ከቶም አልፈር።
[2]በጽድቅህ ታደገኝ፤ አስጥለኝም፤
ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል፤ አድነኝም።
[3]ምንጊዜም የምሸሸበት፣
መጠጊያ ዐለት ሁነኝ፤
አንተ ዐለቴ ምሽጌ ነህና፣
ታድነኝ ዘንድ ትእዛዝህ ይውጣ።
[4]አምላኬ ሆይ፤ ከክፉ እጅ፣
ከግፈኛና ከጨካኝ መዳፍ አውጣኝ።
[5]ጌታ *እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ ተስፋዬ፤
ከልጅነቴም ጀምሮ መታመኛዬ ነህና።
[6]ከተወለድሁ ጀምሮ በአንተ ተደገፍሁ፤
ከእናቴ ማሕፀን ያወጣኸኝ አንተ ነህ፤
አንተ የዘወትር ምስጋናዬ ነህ።
[7]ብዙዎች እንደ ጉድ አዩኝ፤
አንተ ግን ጽኑ አምባዬ ነህ።
[8]ቀኑን ሙሉ ክብርህን ያወራ ዘንድ፣
አፌ በምስጋናህ ተሞልቶአል።
[9]በእርጅናዬ ዘመን አትጣለኝ፤
ጕልበቴም ባለቀበት ጊዜ አትተወኝ።
[10]ጠላቶቼ ተነጋግረውብኛልና፤

፤34፥2
69፥33 መዝ12፥5
69፥34 መዝ96፥11
፤98፥7፤ኢሳ44፥23
69፥35 ዕዝ9፥9፤
መዝ51፥18፤አብ1፥17
69፥36 መዝ25፥13
፤37፥29
70፥1 መዝ22፥19
፤71፥12
70፥2 መዝ6፥10፤
35፥4፡26፤71፥13፤10
9፥29፤129፥5
70፥3 መዝ35፥21
70፥4 መዝ9፥10፤
31፥6-7፤32፥11፤
35፥27፤118፥24
70፥5 መዝ18፥2፤
30፥10፤33፥20፤86፥1
፤109፥22፤119፥60፤
141፥1
71፥1 ዘዳ23፥15፤
ሩት2፥12፤መዝ22፥5
71፥2 2ነገ19፥16
71፥3 መዝ18፥2
71፥4 ዘፍ48፥16፤2
ነገ19፥19፤መዝ140፥4
71፥5 ኢዮ4፥6፤መዝ
9፥18፤25፥5፤ኤር
17፥7
71፥6 ኢዮ3፥16፤
መዝ9፥1፤22፥9፡10፤3
4፥1፤52፥9፤119፥164
፤145፥2
71፥7 ዘዳ28፥46፤
2ሳሙ22፥3፤መዝ61፥
3፤ኢሳ8፥18፤1ቆሮ4፥9
71፥8 ቍ15፤መዝ
51፥15፤63፥5፤96፥6፤
104፥1
71፥9 ዘዳ4፥31፤
31፥6፤መዝ51፥11፤92፥14፤ኢሳ46፥4 71፥10 ዘፀ1፥10፤
መዝ3፥7፤10፥8፤31፥13፤59፥3፤ምሳ1፥18፤ማቴ12፥14

*69፥34-36፤* እግዚአብሔር ይሁዳን መልሶ እንደሚያጸናትና የተስፋዪቱንም ምድር ለሕዝቡ ርስት አድርጐ እንደሚሰጥ በመተማመን የቀረበ የምስጋና ጥሪ ነው (የ9፥1 ማብ ይመ)። ይህ አንጓ እንደሚያመለክተው፣ ይህን ጸሎት የሚጸልዩት በችግር ውስጥ ያሉ ነገሥታት ብቻ ሳይሆኑ ክፉኛ የተሸነፈችውም ይሁዳም ጭምር ናት።

*69፥34፤* ፍጥረት ሁሉ እግዚአብሔርን ያመስግን እንደ ማለት ነው (148፥1-13፤ ኢሳ49፥13 ይመ)።

69፥35-36 *ሕዝቡ ... ዘሮች፤* በየትውልዱ ያሉ የእግዚአብሔር ሕዝቦችና ልጆቻቸው በተለይም የእርሱን ስም የሚወዱትን ለማለት ነው።

69፥35 *ጽዮን፤* የ9፥11 ማብ ይመ።

*መዝ70፤* የጠላቶች ዛቻ ባስጨነቀው ጊዜ እግዚአብሔር ፈጥኖ እንዲታደገው ያቀረበው ጸሎት ነው፤ የ40፥13-17 (ማብ ይመ) ቅጅ ይመስላል። እንዲህ ዐይነት ጸሎት ከያዙት ሦስት ተከታታይ መዝሙሮች ውስጥ ይህ ሁለተኛው ነው። የዚህ መዝሙር ቋንቋ ከመዝ71 ጋር በብዙ መንገድ ተመሳሳይነት አለው። ጸሎቱ፣ "ፍጠን፣ አትዘግይ" በሚሉ የርዳታ ቃላት የተቀነበበ ነው (ቍ1፡5)። የተቀረው የጸሎቱ ክፍል በእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ላይ የሚያተኩር ነው፤ ይኸውም፡- (1) "ሕይወቴን አጥብቀው በሚሿት" (ቍ2-3) እና (2) "አንተን አጥብቀው በሚሹ" ላይ (ቍ4)።

*70ርእስ፤* የመዝ4 ርእስ ማብ ይመ። *ለመታሰቢያ፤* የመዝ 38 ርእስ ማብ ይመ።

*70፥4፤* እግዚአብሔር ባርያውን ሲታደግ ሌሎች በእግዚአብሔር የሚታመኑ ሰዎች ሐሴት ያደርጋሉ፤ ምክንያቱም ለራሳቸው መዳን ማረጋገጫ ይሆናቸዋል። *እግዚአብሔር ከፍ ይበል፤* ምክንያቱም የማዳን ሥራው እርግጠኛና ውጤታማ ነው።

*መዝ71፤* በእርጅናው ዘመን ጠላቶቹ ስላስጨነቁት የእግዚአብሔርን ርዳታ ለማግኘት የቀረበ ጸሎት ነው፤ ምክንያቱም የንጉሡ ጕልበት መድከሙን ጠላቶቹ ተመልክተዋል (የ5፥9 ማብ ይመ)። የመዝሙሩ ደራሲ ማን እንደ ሆነ አልተገለጸም፤ ነገር ግን የመዝሙሩ አርታኢዎች መዝ70ን የመዝ71 መግቢያ አድርገው ስለሚመለከቱት መዝሙሩ በዳዊት ሳይደረስ አይቀርም (መዝሙሩ የተደረሰው በዳዊት እርጅና ዘመን ነው፤ ቍ 9፡18ይመ)። ይህ አስተያየት ተቀባይነት ሊያገኝ የቻለው መዝሙር 72 የንጉሥ ሰለሞን ጸሎት በመሆኑ ነው (የመዝ72 መግቢያን ይመ)። ይህ መዝሙር ከሦስቱ ተከታታይ መዝሙሮች ውስጥ ሦስተኛው ሲሆን የመዝሙሩም ዐቢይ ሐሳብ ተስፋ ነው (ቍ14 ይመ)። መዝሙሩም በቅርጹ እኩኩል ነው፤ ስድስት አንጓዎች ያሉት ሲሆን የአንጓዎቹ አወቃቀርም አምስት-አራት-አምስት፤ አምስት-አራት-አምስት እያለ ይዘልቃል። ይኸውም ከቍ1-4 አምስት መስመር ፣ ከቍ5-8 አራት መስመር፣ ከቍ9-13 አምስት መስመር፣ ከቍ15-18 አምስት መስመር፣ ከቍ19-21 አራት መስመር፣ ከቍ22-24 አምስት መስመር ማለት ነው። መኻል ላይ (ቍ14 እና የ6፥6 ማብ ይመ) ምን ጊዜም ባለ ተስፋ መሆኑን በእርግጠኛነት አስታውቆአል። መዝሙሩ የእግዚአብሔርን ርዳታ ለማግኘት በሚጠይቅ ጸሎትና (ቍ1-4) የእግዚአብሔርን ታዳጊነት ለማመስገን ቃል በሚገባ ልብ የተቀነበበ ነው (ቍ22-24)። ሁለተኛውና አምስተኛው አንጓ የተጕዳኙት ንጉሡ የደረሰበትን መከራ በሚያወሳው ሐሳብ ሲሆን ሦስተኛውና አራተኛው አንጓ የተጕዳኙት ደግሞ የንጉሡን የእርጅና ዘመን በሚያወሳው ሐሳብ ነው።

*71፥1-4፤* የእግዚአብሔርን ርዳታ ለማግኘት በመግቢያ ላይ የቀረበ ልመና ነው።

71፥2 *ጽድቅህ፤* ቍ15-16፡19፡24 እና የ4፥1 ማብ ይመ።

*71፥5-8፤* እግዚአብሔር ዘወትር አለኝታውና ተስፋው መሆኑን ይመሰክራል (ቍ14፡19-21 ይመ)

71፥5 *ከልጅነቴም ጀምሮ፤* 22፥9 ይመ።

71፥7 *እንደ ጉድ፤* መዝሙረኛው ቍጥሩ የበዛ መከራ ቢደርስበትም (ቍ20 ይመ) እግዚአብሔር ግን መጠጊያ ሆኖለታል፤ በዚህም ምክንያት ብዙዎች እንደ ልዩ ሰው ይመለከቱት ነበር።

*71፥9-13፤* ጕልበቱ እየደከመ ሲሄድ እግዚአብሔር ዘወትር ከእርሱ ጋር እንዲሆን ይጸልያል።

71፥10 *ጠላቶቼ ተነጋግረውብኛል፤* የ3፥2፤5፥9 ማብ ይመ።

ሕይወቴን ለማጥፋት የሚሹ በአንድ ላይ
አሢረዋል፤
11 እነርሱም፣ “እግዚአብሔር ትቶታል፤
የሚያስጥለው የለምና፣
ተከታትላችሁ ያዙት” አሉ።
12 አምላክ ሆይ፤ ከእኔ አትራቅ፤
አምላኬ ሆይ፤ እኔን ለመርዳት ፍጠን።
13 ባላንጣ የሆኑብኝ ይፈሩ፤ ይጥፉም፤
ሊጐዱኝ የሚፈልጉ፣
ንቀትንና ውርደትን ይከናነቡ።
14 እኔ ግን ሁልጊዜ ተስፋ አደርጋለሁ፤
በምስጋና ላይ ምስጋና አቀርብልሃለሁ።
15 አንደበቴ ስለ ጽድቅህ፣
ቀኑን ሙሉ ስለ ማዳንህ ይናገራል፤
ማቆሚያ ልኩንም አላውቅም።
16 መጥቼ የጌታ እግዚአብሔርን ብርቱ ሥራ
ዐውጃለሁ፤
የአንተን ጽድቅ ብቻ እናገራለሁ።
17 አምላክ ሆይ፤ አንተ ከልጅነቴ ጀምረህ
አስተማርኸኝ፤
እኔም እስከ ዛሬ ድረስ ድንቅ
ሥራህን ዐውጃለሁ።
18 አምላክ ሆይ፤ ሳረጅና ስሸብትም
አትተወኝ፤
ክንድህን ለመጪው ትውልድ፣
ኀይልህን ኋላ ለሚነሣ ሕዝብ ሁሉ፣
እስከምገልጽ ድረስ።
19 አምላክ ሆይ፤ ጽድቅህ እስከ ሰማያት
ይደርሳል፤
አንተ ታላላቅ ነገሮችን አድርገሃል፤
አምላክ ሆይ፤ እንደ አንተ ያለ ማን ነው?
20 ብዙ መከራና ጭንቅ ብታሳየኝም፣
ሕይወቴን እንደ ገና ታድሳለህ፤
ከምድር ጥልቅም፣
እንደ ገና ታወጣኛለህ።
21 ክብሬን ትጨምራለህ፤
ተመልሰህም ታጽናናኛለህ
22 አምላኬ ሆይ፤ ስለ ታማኝነትህ፣
በበገና አመሰግንሃለሁ፤
የእስራኤል ቅዱስ ሆይ፤
በመሰንቆ እዘምርልሃለሁ።
23 ዝማሬ በማቀርብልህ ጊዜ ከንፈሮቼ
በደስታ ይሞላሉ፤
አንተ የተቤዠሃትም ነፍሴ እልል
ትላለች።
24 አንደበቴ ስለ ጽድቅህ፣
ቀኑን ሙሉ ያወራል፤
የእኔን መጐዳት የሚፈልጉ፣
አፍረዋልና፤ ተዋርደዋልም።

## መዝሙር 72

### በተስፋ የሚጠባበቀው ንጉሥ

ስለ ሰሎሞን

1 እግዚአብሔር ሆይ፤ ፍርድህን ለንጉሥ፣
ጽድቅህንም ለንጉሥ ልጅ ዐድል፤
2 እርሱም ሕዝብህን በጽድቅ ይዳኛል፤*
ለተቸገሩትም በትክክል ይፈርዳል።
3 ተራሮች ብልጽግናን፣
ኰረብቶችም የጽድቅን ፍሬ ለሕዝቡ
ያመጣሉ።

*2 ወይም እርሱ ሕዝቡን በጽድቅ ይዳኝ

71፥11 መዝ7፥2፤9፥10፤ኢሳ40፥27፤54፥7፤ሰቆ5፥20፤ማቴ27፥46
71፥12 መዝ22፥19፤38፥21:22
71፥13 ኢዮ8፥22፤መዝ25፥3፤70፥2፤ኤር18፥19
71፥14 መዝ25፥3፤42፥5፤130፥7፤131፥3
71፥15 ቍ8፤መዝ51፥14፤66፥16
71፥16 መዝ9፥1፤77፥12፤106፥2፤118፥15፤145፥4
71፥17 ዘዳ4፥5፤ኢዮ5፥9፤መዝ26፥7፤86፥10፤96፥3፤ኤር7፥13
71፥18 ዘፀ9፥16፤ኢዮ8፥8፤መዝ22፥30:31፤78፥4፤145፥4፤ኢሳ46፥4፤ኢል1፥3
71፥19 መዝ35፥10፤36፥5፤77፥13፤89፥8፤126፥2፤ሉቃ1፥49
71፥20 መዝ25፥17፤63፥9፤80፥3:19፤85፥4፤ሆሴ6፥2
71፥21 መዝ18፥35፤23፥4፤86፥17፤ኢሳ12፥1፤40፥1-2፤49፥13፤54፥10
71፥22 2ነገ19፥22፤ኢዮ21፥12፤መዝ33፥2፤92፥3፤144፥9
71፥23 ዘፀ15፥13፤መዝ20፥5
71፥24 ቍ13፤አስ9፥2፤መዝ35፥28
72፥1 ዘዳ1፥16፤መዝ9፥8
72፥2 ኢሳ9፥7፤

*71፥13፤* እግዚአብሔርን ጠላቶቹን እንዲበቀልለት ይጸልያል (የ5፥10 ማብ ይመ)።

*71፥14፤* የማይናወጥ ተስፋ እንዳለው ያስታወቀበት ቦታ ነው (42፥8 እንዲሁም የ6፥6፤ 42፥8 ማብ ይመ)።

*71፥15-18፤* የጸሎቱን መታደስ (ቍ8) ምክንያት በማድረግ እግዚአብሔርን ሊያመሰግን ቃል ይገባል፤ የ7፥17 ማብ ይመ።

71፥16-17 *ብርቱ ሥራ ... ጽድቅ ... ድንቅ ሥራህን፤* እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ያደረጋቸው ኀያል (ድንቅ) ሥራዎች የጽድቁ መገለጫዎች ናቸው፤ ስለዚህ፣ “የጽድቅ ሥራዎች” ሊባሉ ይችላሉ (ቍ24)።

71፥16 *መጥቼ፤* የእግዚአብሔር ሕዝብ ለአምልኮ ወደ ተሰበሰበበት ወደ ቤተመቅደሱ ማለት ነው።

*71፥19-21፤* እግዚአብሔር መራራ በሆነ ችግሩ ውስጥ አሁንም አብሮት መሆኑን ይመሰክራል (ቍ5-8:14 ይመ)።

71፥19 *ጽድቅህ እስከ ሰማያት ይደርሳል፤* ከምድር በላይ ካለው ስፍራ ይልቅ እጅግ የሚሰፋ ነው (36፥5 እና ማብ ይመ) እንደ ማለት ነው። አምላክ ሆይ፣ እንዳንተ ያለ ማን ነው? ሚክ 7፥18 ይመ።

71፥20 *ሕይወቴን እንደ ገና ታድሳለህ፤* ሕይወትን የሰጠው እግዚአብሔር ሕይወቱን ደግሞ ያድሳታል። *ከምድር ጥልቅም፤* የሙታንን ዓለም የሚያሳይ ሲሆን መቃብር ደግሞ የዚያ ዓለም መግቢያ በር ነው (የ30፥1 ማብ ይመ)።

*71፥22-24፤* የእግዚአብሔር ማዳን ከእርሱ ጋር እንደሚሆን በመተማመን ሊያመሰግነው ቃል ይገባል (የ3፥8፤ የ7፥17 ማብ ይመ)።

71፥22 *በገና ...መሰንቆ፤* የ57፥8 ማብ ይመ። *የእስራኤል ቅዱስ፤* 78፥41፤ 89፥18፤ እንዲሁም የኢሳ1፥4 ማብ ይመ።

71፥23 *ተቤዠሃትም፤* በዚህ ቦታ የቃሉ ትርጕም ነጻ ያወጣኸኝ ማለት ነው፤ አብዛኛውን ጊዜ በሌላም ቦታ እንዲሁ ነው።

71፥24 *ስለ ጽድቅህ፤* እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ ላይ በተናገረው መሠረት በሕዝቡ መካከል የሚያደርገውን የማዳን ተግባር ያመለክታል።

*መዝ72፤* በዳዊት ዙፋን ላይ ተቀምጦና በምድርም ላይ የእግዚአብሔር እንደራሴ ሆኖ፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለሚገዛው ንጉሥ የተደረገ ጸሎት ነው፤ ይህ ንጉሥ የዳዊት ልጅ ነው። መዝሙሩ ሥርዐተ ንግሥ በሚኖርበት ጊዜ የሚዘመር ሳይሆን አይቀርም (መዝ2፤110 ይመ)። ቍ2-11:17 የአቤቱታ ሐሳብ ያለው ሲሆን በእጅ አዙር የቀረበ ጸሎትም ነው። ጸሎቱ የሕዝቡን ፍላጐት የሚገልጽ ሲሆን፣ የንጉሡ አገዛዝ ደግሞ ጽድቅና ፍትሕ የሰፈነበት መሆኑን ያሳያል፤ ይህም ከአንድ ንጉሥ የሚጠበቅ ከፍተኛ አነጋገር ነው። ጸሎቱ የንጉሡን ትክክለኛ ሐሳብና የግዛቱን ክብር ውጤት ያንጸባርቃል። ኤርምያስ ከዳዊት ወገን በሆኑ ነገሥታት ላይ የሚያቀርበውን ክስና (ኤር22፥2-3:13:15) ስለ መሲሑ የጽድቅ መንግሥት የተነገረውን ትንቢት ይመ (ኢሳ 9፥7፤ 11፥4-5፤ ኤር23፥5-6፤ 33፥15-16፤ ዘካ9፥9 ይመ)። እንደ ጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ አይሁዶችም ይህ መዝሙር የሚናገረው ስለ መሲሑ እንደ ሆነ ያስባሉ። የመጨረሻዎቹ ሦስት ቍጥሮች ከጸሎቱ ጋር አብረው አይሄዱም (የቍጥሮችን ማብ ይመ)።

72ርእስ *ስለ ሰሎሞን፤* በእርሱ ወይም ለእርሱ እንደ ማለት በእርግጥ ሁለቱም ያስኬዳል፤ ይህንን መዝሙር እስራኤል (ይሁዳ) ከዳዊት ወገን ለተነሡ ነገሥታት ትጠቀምበት እንደ ነበር ምንም ጥርጥር የለውም።

*72፥1፤* የጸሎቱ ዋና ሐሳብ ነው። *ፍትህን ...ጽድቅን፤* የንጉሥ አገዛዝ የእግዚአብሔርን አገዛዝ ማንጸባረቅ እንዲችል ንጉሡ በጽድቅ መፍረድና በትክክል መዳኘት እንዲችል እግዚአብሔር እንዲያግዘው የቀረበ ጸሎት ነው። ሰሎሞንም ጥበብን ጠየቀ (1ነገ3፥9:11-12፤ ምሳ16፥12 ይመ)። *ጽድቅ፤* የ4፥1 ማብ ይመ።

*72፥2-7፤* የአገዛዙን ባሕርይ የሚያሳይ ክፍል ነው፤ አገዛዙ የጽድቅና የብልጽግና ከመሆኑም በላይ ጸንቶ የሚኖር ነው።

*72፥3፤* በአገዛዙ ውስጥ ያለው ጽድቅ፣ ምድርን ለማለምለም እንደ ወረደ ዝናብ ይሆናል፤ በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ሕዝቡን አትረፍርፎ ይባርካል (ቍ6-7፤ 5፥12፤ 65፥9-13፤ 133፥3፤

4ለተቸገረው ሕዝብ ይሚገታል፤
የድኾችን ልጆች ያድናል፤
ጨቋኙንም ያደቀዋል።
5ፀሓይ እስካለች ድረስ፣
ጨረቃም በምትኖርበት ዘመን ሁሉ፣
ከትውልድ እስከ ትውልድ ይኖራል።[ሀ]
6እንደ ዝናብ በታጨደ መስክ ላይ
ይወርዳል፤
እንደ ካፊያም ምድርን ያረሰርሳል።
7በዘመኑ ጽድቅ ይሰፍናል፤
ጨረቃ ከሰፍራዋ እስከምትታጣ ድረስም
ሰላም ይበዛል።
8ከባሕር እስከ ባሕር ድረስ፣
ከታላቁም ወንዝ[+] እስከ ምድር ዳርቻ
ይገዛል።
9የበረሓ ዘላኖች በፊቱ ይሰግዳሉ፤
ጠላቶቹም ዐፈር ይልሳሉ።
10የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት፣
ግብር ያመጡለታል፤
የዐረብና የሳባ ነገሥታት፣
እጅ መንሻ ያቀርባሉ።
11ነገሥታት ሁሉ ይሰግዱለታል፤
ሕዝቦችም ሁሉ ይገዙለታል።
12ችግረኛው በጮኸ ጊዜ፣
ምስኪኑንና ረዳት የሌለውን
ይታደገዋል።
13ለድኾችና ለችግረኞች ይራራል፤
ምስኪኖችንም ከሞት ያድናል።
14ሕይወታቸውን ከጭቈናና ከግፍ ያድናል፤
ደማቸውም በእርሱ ፊት ክቡር ነው።
15ዕድሜው ይርዘም!
ከዐረብ ወርቅ ይምጣለት፤
ዘወትር ይጸልዩለት፤
ቀኑንም ሙሉ ይባርኩት።
16በምድሪቱ ላይ እህል ይትረፍረፍ፤
በተራሮችም ዐናት ላይ ይወዛወዝ።
ፍሬው እንደ ሊባኖስ ይንዠርገግ፤
በከተማ ያለውም እንደ ሜዳ ሣር
እጅብ ብሎ ይውጣ።
17ስሙ ለዘላለም ጸንቶ ይኑር፤
ዝናው ፀሓይ የምትኖረውን ዘመን
ያህል ይዝለቅ፤
ሕዝቦች ሁሉ በእርሱ ይባረኩ፤
ሕዝቡ ሁሉ ቡሩክ ነህ ይበለው።
18ብቻውን ድንቅ ነገር የሚያደርግ፣
የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር
ይባረክ።
19ክቡር ስሙ ለዘላለም ይባረክ፤
ምድርም ሁሉ በክብሩ ይሞላ።
አሜን፤ አሜን።
20የእሴይ ልጅ የዳዊት ጸሎት እዚህ ላይ
ተፈጸመ።

11፥4-5፤16፥5፤32፥1፤59፥17፤63፥1፤ኤር 23፥5፤33፥15
72፥4 ቍ13፤መዝ 9፥12፤27፥11፤76፥9፤ ኢሳ11፥4፤29፥19፤32፥7፤49፥13
72፥5 1ሳሙ13፥13 1መዝ33፥11
72፥6 ዘዳ32፥2
72፥7 መዝ92፥12፤ ምሳ14፥11
72፥8 ዘፀ23፥31፤ 1ነገ4፥21፤ዘካ9፥10
72፥10 ዘፍ10፥4:7፤ 1ነገ9፥16፤2ዜና9፥24፤ አስ10፥1
72፥11 ዘፍ27፥29 ፤ዕዝ1፥2
72፥13 ኢሳ60፥10፤ ኢል2፥18፤ሉቃ 10፥33
72፥14 1ሳሙ26፥21 ፤መዝ69፥18፤ሕዝ 13፥23፤34፥10
72፥15 ዘፍ10፥7፤ መዝ35፥28
72፥16 ዘፍ27፥28፤ ዘኍ22፥4፤መዝ4፥7፤ 92፥12፤104፥16፤ኢሳ 4፥2፤27፥6፤44፥4፤ 58፥11፤66፥14፤ሕዝ 34፥27
72፥17 ዘፍ12፥3፤ ዘፀ3፥15፤መዝ89፥36፤ ሉቃ1፥48
72፥18 1ዜና29፥10 ፤ኢዮ5፥9፤መዝ41፥13 ፤106፥48፤ሉቃ1፥68
72፥19 ዘኍ14፥21፤2ሳሙ7፥26፤መዝ41፥13
72፥20 ሩት4፥17

[ሀ]5 *ወይም የተፈራ ይሆናል*
[+]8 የኤፍራጥስ ወንዝ ነው።

ዘሌ 25፥19፤ ዘዳ28፥8 ይመ)።

72፥5 *ፀሓይ እስካለች... ይኖራል፤* 21፥4 እና ማብ ይመ።

*72፥6፤* ቍ3 እና ማብ እንዲሁም ቍ7 ይመ። እግዚአብሔር በአገዛዙ ላይ የሾመውን ንጉሥ አስመልክቶ ምስል ከሣች የሆነ ተምሳሌት ለማግኘት ሰቆ4፥20 ይመ።

72፥7 *ጽድቅ፤* የ1፥5 ማብ ይመ። *ይበዛል፤* ምክንያቱም ንጉሡ ይደግፋቸዋል፣ ይጠብቃቸዋልም፤ ክፉዎችን ለማጥፋት ግን ኀይሉን ሁሉ ይጠቀማል (መዝ101 ይመ)።

*72፥8-14፤* ከጽድቅ አገዛዙ ,የተነሣ (ቍ12-14) የግዛቱ ስፋት ምን ያህል እንደ ሆነ ያመለክታል (ቍ8-11)።

*72፥8፤* መንግሥቱ የተስፋዪቱን ምድር ሁሉ የሚሸፍን ሲሆን ሥልጣኑ ግን እስከ ምድር ዳርቻዎች ድረስ ይዘልቃል (ቍ9-11 ይመ)። በዓለም ላይ የእግዚአብሔር እንደራሴ በመሆኑ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ንጉሣዊ ሥልጣን ይጨብጣል፤ ይህም በክርስቶስ ይፈጸማል።

*72፥9፤* በዐረብ ምድረ በዳ በስተ ምሥራቅ የሚኖሩ ነገዶች ለእርሱ ይገዛሉ። *ዐፈር ይልሳሉ፤* ሚክ7፥17 ይመ።

*72፥10፤* በስተ ምዕራብ ከሜዲትራኒያን ባሕር ጋር የሚዋሰኑ ነገሥታት እንዲሁም በደቡብ ዐረቢያና በምሥራቅ አፍሪካ ጠረፍ ላይ የሚገዙ ነገሥታት ታላቅ ንጉሥ አድርገው ይቀበሉታል። *ተርሴስ፤* በሜድትራኒያን ባሕር የምትዋሰንና ምናልባትም ከእስፔን በስተ ምዕራብ በኩል ርቃ የምትገኝ ወደብ ነች። *ሳባ፤* የዘፍ10፥28፤ የ1ነገ10፥1፤ የኢል3፥8 ማብ ይመ። *ሳባ፤* በብሉይ ኪዳን በሌላ ቦታ ከኩሽ ጋር ተያይዞ ተጠቅሶአል (ዘፍ10፥7፤ኢሳ43፥3)፤ ከግብፅ በስተ ደቡብ፣ በአሁኑ ሱዳን ውስጥ አንድ ሰፊ አካባቢን ሳያመለክት አይቀርም።

*72፥15-17፤* ማጠቃለያ ነው፤ ንጉሡ ረጅም ዕድሜን፣ ብልጽግናንና በዓለም ሁሉ የታወቀ መሆንን ይጐናጸፍ፤ ደግሞም የዓለምን ሕዝቦች ሁሉ የሚባርክ ይሁን።

72፥17 *ሕዝቦች ሁሉ፤* ለአብርሃም የሰጠውን ተስፋ የሚያስታውስ ሲሆን (ዘፍ12፥3፤ 22፥18 ይመ)፣ ይህም ተስፋ በዳዊት ንጉሣዊ ልጅ ማለትም በማሲሑ እንዲፈጸም ይናገራል።

*72፥18-19፤* የሁለተኛው የመዝሙር መጽሐፍ መደምደሚያ ቡራኬ ነው (41፥13 እና ማብ ይመ)። ሕዝቡ ለመዝሙሩ ማለትም ለመጽሐፍ ሁለት የሰጠው ምላሽ ወይም "አሜን" ነው (የመዝ4 ርእስ ማብ ይመ)።

72፥19 *በክብሩ ይሞላ፤* የ85፥9 ማብ ይመ።

*72፥20፤* ከዚህ በፊት ያሉትን በዳዊት እንደ ተጻፉ የሚታመኑትን መዝሙሮች መሠረት በማድረግ አርታኢዎች የጨመሩት ልዩ ማስታወሻ ሳይሆን አይቀርም። *የዳዊት ጸሎት፤* የመዝ86 እና 142 ርእሶችን ይመ።

*መዝ73፤* ስለ ጽድቅና ስለ ክፉ ሰዎች ዕድል ፋንታ የሚገልጽ የጥበብ ቃል ነው። የመዝሙሩ አርታኢዎች መዝ1 የመጽሐፉ የመጀመሪያ መዝሙር እንዲሆን እንዳደረጉ ሁሉ (የመዝ1 መግቢያን ይመ) ይህንም መዝሙር የመጽሐፍ ሦስት የመጀመሪያው መዝሙር እንዲሆን አድርገውታል። "ኀጢአተኛ ሰዎች ሲበለጽጉ ጻድቅ ሰዎች ግን በመከራ የሚማቅቁት ለምንድን ነው?" የሚለው አስቸጋሪ ጥያቄ በዚህ መዝሙር ውስጥ ተነሥቶአል። የዚህ መዝሙር ዐቢይ ሐሳብ ከመዝ49 ጋር በብዙ መልኩ ይዛመዳል (የመዝ49 መግቢያን እንዲሁም መዝ37 ይመ) መዝሙሩ ከባቢሎን ምርኮ በኋላ የተጻፈ ሳይሆን አይቀርም። የመዝሙሩ ዐቢይ ሐሳብ መዝሙሩን ሁለት እኩል ቦታ ሲከፍለው እያንዳንዱ ክፍል 14 ቍጥሮች አሉት። በጥቅሉ ሲታይ ግን መዝሙሩ በሁለት ክፉኛ ተነጻጻሪ ሐሳቦች የተቀነበበ ነው (ቍ1 እና ቍ27)።

*73ርእስ፤* ይህ መዝሙር የተሰየመው በአሳፍ ስም ሲሆን እርሱም ከዳዊት የሌዋውያን መዘምራን የአንዱ መሪ ነበር (የመዝ39፤42፤50 የርእስ ማብ ይመ)። መዝሙሩ ከዐሥራ አንዱ የአሳፍ መዝሙሮች (መዝ73-83) የመጀመሪያው ሲሆን፣ መዝ 50ም በአንድ ወቅት በዚህ ክፍል ውስጥ ተመድቦ ነበር። ከአሳፍ በኋላም ዘሮቹ በእርሱ እግር ተተክተው ሲያገለግሉ ስለ ነበር፣ እነርሱ የዘመሩት የጸሎት መዝሙሮች በዚህ ስብስብ ውስጥ ተጨምሮአል (መዝ74፤79፤83) የመዝ50 ርእስ ማብ ይመ። የአሳፍ መዝሙሮች እግዚአብሔር የራሱ ሕዝብና የሌሎች መንግሥታት ገዥ መሆኑን በአጽንዖት ይናገራሉ። በመግቢያው ላይ ካለው ቃል (መዝ73) በስተቀር የመዝሙሮቹ ስብስብ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከባዕዳን መንግሥታት እጅ እንዲታደግ የሚማልዱ ናቸው (መዝ74፤83)። የተቀሩት ስብስቦች ግን (መዝ75-82) በዐቢይ ሐሳብ ደረጃ የተጣመሩና ይህንኑም የሚያንጸባርቁ ናቸው፤ (1) ዐመፀኞችን የሚያዋርድ፣ ጻድቃንን ግን ከፍ ከፍ

# ሦስተኛ መጽሐፍ
## ከመዝሙር 73-89

## መዝሙር 73
### የፍትሕ አሸናፊነት

የአሳፍ መዝሙር

1 እግዚአብሔር ልባቸው ንጹሕ ለሆነ፣
ለእስራኤል እንዴት ቸር ነው!
2 እኔ ግን እግሬ ሊሰናከል፣
አዳልጦኝም ልወድቅ ጥቂት ቀረኝ::
3 ክፉዎች ሲሳካላቸው አይቼ፣
በዐመፀኞች ቀንቼ ነበርና::

4 እንዳች ጣር የለባቸውም፤
ሰውነታቸውም ጤናማና የተደላደለ
ነው::
5 በሰዎች የሚደርሰው ጣጣ
አይደርስባቸውም፤
እንደ ማንኛውም ሰው መከራ
አያገኛቸውም::
6 ስለዚህ ትዕቢት የዐንገት ጌጣቸው ነው፤
ዐመፅንም እንደ ልብስ ተጐናጽፈዋል::
7 የሰባ ዐይናቸው ይጕረጠረጣል፤*
ልባቸውም በከንቱ ሐሳብ ተሞልቶ
ይፈስሳል::
8 በፌዝና በክፋት ይናገራሉ፤
ቀና ቀና ብለውም በዐመፅ ይዝታሉ::
9 አፋቸውን በሰማይ ላይ ያላቅቃሉ፤
አንደበታቸውም ምድርን ያካልላል::
10 ስለዚህ ሕዝቡ ወደ እነርሱ ይነጐዳል፤
ውሃቸውንም በገፍ† ይጠጣሉ::
11 "ለመሆኑ እግዚአብሔር እንዴት ያውቃል?
በልዑልስ ዘንድ ዕውቀት አለ?" ይላሉ::

12 እንግዲህ፣ ክፉዎች ይህን ይመስላሉ፤
ሁልጊዜ ግድ የለሽና ሀብት በሀብት
ናቸው::
13 ለካ ልቤን ንጹሕ ያደረግሁት በከንቱ
ነው፤
እጄንም በየዋህነት የታጠብሁት
በከንቱ ኖሯል!
14 ቀኑን ሙሉ ተቀሠፍሁ፤
ጠዋት ጠዋትም ተቀጣሁ::

15 "እኔ እንደዚህ እናገራለሁ" ብልማ ኖሮ፣
የልጆችህን ትውልድ በከዳሁ ነበር::
16 ይህን ነገር ለመረዳት በሞከርሁ ጊዜ፣
አድካሚ ተግባር መስሎ ታየኝ::
17 ይኸውም ወደ ስምላክ መቅደስ እስክገባ፣
መጨረሻቸውንም እስካይ ድረስ ነበር::
18 በእርግጥ በሚያዳልጥ ስፍራ
አስቀመጥኻቸው፤
ወደ ጥፋትም አወረድሃቸው::
19 እንዴት ፈጥነው በቅጽበት ጠፉ!
በድንጋጤ ፈጽመው ወደሙ::
20 ሰው ከሕልሙ ሲነቃ እንደሚሆነው፣
ጌታ ሆይ፤ አንተም በምትነሣበት ጊዜ፣
እንደ ቅዠት ከንቱ ታደርጋቸዋለህ::

21 ነፍሴ በተማረረች ጊዜ፣
ልቤም በተቀሠፈ ጊዜ፣
22 ስሜት የሌለውና አላዋቂ ሆንሁ፤
በፊትህም እንደ እንስሳ ሆንሁ::

23 ይህም ሆኖ ዘወትር ከአንተ ጋር ነኝ፤
አንተም ቀኝ እጄን ይዘኸኛል::
24 በምክርህ መራኸኝ፤
ኋላም ወደ ክብር ታስገባኛለህ::
25 በሰማይ ከአንተ በቀር ማን አለኝ?
በምድርም ከአንተ ሌላ የምሻው

*7 የዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሱርስቱና የሰብዓ ሊቃ
ናት ትርጒም ግን፣ *ከደንደነው ልባቸው በደል ይወጣል* ይላል::
†10 በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጒም በትክክል አይታወቅም::

73፥1 መዝ24፥4፤ ማቴ5፥8
73፥2 ዘዳ32፥35፤ መዝ69፥2፤ኤፌ4፥27
73፥3 ኢዮ9፥24፤ 21፥7፤ምሳ3፥31፤23፥17፤24፥1-2፤ኤር12፥1፤ሚል3፥15
73፥5 ቍ12፤ሕዝ 23፥42
73፥6 ዘፍ6፥11፤ 41፥42፤ዘሌ26፥19፤ ምሳ4፥17፤መሐ4፥9፤ ሕዝ16፥11
73፥7 መዝ17፥10
73፥8 መዝ10፥7፤ 12፥5፤17፥10፤41፥5፤ ሕዝ25፥15፤ቈላ3፥8
73፥12 ቍ5፤መዝ 49፥6
73፥13 ዘፍ44፥16፤ ኢዮ9፥29-31፤21፥15
73፥14 ቍ5
73፥16 መክ8፥17
73፥17 ዘፀ15፥17፤ ኢዮ8፥13፤መዝ15፥1፤ፊል3፥19
73፥18 ዘዳ32፥35፤ መዝ17፥13፤35፥6
73፥19 ዘፍ19፥15፤ ዘዳ28፥20፤ምሳ24፥22፤ኢሳ47፥11
73፥20 ኢዮ20፥8፤ መዝ78፥65፤ምሳ12፥ 11፤28፥19፤ኢሳ29፥8
73፥22 መዝ49፥10፡12፡20፤92፥6፤94፥8፤ መክ3፥18፤9፥12
73፥23 ዘፍ48፥13
73፥24 1ነገ22፥5፤ መዝ48፥14
73፥25 መዝ16፥2፤ ፊል3፥8

የሚያደርግ (መዝ75) እርሱ የእስራኤል አምላክና ታዳጊ ነው (መዝ76)፤ (2) እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል የሚያደርገው የማዳን ሥራ ሲታወስ ይኖራል (መዝ77-78) (3) እግዚአብሔር እስራኤልን ከጠላቶቿ እንዲታደግ ብርቱ ጸሎት ተደርጎአል (መዝ79-80) (4) እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ (መዝ81) እና በዓለም መሪዎች ላይ (መዝ82) የበላይ ፈራጅ ነው::

*73፥1-14፤* እምነቱ ሊጠፋ የተቃረበ ሰው ንግግር ነው፤ መራራ በሆነ መከራ ውስጥ ያለ ጻድቅ ዐይኑን በዐመፀኞች ብልጽግና ላይ አሳርፎአል::

73፥1 ***ልባቸው ንጹሕ፤*** ቍ13 እና የ24፥4 ማብ ይመ:: ***ልባቸው፤*** የ4፥7 ማብ ይመ::

73፥2 ***እግሬ ... አዳልጦኝ ልወድቅ ጥቂት ቀረኝ፤*** ከእውነትና ከጽድቅ መንገድ (37፥13 እና ማብ ይመ) ለማለት ነው::

*73፥4-12፤* ስለ ክፉዎች ብልጽግና የሚናገር ክፍል ነው፤ ስለ ክፉዎች ማንነት ለማየት መዝ10፥2-11 ይመ፤ ኢዮብ ስለ ክፉዎች ብልጽግና የተናገረው በኢዮ21 ላይ ይመ::

73፥6 ***ትዕቢት ... የዐንገት ጌጣቸው፤*** ከምሳ1፥9፤ 3፥3፡22 ጋር ያነጻጽሩ::

73፥11 ***እግዚአብሔር ... ልዑል፤*** ልዑል እግዚአብሔር እንደ ማለት ነው (57፥2 እና የ3፥7 ማብ ይመ):: ***ልዑል፤*** የዘፍ 14፥19 ማብ ይመ::

*73፥13-14፤* የክፉዎችን ሕይወት ከራሱ ሕይወት ጋር ሲያነጻጽረው እጅግ ተገርሞአል::

73፥13 ***ልቤን ንጹሕ፤*** የቍ1 ማብ ይመ::

73፥14 ***ተቀጣሁ፤*** አባት ልጁን በትክክለኛው መንገድ ላይ ለመምራት እንደሚቀጣ ማለት ነው (ምሳ3፥12፤23፥13-14 ይመ)::

*73፥15-28፤* የእምነት ተሐድሶ ነው፤ የእግዚአብሔር ሰው በቤተ መቅደስ ውስጥ ሆኖ እግዚአብሔር በክፉዎች ላይ የወሰነውን አንድ በአንድ ያስተውላል::

73፥15 ***ብልማ ኖሮ፤*** አሳቤን በይፋ ተናግሬው ብሆን ኖሮ እንደ ማለት ነው:: ***ልጆችህን፤*** ትሑትና መለያቸው የሆነና ራሳቸውንም ለእግዚአብሔር የሰጡ ናቸው::

*73፥18-20፤* ክፉዎች የተሳካላቸው ቢመስሉም እግዚአብሔር ግን ያለ ምንም ማስጠንቀቂያ አንድ ቀን ጠራርጐ ያጠፋቸዋል:: መዝሙረኛው ክፉዎች ከሞቱ በኋላ ዕጣ ፈንታቸው ምን እንደ ሆነ አልገለጸም፤ ነገር ግን ክፉዎች እንዳልነበሩ የሚሆኑበትና እንደ ማለዳም ሕልም ተረስተው የሚቀሩበት ጊዜ እንደሚመጣ ተናግሮአል (መዝ49 ይመ፤ የጻድቃን መጨረሻ ግን ምን እንደ ሆነ ከቍ24 ጋር ያነጻጽሩ)::

*73፥20፤* እግዚአብሔር በክፉዎች ላይ በተነሣ ጊዜ (የ7፥6 ማብ ይመ) እንደ ጥላ ያልፋሉ፤ እንደ ሕልምም ቅዠት ብቻ ሆነው ይቀራሉ::

73፥21 ***ነፍሴ፤*** ቃል በቃል ሲተረጐም፣ "ኵላሊቴ" ማለት ነው (የ7፥9 ማብ ይመ):: ***ልቤ፤*** የ4፥7 ማብ ይመ::

73፥22 ***እንደ እንስሳ፤*** እንደ ደደብ እንስሳ ማለት ነው (ኢዮ18፥3 ይመ)::

*73፥23-26፤* እንደ እንስሳ ማሰብ ከማይችልበት ደረጃ ላይ ለመድረስ ምንም ባይቀረውም፣ እግዚአብሔር ግን ወድቆ እንዲቀር ከቶ አያደርገውም::

*73፥24፤* የእግዚአብሔር ምክር ሞኝነቱን ያስወግድለታል፤ ወጣ ገባ በሆነም የሕይወት ጐዳና ይመራዋል (16፥7፤ 32፥8፤ 48፥14 ይመ):: ***ወደ ክብር ታስገባኛለህ፤*** በእምነት ጒዞው መጨረሻ የሚያገኘው በረከት ነው (49፥15 እና ማብ ይመ)::

*73፥25፤* የክፉዎችን ሀብት በማየት ቢቀናም አሁን ግን በሰማይ ሆነ በምድር እንደ እግዚአብሔር ሊመኙት ያለ ምንም

የለኝም።
[26]ሥጋዬና ልቤ ሊደክሙ ይችላሉ፤
እግዚአብሔር ግን የልቤ ብርታት፣
የዘላለም ዕድል ፈንታዬ ነው።
[27]እነሆ፤ ከአንተ የሚርቁ ይጠፋሉና፤
አንተ ታማኞች ያልሆኑልህን ሁሉ
ታጠፋቸዋለህ።
[28]ለእኔ ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ
ይሻለኛል፤
ጌታ እግዚአብሔርን መጠጊያዬ
አድርጌዋለሁ፤
ስለ ሥራህም ሁሉ እናገር ዘንድ።

## መዝሙር 74

### ስለ መቅደሱ መፍረስ የቀረበ ጸሎት

የአሳፍ ትምህርት

[1]አምላክ ሆይ፤ ለዘላለም የጣልኸን
ለምንድን ነው?
በማሰማሪያህ ባሉ በጎችህስ ላይ ቍጣህ
ለምን ነደደ?
[2]ጥንት ገንዘብህ ያደረግሃትን ጉባኤ፣
የዋጀሃትን የርስትህን ነገድ፣
መኖሪያህ ያደረግሃትን የጽዮን ተራራ
አስብ።
[3]እርምጃህን ለዘላለሙ ባድማ ወደ ሆነው
አቅና፤
ጠላት በመቅደስህ ውስጥ ያለውን ሁሉ
አበላሽቶአል።
[4]ጠላቶችህ በመገናኛ ስፍራህ መካከል
ደነፉ፤
አርማቸውንም ምልክት አድርገው
በዚያ አቆሙ።
[5]በጫካ መካከል ዛፎችን ለመቍረጥ፣
መጥረቢያ የሚያነሣ ሰው መሰሉ።
[6]በእደ ጥበብ ያጌጠውን ሥራ ሁሉ፣
በመጥረቢያና በመዶሻ ሰባበሩት።
[7]መቅደስህን አቃጥለው አወደሙት፤
የስምህንም ማደሪያ አረከሱ።
[8]በልባቸውም፣ "ፈጽሞ እንጨቍናቸዋለን"
አሉ፤
እግዚአብሔር በምድሪቱ ላይ የተመለከበትን
ስፍራ ሁሉ አቃጠሉ።
[9]የምናየው ምልክት የለም፤
ከእንግዲህ የሚነሣ አንድም ነቢይ የለም፤
ይህ እስከ መቼ እንደሚቀጥል
የሚያውቅ በእኛ ዘንድ የለም።
[10]አምላክ ሆይ፤ ጠላት የሚያሾፈው እስከ

73፥26 ዘዳ32፥9፤ መዝ18፥1፤31፥10፤40፥12፤84፥2
73፥27 ዘሌ6፥2፤ መዝ34፥21፤ኤር5፥11፤ሆሴ4፥12፤9፥1
73፥28 መዝ9፥9፤ 26፥7፤40፥5፤ሰቆ3፥2፤ ዕብ10፥22፤ያዕ4፥8
74፥1 መዝ43፥2፤ 44፥23፤79፥13፤95፥7፤100፥3
74፥2 ዘፀ15፥13፡16፤34፥9፤ዘዳ32፥7፤መዝ 2፥6፤43፥3፤68፥16፤ ኢሳ46፥13፤48፥20፤ ኢል3፥17፡21፤ሐብ 1፥17፤1ቆሮ 6፥20
74፥3 ኢሳ44፥26፤ 52፥9
74፥4 ዘኍ2፥2፤ ኤር4፥6፤ሰቆ2፥7
74፥5 ኤር46፥22
74፥6 1ነገ6፥18
74፥7 ዘሌ15፥31፤ 20፥3፤መዝ75፥1፤ ሕዝ21፥28
74፥8 2ነገ25፥9፤ 2ዜና36፥19፤መዝ94፥5፤ኤር21፥10፤34፥22፤52፥13
74፥9 ዘፀ4፥17፤ 10፥1፤1ሳሙ3፥1

ነገር እንደ ሌለ ይመሰክራል።

73፥26 *ሥጋዬና ልቤ፤* መላ ሰውነቴ ለማለት ነው (84፥2 ይመ)። *ልቤ፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *ዕጣ ፈንታዬ፤* መዝሙረኛው ሌዋዊ እንደመሆኑ ዕጣ ፈንታው እግዚአብሔር ብቻ ነው፤ ኑሮውም የተመሠረተው ሕዝቡ ለእግዚአብሔር በሚሰጠው ዐሥራት ላይ ነው (ዘኍ18፥21-24፤ ዘዳ10፥9፤ 18፥1-2 ይመ)፤ በዚህ ቦታ መዝሙረኛው ብዙ ነገር ይመሰክራል፤ ሕይወቱን የሚጠብቅና የሚያጸና እግዚአብሔር ነውና።

73፥28 *ሥራህንም ሁሉ እናገር ዘንድ፤* እግዚአብሔር ስላ ደረገለት ምሕረት እግዚአብሔርን ለማመስገን ቃል የገባበት የመጨረሻ ክፍል ነው (የ7፥17 ማብ ይመ)።

*መዝ74፤* ጠላት በሚደነፋበት ሰዓት እግዚአብሔር የራሱ የሆነውን ሕዝብ እንዲታደግና ስለ ሕዝቡም እንዲሟገት፣ እንዲሁም ንጉሥ ለአገሩ ሕዝብ እንደሚቆም ሁሉ እግዚአብሔርም ለሕዝቡ እንዲቆም ወደ እግዚአብሔር የቀረበ ጸሎት ነው። መዝሙሩ የተጻፈው እስራኤል በተደመሰሰችበት፣ የተስፋዪቱ ምድር ባድማ በሆነችበትና ቤተ መቅደሱም ዐመድ በሆነበት የምርኮ ወቅት ነው (መዝ79፤ ሰቆ2 ይመ)። ይህ መዝሙር ከኤርምያስና ከሕዝቅኤል አገልግሎት ጋር መያያዝ አለመያያዙ ግን በትክክል አይታወቅም (የቍ 9 ማብ ይመ)። የመዝሙሩ ዐቢይ ሐሳብ ሁለት እኩል ቦታዎች የተከፈለ ሲሆን እያንዳንዱም ክፍል 11ቍጥሮች አሉት። ቍ12 የመዝሙሩን ዐቢይ ሐሳብ አጕልቶ ከማሳየቱም በላይ ሁለቱን ክፍሎች የሚያስተሳስር ነው። ቍ1-11 "ስለ ምንድን ይህ ሆነ?" በሚለው የሕዝቡ ጩኸት የተቀነበበ ነው (ቍ1፤11)። መዝሙሩ በአጠቃላይ ሲታይ ግን፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን፣ "እንዲያስብ" አቤቱታ የሚያቀርብ ነው (ቍ2፤22)። በቍ4-8 ተደጋግሞ የተጠቀሰው፣ "እነዚያ" የሚለው የተውላጠ ስም በቍ13-17 ተደጋግሞ ከተጠቀሰው፣ "አንተ" ከሚለው ተውላጠ ስም ጋር ጐን ለጐን ሲታይ ብርቱ የሆነውን የእግዚአብሔርን ሥራ ደካማና ጠፊ ከሆነው የጠላት ሥራ ጋር ያነጻጽራል።

74ርእስ፤ *የአሳፍ ትምህርት፤* የመዝሙር 32 ርእስ ማብ ይመ፤ *የአሳፍ፤* የመዝ73 ርእስ ማብ ይመ።

*74፥1-2፤* በመግቢያው ላይ የቀረበ አቤቱታና ጕርምርምታ ነው።

74፥1 *ስለ ምንድነው?... ለምን ...?* በቍ10 ላይ ካለው፣ "እስከ መቼ ነው?" ከሚለውና በቍ11 ላይ፣ "ለምን?" ከሚለውም ጋር ያነጻጽሩ፤ የ6፥3 ማብ እና በመግቢያው ላይ "ትምህርተ መለኮት" የሚለውን ይመ። *ለዘላለም፤* ምንም ሰላም ስላላገኙ ቍጣው ጸንቶ የሚቀጥል መሰላቸው። *ቍጣ፤* የ2፥5 ማብ ይመ። *በማሰማርያህ በጎች፤* የ23፥1 ማብ ይመ።

74፥2 *የዋጀሃትን፤* ወይም "ያገኘኸው" ወይም "የፈጠርኸው" ለማለት ነው። *ነገድ፤* በዚህ ቦታ የእስራኤልን ሕዝብ ሁሉ ያመለክታል። *ርስትህ፤* ዘዳ9፥29 ይመ። *የዋጀሃት፤* በሌሎችም ቦታዎች ላይ ተደጋግሞ እንደ ተወሳው በዚህም ቦታ "ነጻ ያወጣኸው" ማለት ነው። *የጽዮን ተራራ፤* የ9፥11 ማብ ይመ። ይህ ቍጥር በዘፀ15 ላይ ያለውን የድል መዝሙር ያስታውሳል (በተለይም ቍ13-17 ይመ። የዚህን መዝሙር ማእከላዊ ቍጥር ይኸውም ቍ12ን ከዘፀ15፥18 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይህ ቍጥር ሌላ፣ "ዘፀአት" ማለትም ሌላ፣ "ነጻ መውጣት" መኖሩን ያመለክታል። እግዚአብሔር ግብጻውያንን ድል አድርጐ ሕዝቡን ለመታደግ ሲነሣ ባቢሎናውያን ጽዮንን የፍርስራሽ ክምር እንዲያደርጓት አድርጐ ነበር፤ እንዲህም ያደረገው ሕዝቡን ለመታደግ ምክንያት እንዲሆነው ነው።

*74፥3-8፤* ባቢሎናውያን በታላቅ ጭካኔ ቤተ መቅደሱን ዐመድ ማድረጋቸውን ያመለክታል።

74፥3 *እርምጃህን ... አቅና፤* መልስህ ለመሥራት ፈጥነህና ማለት ነው።

74፥4 *ዐርማቸውን፤* የጦር ሰራዊት ዐርማ ሳይሆን አይቀርም (ዘኍ1፥52፤ ኢሳ31፥9፤ ኤር4፥21 ይመ)። *ምልክት አድርገው፤* ድል ማድረጋቸውን ይገልጻል።

74፥6 *በእደ ጥበብ ያጌጠውን፤* 1ነገ6፥15 ይመ።

74፥7 *ስምህን፤* የ5፥11 ማብ ይመ።

74፥8 *አሉ፤* የ10፥11 ማብ ይመ። *እግዚአብሔር ... የተመለከበትን ስፍራዎች ሁሉ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም የእግዚአብሔር ስም የሚጠራባቸው ወይም የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚሰበሰብባቸው ስፍራዎች ሁሉ ማለት ነው (ቍ4 ይመ)፤ ምን ለማለት እንደ ተፈለገ ግን ብዙ ግልጽ አይደለም። ባቢሎናውያን ጥቃት ባደረሱ ጊዜ በይሁዳ አገር ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት ብዙ ቦታዎች ይኖሩ ይሆናል (የ1ነገ3፥2፤ የ2ነገ18፥4 ማብ ይመ)።

*74፥9-11፤* ማጕረምረሙ እንደ ገና የቀጠለበት ክፍል ነው (ቍ1-2 ይመ)።

74፥9 *የምናየው ምልክት የለም፤* በግብፅ ምድር ያደረጋቸውን ታምራት ዐይነት ለማለት ነው (ቍ13-15፤78፥43 ይመ)። *ነቢይ የለም፤* ኤርምያስ ወደ ግብፅ ተወስዶአል (ኤር 43፥6-7 ይመ)፤ ሕዝቅኤል ትንቢት መናገር አለመናገሩ ግን በግልጽ አይታወቅም። መዝሙሩ በእስራኤል ቀርቶ በነበረ አንድ የአሳፍ ወገን ሳይጻፍ አይቀርም፤ ዮሐናን የተባለ የጦር መሪ ቀሪውን የእስራኤል ሕዝብ ወደ ግብፅ በወሰዱ ጊዜ (ኤር43፥4-7 ይመ) በወቅቱ አነስተኛ ቡድን የነበረውን የአሳፍን ወገን ንቆት ነበር።

74፥10 *የሚያሾፈው ... በስምህ ያላግጣል፤* ቍ18፤ ቍ22፤

*መቼ ነው?*
ባላንጣስ ለዘላለም በስምህ ያላግጣልን?
11እጅህን ለምን ትሰበስባለህ?
ቀኝ እጅህን ለምን በብብትህ ሥር
ታቆያለህ?
12አምላክ ሆይ፤ አንተ ከጥንት ጀምሮ
ንጉሤ ነህ፤
በምድር ላይ ማዳንን አደረግህ።
13ባሕርን በኀይልህ የከፈልህ አንተ ነህ፤
የባሕሩንም አውሬ ራሶች በውሃ ውስጥ
ቀጠቀጥህ።
14የሌዋታንን ራሶች አደቀቅህ፤
ለምድረ በዳ ፍጥረታትም ምግብ
አድርገህ የሰጠሃቸው፣
15ምንጮችንና ፈሳሾችን ያፈለቅህ
አንተ ነህ፤
ሳያቋርጡ የሚፈሱትንም ወንዞች
አደረቅህ።
16ቀኑ የአንተ ነው፤ ሌሊቱም የአንተ ነው፤
ጨረቃንና ፀሓይን አንተ አጸናሃቸው።
17የምድርን ዳርቻ ሁሉ የወሰንህ አንተ ነህ፤
በጋውንም ክረምቱንም አንተ ሠራህ።
18*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ጠላት እንዴት
እንደሚያሾፍ፣
ከንቱ ሕዝብም ስምህን እንዴት
እንዳቃለለ አስብ።
19የርግብህን ነፍስ አሳልፈህ ለዱር
አራዊት አትስጥ፤
የችግረኞች ሕዝብህን ሕይወት
ለዘላለሙ አትርሳ።
20ኪዳንህን አስብ፤
የዐመፅ መናኸሪያ በምድሪቱ ጨለማ
ስፍራዎች ሞልተዋልና።
21የተጨቈኑት አፍረው አይመለሱ፤
ድኾችና ችግረኞች ስምህን ያመስግኑ።
22አምላክ ሆይ፤ ተነሥ፤ ለዐላማህ
ተሟገት፤
ከንቱ ሰው ቀኑን ሙሉ
እንደሚያላግጥብህ አስብ።
23የባላጋራዎችህን ድንፋታ፣
ዘወትር የሚነሣውን የጠላቶችህን
ፉከራ አትርሳ።

## መዝሙር 75

### ለመለኮታዊው ዳኛ የቀረበ ዝማሬ

*ለመዘምራን አለቃ፤ "አታጥፋ" በሚለው ቅኝት የሚዜም፤ የአሳፍ መዝሙር ማሕሌት*

1አምላክ ሆይ፤ ምስጋና እናቀርብልሃለን፤
ስምህ ቅርብ ነውና ምስጋና
እናቀርብልሃለን፤

74፥10 ቍ22፤መዝ 6፥3፤44፥16፤79፥5፤ 80፥4
74፥11 ዘፀ15፥6፤ኀህ 5፥13፤ሕዝ5፥3
74፥12 መዝ2፥6፤ 24፥7፤27፥1፤68፥24
74፥13 ዘፀ14፥21፤ ኢሳ27፥1፤51፥9፤ሕዝ 29፥3፤32፥2
74፥14 ኢዮ3፥8፤ ኢሳ13፥21፤23፥13፤ 34፥14፤ኤር50፥39
74፥15 ዘፀ14፥29፤ 17፥6፤ዘኍ20፥11፤ ኢሱ2፥10
74፥16 ዘፍ1፥16፤ መዝ136፥7-9
74፥17 ዘፍ8፥22፤ ዘዳ32፥8፤ሐሥ17፥26
74፥18 ዘዳ32፥6
74፥19 ዘፍ8፥8፤ መዝ9፥18፤ኢሳ59፥11
74፥20 ዘፍ6፥18፤ ኢዮ34፥22
74፥21 መዝ9፥9፤ 10፥18፤35፥10፤103፥ 6፤ኢሳ58፥10
74፥22 መዝ17፥13 ፤53፥1
74፥23 ዘኍ25፥17 ፤መዝ46፥6፤65፥7፤ ኢሳ31፥4
75፥1 ኢሱ3፥5፤ መዝ44፥1፤71፥16፤77

2ነገ18፥32-35፤ ኢሳ37፥6፡23 ይመ።

*74፥12፤* በዕብራይስጡ ቅጅ ላይ፣ የመዝሙሩ ማእከላዊ ቍጥር መሆኑን ማስተዋል ይቻላል (የ6፥6 ማብ ይመ)። የመዝሙሩ ጠቅላይ ሐሳብ በአጭሩ የተቀመጠው በዚህ ቦታ ነው፤ ይኸውም፣ እግዚአብሔር የእስራኤል ንጉሥ፣ ተስፋና አዳኝ ነው፤ እስራኤል ደግሞ የእግዚአብሔር ሕዝብ (*መንግሥት*) ናት። የመዝሙሩን ደራሲ ክፉኛ ያነጫነጨው፣ እስራኤል በእግዚአብሔር ተመርጣ ሳለ እንዲህ የፍርስራሽ ክምር መሆኗ በእግዚአብሔርም ላይ መሣቂያና መዘባበቻ በመሆኗ ነው። *ከጥንት ጀምሮ፤* የእስራኤል ሕዝብ ከግብፅ ከወጣበት ጊዜ አንሥቶ (ዘፀ3፥7፤ 19፥5-6 ይመ)።

*74፥13-17፤* እግዚአብሔር የሁሉ ፈጣሪና ታዳጊ አምላክ ነው (65፥6-7 እና ማብ ይመ)።

*74፥13-14፤* እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ ባርነት ነጻ ባወጣ ጊዜ ያደረገውን አስደናቂ ተግባር፣ ወደ ኋላ ተመልሶ ያስታውሳል። ይህ ምስል የተቀዳው ከጥንት ቅርብ ምሥራቅ ተረት ላይ ሲሆን ከጥንት ጀምሮ ዐመፀኛ የነበረው ውሃ ብዙ ራሶች ባሉት የባሕር ውስጥ አውሬ ተመስሎአል፤ አማልክት ሥርዐት ያለውን ዓለም የፈጠሩት ይህን አውሬ ድል ካደረጉ በኋላ ነው (የ32፥6 ማብ ይመ)። ባለቅኔው በዚህ ቦታ ምስጋናውን የሚያቀርበው የፍጥረትንና የደኅንነትን ሐሳቦች እያዋሰበና እያፍገረገረ በማቅረብ ነው፤ ምክንያቱም የእስራኤል አምላክ እውነተኛ አዳኝ መሆኑን (ቀይ ባሕርን ለሁለት ከፍሎ ሕዝቡን በደረቅ መሬት ላይ ሲያሻግር፣ ግብፃውያንን ግን በዚያው በባሕሩ ውስጥ ቀብሮአቸዋል) ብርቱ የሚመስሉ ነገሥታትን በመስባበር፣ ሕዝቡን በመቤዠትና በዓለምም ላይ አዲስ ሥርዐትን በመመሥረት አስመስክሮአል። እንዲህ ያሉ ቅኔያዊና ምስል ከሣች አገላለጾችን ለማየት (1) የእግዚአብሔርን የሥነ-ፍጥረት ተግባር በ89፥10፤ በኢዮ9፥13፤ 26፥12-13 ላይ ይመ፤ (2) ከግብፅ ባርነት ነጻ መውጣትን በኢሳ51፥9 ይመ፤ (3) እስራኤል አንድ ቀን ሙሉ በሙሉ ነጻ እንደምትወጣ በኢሳ27፥1ላይ ተመልከት ተመሳሳይ የሆነ ምስል ከሣች አገላለጽ፣ በግብፅ ላይ በተላለፈው የፍርድ ቃል ውስጥ ይገኛል (ሕዝ29፥3-5፤ 32፥2-6 ይመ)።

*74፥15፤* እግዚአብሔር በቀይ ባሕር በምድረ በዳና በዮርዳኖስ ወንዝ ላይ ያደረጋቸውን ታምራቶች የሚያስታውስ ነው።

*74፥16-17፤* ፍጥረታትን በሥነ ሥርዐት ያደራጀ እግዚአብሔር ብቻ ነው፤ እርሱ የፍጥረታትን ኀይል በመሰባበር የማዳን ሥራውን ያከናውናል፤ መንግሥቱንም በዓለም ላይ ያጸናል።

*74፥18-23፤* እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲታደግና ዐላማውንም እንዲፈጽም የቀረበ ጸሎት ነው።

*74፥18፤* ቍ2፥10 ይመ። *ከንቱ ሕዝብ፤* በቍ10 ላይ የተጠቀሰው፣ "ባለጋራ" እግዚአብሔርን በመናቁ በዚህ ቦታ፣ "የማይረባ" ተብሎአል (ቍ22 ይመ)።

74፥19 *ርግብህን፤* እስራኤልን ነው፤ የፍቅር መግለጫም ሳይሆን አይቀርም (ማሕ2፥14፤ 5፥2፤ 6፥9፤ እንዲሁም መዝ 68፥13 እና ማብ ይመ)። *ለዱር አራዊት፤* የ7፥2 ማብ ይመ።

74፥20 *ኪዳንህን፤* እግዚአብሔር የእስራኤል አምላክ መሆኑንና በተስፋዪቱም ምድር የሚጠብቃቸውና አትረፍርፎም የሚባርካቸው መሆኑን የሚገልጽ ቃል ኪዳን ነው (ዘፀ19፥5-6፤ 23፥27-31፤ 34፥10-11፤ ዘሌ26፥11-12፡42፡44-45፤ ዘዳ28፥1-14፤ እንዲሁም መዝ105፥8-11፤ 106፥45፤ 111፥5፡9፤ ኢሳ54፥10፤ ኤር 14፥21፤ ሕዝ16፥60 ይመ)።

74፥21 *ድኾችና ችግረኞች፤* የ34፥6 ማብ ይመ። *ስምህን ያመስግኑ፤* እግዚአብሔር እንዲመሰገን ምክንያት ይሆኑ እንደ ማለት ነው።

74፥22 *ተነሥ፤* የ3፥7 ማብ ይመ።

74፥23 *ድንፋታ ... ፉከራ፤* 64፥2 ይመ።

*መዝ75፤* ጠላት የእስራኤልን ሕዝብ ሰላም በሚያውክበት ሰዓት የእግዚአብሔር ጥበቃ ከእነርሱ የማይለይ መሆኑን ለማረጋገጥ የተቀኘው ቅኔ ነው። መዝሙሩ በአሦር ምርኮ ዘመን የተዘመረ ሳይሆን አይቀርም (2ነገ18፥13-19፡37 ይመ)። እንዲሁም መዝ11፥76 ይመ። በዐቢይ ሐሳብ ረገድ ሐና ከዘመረችው መዝሙር ጋር (1ሳሙ2፥1-10) ተመሳሳይነት አለው። ለአምልኮ የመጣው ሕዝብ ሲዘምር (ቍ1)፣ መዝሙሩን ደግሞ ከአሳፍ ዘሮች አንዱ ይመራ ነበር (ቍ9)። መዝሙሩ የተቀነበበው በምስጋናና (ቍ1) በውዳሴ (ቍ9-10) ነው። በዕብራይስጡ ቅጅ ላይ የመዝሙሩ ፍሬ ሐሳብ የተዋቀረው ሁለት አንጓዎች ባሉት አራት መስመሮች ሲሆን፣ እያንዳንዱ አንጓ ደግሞ በሁለት በሁለት ቤት የተዋቀረ ነው። የመጀመሪያው አንጓ ከአርያም የተላከ የማረጋገጫ ቃል የያዘ ሲሆን፣ ሁለተኛው አንጓ ደግሞ ከምድር ወደ ሰማይ የሚያርግ የድል ምላሽ ይዞአል።

*መዝ75ርእስ፤ ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ4 ርዕስ ማብ ይመ። *ቅኝት፤* የመዝ9 ርእስ ማብ ይመ። *አታጥፋ፤* የመዝ57፤ 58፤ 59 ርእስት ይመ። *አሳፍ፤* የመዝ73ርእስ ማብ ይመ። *መዝሙር፤* የመዝ30 ርእስ ማብ ይመ።

*75፥1፤* ማኅበሩ ምስጋናውን በውዳሴ ይጀምራል (7፥17፤ 28፥7፤ 30፥12፤ 35፥18 ይመ)። *ስም፤* የ5፥11፤ 74፥7 ማብ ይመ። *ድንቅ ሥራህ፤* የ9፥1 ማብ ይመ።

ሰዎችም ስለ ድንቅ ሥራህ ይናገራሉ::
2 አንተም እንዲህ አልህ፤ "ለይቼ
በወሰንኋት ሰዓት፣
በቅን የምፈርድ እኔ ነኝ::
3 ምድርና ሕዝቦቿ ሁሉ በሚናወጡበት
ጊዜ፣
ምሰሶቿን አጽንቼ የምይዝ እኔ ነኝ::
ሴላ
4 እብሪተኛውን፣ 'አትደንፋ'፤
ክፉውንም 'ቀንድህን ከፍ
አታድርግ እለዋለሁ፤
5 ቀንድህን ወደ ሰማይ አታንሣ፤
ዐንገትህንም መዝዘህ አትናገር::' "
6 ክብር ከምሥራቅ ወይም ከምዕራብ፣
ወይም ከምድረ በዳ አይመጣምና፤
7 ነገር ግን የሚፈርድ እግዚአብሔር ነው፤
እርሱ አንዱን ዝቅ፣ ሌላውን ከፍ
ያደርጋል::
8 በእግዚአብሔር እጅ ጽዋ አለ፤
በሚገባ የተቀመመና ዐረፋ የሚወጣው
የወይን ጠጅ ሞልቶበታል፤
ይህን ከውስጡ ወደ ውጭ ገለበጠው፤
የምድር ዐመፀኞችም አተላውን ሳይቀር
ይጨልጡታል::
9 እኔ ግን ይህን ለዘላለም ዐውጃለሁ፤
ለያዕቆብም አምላክ ዝማሬ አቀርባለሁ::
10 የክፉዎችን ሁሉ ቀንድ እሰብራለሁ፤
የጻድቃን ቀንድ ግን ከፍ ከፍ ይላል::

## መዝሙር 76

### ግርማው ለሚያስፈራው አምላክ የቀረበ ቅኔ

ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች፤ የአሳፍ መዝሙር፤ ማኅሌት

1 እግዚአብሔር በይሁዳ ታወቀ፤
ስሙም በእስራኤል ታላቅ ነው::
2 ድንኳኑ በሳሌም፣
ማደሪያውም በጽዮን ነው::
3 በዚያም ተወርዋሪውን ፍላጻ፣
ጋሻንና ሰይፍን፣ ጦርንም ሰበረ:: ሴላ
4 አንተ ብርሃን ተላብሰህ ደምቀሃል፤
ግርማዊነትህም ከዘላለም ተራሮች
ይልቃል::
5 ልበ ሙሉ የሆኑት ተዘርፈዋል፤
አንቀላፍተውም ተኝተዋል፤
ከጦረኞቹም መካከል፣
እጁን ማንቀሳቀስ የቻለ የለም::

፥12፥105፥2፥107፥8:15፥145፥5:12:18
75፥2 ዘፀ13፥10፤ መዝ7፥11
75፥3 1ሳሙ2፥8፤ 2ሳሙ22፥8፤ኢሳ 24፥19
75፥4 1ሳሙ2፥3፤ መዝ5፥5፤ዘካ1፥21
75፥5 ኢዮ15፥25
75፥7 ዘፍ16፥5፤ 1ሳሙ2፥7፤ኢዮ5፥11 ፤መዝ50፥6፤58፥11፤147፥6፤ሕዝ21፥26፤ ዳን2፥21፤ሐእ18፥8
75፥8 ምሳ23፥30 ፤ኢሳ51፥17፤ኤር 25፥15፤ዘካ12፥2
75፥9 ዘፍ24፥12፤ መዝ40፥10፤76፥6፤ 108፥1
75፥10 መዝ89፥17 ፤92፥10፤112፥9፤148 ፥14
76፥1 መዝ99፥3
76፥2 ዘፍ14፥18፤ 2ሳሙ5፥7፤መዝ2፥6፤ ዕብ7፥1
76፥3 መዝ46፥9፤ ሕዝ39፥9
76፥4 መዝ36፥9
76፥5 መሳ20፥44፤ መዝ13፥3፤ማቴ9፥24

*75፥2-5፤* ከሰማይ የመጣ የማረጋገጫ ቃል ነው፤ እግዚአብሔር በደለኛውን ወደ ፍርድ ማምጣቱ የማይቀር ነው:: ከጌታ ዘንድ አዲስ ቃል ስለመምጣቱ፣ ወይም እነዚህ ቍጥሮች ከዚህ በፊት በኢሳይያስ በ2ነገ19፥21-34 ላይ የተናገረውን ትንቢታዊ ቃል ስለማስታወሱ ምንም የሚታወቅ ነገር የለም::

*75፥2፤* እግዚአብሔር መፍረዱ አይቀርም፤ ነገር ግን ፍርዱን የሚሰጠው በራሱ ጊዜ ነው::

*75፥3፤* ከክፋት ብዛት የተነሣ የዓለም ምግባራዊ ሥርዐት የተበላሸ ቢመስልም፣ እግዚአብሔር ግን ለዘላለም የማይነቃነቅ ጽኑ መሠረት ነው (የ11፥3 ማብ ይመ):: *ምሰሶ፤* የዓለምን ሥርዐት የሚጠብቅ መሆኑን የሚያመለክት ዘይቤያዊ ወይም ምሳሌአዊ አገላለጽ ነው (የ24፥2 ማብ ይመ)::

75፥4 *እብሪተኛ ... ክፉ፤* በመዝሙረኞቹ አመለካከት ክፉዎች እብሪተኞችና (መዝ10፤ 73፥4-12፤ 94፥4፤ እንዲሁም የ31፥23 ማብ ይመ) ሞኞች ናቸው (14፥1፤ 74፥18:22፤ 92፥6፤ 94፥8 ይመ):: *ቀንድህን ወደ ሰማይ አታንሣ፤* እንደ ተዋጊ በሬ ልቡን ያሳበጠና ያለ እኔም ማንም የለም እያለ የሚደነፋን ሰው የሚያመለክት ምሳሌአዊ አነጋገር ነው፤ "ቀንድ" (ቍ10 ይመ) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንፈስ ጠንካራነትንና አካላዊ ጥንካሬን የሚያመለክት የተለመደ ተምሳሌት ነው::

75፥5 *አንገትህንም መዝዘህ፤* የተቃውሞ ወይም የትዕቢት ምልክት ነው::

*75፥6-8፤* ከምድር የተሰማ የድል ቃል ነው፤ ምናልባት ሌዋዊ የሆነ የመዝሙሩ መሪ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣውን የማጽናኛ ቃል አስፋፍቶ የተናገረው ሳይሆን አይቀርም::

75፥8 *ጽዋ፤* የ16፥5 ማብ ይመ:: *አተላውን፤* ቅመሙ የስካሩን መጠን ጨምሮታል (ምሳ9፥2:5፤ 23፥29-30፤ ማሕ8፥2፤ ኢሳ 65፥11 ይመ):: *ይጨልጡታል፤* እግዚአብሔር ስለሚደፋው ሌላ አማራጭ የላቸውም::

*75፥9፤* ቅን ፈራጅ የሆነውን እግዚአብሔርን ለዘላለም ለማመስገን ቃል የገባበት ክፍል ነው (የ7፥17 ማብ ይመ):: *እኔ፤* ሌዋዊው የመዝሙር መሪ ሕዝቡን ወክሎ የተናገረው ቃል ሳይሆን አይቀርም፤ ተውላጠ ስሙ ግን በ74፥12 ላይ እንደ ተጠቀሰው ለብዙ ቍጥር አነጋገርም ሊውል ይችላል (የመዝ30 ርእስ ማብ ይመ):: *ያዕቆብ፤* እስራኤል ማለት ነው (ዘፍ32፥28 ይመ)::

*75፥10፤* ማን እንደተናገረው አይታወቅም:: ቃሉን የተናገረው ሌዋዊ ሳይሆን ንጉሥ ይመስላል (መዝ101 ይመ):: ሆኖም መዝሙሩ ግን የቤተ መንግሥት መዝሙር አይደለም:: ስለዚህ የቍ9 ተናጋሪ ጌታ የተናገረውን ነገር እያስታወሰ የተናገረው ሳይሆን አይቀርም ብሎ ማሰብ ይሻላል:: *የጻድቃን፤* የ1፥5 ማብ ይመ:: *ከፍ ከፍ ይላል፤* ቍ7፤ እንዲሁም የቍ4 ማብ ይመ::

*መዝ76፤* እግዚአብሔር የእርሱ ከተማ የሆነችውን ኢየሩሳሌምን ለመከላከል ኀይል ያለው መሆኑን የሚያውጅ መዝሙር ነው:: የመዝሙሩ ዐቢይ ሐሳብ ከመዝሙር 46፤ 48፤87 ጋር ይመሳሰላል (የመዝ46 መግቢያን ይመ):: ይህ መዝሙር የተደረሰው የሰናክሬም ሰራዊት ኢየሩሳሌምን ለማጥፋት ሲደነፋ ሳለ፣ እግዚአብሔር እንዳልነበረ ካደረገው በኋላ ነው የሚለው ጥንታዊ ወግ ትክክል ሳይሆን አይቀርም (2ነገ19፥35 ይመ):: ባወቃቀር ረገድ ሲታይ የመዝሙሩ የመግቢያና (ቍ1-3) የመዝጊያ (ቍ11-12) አንጓዎች የመዝሙሩን ዋና ሐሳብ ይዘዋል:: በመካከል ላይ ያለው ባለ ሰባት ቍጥር አንጓ (ቍ4-10)፣ የእግዚአብሔር ፍርድ አስፈሪ መሆኑን በመግለጽ እግዚአብሔርን ያወድሳል:: ቍ4:7:10 አጠቃላይ የሆኑ ጕዳዮችን የሚያወሱ ሲሆን፣ የተቀሩት ቍጥሮች ግን ፍርዱን ይናገራሉ:: ቍ7 ላይ የሚገኘው ማእከላዊ መሥመር (የ6፥6 ማብ ይመ) የአንጓውን ዋና አሳብ የሚናገር ነው::

76ርእስ፤ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ4ርእስ ማብ ይመ:: *በበገናዎች፤* የመዝ4ርእስ ማብ ይመ:: *አሳፍ፤* የመዝ73 ርእስ ማብ ይመ:: *መዝሙር፤* የመዝ30 ርእስ ማብ ይመ::

*76፥1-3፤* እግዚአብሔር የጽዮንን ጠላቶች ዐመድ እንዳደረጋቸው የሚያወሳ ክፍል ነው::

76፥1 *ታወቀ፤* ከአስደናቂ ተግባሩ የተነሣ ለማለት ነው:: *እስራኤል፤* ባለቅኔው ሁለቱን መንግሥታት (ይሁዳንና እስራኤልን) ለያይቶ ለማቅረብ ያሰበ አይመስልም፤ ሆኖም ሁለቱም የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝቦች በመሆናቸው አንድ ላይ ያቀርባቸዋል:: ከአሦራውያን ጦርነት በኋላ ግን፣ ከሰሜኑ መንግሥት የተፈናቀሉ እስራኤላውያን በኢየሩሳሌም ውስጥ በአካባቢዋ ሰፍረዋል::

76፥2 *ድንኳኑ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም፣ "ትንሽ ቤት" ማለት ሲሆን የሚያመለክተውም ቤተ መቅደሱን ነው:: እግዚአብሔር ጠላትን ከፉኛ ስለ መታና ድልንም ስለ ተቀዳጀ ባለቅኔው የእግዚአብሔር የጦር ሜዳ ድንኳን ስለ ሆነው ስለ ቤተ መቅደስ ጥቂት መናገር ይፈልጋል (2ሳሙ11፥11፤ 1ነገ20፥12:16 ይመ):: ነገር ግን 18፥11፤ 31፥20 ይመ:: *ሳሌም፤* ንጽጽሩ እንደሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ማለት ነው (የዘፍ14፥18 ማብ ይመ):: *ጽዮን፤* የ9፥11 ማብ ይመ::

*76፥4-10፤* ግርማ ሞገሱ አስፈሪ የሆነውን እግዚአብሔርን የሚያመሰግን ክፍል ነው፤ ምክንያቱም ታላቅ ፍርዱ የሚያስደነግጥና የሚያርበደብድ ነው (መግቢያውን ይመ)::

*76፥5-6፤* እስራኤላውያን ቀይ ባሕርን በተሻገሩ ጊዜ (ዘፀ 14፥28:30፤ 15፥4-5:10 ይመ)፣ እግዚአብሔር በግብፃውያን ላይ የሰጣቸውን ድል ሳያሳስብ አልቀረም::

6የያዕቆብ አምላክ ሆይ፤ ከተግሣጽህ የተነሣ፣
ፈረስና ፈረሰኛው ጭልጥ ብለው
ተኝተዋል::
7*መፈራት* ያለብህ አንተ ብቻ ነህ፤
በተቈጣህ ጊዜ ማን በፊትህ መቆም
ይችላል?
8አንተ ፍርድን ከሰማይ አሰማህ፤
ምድርም ፈራች ጸጥ አለች፤
9አምላክ ሆይ፤ ይህም የሆነው አንተ
የምድር ጕስቍሎችን ለማዳን፣
ለፍርድ በተነሣህ ጊዜ ነው::　　　ሴላ
10ሰውን ብትቈጣ እንኳ ለክብርህ ይሆናል፤
ከቍጣ የተረፉትንም ትገታቸዋለህ::[1]

11ለአምላካችሁ *ለእግዚአብሔር* ተሳሉ፤
ስእለቱንም አግቡ፤
በእርሱ ዙሪያ ያሉ ሁሉ፣
አስፈሪ ለሆነው ለእርሱ እጅ መንሻ
ያምጡ::
12እርሱ የገዦችን መንፈስ ይሰብራል፤
በምድር ነገሥታትም ዘንድ የተፈራ
ነው::

## መዝሙር 77

### የእስራኤል ጥንተ ነገር አሰላስሎ

*ለመዘምራን አለቃ፤ ለኤዶታም፤ የአሳፍ መዝሙር*

1ድምፄን ከፍ አድርጌ ወደ እግዚአብሔር
ጮኽሁ፤
ይሰማኝም ዘንድ ወደ አምላክ ጮኽሁ::
2በመከራዬ ቀን እግዚአብሔርን ፈለግሁት፤
በሌሊትም ያለ ድካም እጆቼን ዘረጋሁ፤
ነፍሴም አልጽናና አለች::

3አምላክ ሆይ፤ አንተን ባሰብሁ ቍጥር
ቃተትሁ፤
ባወጣሁ ባወረድሁም መጠን
መንፈሴ ዛለች::　　　ሴላ
4ዐይኖቼ እንዳይከደኑ ያዝሃቸው፤
መናገር እስኪሳነኝ ድረስ ታወክሁ::
5የድሮውን ዘመን አሰብሁ፤
የጥንቶቹን ዓመታት አውጠነጠንሁ::
6ዝማሬዬን በሌሊት አስታወስሁ፤
ከልቤም ጋር ተጫወትሁ፤ መንፈሴም
ተነቃቅቶ እንዲህ ሲል ጠየቀ:-

7"ለመሆኑ፣ ጌታ ለዘላለም ይጥላልን?
ከእንግዲህስ ከቶ በጎነትን አያሳይምን?
8ምሕረቱስ ለዘላለም ጠፋን?
የገባውስ ቃል እስከ ወዲያኛው ተሻረን?
9እግዚአብሔር ቸርነቱን ዘነጋ?
ወይስ ከቍጣው የተነሣ ርኅራኄውን
ነፈገ?"　　　ሴላ::

10እኔም፣ "የልዑል ቀኝ እጅ እንደ
ተለወጠ ማሰቤ፣
ይህ ድካሜ ነው" አልሁ::
11*የእግዚአብሔርን* ሥራ አስታውሳለሁ፤
የጥንት ታምራትህን በእርግጥ
አስታውሳለሁ፤
12ሥራህን ሁሉ አሰላስላለሁ፤
ድንቅ ሥራህን ሁሉ አውጠነጥናለሁ::
13አምላክ ሆይ፤ መንገድህ ቅዱስ ነው፤
እንደ አምላካችን ያለ ታላቅ አምላክ ማን
ነው?

[1]10 *በሕዝብህ ላይ የምታወርደው ቍጣ ለክብርህ ይሆናል ወይም በቍጣውም መታሰቢያነት ራስህን ታስታጥቃለህ* የሚሉ አሉ::

76፥6 ዘፀ15፥1፤መዝ50፥21
76፥7 1ዜና16፥25፤ዕዝ9፥15፤መዝ2፥51 ናሆ1፥6፤ራእ6፥17
76፥8 1ዜና16፥30፤ሕዝ38፥20
76፥9 መዝ9፥8፤58፥11፤72፥4፤74፥22፤82፥8፤96፥13
76፥10 ዘፀ9፥16፤ሮሜ9፥17
76፥11 ዘሌ22፥18፤2ዜና32፥23፤መዝ50፥14፤መክ5፥4-5
77፥1 1ነገ8፥52
77፥2 ዘፍ32፥7፤37፥35፤ዘፀ9፥29፤2ሳሙ 22፥7፤ኢዮ11፥13፤መዝ6፥6፤22፥2፤88፥1፤118፥5፤ማቴ2፥18
77፥3 ዘፀ2፥23፤መዝ6፥2፡6፤78፥35፤ኤር45፥3
77፥4 መዝ39፥2
77፥5 ዘዳ32፥7፤መዝ44፥1፤143፥5፤መክ7፥10
77፥7 1ዜና28፥9፤መዝ85፥1፤102፥13፤106፥4
77፥8 መዝ6፥4፤90፥14፤2ጴጥ3፥9
77፥9 መዝ25፥6፤40፥11፤51፥1፤ኢሳ49፥15
77፥10 ዘፀ15፥6
77፥11 ነህ9፥17
77፥12 ዘፍ24፥63፤መዝ143፥5
77፥13 ዘፀ15፥11፤መዝ71፥19፤86፥8

76፥6 *የያዕቆብ አምላክ፤* ከመዝ75 ጋር የሚ ያያዝ ነው (መዝ75፥9 እና ማብ ይመ):: *በተግሣጽህ፤* ከእግዚአብሔር አንጻር ሲታይ ይህ ቃል የሚያመለክተው፤ (1) በሥነ ፍጥረት ላይ የሚገለጠውን እንደ ነጐድጓድ የሚያስፈራውን ክብሩን (18፥15፤ 104፥7፤ 106፥9፤ ኢዮ26፥11፤ ኢሳ50፥2፤ ናሆ1፥4 ይመ) ወይም ጠላቶቹን መሰባበሩን (9፥5፤ 68፥30፤ ኢሳ17፥13 ይመ) ወይም (2) የቍጣውን መብረቅ (80፥16፤ ኢሳ51፥20፤ 54፥9፤ 66፥15፤ ሚል2፥3 ይመ) ሊሆን ይችላል::

*76፥7፤* ከቍ4-10 ላለው ክፍል ማእከላዊና ዐቢይ ሐሳብ ነው (የ6፥6 ማብ ይመ)::

76፥8 *ከሰማይ፤* እግዚአብሔር በጽዮን የሚያድር ቢሆንም (ቍ2 ይመ) በሰማያት ሆኖ ግን ዓለምን በሥልጣኑ ያስተዳድራል::

76፥10 *ሰትቈጣ፤* የ2፥5 ማብ ይመ:: *ለክብርህ ይሆናል፤* ፍርዱን በሰጠ ጊዜ ብዙዎች ነጻ ይወጣሉ፤ ነጻ የወጡ ትም ሰዎች እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ::

*76፥11-12፤* እስራኤል የእግዚአብሔርን ጥበቃ በማስተዋል ለእግዚአብሔር ስእለት እንድትሳልና ሌሎች ሕዝቦችም እግዚ አብሔር የሁሉ ገዥ መሆኑን በመገንዘብ የእጅ መንሻ (ስጦታ) እንዲያመጡለት የሚያሳስብ ክፍል ነው::

76፥11 *ተሳሉ፤* የ50፥14 ማብ ይመ::

76፥12 *የገዥዎች መንፈስ፤* በእብሪት የተሞላ ዐመፀኝ ነታቸው ማለት ነው::

*መዝ77፤* በመከራ ጊዜ የመጽናኛ መዝሙር ነው:: ከቍ1-6 ያለው ሐሳብ መዝሙሩ የመጽናኛ ጸሎት ወይም ከዚህ በፊት የደረሰውን ነገር የሚያስታውስ ይሁን አይሁን ምንም የሚታወቅ ነገር የለም:: በዚህ ክፍል የተገለጸው መከራ የግል እንጂ የሕዝብ (የአገር) አይደለም:: በቍ16-19 ያለው ሐሳብ ከዕን3፥8-10 ጋር ሲነጻጸር መዝሙሩ የተጻፈው ንጉሣዊ አገዛዝ ሊያከትም በተቃረበበት ሰዓት ነው:: መዝሙሩ በመከራ ይጀምርና (ቍ1-9) ጌታ ያከናወናቸውን ሥራዎች በማስታወስ (ቍ10-20) ይጨርሳል::

77ርእስ፤ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ4 ርእስ ማብ ይመ:: *ለኤዶታም፤* የመዝ39 ርእስ ማብ ይመ:: *አሳፍ፤* የመዝ73 ርእስ ማብ ይመ::

*77፥1-9፤* ያለመታከት ለቀረበ ጸሎት እግዚአብሔር መልስ ሳይሰጥ ሲቀር የሚከሰት ጥልቅ ሐዘንና ግራ መጋባት ነው::

77፥2 *ነፍሴ፤* የ6፥3 ማብ ይመ::

*77፥3-6፤* እግዚአብሔር ከዚህ ቀደም ያደረገለትን ምሕ ረት ሲያስብ፣ የበለጠ ግራ ተጋባ (22፥1-11 ይመ):: እግዚአብሔር ፈጥኖ ስላልደረሰለትና ለጸሎቱም መልስ ስላልሰጠው እንቅልፍ አልወሰደውም (ከ3፥5፤ 4፥8 ጋር ያነጻጽሩ)፣ መናገርም አልቻለም (ቍ10-20 ይመ)::

77፥6 *ልቤ፤* የ4፥7 ማብ ይመ::

*77፥7-9፤* መናገር ቢያቅተውም (ቍ4) ልቡ ግን እንደታወከ ነው::

77፥8 *ምሕረቱ፤* የ6፥4 ማብ ይመ::

77፥9 *ቍጣው፤* የ2፥5 ማብ ይመ::

*77፥10-20፤* እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ከግብፅ ባወጣ ጊዜ ያደረጋቸውን ታላላቅ ሥራዎች በማስታወስ፣ የእግዚአብሔ ርን ውለታ ያረጋግጣል::

*77፥10-12፤* እግዚአብሔር መልስ ባይሰጠውም ሐሳቡን ግን አሁን ካለበት አስጨናቂ መከራ ላይ አንሥቶ እግዚአብሔር ከዚህ ቀደም ኀይሉን ወደ ገለጠባቸው ዘመናት ላይ በመመለስ አዲስ ተስፋን ለማግኘት ይሞክራል፤ እንዲህ ያለው ውሳኔ ጽኑ እምነ ትን የሚጠይቅ ነው::

77፥10 *ልዑል፤* የዘፍ14፥19 ማብ ይመ::

77፥11፡14 *ታምራት፤* የ9፥1 ማብ ይመ::

*77፥13-20፤* እግዚአብሔር በግብፃውያን ላይ ያደረገውን ታምራት የሚያስታውስ ክፍል ነው::

*77፥13፤* በዘፀ15፥11 ላይ የተጠቀሰውን ሐሳብ የሚያስ ተጋባ ነው:: *ቅዱስ ነው፤* ወይም፣ "በመቅደሱ ውስጥ ናቸው" ለማ ለት ነው (63፥2 ይመ)::

14ታምራትን የምታደርግ ስምባክ አንተ ነህ፤
በሕዝቦችም መካከል ኀይልህን
ትገልጣለህ።
15የያዕቆብንና የዮሴፍን ልጆች፣
ሕዝብህን በክንድህ ተቤዠሃቸው። ሴላ
16አምላክ ሆይ፤ ውሆች አዩህ፤
ውሆች አንተን አይተው ተሸማቀቁ፤
ጥልቆችም ተነዋወጡ።
17ደመናት ውሃን አንጠባጠቡ፤
ሰማያት አንጐደጐዱ፤
ፍላጾችህም ዙሪያውን አብለጨለጩ።
18የነጐድጓድህ ድምፅ በዐውሎ ነፋስ ውስጥ
ተሰማ፤
መብረቅህ ዓለምን አበራው፤
ምድርም ራደች፤ ተንቀጠቀጠች።
19መንገድህ በባሕር ውስጥ ነው፤
መሄጃህም በታላቅ ውሃ ውስጥ ነው፤
ዱካህ ግን አልታወቀም።
20በሙሴና በአሮን እጅ፣
ሕዝብህን እንደ በግ መንጋ መራኸው።

## መዝሙር 78

## በእስራኤል የተገኘ ታሪክ

የአሳፍ ትምህርት

1ሕዝቤ ሆይ፤ ትምህርቴን ስማ፤
ጆሮህንም ወደ አንደበቴ ቃል
አዘንብል።
2አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ፤
ከጥንት በነበረ እንቈቅልሽ እናገራለሁ፤
3ይህም የሰማነውና ያወቅነው፣
አባቶቻችንም የነገሩን ነው።

77፥14 ዘፀ3፥20፤ 34፥10
77፥15 ዘዐ6፥6
77፥16 ዘፀ14፥21፡ 28፤መዝ114፥4፤ኢሳ 50፥2፤ዕን3፥8፡10
77፥17 ዘፀ9፥23፤ ዘጸ32፥23፤መሳ5፥4፤ መዝ29፥3
77፥18 መሳ5፥4፤2 ሳሙ22፥13፤መዝ 55፥8
77፥19 ዘፀ14፥22፤ ኢዮ9፥8
77፥20ዘፀ4፥16፤13፥ 21፤ዘኍ33፥1፤መዝ 78፥52፤ኢሳ63፥11
78፥1 ኢሳ51፥4፤ 55፥3
78፥2 መዝ49፥4፤ ማቴ13፥35

77፥15 *ተቤዠሃቸው፤* እንደ ተለመደው ሁሉ በዚህም ቦታ፣ “ነጻ አወጣህ” ማለት ነው (74፥2 ይመ)። *ዮሴፍ፤* የብሉይ ኪዳን ጸሐፊዎች አንዳንድ ጊዜ ሰሜናዊውን የእስራኤልን መንግሥት፣ “ዮሴፍ” (ወይም በዮሴፍ ልጅ ስም “ኤፍሬም”) ብለው ይጠሩታል፤ እንዲህም ያደረጉት ከደቡባዊው መንግሥት ከይሁዳ ለመለየት ሲሉ ነው (78፥67፤ 2ሳሙ19፥20፤ 1ነገ11፥28፤ ዕዝ 37፥16፡19፤ አሞ5፥6፡15፤ 6፥6፤ ዘካ10፥6 ይመ)። ሆኖም በዚህ ቦታና በሌላም ስፍራ (80፥1፤ 81፥5፤ አብ18 ይመ) ወደ በኵር ልጅነት ደረጃ ከፍ የተደረገው ዮሴፍ (ዘፍ48፥5 እና ማብ እንዲሁም ኢሱ16፥1-4፤ 1ዜና5፥2፤ ሕዝ47፥13 ይመ) መላ ትውልዱንና የያዕቆብን ዘሮች ሁሉ ይወክላል።

*77፥16-19፤* እግዚአብሔር ቀይ ባሕርን ለሁለት በከፈለ ጊዜ የገለጸውን ክብሩን የሚያስተጋባ ክፍል ሲሆን፣ ቍ16 እና 19 የሚያወሱትም ስለዚሁ ድንቅ ተግባር ነው። በእነዚህ ሁለት ቍጥሮች መካከል ያሉት ቍ17 እና 18 በነጐድጓድና በመሬት መንቀጥቀጥ አምሳል ስለ ተገለጠው የእግዚአብሔር ግርማ ይናገራሉ። ዘፀ14፥19 የሚናገረው ስለ ደመና እንጂ ስለ ነጐድጓድና ስለ መናወጥ አይደለም፤ የዕብራውያን ባለቅኔዎች ግን እግዚአብሔር ለመፍረድ ወይም ሕዝቡን ነጻ ለማውጣት መምጣቱን የሚገልጡት ከሁለቱ አንዱን ወይም ሁለቱንም ተምሳሌቶች በመጠቀም ነው፤ ለእነርሱ የእግዚአብሔር ኀይል አስፈሪ በሆነ መንገድ ከሚገለጥባቸው ነገሮች ውስጥ እነዚህ ሁለቱ ዋናዎቹ ናቸው (18፥12-14፤ 68፥8፤ መሳ5፥4-5፤ ዕን3፥6፡10 ይመ)። በዚህ ቦታ መዝሙረኛው የሚናገረው በብርቱ ውሆች መካከል ተራምዶ ሕዝቡን ነጻ ያወጣው የነጐድጓድና የመሬት መናወጥ አምላክ የሆነው ልዑል እግዚአብሔር መሆኑን ነው። ለክርስቲያኖች እግዚአብሔር ክብሩንና ኀይሉን በሕዝቡ መካከል የገለጠው፣ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ አማካይነት ነው (ማቴ28፥2 ይመ፤ ከኤፌ1፥18-23 ጋር ያነጻጽሩ)።

77፥17 *ፍላጾችህም፤* የመብረቅ ቀስቶች ናቸው።

*77፥20፤* በቍጥር 15 ላይ ላለው ሐሳብ የሚደመድም ነው። *ሕዝብህን ... መራኸው፤* በሲና ምድረ በዳ ማለት ነው።

*መዝ78፤* በብዙ ጕዳዮች ላይ ትምህርት የሚሰጥ መዝሙር ሲሆን በተለይም ደግሞ እስራኤል ከዚህ ቀደም እንዳደረገችው ሁሉ፣ አሁንም በዐመፀኝነት ጸንታ እንዳትቀጥል ነገር ግን የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራና አስደናቂውንም ጸጋ እንድታስተውል እንዲሁም በእግዚአብሔር ላይ ባላት እምነት እየተጋች ቃል ኪዳን ጠብቃ እንድትኖር የሚያስጠነቅቅ ነው። በእግዚአብሔር መታመንና ለእግዚአብሔርም ታማኝ ሆኖ መገኘት ከእግዚአብሔር ሕዝብ የሚጠበቅ መሆኑን በዚህና በሌሎችም የብሉይ ኪዳን ክፍሎች ላይ በስፋት ተገልጾአል። ይህም ታላቁን የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ ከማስተዋል እንጂ፣ እንዲያው ለይስሙላ ከሚደረግና ካልተጨበጠ መመሪያ ወይም አጠቃላይ ከሆነው የሰው ልጆች ንቃተ ኅሊና የሚመነጭ አይደለም፤ ባንጻሩም ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ አለመገኘት እግዚአብሔር በሕዝቡ ሕይወት ውስጥ ያደረጋቸውን ታምራት ስለሚያጣጥል (ስለሚያራክስ) በበለጠ መኰነን አለበት (መዝ105-106 ይመ)። ይህ መዝሙር የእስራኤል መንግሥት ከሁለት ከተከፈለ በኋላ ወይም ነቢዩ ሆሴዕ በነበረበት ዘመን የተጻፈ ሳይሆን አይቀርም (ኤፍሬም የሰሜኑ መንግሥት ትልቁ ነገድ ስለነበር፣ ሆሴዕና ኢሳይያስ የሰሜኑን መንግሥት ኤፍሬም ብለው ይጠሩት ነበር)። በዚህ ቦታ የእስራኤል እምነተ ቢስነት በኤፍሬም ኀጢአት ተመስሎአል (ቍ9)፤ መዝሙሩ እስራኤል በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ተናቀች (ቍ59)፣ ሴሎም በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ተተወች (ቍ60)፣ ይሁዳና ጽዮን ግን እንደ ተመረጡ በማስታወስ (ቍ68) ይደመድማል። ከአሳፍ ወገን በሆነ አንድ ሰው እንደ ተጻፈ የሚገመተው ይህ መዝሙር፣ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በሰሜኑ ያሉ ወንድሞቻቸውን በመከተል ከእምነታቸው እንዳይስቱ የተጻፈ ማስጠንቀቂያ ነው። የመዝሙሩ አርታኢዎች ይህን መዝሙር ከመዝ77 ቀጥለው በማስቀመጣቸው፣ ዳዊት እንደ ሙሴና እንደ አሮን ሁሉ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ የሾመው እረኛ አድርገው አቅርበውታል (ቍ70-72፤ 77፥20 ይመ)፤ በዚህም፣ ዳዊት ጠላቶቹን ድል በማድረግና የተስፋዪቱንም ምድር በመውረስ የቀድሞውን ድል የበለጠ እንዲያብብ ያደርጋል። ይህ መዝሙር ከ77 መስመሮች (በቍጥር ደረጃ ግን 72 ቍጥሮች አሉት) እና ከሰባት አንጓዎች የተዋቀረ ሲሆን 11 መስመሮች ያሉት መግቢያም አለው። ከመግቢያው በኋላ የሚገኙት አንጓዎች፣ ባወቃቀር ረገድ እኩኩል ናቸው፤ ይኸውም 8መስመር፣ 16መስመር፣ 9መስመር፣ 16መስመር፣ 8መስመር ናቸው። በተከታታይ የቀረቡት ሁለቱ ባለ 16 መስመሮችና ሁለቱ ባለ 9መስመር አንጓዎች የመዝሙሩን ዐቢይ ሐሳብ የሚያስተጋቡ ሲሆን፣ ሁለቱ ባለ 8መስመር አንጓዎች ግን የዋናው ሐሳብ መቀንበቢያ ናቸው፤ እነዚህ መቀንበቢያዎች በእስራኤል ሕዝብ ኀጢአትና (በቍ9-16 ላይ ኤፍሬም የተባለው ነው) መጨረሻ በሌለው የእግዚአብሔር ምሕረት መካከል ያለውን ንጽጽር ያሳያሉ፤ የእግዚአብሔር ምሕረት በጠላቶቹ ላይ ድልን በመቀዳጀቱ፣ ጽዮንና ዳዊትን (ቍ65-72) በመምረጥ ተረጋግጦአል።

*መዝ78 ርእስ ትምህርት፤* የመዝ32 ርእስ ማብ ይመ። *አሳፍ፤* የመዝ73 ርእስ ማብ ይመ።

*78፥1-8፤* ልጆቻችን ለእግዚአብሔር ታማኝ ይሆኑ ዘንድ አባቶቻችን የነገሩንን መስማት አለባቸው።

*78፥1-2፤* ይህ መግቢያ ቅኔያዊ በሆነ የአጻጻፍ ስልት የተጻፈ ነው (የመጽሐፈ ምሳሌ መግቢያን እንዲሁም መዝ49፥1-4 ይመ)።

78፥2 *ምሳሌዎች ... የተሰወሩትን፤* የዕብራይስጡ ቅጅ እነዚህን ሁለት ቃላት በ49፥4 ላይ (“ምሳሌ”፣ “እንቆቅልሽ”) በሕዝ17፥2 ላይ ደግሞ (“ምሳሌ”፣ “ምስያ”) በማለት አቅርቦአቸዋል። እዚህ ላይ የመዝሙሩ ደራሲ እነዚህን ቃላት የወሰደው የጥበብ ቋንቋን ከሚጠቀሙ ትንቢታዊ ጽሑፎች ላይ ስለመሆኑ አጠያያቂ ነው። በመዝ49፥4 ላይ የተጠቀሱት ሁለት ቃላት ልዩ አግባብ ያላቸው ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ግን ሰፊ ትምህርቶችን ለመስጠት ጥቅም ላይ የሚውሉ ቃላት ነበሩ። *ከጥንት ጀምሮ፤* ከድሮ ጊዜ ጀምሮ ትምህርት ለመስጠት ይጠቀሙባቸው ነበር ለማለት ነው። ማቴ13፥35 ይህንን ክፍል በመጥቀስ ኢየሱስ በምሳሌ እንደሚያስተምር ትንቢት ተነግሮ እንደ ነበር ያወሳል። ማቴዎስ በዚህ መዝሙር ውስጥ በአንድ ታላቅ ነቢይ ላይ የሚፈጸም ትንቢታዊ ቃል እንዳለ አስተውሎአል። ሆኖም በመዝሙሩ ውስጥ ያሉት “ምሳሌዎች” ኢየሱስ ካስተማራቸው ነገሮች ጋር ሳይሆን እስጢፋኖስ (ሐሥ7) ካስተማረው ነገር ጋር ነው የሚመሳሰሉት።

*78፥4-5፤* የእግዚአብሔርንም የማዳን ሥራና የቃል ኪዳኑንም ሥርዐት የሚናገር ክፍል ነው፤ እነዚህን ሁለቱን ነገሮች በሚገባ ዘርዝሮ ማስተማር ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም እያንዳንዱ ትውልድ እግዚአብሔርን እየታመነና እየታዘዘ እንዲኖር ለማድ

[4]እኛም ከልጆቻቸው እንደብቀውም፤
የእግዚአብሔርን ምስጋና፣
ኀይሉንና ያደረገውን ድንቅ ሥራ፣
ለሚቀጥለው ትውልድ እንናገራለን።
[5]ለያዕቆብ ሥርዐትን መሠረተ፤
በእስራኤልም ሕግን ደነገገ፤
ልጆቻቸውንም እንዲያስተምሩ፣
አባቶቻችንን አዘዘ።
[6]ይህም የሚቀጥለው ትውልድ እንዲ
ያውቅ፣
እነርሱም በተራቸው ለልጆቻቸው፣
ገና ለሚወለዱት እንዲነግሩ ነው።
[7]እነርሱም በእግዚአብሔር ይታመናሉ፤
የእግዚአብሔርን ሥራ አይረሱም፤
ትእዛዞቹንም ይጠብቃሉ።
[8]ነገር ግን እንደ አባቶቻቸው፣
እልከኞችና ዐመፀኞች፣
ልቡን ያላቀና፣
መንፈሱም በእግዚአብሔር የማይታመን
ትውልድ አይሆኑም።

[9]የኤፍሬም ልጆች የታጠቁ ቀስተኞች
ቢሆኑም፣
በጦርነት ቀን ወደ ኋላ ተመለሱ።
[10]የእግዚአብሔርን ኪዳን አልጠበቁም፤
በሕጉም መሠረት ለመሄድ እንቢ አሉ።
[11]እርሱ የሠራውን ሥራ፣
ያሳያቸውንም ድንቅ ነገር ረሱ።
[12]አባቶቻቸው በዐይናቸው እያዩ፣
በግብፅ አገር፣ በጣኔዎስ ምድር ታምራት
አደረገ።
[13]ባሕሩን ከፍሎ አሻገራቸው፤
ውሃውንም እንደ ክምር አቆመ።
[14]ቀን በደመና መራቸው፤
ሌሊቱንም ሁሉ በእሳት ብርሃን።
[15]ዐለቱን በምድረ በዳ ሰነጠቀ፤
እንደ ባሕር የበዛ ውሃ
አጠጣቸው፤
[16]ምንጭ ከቋጥኝ አፈለቀ፤
ውሃን እንደ ወንዝ አወረደ።

[17]እነርሱ ግን በምድረ በዳ በልዑል
ላይ በማመፅ፣
በእርሱ ላይ ኀጢአት መሥራታቸውን
ቀጠሉ።
[18]እጅግ የተመኙትን ምግብ በመጠየቅ፣
እግዚአብሔርን በልባቸው ተፈታተኑት።
[19]እንዲህም ብለው በእግዚአብሔር ላይ
ተናገሩ፤
"እግዚአብሔር በምድረ በዳ ማዕድ
ማሰናዳት ይችላልን?
[20]ዐለቱን ሲመታ፣ ውሃ ተንዶለዶለ፤
ጅረቶችም ጐረፉ፤
ታዲያ፣ እንጀራንም መስጠት ይችላል?
ሥጋንስ ለሕዝቡ ሊያቀርብ ይችላል?"
[21]እግዚአብሔር ይህን ሲሰማ፣ እጅግ
ተቈጣ፤
በያዕቆብም ላይ እሳት ነደደ፤
ቍጣውም በእስራኤል ላይ ተነሣ፤
[22]በእግዚአብሔር አላመኑምና፤
በእርሱም ማዳን አልታመኑም።
[23]እርሱ ግን ከላይ ደመናትን አዘዘ፤
የሰማይንም ደጆች ከፈተ፤
[24]ይበሉም ዘንድ መና አዘነበላቸው፤
የሰማይንም መብል ሰጣቸው።
[25]ሰዎች የመላእክትን እንጀራ በሉ፤
ጠግበው እስከሚተርፍ ድረስ ምግብ
ላከላቸው።

78፥3 መሳ6፥13
78፥4 ዘዳ11፥19፤ 32፥7፤ኢዮ5፥9፤መዝ 26፥7፤71፥17:18
78፥5 መዝ19፥7፤ 81፥5፤147፥19
78፥6 መዝ22፥31
78፥7 ዘዳ5፥29፤ 6፥12
78፥8 ዘፀ23፥21፤ 32፥9፤ዘዳ21፥18፤ 2ዜና30፥7፤ኢሳ 30፥9፤65፥2
78፥9 ቍ57፤መሳ 20፥39፤1ዜና12፥2፤ ሆሴ7፥16
78፥10 ዘፀ16፥28፤ ኢሱ7፥11፤2ነገ17፥15 ፤ኤር11፥8
78፥11 መዝ106፥13
78፥12 ዘፀ11፥9፤ ዘኍ13፥22፤ነህ9፥17፤ መዝ106፥22
78፥13 ዘፀ14፥21: 22፤15፥8፤መዝ66፥6፤ 136፥13
78፥14 ዘፀ13፥21፤ 105፥39
78፥15 ዘኍ20፥11፤ 1ቆሮ10፥4
78፥17 ቍ32:40፤ ዘዳ9፥22፤ኢሳ30፥1፤ 63፥10፤ዕብ3፥16
78፥18 ዘፀ15፥24፤ 17፥2፤ዘኍ11፥4፤ 1ቆሮ10፥9
78፥19 ዘኍ21፥5
78፥20 ዘኍ11፥18፤ 20፥11፤ኢሳ35፥6
78፥21 ዘኍ11፥1
78፥22 ዘዳ1፥32፤ ዕብ3፥19
78፥23 ዘፍ7፥11፤ 2ነገ7፥2
78፥24 ዘፀ16፥4፤

ረግ ሁለቱም ወሳኝነት አላቸው (ቍ7-8 ይመ)።

78፥4 *እንደብቀውም፤* ኢዮ15:18 ይመ።

78፥5 *ልጆቻቸውንም እንዲያስተምሩ፤* ዘፀ10፥2፤ 12፥26-27፤ 13፥8:14፤ ዘዳ4፥9፤ 6፥20-21 ይመ።

78፥8 *እልከኞችና ዐመፀኞች፤* ለወላጆቹ እንደማይታዘዝ ልጅ ማለት ነው (ዘዳ9፥6-7:24፤ 31፥27 ይመ)። *ትውልድ፤* ከግብፅ የወጡት ሕዝቦች ብቻ ሳይሆኑ (ቍ9-11:56-64)፣ በየትኛውም ዘመን ያሉና ተመሳሳይ ባሕርይ ያላቸው ሕዝቦች ማለት ነው (24፥6፤ ዘዳ 32፥5:20 ይመ)። *ልቡን፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

*78፥9-16፤* ሰሜናዊው መንግሥት የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን አፍርሶአል፤ የማዳን ሥራውንም ረስቶአል (ይህ ሐሳብ በነቢዩ አሞጽና ሆሴዕ ተደጋግሞ ተነግሮአል)፤ የእስራኤል ታሪክ የዐመፀኝነት ታሪክ ነው (ቍ9-16:32-39:56-64)፤ ገና ከምድረ በዳው ጒዞ ጀምሮ በእግዚአብሔር ላይ ስታምፅ ነበር (ቍ17-31:40-55)።

78፥9 *የኤፍሬም ልጆች፤* ሰሜናዊው መንግሥት በአብዛኛው የኤፍሬም ነገድ ነው (መግቢያውን ይመ)። *ወደ ኋላ ተመለሱ፤* የኤፍሬምም ነገድ ሆነ ሰሜናዊው መንግሥት በጦርነት ቀን ፈርቶ ብርቱ ተዋጊ የሆኑበት ጊዜ የለም (ዘዳ33፥17 ይመ)። ይህ ጥቅስ እስራኤል በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ላይ ማመፁን የሚያመለክት ተምሳሌት ተደርጐ ቢወሰድ የተሻለ ነው (ቍ10 ይመ)፤ ይህም በቍ57 ላይ፣ "ሰንካላ ቀስት" ከሚለው ነገር ጋር የሚመሳሰል ነው።

*78፥12-16፤* በግብፅ ምድር የተደረጉትን ታምራቶች፣ የቀይ ባሕርን ለሁለት መከፈልና በምድረ በዳም የተፈጸሙትን ትንግርቶች አጠቃሎ የሚያቀርብ ክፍል ነው።

*78፥12፤* ዘፀ7-12 ይመ። *ጣኔዎስ፤* ከዐባይ ወንዝ ተፋሰስ በስተ ሰሜን ምሥራቅ የምትገኝ ከተማ ናት (ቍ43፤ ዘኍ13፥22 እና ማብ ይመ)።

*78፥13፤* ዘፀ14፥1-15፥21 ይመ።

*78፥15-16፤* ቍ20፤ ዘፀ17፥6፤ ዘኍ20፥8:10-11 ይመ።

*78፥17-31፤* የእስራኤል ሕዝብ በምድረ በዳ ስላሳየው ዐመፀኝነት፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ስላደረገው ቸርነትና ስለ ቍጣውም የሚናገር ክፍል ነው።

78፥17 *ቀጠሉ፤* ምንም እንኳን እስራኤላውያን በምድረ በዳ የፈጸሙት በደል በግልጽ ባይጠቀስም፣ ባለቅኔው ግን እስራኤላውያን ማራ ተብሎ በሚጠራው ቦታ ውሃ በማጣታቸው (ዘፀ 15፥24 ይመ) እንዴት እንዳጕረመረሙና እግዚአብሔርም እንዴት በታምር ውሃ እንዳዘጋጀላቸው አንባቢዎቹ እንዲያስታውሱ የፈለገ ይመስላል።

*78፥18፤* ዘፀ16፥2-3 ይመ። *እግዚአብሔርን ... ተፈታተኑት፤* ቍ41:56 እንዲሁም የዘፀ17፥2 ማብ ይመ።

78፥19 *እግዚአብሔር ... ማዕድ ማዘጋጀት ይችላልን?* ከዚህ የተለየ ዐላማ የዋለውን ተመሳሳይ አጠቃቀም በ23፥5 ላይ ይመ።

78፥20 *እንጀራ ... ሥጋ፤* ባለቅኔው ምናልባት ሁለት ተከታታይ ትረካዎችን (ዘፀ16፥2-3፤ ዘኍ11፥4) አንድ ላይ ጨምቆ ሳያቀርብ አልቀረም።

78፥21 *ቍጣ፤* ቍ31:49-50:58-59:62 እንዲሁም የ2፥5 ማብ ይመ።

78፥23 *የሰማያትንም ደጆች ከፈተ፤* ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነን አጠቃቀም በዘፍ7፥11፤ በ2ነገ7፥2፤ በሚል3፥10 ይመ።

78፥25 *የመላእክት እንጀራ፤* እንዲህ የተባለው ከሰማይ ስለ ወረደ ነው። *መላእክትን፤* ቃል በቃል ሲተረጐም፣ "ኀያላን" ማለት ነው። "መላእክት" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል በዚህ ቦታ ብቻ የሚገኝ ሲሆን ቃሉ ግን የሰማይ አካላትን እንደሚያመለክት

26 የምሥራቁን ነፋስ ከሰማይ አስነሣ፤
የደቡብንም ነፋስ በኀይሉ አመጣ::
27 ሥጋን እንደ ዐፈር፣
የሚበሩትን ወፎች እንደ ባሕር አሸዋ
አዘነበላቸው፤
28 በሰፈራቸውም ውስጥ፣
በድንኳናቸው ዙሪያ አወረደ::
29 እነርሱም እስኪጠግቡ ድረስ በሉ፤
እጅግ የጐመጁትን ሰጥቶአቸዋልና::
30 ነገር ግን ገና ምኞታቸውን ሳያረኩ፣
ምግቡ ገና በአፋቸው ውስጥ እያለ፣
31 የእግዚአብሔር ቍጣ በላያቸው ላይ መጣ፤
ከመካከላቸውም ብርቱ ነን ባዮችን
ገደለ፤
የእስራኤልንም አበባ ወጣቶች ቀጠፈ::
32 ይህም ሁሉ ሆኖ በበደላቸው ገፉበት፤
ድንቅ ሥራዎቹንም አላመኑም::
33 ስለዚህ ዘመናቸውን በከንቱ፣
ዕድሜአቸውንም በድንጋጤ ጨረሰ::
34 እርሱ በገደላቸው ጊዜ ፈለጉት፤
ከልባቸው በመሻትም ወደ እግዚአብሔር
ተመለሱ::
35 እግዚአብሔር ዐለታቸው፣
ልዑል አምላክ ቤዛቸው እንደ ሆነ
አሰቡ::
36 ነገር ግን በአፋቸው ሸነገሉት፤
በአንደበታቸው ዋሹት::
37 ልባቸው በእርሱ የጸና አልነበረም፤
ለኪዳኑም ታማኞች አልነበሩም::
38 እርሱ ግን መሓሪ እንደ መሆኑ፣
በደላቸውን ይቅር አለ፤
አላጠፋቸውም፤
ቍጣውን ብዙ ጊዜ ገታ፤
መዓቱንም ሁሉ አላወረደም::
39 ወጥቶ የማይመለስ ነፋስ፣
ሥጋ ለባሾች መሆናቸውን አሰበ::

ዮሐ6፥31
78፥26 ዘኍ11፥31
78፥27 ዘፀ16፥13፤ ዘኍ11፥31
78፥29 ዘኍ11፥20
78፥30 ዘኍ11፥33
78፥31 ኢሳ10፥16
78፥32 ቍ11፡17፡ 22
78፥33 ዘኍ14፥29፡ 35
78፥34 ዘዳ4፥29፤ ሆሴ5፥15
78፥35 ዘፍ49፥24፤ ዘዳ9፥26
78፥36 ሕዝ33፥31
78፥37 ቍ8፤ሐሥ 8፥21
78፥38 ዘፀ34፥6፤ ኢዮ9፥13፤መዝ25፥11 ፤85፥2፤ኢሳ1፥25፤27፥ 9፤30፥18፤48፥10፤ ዳን11፥35
78፥39 ዘፍ6፥3፤ ኢዮ7፥7፤ኢሳ29፥5፤ ያዕ4፥14
78፥40 ዘፀ23፥21፤ መዝ95፥8፤106፥14፤ ኤፌ4፥30
78፥41 ዘፀ17፥2፤ 2ነገ19፥22፤መዝ71፥2 2፤89፥18
78፥42 መሳ3፥7፤ ነህ9፥17፤መዝ27፥11
78፥43 ዘፀ3፥20፤ 10፥1
78፥44 ዘፀ7፥20፡21 ፤መዝ105፥29
78፥45 ዘፀ8፥2፡6፡ 24፤መዝ105፥31
78፥46 ዘፀ10፥13፤ ናሆ3፥15
78፥47 ዘፀ9፥23፤መዝ 105፥32፤147፥17
78፥48 ዘፀ9፥25
78፥49 ዘፍ19፥13፤ ዘፀ15፥7፤1ቆሮ10፥10
78፥51 ዘፀ12፥12፤ መዝ105፥23፤

40 በምድረ በዳ ስንት ጊዜ ዐመፁበት!
በበረሓስ ምን ያህል አሳዘኑት!
41 ደግመው ደጋግመው እግዚአብሔርን
ተፈታተኑት፤
የእስራኤልንም ቅዱስ አስቈጡት::
42 እነርሱን በዚያን ቀን ከጠላት
የታደገበትን፣
ያን ኀይሉን አላስታወሱም፤
43 በግብፅ ያደረገውን ታምራዊ ምልክት፣
በጣኔዎስም በረሓ ያሳየውን ድንቅ ሥራ
አላሰቡም::
44 ወንዞቻቸውን ወደ ደም ለወጠ፤
ከጅረቶቻቸውም መጠጣት አልቻሉም::
45 የዝንብ ሰራዊት ሰደደባቸው፤
ነደፏቸውም፤
ጓጉንቸርም ላከባቸው፤ ሰዎችንም
አጠፉ::
46 አዝመራቸውን ለኵብኵባ፣
ሰብላቸውንም ለአንበጣ ሰጣቸው::
47 የወይን ተክላቸውን በበረዶ፣
የበለስ ዛፋቸውንም በውርጭ አጠፋ::
48 ከብቶቻቸውን ለበረዶ፣
የከብት መንጋቸውን ለመብረቅ እሳት
ዳረገ::
49 ጽኑ ቍጣውን በላያቸው ሰደደ፤
መዓቱን፣ የቅናቱን ቍጣና መቅሠፍቱን
ላከባቸው፤
አጥፊ የመላእክት ሰራዊትም
ሰደደባቸው::
50 ለቍጣው መንገድ አዘጋጀ፤
ነፍሳቸውንም ከሞት አላተረፈም፤
ነገር ግን ሕይወታቸውን ለመቅሠፍት
አሳልፎ ሰጠ::
51 የዐፍላ ጕልበታቸው መጀመሪያ
የሆኑትን በኵር ድንኳን፣
በኵሮቻቸውንም ሁሉ በግብፅ ምድር
ፈጀ::

በግልጽ ማጤን ይቻላል (103፥20 ይመ)::

*78፥26-28፤* ዘፀ16፥13፤ ዘኍ11፥31 ይመ::

78፥26 *የምሥራቁን ነፋስ ... የደቡብንም ነፋስ፤* በዚህ ወቅት ድርጭቶቹ ከግብፅ ተሰደው ወደ ሌላ ስፍራ ይሄዱ ስለ ነበር የደቡብ ነፋስ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ሲወስዳቸው የምሥራቅ ነፋስ ደግሞ እስራኤላውያን ወደ ሚገኙበት ወደ ምድረ በዳ ጠምዘዞ ወስዶአቸው ሊሆን ይችላል (የዘኍልቍ መጽሐፍ ግን የነፋ ስን አቅጣጫ አያመለክትም)::

78፥27 *እንደ ዐፈር ... እንደ ... አሸዋ፤* ከፍተኛ ቍጥ ርን ለማመልከት የገቡ ምሳሌዎች ናቸው (የዘፍ 13፥16 ማብ ይመ)::

*78፥30-31፤* ዘኍ11፥33 ይመ::

*78፥32-39፤* ዐመፀኝነት የእስራኤል ሕይወት መሆኑ የታወ ቀው ሕዝቡ የምድረ በዳውን ጕዞ ገና በጀመረበት ወቅት ነው (ቍ17-31)፤ ይህም ዐመፀኝነት በምድረ በዳው ጕዞም ቀጥሎ ነበር::

78፥32 *አላመኑም፤* በከነዓናውያን ላይ እግዚአብሔር ድልን እንደሚሰጣቸው ለማለት ነው (ዘኍ14፥11 ይመ)::

*78፥33፤* ከግብፅ የወጣው የእስራኤል ሕዝብ፣ በምድረ በዳ ወድቆ እንዲቀር ተፈረደበት (ዘኍ14፥22-23፡28-35 ይመ)::

*78፥34-37፤* በመሳፍንት ዘመን አንዴ ወደ እግዚአብሔር መመለስ አንዴ ደግሞ/ከእግዚአብሔር መራቅ የእስራኤል ሕዝብ የዕለት ተዕለት ሕይወት ነበር::

78፥35 *ዐለታቸው፤* የ18፥2 ማብ ይመ:: *ቤዛቸው፤* ነጻ ያወጣቸው ለማለት ነው (የዘፀ6፥6 ማብ ይመ)::

*78፥36፤* ኢሳ29፥13 ይመ::

78፥37 *ልባቸው፤* የ4፥7 ማብ ይመ::

*78፥38፤* ዘፀ32፥14፤ ዘኍ14፥20 ይመ:: *በደላቸውን ይቅር አለ፤* የ65፥3 ማብ ይመ::

*78፥39፤* 103፥14 እንዲሁም የ10፥18 ማብ ይመ::

*78፥40-64፤* ይህ ሁለተኛው ዑደት ነው (የመጀመሪያው በቍ17-39 ይገኛል)::

*78፥40-55፤* የእስራኤል ዐመፀኝነት የጀመረው በምድረ በዳ ነው፤ እግዚአብሔር የተለያዩ መቅሰፍቶችን በማዝነብ ከግብፅ ባርነት እንዴት እንዳወጣት ልታስታውስ አልቻለችም (ቍ12 ይመ)፤ እግዚአብሔር ግን በባሕርና በምድረ በዳ ውስጥ እየመራ ወደ ተስፋዪቱ ምድር አድርሷት ነበር::

78፥41 *የእስራኤልንም ቅዱስ፤* 71፥22፤ 89፥18ይመ፤ እን ዲሁም የኢሳ1፥4 ማብ ይመ::

*78፥44-51፤* በግብፃውያን ላይ የዘነበውን መቅሠፍት ይዘረ ዝራል (ዘፀ7-12 ይመ):: በዘፀአት መጽሐፍ ላይ በቅደም ተከተል የመጀመሪያውና የመጨረሻው መቅሠፍት ብቻ የተጠቀሰ ሲሆን 3ኛው፣ 5ኛው፣ 6ኛውና 9ኛው መቅሠፍት ግን በዚህ ክፍል አልተገለጸም::

78፥47 *የበለስ ዛፋቸውንም፤* የአሞ7፥14 ማብ ይመ::

78፥49 *አጥፊ የመላእክት ሰራዊት፤* ባለቅኔው የእግዚአ ብሔርን ቍጣ መዓትና ጥላቻ በጥፋት መልእክተኞች መስሎ አቸዋል::

78፥51 *ድንኳን፤* ጊዜያዊ መኖሪያ ናቸው:: *ካም፤* ከግብፅ ጋር ያለውን ዝምድና ለመረዳት 105፥23፡37፤ 106፥21-22፤

52ሕዝቡን ግን እንደ በግ አወጣቸው፤
በምድረ በዳም እንደ መንጋ መራቸው።
53በሰላም መራቸው፤ እነርሱም አልፈሩም፤
ጠላቶቻቸውን ግን ባሕር ዋጣቸው።
54ቀኝ እጁም ወዳስገኘችው ወደዚህ ተራራ፣
ወደ ቅድስት ምድር አገባቸው።
55ሕዝቦችን ከፊታቸው አባረረ፤
ምድራቸውን ርስት አድርጎ
አከፋፈላቸው፤
የእስራኤልንም ነገዶች በጠላቶቻቸው
ቤት አኖረ።

56እነርሱ ግን ልዑል አምላክን ተፈታተኑት፤
በልዑልም ላይ ዐመፁ፤
ሥርዐቱንም አልጠበቁም።
57ተመልሰው እንደ አባቶቻቸው ከዳተኛ
ሆኑ፤
እንደማያስተማምን ጠማማ ቀስት
ተወላገዱ።
58በኰረብታ ማምለኪያዎቻቸው
አስቈጡት፤
ተቀርጸው በተሠሩ ጣዖቶቻቸው
አስቀኑት።
59እግዚአብሔር ይህን በሰማ ጊዜ እጅግ
ተቈጣ፤
እስራኤልንም ፈጽሞ ተወ።

60በሰዎች መካከል ያቆማትን ድንኳን፣
የሴሎን ማደሪያ ተዋት።
61የኀይሉን ምልክት አስማረካት፤
ክብሩንም ለጠላቶቹ እጅ አሳልፎ ሰጠ።
62ሕዝቡን ለሰይፍ ዳረገ፤
በርስቱም ላይ እጅግ ተቈጣ።
63ጕልማሶቻቸውን እሳት በላቸው፤
ልጃገረዶቻቸውም የሰርግ ዘፈን
አልተዘፈነላቸውም።
64ካህናታቸው በሰይፍ ተገደሉ፤
መበለቶቻቸውም ማልቀስ ተሳናቸው።

65ጌታም ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ፤
የወይን ጠጅ ስካር እንደ በረደለት
ጀግናም ብድግ አለ።
66ጠላቶቹን መትቶ ወደ ኋላ መለሳቸው፤
የዘላለም ውርደትም አከናነባቸው።
67የዮሴፍን ድንኳን ተዋት፤
የኤፍሬምንም ነገድ አልመረጠም።
68ነገር ግን የይሁዳን ነገድ፣
የወደዳትን የጽዮንን ተራራ መረጠ።
69መቅደሱን እንደ ታላቅ ከፍታ፣
ለዘላለም እንደ መሠረታት ምድር
ሠራት።
70ባሪያውን ዳዊትን መረጠ፤

106፥22፤135፥8
78፥52 ኢዮ21፥11፤ መዝ28፥9
78፥53 ዘፀ14፥28፤ 15፥7፤106፥10
78፥54 መዝ44፥3
78፥55 ዘዳ1፥38፤ ኢሱ13፥7፤መዝ44፥2፤ ሐሥ13፥19
78፥57 ቍ9፤2ዜና 30፥7፤ሕዝ20፥27
78፥58 ዘፀ20፥4፤ ዘሌ26፥30፤ዘዳ5፥8፤3 2፥21፤መሳ2፥12
78፥59 ዘሌ26፥28፤ ዘኍ32፥14፤ዘዳ32፥19 ፤መዝ55፥19
78፥60 ኢሱ18፥1፤ ሕዝ8፥6
78፥61 1ሳሙ4፥17 ፤መዝ132፥8
78፥62 ዘዳ28፥25፤ 1ሳሙ10፥1
78፥63 ዘኍ11፥1፤ 1ነገ4፥32፤ኤር7፥34፤ 16፥9፤25፥10
78፥64 1ሳሙ4፥17
78፥65 መዝ44፥23
78፥66 1ሳሙ5፥6
78፥67 ኤር7፥15፤ ሆሴ9፥13፤12፥1
78፥68 ዘፀ15፥17፤ ዘኍ1፥7፤መዝ68፥16፤ 108፥8
78፥69 መዝ15፥1 78፥70 1ሳሙ16፥1

ዘፍ10፥6 እና ማብ ይመ።

78፥53 *ባሕር፤* ቀይ ባሕርን ለማለት ነው።

*78፥55፤* በኢያሱ መጽሐፍ ላይ የተነገረው ታሪክ ባጭሩ የቀረበበት ቦታ ነው።

*78፥56-64፤* ዐመፀኛነት የእስራኤል ሕዝብ ሕይወት እንደ ሆነ በተስፋዪቱም ምድር ቀጥሎአል (ይህም በመጽሐፈ መሳፍንት ላይ ተደጋግሞ የተነገረ ታሪክ ነው 1ሳሙ2፥12-7፥2 ይመ)፣ ስለዚህ እግዚአብሔር እስራኤልን እርግፍ አድርጎ ተወ (ቍ59፤ ኤር7፥15 ይመ)።

78፥57 *ጠማማ ቀስት፤* የቍ9 ማብ ይመ።

78፥58 *በኰረብታ ማምለኪያቸዎቻቸው፤* የ1ሳሙ9፥12 ማብ ይመ። *አስቀኑት፤* እግዚአብሔር እርሱን በማይታዘዙት ላይ የሚገልጸውን የሚያሳይ ባሕርይ ነው (የዘፀ20፥5 ማብ ይመ)።

78፥59 *እስራኤልንም ፈጽሞ ተወ፤* ለጠላቶቿ አሳልፎ ለጣት ማለት ነው፤ እንዲህ ማለት ግን እግዚአብሔር እስራኤልን ለዘላለም ይተዋታል ማለት አይደለም፤ ሌላው ቀርቶ ዐሥሩን የሰሜን ነገዶች እንኳ ለዘላለም አይተዋቸውም፤ መዝሙረኛውም እስራኤል ለዘላለም ትተዋለች የሚል ሐሳብ ጨርሶ የለውም።

78፥60 *ሴሎ፤* ከኢያሱ ዘመን ጀምሮ የአምልኮ ማዕከል ነበረች (ኢሱ18፥1፡8፤ 21፥1-2፤ መሳ18፥31፤ 1ሳሙ1፥3፤ ኤር 7፥12 ይመ)፤ ሴሎ በኤፍሬም አገር በቤቴልና በሴኬም መካከል ትገኛለች መሳ21፥19 ይመ)። ፍልስጥኤማውያን የቃል ኪዳኑን ታቦት በማረኩ ጊዜ ወይም ከዚያ በኋላ የሴሎን ከተማ እንዳጠፉ ይታወቃል (የኤር7፥12 ማብ ይመ)።

78፥61 *የኀይሉን... ክብሩን፤* የቃል ኪዳኑ ታቦት መጠሪያ ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ንጉሥ መሆኑን፣ የኀይሉና የክብሩም መገለጫ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው (26፥8፤ 63፥2፤ 1ሳሙ4፥3፡21-22 ይመ)።

78፥62፡71 *ርስቱ፤* ዘዳ9፥29 ይመ።

78፥63 *እሳት፤* አብዛኛውን ጊዜ ከሰይፍ ጋር የሚዛመድ ሲሆን (ቍ62፡64 ይመ)፣ በጥንት ዘመን ሰዎች ጠላትን ለመደምሰስ ከሚጠቀሙባቸው ሁለት የጦር መሣሪያዎች ውስጥ አንዱ ነው። *የሰርግ ዘፈን አልተዘፈነላቸውም፤* ምድሪቱ የደረሰባት ጥፋት እጅግ ታላቅ ከመሆኑ የተነሣ፣ የሰርግ ዘፈንና የመበለቶች የለቅሶ ድምፅ (ቍ64 ይመ) ሁሉ ቀርቶ ነበር።

78፥64 *ካህናቶቻቸው በሰይፍ ተገደሉ፤* 1ሳሙ4፥11 ይመ።

*78፥65-72፤* እግዚአብሔር የይሁዳ ነገድ በእስራኤል ላይ ዋና መሪ እንዲሆን መምረጡን (በኤፍሬም ነገድ ፋንታ) ያዕቆብ በሞት ዐልጋ ላይ ሆኖ ለልጆቹ በተናገረው መሠረት የተፈጸመ ነው (ዘፍ49፥8-12)፣ የጽዮንን ተራራ (በሴሎ ፋንታ) የመቅደሱ ስፍራ (የዙፋኑ መቀመጫ) ማድረጉንና ዳዊትን ደግሞ የእግዚአብሔር እንደራሴና የሕዝቡም እረኛ እንዲሆን መምረጡን የሚያመለክት ክፍል ነው። እግዚአብሔር በዚህ ሁኔታ ከኢያሱ ሞት አንሥቶ እስከ ሳኦል ሞት ድረስ ከነበረው የእስራኤል ሕዝብ ረጅም መከራ በኋላ ሕዝቡን በተስፋዪቱ ምድር እንደ ራሱ መንግሥት አድርጎ አቋቁሞአል። በዚያን ወቅት የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ (ደኅንነት) የተጠናቀቀው ሕዝቡን ከግብፅ ባርነት ነጻ በማውጣትና ወደ ተስፋዪቱም ምድር በማድረስ ነበር (ለዚህም የመዝ68 መግቢያን፣ በዘፀአት መጽሐፍ የተገለጸውን የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ እንዲሁም በኢሳይያስ ትንቢት ውስጥ (11፥11-16) እግዚአብሔር በዳዊት ዘር በኩል እስራኤልን አንድ ቀን ነጻ እንደሚያወጣት የተነገረውን ይመ።

78፥65 *ከእንቅልፍ እንደሚነቃ፤* እግዚአብሔር በዳዊት ዘመንና ከዚያም በፊት በሕዝቡ መካከል ያደረጋቸውን ተግባራት በግነት ወይም ዘይቤ የቀረበ ነው (የ7፥6 ማብ ይመ)።

*78፥66-72፤* የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት እነርሱም (1) እግዚአብሔር በአስደናቂ ሁኔታ ጠላቶቹን ድል ማድረጉና ጽዮንን የመናገሻ ከተማው አድርጎ መመሥረቱ፣ (2) ዳዊትን የሕዝቡ እረኛ አድርጎ መሾሙ ናቸው።

78፥67 *የዮሴፍን ድንኳን፤* የኤፍሬምን ነገድ የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው (ስለ "ድንኳኖች" ዘይቤያዊ አነጋገር ለመረዳት ቍ51፣ እንዲሁም 69፥25፤ 83፥6፤ 84፥10፤ 120፥5፤ ዘፍ 9፥27፤ ዘዳ33፥18፤ 1ነገ12፥16፤ ኢዮ8፥22፤12፥6፤ ዕን3፥7፤ ሚል 2፥12 ይመ)።

78፥68፡70 *የጽዮንን ተራራ ... ዳዊትን መረጠ፤* መዝ132 ይመ።

78፥69 *ታላቅ ከፍታ ... ምድር፤* ይህ ጥቅስ በሁለት መንገድ ሊተረጐም ይችላል፤ (1) እግዚአብሔር መቅደሱን እንደ ማይናወጥ የተራራ ቅጥርና እንደማይታወክም የምድር መሠረት አድርጎ መሥርቶታል፤ (2) እግዚአብሔር መቅደሱን እንደ ሰማይና እንደ ምድር (የ24፥2 ማብ ይመ) አጽንቶ ከቆመ በኋላ የክብር ጌትነቱን ገልጦአል (24፥7-10፤ 26፥8፤ 63፥2፤ 96፥6 ይመ)፤ ይህም እግዚአብሔር በሰማያት አማካይነት ገናና ክብሩን እንደ ገለጠ ሁሉ ማለት ነው (19፥1፤ 29፥9፤ 97፥6 ይመ)።

*78፥70-71፤* 1ሳሙ16፥11-13፤ 2ሳሙ7፥8 ይመ።

78፥70 *ባሪያውን፤* በዚህ ቦታ ይህ ቃል ዳዊት የእግዚ